ድርቅና ጠኔ በኢትዮጵያ

የጽሬክተርኞ ቦርድ
እሴይ ፎርድ
ሴቱ መንበር
ደዕቶብ ሀዩለማርያም
ፈንታሁን ጥሩነህ
እህመድ ኑር

ዋና አዘጋጅ ፈንታሁን ጥሩነህ

የአዘጋጅ ቦርድ ኢሰላቢጥ ተስፋዬ
ገብርኢል ዳንኢል

የስርጭት ሀላፊ እህመድ ኑር

የአማካሪ ቦርድ ከፍአለ ገብረ ጊዮርጊስ (ዶ/ር)
(ሚሪላንድ፣ ሰሜን አሜሪካ)
ኤንዩ ቦናኖ
(ጣልያን)
ፍቅሬ ቶሎሳ (ዶ/ር)
(ምዕራብ ጀርመን)
ሐረጎ ጌሙ (ዶ/ር)
(ቶሮንቶ፣ ካናዳ)

ጽሑፎችን በዚህ አድራሻ መላክ ይቻላል።

SEM INNA WORQ

P. O. BOX 43003

WASHINGTON, D. C. 20010

U. S. A.

ISSN: 0891-9119

Sem Inna Work Corporation is a non-profit tax-exempt organization. Washington, D. C., U.S.A.

ሰ ም ና ወ ር ቅ

፪ኛ ዓመት ቁ ፩/፯ የካቲት ፲፱፻፹፩ ዓ.ም

ማ ው ጫ

ርዕሰ አንቀጽ 1

ረሀብና ተስፋ በኢትዮጵያ 7
ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ

ረሀብ ድርቅና መንስኤዎቻቸው 38
ከአቶ ገብርኤል ዳንኤል

የኢትዮጵያ ረሀብና የምዕራባውያን ጋዜጠኞች አስተያየት 73
ቶርቾ ሬይሳና ጊደኞች

ሰላም በኤርትራ 113
ከደ/ር ያዕቶብ ኃይለማርያም

ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች 128

ማስታወሻዎች 133

ርዕሰ አንቀጽ

ድርቅና ጠኔ ከምርምር አንጻር ሲታይ

ስለድርቅና ስለጠኔ በምርምር ደረጃ በምንነጋገርበት ጊዜ ከተራ ገለጻ ማዶ ዘልቀን ጠለቅ ወዳለ ትንተና እንገባለን። በተራ አነጋገር የድርቅና የጠኔ እንዲሁም አብረው ተከትለው የሚሄዱት ችግሮች ሁሉ መንስኤና እንዴት፣ ለምንና ለማን የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልሱ አይደሉም። በጽሑፍ ደረጃ አያሌ ድርሰቶች በምርምር ላይ ያልተመሠረቱ፤ ጥልቅ ጥናት ያልተደረገባቸው ሐሳቦችን አዝለው ይወጣሉ። በዚህ ደረጃ የሚሰነዘሩ መንስኤዎችም ሆኑ መፍትሄዎች በሃገር ደረጃ ሊወሰዱ ለሚገባቸው እርምጃዎች እምብዛም የሚያገለግሉ አይሆኑም። አገልግሎት ላይ ቢውሉም አገልግሎታቸው መሠረታዊ መፍትሄ በማበርከት ደረጃ ሊታይ አይችልም ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ምርምርና ጥናት የተደረገባቸው ድርሰቶች ስለድርቅና ስለጠኔ እንዲሁም አብረው ስለሚሄዱት እክሎች ሁሉ መሠረታዊ የሆነ ግንዛቤና ዕውቀት እንዲኖረን ከመርዳታቸውም ሌላ መፍትሄም ለመዘየድ አመቺ ሁኔታን ያዘጋጃሉ። በተጨማሪም ጠቃሚ የሆነ የዕውቀትና የምርምር ዘዴ ክምችት እንዲኖር ይረዳሉ።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የምድር መድረቅ ብቻ ሳይሆን የሐሳብና የአስተሳሰብ ድርቅ ሰፍኖ ይገኛል። አስቸኳይ እርምጃዎችና መፍትሄዎች በሚያስፈልጉባቸው አንዳንድ

አቢይ የሃገሪቱ ጥያቄዎች ላይ አርኪና አጥጋሚ መፍትሄዎች አይቀርቡም። ለዚህ እክል አንዱና ዋነኛው በቅንጅልና በጊዜያዊ ግንፍል ሀሳቦች ላይ የተመሠረቱ መፍትሄዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ስለሚደረግ ሊሆን ይችላል። ለእክሉች የሚቀርቡ ሐሳቦች በጥናት ላይ የተመሠረቱ የምርምር ውጤቶች ይሁኑ ቢባልም ሕዝቡ ያልተሳተፈባቸው ጥናቶች ብቻቸውን የሚያመጡት ውጤት አልባት ሊያስገኝ የሚችል አይሆንም። በሕዝቡ ተሳትፎ ያልተመሠረተ ጥናት የማድረጉ አርምጃ ሕዝቡን ለሚዘየዱ መፍትሄዎች እንግዳ ከማድረጉም በላይ ለመፍትሄዎች ተጨባጭ አስተዋጽዎ እንዳያደርጉ የሚገረግር እክል ነው። በምሁሮቻችንና በሕዝቡ መካከል ያለው የግንኙነት ዓይነት መታወቅ አለበት። በምሁሮቻችንና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት ምን እቅድ ይዞ እንደሚሄድና ምን መሆን እንደሚገባው ራሱን የቻለ ጥናት ያስፈልገዋል። ባሁኑ ጊዜ ግን ምሁሩ ጥናት ቢያቀርብ በጠረጴዛ ክልል ብቻ የተወሰነ ከመሆን አይዘልም። መፍትሄ በመዘየድ ረገድም ጥንት ይሠራባቸው ከነበሩ አሠራሮች ማደ የማቅረብ ሆነ የፈጠራ ችሎታ የማሳደግ ዝንባሌ እምብዛም አይታይም። ድርቅም ድርቅ ይባል እንጅ ከጥንት ይዘቱ እየተለየ በዚያው ልክም ልዩ መፍትሄ እየጠየቀ መሄዱ የማይቀር ነው። ጊዜያዊ ተጨማሪ ምክንያቶች በየታሪካችን አጽቅ ስለሚከሰቱ ድርቅን በድርቅነቱ ብቻ ተመልክቶ የጥንት መፍትሄዎችን ብቻ ለማቅረብ መታጣት ራሱን የቻለ ድክመትን ያስከትላል። ስለዚህ አዳዲስ ዘዴዎችን (መፍትሄዎችን፤ አስተዳደርን፤ አቀራረብን፤ አስመልክቶ) ለማቅረብ የችግሩን እድገት ታሪክና ሕዝቡ የሚያቀርባቸውን መቋቋሚያ ዘዴዎች መከታተል ያስፈልጋል።

በዚህ እትም የቀረቡልን ጽሑፎች ከተለያየ አቀራረብ

አንጻር ተቀነባብረው የመጡ ጥናቶች ሲሆኑ ለወደፊት ስለዚሁ ርዕስ ለሚደረጉ ጥናቶች ዓይነተኛ መነሻ እንደሚሆኑ የማያጠራጥር ነው። እነዚህ ጽሑፎች በአንድ ርዕስ ላይ ያተኩሩ እንጂ ደራሲዎቹ ከተለያየ አቅጣጫ የራሳቸውን (የግላቸውን) ሀሳብና ድምዳሜ ነው ያቀረቡልን። የሀሳቦች ልዩነት ሆነ መቃረን ቢኖርም የሚያስፈራ ሳይሆን በብሩህ ልቦና ተመልክቶ መገምገም ተገቢ ይመስለናል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌ በተለይ የጥንቱን የድርቅ የረሀብና የተስቦ ታሪክ ከነማስረጃው አቅርበውልናል። ይህ ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ የሚያጠቃው እክል በታሪክ ውስጥ ብዙ ዓይነት ጠባይ ይዞ መከሰቱን ጽሑፋቸው ያመለክታል። የተለያዩ መንግሥታትም የሞከሩትን የተለያየ መፍትሄ አብራርተው ገልጸውልናል። ከዚህ ታሪክ የምንማራቸው አያሌ ጠቃሚ ቁም ነገሮች መኖራቸውን ጠቁመን ለአንባቢያን እንተወው። በቅርቡ የድርቅና የጠኔ ታሪክ በኩል መንስኤዎቹን አስመልክተው አቶ ገብርኤል ዳንኤል ሰፋ ያለ ማብራሪያ አቅርበዋል። ይህ ክስተት ኢትዮጵያን ብቻ የሚያጠቃ ሳይሆን የአፍሪካን ሰሜናዊና ሰሜን ምስራቅ ክፍል ወደምድረበዳነት እየለወጠ በመሄድ ላይ መሆኑን እንረዳለን። «የምድረ-በዳነት ወረርሽኝ» ልንለው ይቃጣናል።

«ኢትዮጵያ» የሚለው ስያሜ ወደቅጽልነት ወይም የረሀብ መግለጫ ወደመሆን እንዴት ተሸጋገረ። «የዳቦ ቅርጫት» ትባላለች እየተባለች የምትጠበቅ ሀገር የረሀብ ምሳሌና የረሀብ ተምሳሌት ወደመሆን የተሸጋገረችበት ምክንያት አለ። በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተጎነጎነ ያለው ፖለቲካዊ ውስብስብ የኢትዮጵያውያንን በድርቅ መመታትና በጠኔ መሰደድ ምክንያት

በማድረግ በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት ሳቢያ በሰሻሊዝም ርዕዮተ-ዓለም ላይ፤ በኢትዮጵያ የጥንት ታሪካዊ ዝና ላይ፤ በሀገሪቱ ሕዝብ ነፃነት ወዳድነት ላይ፤ እንዲሁም በአፍሪካ ውስጥ ሀገሪቱ ባላት ተምሳሌአዊ ቦታ፤ .....ወዘተ ምዕራባውያን ጋዜጠኞችና የየጋዜጣው ርዕዮተ-ዓለም ታሪክን የመናድ ዘመቻ በማካሄድ ላይ መሆናቸውን አነቆርቾ በሰፊው መዝግበው አቅርበዋል። ይህ ዓይነት ዘመቻ እንዲቆም የኢትዮጵያውያን ግንዛቤና ትግል የሚያስፈልግ ይመስላል። ግንዛቤው በቅድሚያ ከገዛራስ ጋር የሚደረግ ትግልን ሲጠይቅ ሌላው ትግል ዳግሞ ታሪክን የማስከበሩና ትክክለኛ ቦታውን ማስያዝ ይሆናል ማለት ነው።

የሀገሪቱ የውስጥ ፖለቲካዊ ውዝግብ በብዙ የፖለቲካ ደራሲዎች በቸልታ የሚታለፍ ጉዳይ እየሆነ መጥቶአል። የፖለቲካ ቁርቁስ የሕዝብ አልቂት የሚገታበትን መፍትሄ ለመሻት መሆን ሲገባው የሕዝብን ችግርና አልቂት እያባባሰ በመሄድ ላይ ነው። ፖለቲካ በአልህ አሸክርሬት ውስጥ ከገባ የአልህ ፖለቲካ እንጂ ሌላ ሊባል አይችልም። በዚህ የፖለቲካ መተላለክ ሳቢያ አንዱ ከሌላው ወገን የሚገድለውን ሰው ብዛት ከማስላት ሌላ አይታየውም፤ ሌላውን ወገን እጸከምኩ ለማለት የአልቂት ዘመቻወችን መዘየድ እያስከተለ ይመጣል እንጂ። ይህ ከመሬት መድረቅ እክል ጋር ሲዳመር የሕዝብን አልቂትና መሰደድ፤ የረሃብንና የጠኔን በተከታታይ መከሰት ያመጣል። በኢትዮጵያ ውስጥ የጠኔና የረሀብ መባባስ እንዲሁም የእድገት መሰናክል ሁሉ በፖለቲካው ሁኔታ በተለይ በብሔርችና በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ ያረፈ መፍትሄ አለመገኘት ምክንያት መሆኑን እንገነዘባለን። በኤርትራ በኩል ያለው በተደጋጋሚ የሚከሰት

እልቂት አገሪቱን በጠቅላላ ከዳር እስከዳር በማድማት ላይ ይገኛል። ይህን ጥያቄ በሚመለከት ደክተር ያዕቆብ ሀይለ ማርያም አስፋፍተው በመተንተን ለፖለቲካው ውዝግብ መፍትሄ ለሕዝቦችም ሰላም የሚገኝበትን መንገድ የሚከፍት ጽሑፍ አቅርበዋል።

በዚህ አጋጣሚ ምርምርና ጥናትን አስመልክቶ እነቆርቾ በቡድን ተደራጅተው ያሳዩትን አርአያነት ማንስት ትምህርታዊ ነው ብለን እናስባለን። መልካም አርአያነቱ በአሁኑ ጊዜ ተበታትኖ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ አደሌ በመሆኑና ከአብዮቱ አንቅስቃሴ ወዲህ እንዲሁም በተለያዩ ጦርነቶች ሳቢያ መፈራረቅ፤ አለመተማመን እና አንዱ ለሌላው ባዕታወር የመሆን ዝንባሌ እየገፋበት ስለቀጠለ ይህን አሉታዊ ሂደት በመቋቋም ያላቸውን ልዩነት በማጥበብ የጥናት ቡድን መፍጠር በመቻላቸው ነው። ሀገራችን ያለችበት ዝቅተኛ ስፍራ ጥቃቅን ልዩነቶችን ቦታ የማይሰጥ መሆኑን መረዳት ባሁኑ ጊዜ እጅግ አስፈላጊ ይመስለናል። የነቆርቾ የጥናት ቡድን ትምህርታዊ የሆነ አርአያነት አለው የምንለው የምርምር ጽሑፎች ለማውጣት ውሳኔ በማድረጋቸው ነው። ለሃገራቸው ሕዝብ በገቡት ቃል መሠረት የመጀመሪያ ውጤታቸው የሆነውን ጥናታዊ ጽሑፍ በዚህ መጽሔት ሳቢያ አቅርበውልናል።

* * * *

የአዘጋጅዎች ማሳሰቢያ፤

ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እና እንዳመቸ ኢትዮጵያን በሚመለከቱ አንገንጋቢ ጥያቄዎች በአንዱ ላይ ልዩ ጥናት እንዲደረግ ጥረት እናደርጋለን። እነዚህ ጥናቶች በልዩ የጥናት እትም ለአንባቢዎች ይቀርባሉ። ይህ እትም የመጀመሪያ ውጤታችን መሆኑ ነው። አሰካሁን ከተለያዩ አንባቢዎች የቀረቡልን ሀሳቦች በኢትዮጵያ ጊዜያዊ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ጥናት እንዲደረግ እና ሀሳብ እንዲንሸራሸር የሚጠይቁ ናቸው። ስለዚህ የሚቀጥለው ልዩ የጥናት እትም የሚያተኩረው በዚሁ ጥያቄ ላይ ይሆናል። የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የጥናትና የምርምር ጽሑፍ ማቅረብ የምትሹ ግለሰቦች፤ ቡድኖችና ድርጅቶች የጥናቶቻችሁን አርእስት ከአሁኑ እንድታስታውቁን ይሁን።

ስለደራሲዎቹ አጭር ሃተታ

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣
ፕሮፌሰር ጌታቸው በቀጳጳዊ ኃይለ ስላሴ ዮኒቨርሲቲ በመምህርነት አገልግለዋል።
ኢትዮጵያን በሚመለከት አያሌ የምርምር ጽሁፎች ን አበርክተዋል።
የማክስተር ፋዉንዴሽን የምርምር ስራዎቻዉን ተመልክቶ የከፍተኛ ሽልማት ተተባይ አድርጎዋቸዋል።በሚተጥለዉ አትግችን የህይወት ታሪካቸዉን ባጭሩ ስለምናወጣ ብዙ ከመተረክ እንቆጠባለን።

ዶክተር ያእቆብ ሃይለ ማሪያም፣
ዶክተር ያእቆብ በናርፎልክ ስቴት ዮኒቨርሲቲ አረጻት ፕሮፌሰር ናቸዉ።
የህገና የንገድ ስራ ትምህርት የገበዮ ሲሆን በነዚሁ የስራ መስኮች በመምህርነት በመስራት ላይ ይገኛሉ።

አቶ ገብርኤል ጳንኤል፣
አቶ ገብርኤል በመድሃኒት ቅመማ ትምህርት የሰለጠኑ ሲሆን በዚሁ መስክ የማስተሪት ዲገሪ አላቸዉ።በአሁኑ ጊዜ በአፍሪኪር ድርጅት ዉስጥ በሙያቸዉ በስራ ተሰማርተዉ ይገኛሉ።

አነቆሪቸ ፈይሳ፣
ስለእነ ቆሪቸ ማንነት ቡድኑ ራሱ የጻፈዉን ይመልከቱ።

ረኀብና ተስቦ በኢትዮጵያ

ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ*

ለፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም

መቅድም

በኢትዮጵያ ላይ የሚወርደውን የዝናም መጠንና የሀገሪቷን የአየር ብልጽግና ያየ ሰው ኢትዮጵያን ጥጋብ እንጂ ረኀብ ያስቸገራታል ብሎ መገመት ያዳግተዋል። ዛፉ (ጫካው ደኑ) እየተመነጠረ ሲሄድ ሰማያትም ንፉጎች ሆኑ። ዝርዝሩን የአየሩን ጠባይና የዓፈሩን ዓይነት ለሚያጠኑ ልተወውና ረኀብና ተስቦ በኢትዮጵያ በታሪክ በኩል የቱን ያህል እንደነበሩ ለማሰየት አንዳንድ ማስታወሻዎችን ከታሪክ ገጾች ልጥቀስ። ማስታወሻዎቹ እንዳንድ መጻሕፍት ስመለከት እንዳጋጣሚ ያገኘኋቸው ስለሆኑ ጥናቱ መነሻና ውጥን እንጂ የተሟላ አይደለም። <u>የሰምና ወርቅ</u> አዘጋጆች ደጋግመው ባይጠይቁኝ ደፍሬም ለእንባቢዎች አለቀርበውም ነበር።

በኢትዮጵያ የረኀብ ምክንያት ሆነው ከገኘኋቸው ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ይገኙበቸዋል።

(1) የዝናም አልፎ አልፎ መቅረት እንዳንዴም መብዛት።
(2) የአንበጣ በየጊዜው መምጣት።
(3) ሰብሉን በረዶ፣ ተምችና አመዳይ መምታት።
(4) ተለለፊ በሽታዎች በሰውና በከብት ላይ በየጊዜው መነሣት።
(5) የእስተዳደር በደል።
(6) የእርስ በርስ ጦርነት።
(7) ረኀቡን መቋቋሚያ ዘዴዎች አለማግኘት።
(8) የመሬቱ ዐፈር በዝናም መታጠብ።

የበዓለት መብዛትም በግበሬው ላይ ችግር ሰይፈጥር አልቀረም። ምንም እንኪን በነሱ ምክንያት መሬቱ ባያድርም ጊዜ ለመሸማት ገበሬዎች ሁል ጊዜ ሲጣደፉ ይታያል።

ሰፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንኛውም ጊዜ ረኀብተኛ ነው ማለት ከበድ

እነጋገር ይሆናል። ግን ልብ ብሰን ብንመለከትው ኢትዮጵያ ገበራው ከነቤተሰቡ ወተት ጠምቶት፤ ሥጋ እምርት የሚኖርበት አገር ናት። ሥጋ የበሉ እንደመሰላቸው በጥቂት ቋንጮች እንጻር ተቀምጠው እነሱን እነሱን እያ ዩ የሽሮ ወጥ ራት የመብላት ዘዴ ያላቸው ወገኖች አሉ ሲባል ቀልድ ይመስለኝ ነበረ። ሁላችንም ወደምናውቀው እንመለስና ከቀኑ በማንኛውም ሰዓት እንግዳ ቢመጣ መጀመሪያ እህል ውሀ ይቀርብለታል፤ ይህ መስተንግዶ እንግዳው ረኅብተኛ መሆኑን መመስከር ይመስለኛል። ሐሳቤን የሚደግፉልኝ የሚመስሉኝ ተጨማሪ ነገሮች አነሣለሁ።

ንጉሦች በየአውራጃውም ወኪሎቻቸው ለሹማምንትና ለሦር መኪንት ለሕዝብም ተመርጦ ግብር ያገቡ እንደነበረ ሰምተናል፤ ያየንም የተከፈልንም እንኖራለን። የተከፈሉ ሰዎች ከግብሩ ገበታ ለመድረስ ስለአለው «ተጋድሎ» ሲነግሩን ረኅብ የጸናበት ብቻ የሚታገሠው ይመስላል፤ ያለው ግፈያ፤ ጉሽምትና ዱላ ተደጋግሞ በልሰግው ተረት ይመስለኝ ነበር። እንዳንዶቹ እንግዶች ከግብሩ ገበታ ላይ ሥጋ በጉያቸው ይዘው ይሄዱ ነበር።

መምህራን ሊያደርጉን አስበው ነበር መሰለኝ በ1943 ዓ/ም የትምህርት ጊዶኞቼና እኔ ከየቦታው ከመጡ ተማሪዎች ጋራ የከረምት ትምህርት እንድንማር ተደረገ። ትምህርቱ ሲፈጸም የመምህራን ማሠልጠኛ ደረክተር የነበሩት ሰው (ከናዳዊ ነበሩ መሰለኝ) የትምህርት መደምደሚያ በዓል አደረጉልንና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ዘፈኖች እያስያዙን ስናሸበሽብ እምሽተን ሻይና የሚቶረጣጠሙ ነገሮች ወደተዘጋጀበት አዳራሽ እንድንዛዋወር ተጋበዝን። ከዳራሹ ብቅ ስንል በየጠረጴዛው ላይ መግለሊትና ጣባ በመሰሰሉ ዓይን በማይሞሉ ዕቃዎች ቶሎና ብስኩቶች አየን። አሰፈሳጊነታቸው እንደመከሰስ ለማምሸሸ እንጂ ረኅብ ለመግቻ መሆኑን አሳወቅንምና ቀድሞ የደረሰ ከፈሰሰላቸው ወደኋላ ለቀረው ምንም ያህል እንደማይተርፍ ወዲያው ተረዳን። ድርውንም ሰር የሰደደ ጨዋነት ስለሌለ ያሉትን መምህራን (ያችን በልዩ ዓይን እናያት የነበረች ቀንጂ ህንዳዊት ሰትቀር) ሰናፍር በጠረጴዛዎቹ ላይ ተራ ኩትንባቸው። በዚያን ጊዜ የቆጨኝ ወደኪሰችን ከገባነው ይልቅ እቃዎቹ እየተደፉ ከመራት የፈሰሰው ቶሎ መብለጡ ነው። እንግዲህ ይህ የሆነው የዛሬ ሠላሳ ሰምንት ዓመት ነው።

የዛሬ ሐያ አንድ ዓመት ግድም ደግሞ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በለ ሥልጣኖች አዲሱን ሕንፃ ለማስመረቅ ወደጉለሌ አንድ አውላላ ሜዳ ፈልገው ሰፉ ያለ ግብዣ አደረጉ። የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ሁሉም የተጠሩ

ይመስለኛል። በዚያ ላይ እንደኔ ያሉ የውጭ እንግዳዎች ነበሩ። ሥርዓቱ ምግብ ያዘለው ከድንኪን ውስጥ ያለው ሪጅሙ ገበታ ሲከፈት በሳህን የምንፈልገውን ያህል እያነሣን ለተረኛ ገለል ማለት ነበር። እንደታሰበው አልሆነም፤ ከላይኛው ታሪክ የገለጽኩት መራከት መልኩን ሰይለውጥ መጣ። ልዩነቱ እዚህኛው ሳይ ጊደኞቼና እኔ ሲሎችም እንዳይኾ ከትግሉ አለመከፈላችን ነው።

ወደሽርሽር ሄደ እገልግል ሲከፈት በእከባቢው ያለው እረኛ ሁሉ ከበቀጭ የሚለውና ፍርፋሪ ሲጣልለት እጅ ነሥቶ ጎረሰ ጎረሰ የሚያደርገው በቤቱ በሰዱቃ በወግ በማረግ ከሚቀርብለት ይልቅ የሰው እጅ እይቶ የሚያገኘውን ትራፊ መርጦ ነው ብየ አሰምንም። እኔም አንድ ጊዜ እነሱን ነበርኩና በቅርብ አውቀዋለሁ። ባጭሩ የሐያ አራት ሰዓት ራብተኞች በንሆንም የእህል ሰቀቀን ያልወጣልን ሕዝብ ሲንሆን እንቀርም።

ይኸንኛውን ማስረጃ ደግሞ በቅርብ ጊዜ ነው የሰማሁት። ለቅሶኛ ከቀብር ሲመለስ እንበ አድርቅ ንፍር እንደሚቀርብ ሁሉችንም እናውቃለን። በእንደዚህ ያለ እንድ አጋጣሚ ግማሹ ለቅሶኛ አስከራኑን እጅበ ወደ ቀብር ሲሄድ ግማሹ ከልቅሰው ቤት ቀርቶ ነበር። ወደ ቀብር የሄዱት ሲመለሱ ከልቅሰ ቤት የቀሩት እንበ አድርቁን ጪርሰውት ኖሮ ተሰቀው ወደየቤታቸው ተበታተኑ።

ከላይ የረኀብ ምክንያቶች ያልኪቸው ሁሉም ግብራሪያ አይደሉጉም። ኢትዮጵያ ከአንበጣ መዶልዶያ አገሮች አንዷ መሆኗ የታወቀ ነው። በአምሰተኛው ቁጥር የአስተዳደር በደል ያልኩት የመራት ይዘታንና ግብርን ይመለከታል። ይህንንም ከዚህ በሰፊው መተቸት የተበለን ማጭበኪት ይሆናል። የሀገራችን የመራት ይዘታ በብዙ አውራጀዎች የተዘበ እንደነበርና ገበሬው ለሚከፍለው ዓሥራትና ግብር ተመጣጣኝ ጥቅም እንዳላገኘበት በሰፊው በየቦታው ተተችቷል። ብቻ ጪርሰን እንዳናልፈው ልዑል ራስ እምሩ ስለዚህ ጉዳይ ገና በልታተመው ማስታወሻቸው የጻፉትን እንደለ ልጠቅሰው እወዳለሁ። ጊዜውም 1923 ዓ/ም ከዘውድ በዓል በኋላ ነው።

> በዚያ ወራት የሹም ሽሩ ስራ ሁሉ ካለቀ በኋላ እንድ ቀን ወደሚኒስትሮች ከፍል የምክር ቤት ስለተመራሁ ሄጀ። እንደኔውም ሚኒስትሮች ያልሆኑ ሌሎች ጥቂት መኪንናቶች ነበሩ ከሚኒትሮች ጋር ወደ አስራምስቱ እንሆን ነበር ወደተዘጋጀው ስፍራ ገብተን እንደተቀመጥን፦ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ መስቀል የተጠራንበትንና የተሰበሰብንበትን ጉዳይ በዝርዝር እመለከትን፤

ነገሩም በጉራጌና በከንበታ ወገን ያለው እገር ባለባቶች ባንድነት ሆነው እቤቱታ ለሰታወቁት ጉዳይ ነበር፡- ታሉም የገበሩ ግብር ጥንት ትኒሽ ነበር እንደ መሬቱ መጠን ለመልከኛውና ለሸለቃው የሚከፈለው በየጊዜው የሚለዋወጠው የሸለቃው ሁሉ ግን እንደንድ ነገር እየጨመረ ግብሩን ሁሉ አሰድጎብን እሁን ብዙው ገበር መገበር አቅቶት መሬቱን እየተወ ተሰደደ። የዚህንም የተሰደደውን ገበር ግብር እኛን ባለባቶችን የገድ ገብሩ ብለው ያዙን። የተሰደደው ገበር እየመኪንቱ የወለሰማና የጉልት መሬት ነው የገበው። ይኸውም የወለሰማና የጉልት መሬት የመንግሥት ግብር ብዙ ስለሌለበት እየተሰማማ እየሄደ እርቦ እራሽ ሆነ። ለሄደውና ለሚሄደው ሁሉ የሰንቱን ገበር ጠፍ መሬት ገብረን እንዘልቀዋለን። የሄደውንም ገበር ከሄደበት ተከታትለን እያመጣን በግድ ለመመለስ እንችልም ባለጉልቱም ይከለክለናል። ስለዚህ እጥብቀን ተቸግረናልና ጠፉን መሬት ቢፈልጉ ገበሩ ጥሎት የሄደውን እናስረክበለን በሄደው ገብሩ ተብለን እንደንያዝ። ደግሞም እሁን ያለውም ጨርሶ እንደይጠፋ በየጊዜው የሸለቃና መልከኛ ያሰደገውና የጨመረው ግብር እንዲፋቅልን እናመለከታለን ብለው በየጊዜው የተጨመረውንም ግብር በዝርዝሩ አጽፈው የሰጡትን ደጋግመው እንበው ይኸን እንድታስቡበትና እንድትመከሩበት ስለዚሁም የወሰናችሁትን እንደውቀው ብለዋል ጄንሆይ [ቀ.ኃ.ሥ.] ብለው አመለከቱን። ነገሩን ሰምተን ጥቂት ዝምታ ከሆነ በኋላ እንደንደቹ መኪንንቶች መናገር ጀመሩ። እነሱም የበለተኛውን ወገን የመልከኛና የሺአለቃውን እበል ለመንከት የተጨመረውንም ግብር ዝቅ ለማድረግ እጅግ ፈርተው መልከኛው ደግሞ እበሳችንን ከለከላችሁ ብሎ ይነሳብናል የሚያስቸገር ነገር ነው እያሉ ተናገሩ፤ ደግሞ ጥቂቶችም መሬቱን እየለቀቁ የሚሄደውን ገበር ያው መልከኛው እየፈለገ እ[የ]ተከታተለ እየያዘ ይመልሰውና ያስገብርው በያንዳንዱ እገርስ እንደዚሁ ያለ ደምብ አለ የለሞይ። በንደዚሁ ያለው ባለባት መያዙ ይቅር። እሉ። እኔም በተራዬ ሁሉንም ከደመጥኩ በኋላ ነገሬን ስጀምር ሁሉም ዝም ብለው እደመጡኝ። የተናገርኩትም በሐረርጌ ወገን ያለው ገበር እስተደደሩ ከዚህ ከተነገረው ልዩነት ስለሌለው መጀመሪያ የዚያን እኪሆን ነበር። በሐረርጌ ገበር መሬቱን ጥሎ ቢሄድ መልከኛው እራሱ መሬቱን ቢያርሰው ወይም ሌላም እራሽ እጋዝቶም ቢሆን የሚገኘውን (ይበላል) ይወሰዳል እንጂ ገበር አልችልም ከለ እንኪን ተሰደና እዚያውም እገር ለገር እስታውቶ ለቶ ቢቀመጥ የሚነካው የለም። የተወሰነውም ዓመት ሳይደርስ እንኪን ወደ መሬቱ ለመመለስ ፈልጎ በፈቃዱ ቢመለስ ገብቶ አለችግር መያዝ ይችላል።

ስለዚህ ሰው የሚገብረው ለኑሮውና ለትዳሩ ሲል መሬት ይዘ ቤት ሰርቶ ሚስት አግብቶ ልጅ ወልደ ተቀመጠበት እንጂ። የማይችለውን ፅዳ ሊከፍልበት አይ[ደ]ለም።

ደግሞስ ይሽንኑ መራቱን ዕዳውን እልችልም ብሎ ደህይቶ ቢሰደድ የግድ እየተፈለገ የሚያዘው ምን ባደረገ ነው። እስኪ እራሳችን እናስበው ሰው የሚወደውን ቤቱን እኖርበታለሁ ያለውን እርስቱን። እንዲኖር የሚረዳውና የሚደግፈው ዳኛ በማጣት። ይሽው በየጊዜው የተጠመረበትንና ያደገበትን ጽር እቅርበልን እናያለን። ይሽን ያለ መንግሥት ፈቃድ የተጠመረውን ለመቀነስና ለማሸሽል መከራ መሰሎ ይታያችኋል። በሳተኛውን በመፍራት ከዚህ ለማዳን የማይቻል ሲመስላችሁ። ድኃውን ከተሰደደበት አብርሮ መያዝና የግድ ገብር ማለት ትልቅ የግፍ ግፍ ነው። ብየ ከተናገርኩ በሰተኋላ። ቀጥዬ ይልቅስ እኔ እሰቤን ሲመልከታችሁ የምሸው እውነተኛው ነገር። ለመንግሥቱም ሆነ ለሀገሩ። ታሳች እንቅፋት ሆነን ለማሸሽል ያስቸገርንው እኛና እኛን የመሰለው ሹማምንት ሁሉ ነን። ምክንያቱም ከመንግሥት ደሞዝ እንቀበሳለን። እገርም እየገዛን የገበሩን ገብር እንወስዳለን። ደግሞም በዚሁ ሳይ ብዙ ሰፈሬ መራት እርስት እያልን እየያዝን መቶውን ጋሻ ባምሰት ሸማ። እምሳውን ጋሻ በሶስት ጉንደ ማር እየሆነ ብዙውን ሰፈሬ መራት ሁሉ ያለ ገብር ይዘን። እያወከን ባንድ ወገን በዚህ አኪሆን የመራቱ ገብር ሁሉ እየጎደለ። በሌሳ ወገን ደግሞ። በገበሩ ሳይ በመጠመሩ ሊኖር አቃተው።

በሌሳው መፍረድ እንድንችል እስቲ መጀመሪያ በራሳችን እንፍረድ ሌሳው ነገር እንኪን ለጊዜው ቢቆይ። እርስት ብለን ያለደንበኛው ገብር የያዝነውን መራት። እንደድኃው ገበር ልክ በየእንዳንዱ ጋሻ ግብሩን ተከክለን እንገብር። ይሽንኑም ብናደርግ ከበሳገሩ ሳይ የከበደውን ታሳች የገብር ሸክም መቀነስና ማቅለል ይቻሳል። ገበሩም ገብሩ ከቀለለ[ለት በመራቱ መኖር ይችሳል። ደግሞ በየጊዜው በየሸለቃው ምክንያት እንዲይጠመር መንግሥቱ የሚጠበቅበትን ደምብ ከሰራለት መራቱን ለቆ የሚሄድ ገበር ምንም ያህል አይገኝም። ግብሩም በሚሄድበት ሥፍራ ሁሉ ተመሳሳይ ስለሆነ። ይሽ የቀረበልን ነገር ትልቅ ነው። ዳር እገር በተባለው እገር ሁሉ። በሳገሩ አቅም እያነሰው ነው እንጂ በዚህ በቀረበው እቢቅታ እይነት። ወሬውን እንደምንሰማው ያልደሽየና ያልተቸገረ እገር እይገኝም። ይሽውም በብርታት ቶሎ የሚድንበት ነገር ካልተሰራ። ይሽ አሁን የተፈራው በሳተኛ እገሩን ፈጽሞ ካደሽየ በኋላ የሚበሳው ሲያጣ እንደገና መንግሥቱን እያስቸገረ የከፋ ነገር ሳይሆን እይቀርም። አሁን እንኪን የተመቻቸው ሹማምንቶች እገር ሲለምኑ ይሽ ያልተበሳ እገር ነውና ስጡን ይሳሉ ይባሳል። ብዙ ነገሬን እንደጨረስኩ።

አዚያም ከነበሩት እንዳንድ ትልልቶች መኪንንቶች አዎ የአደሜን እርስት ሁሉ ልትነቅል የማይሆነውን ነገር እያሉ አንድ ጊዜ ነገራቸውን አወረዱብኝ።

ከልጅ አገርኽ ወገን ግን እንደንደኽ ምንም ቢያንሱ የኔኑ እይነት አሰብ የመሰለውን ተናግሩ። በዚሁ ስንጨ ቃጨቅ ያንለት ሰዓቱ

ደርሰ ተለያየን። ሁለተኛም በዚሁ ነገር የተነጋገርንበትና የተፈጸመ እኔ የማውቀው የለም። እንደመሰለኝም ለእቤት ባዮቹ መልስ ያህል ምንእልበት ጥቂት ነገር ያደረጉላቸው ይኖር ይሆናል።

ዛሬ የምናየው የእርስ በርስ ጦርነት የኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ አይደለም። ኢትዮጵያ በረጅሙ ታሪኪ ሁሉ ያለ እንደኾ እርስ በርስ ጦርነት አንድ መቶ ዓመት ኖራ እንደሆን ያንን ዘመን ለማወቅ እንፈልጋለን። አልፎ አልፎ «በዚህ ዓመት ንጉሡ ከመዲናው አልወጣም» ከሚለው በቀር ታሪክ ነግሥቱ የሚነግረን በየዓመቱ ንጉሡ አለዚያም የጦር አበጋዝቹ የዘመቱትን ዘመቻና ያገኙትን ወይም ያጡትን ድል ነው። በጦርነት ጊዜ ገበሬው ሰይቀር ወታደር ይሆናል፤ ያልዘመተ በወዋጁ መሠረት ርስቱ ይነቀላል። ዘመቻውም በእርሻ ወራት ከሆነ መሬቱ ጦሙን ያድርበትና እሱም ከዘመቻ በሰላም ከተመለሰ እንደመሬቱ ጦም እደሪ ይሆናል።

በዘሬው ዘመን ለዘግች ሠራዊት አስፈላጊውን ሰንቅ የሚያቀርብለት የሰንቅ አቅራቢ ክፍል አለው። በኢትዮጵያ ታሪክ ግን እስከ ሀያኛው መቶ ዓመት ድረስ ወታደሩ ሰንቁን የሚያገኘው ከሰላማዊ ሕዝብ እየዘረፈ ነበር። በዚህ ሁኔታ በብዙ ሽህ የሚቆጠር ወታደር ከአንድ ጠቅላይ ግዛት ወደሌላው በእግሩ ሲጓዝ ለምሳ ባረፈበት በታ ሁሉ ያለውን ሕዝብ ያደኸያል፤ ያስርባል። ከሁሉም የሚያሳዝነው ገበሬው ለዘር የከተተው ጥራጥሬና ግረሽ በራያቹ ሰይቀሩ ይበሉበታል። እንዲህ ያለ ፍርጀ የመጣበት ገበሬ ከቤተ ሰቡ ጋራ በረኀብ እታሰቶ ከመሞት ወይም ክብሩንና ኩራቱን ዋጥ አድርጎ ወደሌለ አውራጃ በለማኝነት ከመሰደድ በቀር ብዙ ሌላ ምርጫ አይኖረውም። ለምሳሌ በ1888 ዓ/ም በዓድዋ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያው ጦር የኢጣሊያ ወራሪዎችን ለመውጋት ዓድዋ እንደደረሰ አልተዋጋም። የኢትዮጵያ ወታደሮች ሲቀርቡለቸው ተደብቀው ለማዉድ ጣሊያኖች ዓደግራት ሰይ ከዘጋጁት እርድ ውስጥ ገብተው ይጠበበቁ ነበር። እዬ ምኒልክ ይሽንን የጠላት ዘዴ እስቀድመው ስለወቁ ከምሽጉ ከልወጣ ውጊያ አልጀምርም ብለው ከእንድ መቶ ሺ በላይ የሚሆን ወታደር ይዘው ሦስት ወር ያህል ተቀመጡ። በዚህም ምክንያት እንኪን የተጫነው ሰንቅ በዓድዋ አከባቢ ያለው አህል ሰላለቀ ወታደሩ ጠላት መጠበበቁን ትቶ እስከ ሽሬ ድረስ እየሄደ ይዘርፍ ነበር። ጀኔራል ባራቴሪም የጣልያንን ጦር ከምሽግ አውጥቶ የኢትዮጵያን ጦር ለመምታት ሌሊቱን ወደ ዓድዋ ሲገሠግሥና ሲደናበር ያደረው የኢትዮጵያ

ሠራዊት ተርበ እህል ፍለጋ ሄዷል የሚል ወሬ ደርሶት ነው። እውነትም ብዙ ወታደር ከጦርነቱ አልተሰተፈም። ጦርነቱ ሲያልቅ የትግሬ መሬት በሰውና በጭነት ከብት ተልሶ ስለነበር እዬ ምኒልክ ለትግሬው ገዢ ለልዑል ራስ መንገሻ እህል ከስሜን ድረስ እንዲጫንላቸው አዘውላቸው ነበር። ራስ መንገሻና ሠራዊታቸው እህል ተጭኖላቸው ይሆናል፤ ሕዝቡስ?

ከላይ እንደጠቀስኩት ይኸንን ለምሰሌ አነሣሁት እንጂ እርስ በርስ የሚደረገው ጦርነትም የሚያስከትለው ረኀብ ይኸን ኑ ዓይነት ነው። እንዲያውም ይበልጥ ይሆናል። በእርስ በርስ ጦርነት ጊዜ ተሸናፊው ወገን እንደዘራው ሥርዓት ነጭ ጨርቅ በማውለብለብ ጦርነቱን እያቆመውም። ተሸናፊ ሲሸሽ፤ አሸናፊ ሲያባርር ሴቶች ሕፃናት ከብት ጉተራ ከለበት ይደርሰሉ። በዚያን ጊዜ «ጀግናው አሸናፊ» የተሸናፊውን ቤቱንና ጉተራውን እኀሩን ሁሉ በእሳት ያቃጥልና ከብትና ባርያ ዘረፈና ምርኮ ይጀምራል። ታሪክ ጸሐፊውም የጦርነቱን ምዕራፍ «ወግኅረኩ ብእሲቶ ወውሉደ ወእንስሳሁ ወቀተሉ ብዙኃ» በሚል ቃል ይደመድማል። በቅርቡ ጊዜም የ ጉጂው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በእዬ ዮሐንስ ላይ ማመፃቸው እንደተሰማ እዬ ዮሐንስ ወደ ጉጂም ዘምተው ነበረ። ሁኔታውን ከብሳቴን ጌታ ኀሩይ ወልደ ሥላሴ «የኢትዮጵያ ታሪክ» እጠቅሰለሁ።

> ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም የእዬ ዮሐንስን መምጣት በሰሙ ጊዜ ሙተራ ወደሚባለው እምባ ወጥተው ተቀመጡ። እዬ ዮሐንስም የሙተራን እምባ በመድፍ ለማፍረስ ቢሞክሩ በዚያ ዘመን የነበረው መድፍ እንደዘራው ዘመን መድፍ በሩቅ ሄደ ሥራ እይሠራም ነበርና እምባውን ለማፍረስ የማይችሉ ሆኑ። በዚህም ነገር እጅግ ስለተናደዱ አገሩን ጎጂውን ያጠፉት ጀመር። በሌላው በፍራ ይቅርና [የአገሬው ሕዝብ] ከመከራው የሚድን እየመሰለው ገንዘቡን እየያዘ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተግጠነ ሲገባ [የእዬ ዮሐንስ] ወታደር በኃይል እየገባ ገንዘቡን እየቀማ እምቢ ያለውንም እየገደለው ይወጣ ነበር።

እዬ ዮሐንስ ሃይማኖተኛ ስለነበሩ ከደብዳቤዎቻቸው በንዴ ውስጥ ስለዚህ ስለዘመቻው ሲጽፉ «በእኔም በድኃውም [በሕዝቡ ማለታቸው ነው] ኃጢያት እንደሆነ እይታወቅም አገሩን ሰጠፉው ከሪምሁ» ብለዋል። በዚያን ጊዜ እንዲት አልቃሽ የገጠመችላቸው አንድ ቦታ ተጽፎ ማንበቤ ትዝ ይለኛል።

በለይኖው ጌታ በባልንጀራዎ
በቅዱስ ሚካኤል በጋሻ ጃግሬዎ
በጽላተ ሙሴ በነጭ አበዛዎ
ጎጂዎን ይማሩት ፈሪም እንልዎ

የዘመቻ ተስፋው ዘረፋ ስለሆነ ወታደሩ ተው ቢሉትም በቀላሉ እሺ አይልም። ቅል በግኝ ወታደርንና የኔ ብጤ ደሀውን እንርሳ። ሁለቱም ወገኖች ዘረፋ ብናገኝ እያሉ ያለእዘዝ ያለእለቃ የሚዘምቱ ናቸው።

ሁኔታውን አተኩሮ ያየ ሰው እልፎ እልፎ የዝናም እጥረት ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ የኖረ ነው ለማለት ይቃጣል። በእንግሊዝኛ ሱሲ በአማርኛ ድንቅነሽ (እሷን ቢጠይቋት ግን የራሷን ቋንቋ ስም ትመርጥ ይሆናል) የተባለችው የጥንት ሴት በተገኘችበት አከባቢ የብዙ ሰው ዕፅም የተገኘበት ምክንያት ወይ የመቃብር ቦታ ወይም ሰው በእንድነት በረኀብም ሆነ በተስቦ ያለቀበት ቢሆን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስንመለከት በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፵፩ ላይ በፈርዖናውያን ዘመነ መንግሥት በግብፅ የሰባት ዓመት ድርቅ እንደነበር እናነባለን። ግብፅ የምታርሰውና ሰብሏን የምታመርተው በዐባይ ወንዝ መላከተኛነት ከኢትዮጵያ በሚሄድላት ዓፈርና የዝናም ውሀ መሆኑ የታወቀ ነው። በውሀ እጥረት ምክንያት እግብፅ የሰባት ዓመት ረኀብ ከገባ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ላይ ሰባት ዓመት በማከታተል እልዘነበም ነበር ማለት ነው። ድርቅ የሕዝብ እልቂትና ፍልሰትን ስልሚያስከትል እሁን ለይተን ባናውቀውም በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ የጠፉም የወረሩም ነገደች መኖራቸውን ለመገመት ይቻላል። የጥንት ግብፃውያን ዐባይ እየደረቀ ሲያስቸግራቸው ወንዙ ወይም አምላኩ የተቆጣቸው እየመሰላቸው ምሱን ባመት ባመት እንዲት ቆንጆ ልጅአገረድ እየሠውለት ይለማመጡት ነበር። እንግዲህ የዐባይ ወንዝ በዚያን ጊዜ ሁሉ ውሀው መቀነሱ የሚያሰየው በኢትዮጵያ የዝናም እጥረት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንዲያውም ከዚያ በፊት ሁሉ የነበረ መሆኑን ነው። የአከሱም አወዳደቅ እንዲት እንደሆነ እንዳንድ አሰቦች ተሰንዝረዋል። ከነሱም ውስጥ የመሬት መንቀጥቀጥ፤ የሌላ ሃይማኖት መነሣት ይገኙበታል። በኔ አስተያየት ድርቅና ተስቦም ሊታከሉ ይገቢቸዋል።

የጥንት ግብፃውያንን ዘመን አልፈን ወደክርስቲያኑና ወደእስላሙ ዘመን ስንመጣ በተለይ ከዓሥራ ሁለተኛው እስከ ዓሥራ አራተኛው መቶ ዓመት እግብፅ የተጻፉትን የማርያም ታምር በግዕዝ ተተርጉመው ሰናነብ በየጊዜው

የዓባይ ወንዝ ውሀ መቀነስ ይህም በሀገራቱ ላይ የእህል እጥረትን ማስከተሉ በግልጽ ይታያል። በየጊዜው የተነሡ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ታሪክም (ገድላቸው) በየዘመናቸው ተሰቦ (ሕማመ ብድብድ) እና ረኀብ (አስረ እክል) ተደጋግሞ መነሣቱን ይናገራል።

ረኀብና ተሰቦ አብዛኛውን ጊዜ አብረው ይሄዳሉ። ተሰቦ በሚል አጠቃላይ ስም የምጠራው ማንኛውም ተላላፊ በሽታ ነው። ግዕዙም እንደዚሁ በጠቃላይ «ብድብድ» ይለዋል። እሱም በሕሳችን እንደሚያምንበት ኃጢአታችን ሲበዛ እግዚአብሔር ለመቀጮ የሚያመጣብን መቅሠፍት ነው። ተሰቦ አርፈን በለመቀመጣችን ራሳችን በራሳችን ላይ የምናመጣው መዐት መሆኑ ነው። ድርሰነ ሚካኤሉ እንደሚያስተምረን ማንኛውም በሽታ (ብድብድም ሆነ ወይም ሌላ ዓይነት) የሚመጣው ከአጋንንት ነው። በዚህ አነጋገር የታመመ ሰው ከፈለገ ጋኔን ይዘኛል ማለት ይችላል። በሽተኛን ወደ ጠበል የምንወስደው ስለዚህ ነው። አጋንንት ሰይጣናት አይደሉም። ሰይጣናት አምላክን በመዳፈር የወደቁ መላእክት እንደመሆናቸው አይጋቡም አይባዙም አይሞቱምም። ሥራቸውም ሰውን ኃጢአት ማስገበት ብቻ ነው። አጋንንት ግን፦

> ሥጋ የሌላቸው በውሀና በየብስ (በደረቅ መሬት) የሚኖሩ ናቸው። እነሱ እንደሰው ይጋባሉ ይረባሉ፤ በመጨረሻም ይሞታሉ። መልካቸው እንደ ሰው ነው፤ እውሬ እባብ ወይም ሌላ ነገር የሚመስሉም አሉ። ሰውን ኃጢአት ማሠራት የነሱ ጉዳይ አይደለም። ግን በሽታ ይሆናሉ፤ ለሞትም ያደርሳሉ። ከነሱ ማህል ብድብድ የሚሆኑ አሉ፤ ንዳድ የሚሆኑም አሉ፤ ሌላ ሌላ በሽታ የሚሆኑም አሉ። በዓለም ላይ ያሉነሱ እንዳችም በሽታ የለም። ሆኖም ያለዉሉ (እግዚአብሔር) ፈቃድ መግደል አይችሉም። ሲፈልጉ (የማንንም) ነፍስ መያዝ ይችላሉ። የዚያች ነፍስ ውቃቢ መልአክ ከልተዉ መረበት ግን ሊያወጧት አይችሉም።

መከከለኛው ዘመን

የግብፅ ድርቅ ከኢትዮጵያ አየር ሁኔታ ጋር የተያያዘ መሆኑን ከተቀበልን ከዚህ በታች ያለውን ከልታተመው ከመጽሐፈ ሐዊ ያገኘሁትን ልጠቅስ እወዳለሁ፦

ከነ በመዋዕለ ቅዱስ ኣኩሚስ ረኅብ ወኃጥኡ እኃው ሥርናየ ወተኃጥኦ እከል ውስተ ኩሉ ምድረ ግብጽ።

በቅዱስ ኣኩሚስ ዘመን ረኅብ ሆነ። መነከሳቱም ሰንዱ ተሞገሩ፤ በግብፅ ምድር ሁሉ እህል ጠፋ።

የመነኮሴዎች አብሮ መኖርን ያመጡ ቅዱስ ኣኩሚስ የኖሩት ከ290 እስከ 346 ዓ/ም ግድም ሲሆንና በሰቸውም ዘመን ግብፅ ረኅብ ከገባ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያም ሰትራብ እትቀርም። ወደኋላው ዘመን በግብፅ ረኅብ እንደገባ የሚያሰረዱ የግዕዝ መጻሕፍት ብዙ ናቸው።

በኢትዮጵያ ላይ በየጊዜው የደረሰውን ችግር በቀጥታ ወደሚመሰክሩት ማስረጃዎች እናተኩር። ከነዚህም አንዱ ሰንክሰር ነው። ሰንክሰር ጻድቃን በዕለተ ሞታቸው በየዓመቱ የሚነበብላቸው መታሰቢያቸው ነው። እሰንክሰሩ ውስጥ ያለው ከግብፅ በትርጉም የመጣልን የሦስት የግብፅና የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳት ታሪክ ኢትዮጵያ በረኅብና በተስፎ እንደተቀጣች ያመለክታል። ሦስት ጊዜም መቀርዉ ከግብፅ የሚመጡልንን ጳጳሳት ስለበደልን ነው።

የመጀመሪያው በያመቱ በጥቅምት 23 ቀን ከሚነበበው ከሊቀ ጳጳሳቱ ከእቡነ ዮሳብ (831-850 A.D.) ታሪክ ውስጥ ይገኛል፦

> በዚህ አበት ዘመን የኢትዮጵያው ንጉሥ (ለሊቀ ጳጳሳቱ) እንደሀ ሲል መልክት ላከባቸው፤ ‹ሊቀመጡበት የተገባዎንና መንግሥቴም በጸጋው የጸናበትን የወንጌላዊውን የማርቶስን መንበር እጅ እነሣለሁ። ራርተውልኝ ጳጳሳችንን አባ ዮሐንስን (መልሰው) እንዲልኩልን አስምንዎታለሁ። ከሀገራችን ሰዎች ከቅዱሱ ወንጌላዊ ማርቶስ መንበር ብርሀን ተሰስተው እግራቸውን እሸሀ ከተሞላበት መንገድ ላይ ያሰረፉ አሉ። እነዚህ ጳጳሳችንን አባ ዮሐንስን አባረሯቸው። ስለዚህም በላያችን በሀገራችን ላይ ከፍ ያለ ስቃይ ደረሰብን።
>
> ሰዎቻችንም ሁሉ በተስፎ ሞቱ፤ ከብቶቻችንም አለቁ። በሀገራችን ላይ እንዲዘንም እግዚአብሔር ሰማይን ከለከለው። ጠሰቶቻችንም ተነሡብን፤ እሸነፉንም። (ይህ ሁሉ የደረሰብን) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለጣሰን ነው።

ሁለተኛው በጎንደር 12 ቀን ከሚነበበው ከሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ፊሊታዎስ (979-1003 A.D.) መታሰቢያ ውስጥ ተጽፏል፦

በዚች ዕለት ደግሞ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ አባት ፊሊታዎስ አረፉ።... በሳቸው የሹመት ዘመን የኢትዮጵያው ንጉሥ ሰዋነው (ለሱዳኑ) ንጉሥ ለጊዮርጊስ ሰከበት። (እንደሀም) አሰው፤ «ከእኛ እስቀድመው የነበሩ ንጉሦች በሠሩት (ክፉ) ሥራ እግዚአብሔር በኛ ላይ ተቆጥቷል። ይኸውም በጳጳሱ በአባ ሊጥሮስ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጣሳቸው ነው። በሊቀ ጳጳሳቱ በአባ ቶዝሞስ (933 A.D. ያረፉት) ዘመን ጳጳሱን ከሹመታቸው አስረው በሳቸው ምትክ ሚናስ የሚባል ውሸተኛ ሾመው ነበር። እነሆ (ከሳቸው ጀምሮ የተሸሙት) ስድስቱ ሊቃነ ጳጳሳት እንድም ጳጳስ አልሾሙልንም። ስለዚህ አገራችን ጠፋ። ሰውም ከብቱም ሁሉ በረኀብና በተስቦ አለቀ። ጠሊቶቻችንም ተነሡብን ከሀገራችን ሰዎች ብዙዎችን ማረኩ። ከተሞቻችንን ዘረፉዋቸው። ዝናም እንዳይጥል ተከለከለ መሬትም ፍሬዋን ነፈገች ጠሊቶቻችንም ከተሞቻችንን አቃጠሉ፤ ቤተክርስቲያኖቻችንንም ዘረፏቸው። እኛንም ከሀገር ወደሀገር ያባርሩናል። ስለእግዚአብሔርና ስለእርቶዶክስ ሃይማኖት (ብለህ) የጭንቂ ተከፋይ እንድትሆን እለምንሃለሁ። ወደ አባታችን ወደ ግብፁ ሊቀ ጳጳሳት ወደ አባ ፊሊታዎስ ደብዳቤ ጽፈህ እኛንና አገራችንን ስለእግዚአብሔር (ብለው ከግዝት) እንዲፈቱን ይኸንንም የወደቀብንንም ጭንቀትና መከራ እግዚአብሔር ከኛና ከአገራችን ላይ ያስወግድልን ዘንድ እንዲጸል የልን፣ ምሕረትም አድርገው ጳጳስ እንዲልኩልን _(እግልደን)።»

እነዚህ ሁለት ጥቅሶች የጉዲትን መነሣት ሰያመለክቱ አይቀሩም። ከዓሥረኛው መቶ ዓመት ወዲህ ስለ እክሱም ዘመነ መንግሥት የሚናገሩ መጻሕፍት አልተገኙም። ቀጥሎ የሚጠቀሰው ማስረጃ የሚያመለክተው በዘጌ ዘመነ መንግሥት በተለይም በዓሥራ ሁለተኛው መቶ ዓመት ላይ ኢትዮጵያ በመለዋ በረኀብና በተለለፊ በሽታ እንደተሰቃየች ነው። ጊዜው አሁንም በትክክል አይታወቅም ግን ዲግሚ አቡነ ገብርኤል የግብፅና የኢትዮጵያ በትረያሬክ በነበሩበት ጊዜ ስለሆነ በዘመናቸው በ 1131-1145 (A.D.) ነው። በዚያን ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ ለሰዶዋ ኢትዮጵያ እንድ ጳጳስ ብቻ የማይበቃት መሆኑን ተረድቶ፤ ግብፃችም ሌላ ተጨማሪ ጳጳስ ቢጠይቅ እንደማይልኩለት ስለሚያውቅ የዚያን ጊዜውን የኢትዮጵያ ጳጳስ አስጠርቶ

የሰቸው ብጤ ሌላ ጳጳስ እንዲሾሙ አስገደዳቸው። በትሪያርኩ አቡነ ገብርኤል ይሽንን በሰሙ ጊዜ የግዘት (ውግዘት) ቃል ከግብፅ ላኩ። ንጉሡ ግዝቱን ስለተላለፈ በሱና በሀገሩ የደረሰውን ቅጣት ስንከሰሩ በሚያዚያ ፲ ቀን ንባቡ አስፍሮታል፦

ወሰበ በጽሐት ይእቲ መልእክተ ግዘት ውዕየ ጽርሑ በእሰት ወክነ ውስተ ብሔሩ ረጎብ ወብድብድ ወተእጎዘ ዝናም ከመ ኢይዝንም ለዕሊሙ ወበጽሑሙ ምንዳቤ ዓቢይ እስመ ንጉሥ ተአደወ ትእዘዘ እግዚእብሔር።

ያቺ የግዝት ደብዳቤ በደረሰች ጊዜ ቤተ መንግሥቱ በእሰት ተቃጠለ። በሀገሩም ረኀብና ተሰቦ መጣ። ዝናምም እንዳይዘንምላቸው ታገደ። ታላቅ ጭንቅም ደረሰባቸው፤ ንጉሡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሏልና።

ከዚህም ዘመን ጥቂት ቆየት ብሎ፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ግና የዓመት ከሦስት ወር ሕፃን በነበሩበት ጊዜ (በ1208 ዓ/ም ግድም መሆኑ ነው።) በሸዋ ረኀብ ገብቶ ነበር። ገድላቸው «ከነ ዐቢይ ረኀብ ውስተ ኵሉ ብሔረ ሸዋ» ይላል። በሽታውም ሆነ ረኀቡ በኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደተስፋፋ አይታወቅም። ግን የሰቸው ተማሪ የነበሩት አቡነ ዜና ማርቆስ በተራቸው በሚያስተምሩበት ዘመን በሸዋ ረኀብ ገብቶ እንደነበረ ገድላቸው ይናገራል፦

ወእምድኅረ እምኑ ወተጠምቁ እሉ ሕዝበ ተንበለት ዘሀገረ ሞረት ወዘምድረ ወግዳ ወተጉለት ከነ ብዙኅ ረኀብ በዓመት።

እነዚያ የሞረት፤ የወግዳ፤ የተጉለት የእስላም ወገኖች ከእመኑና ከተጠመቁ በኋላ በዓመቱ ብዙ ረኀብ መጣ።

እራሳቸው ትልቁ የኢትዮጵያ ጳጳቅና የሃይማኖት መሪ አቡነ ተክለሃይማኖት በዘጠና ዘጠኝ ዓመታቸው የሞቱት በተሰቦ ነው። በዚያን ጊዜ (1306 ዓ/ም ገደማ) እሳቸው በነበሩበት አከባቢ ተሰቦ ገብቶ በመሠረቱት ገዳም በደብረ አሰቦ (የዘራው ደብረ ሊባኖስ) ከሚኖሩት ተከታዩቻቸው አብዛኞቹ አለቁ። ገድላቸው ጳጳቁ የሞቱበትን ሁኔታ ሲገልጽ፦

ወበይእቲ ዕለት በእ ሕማመ ብድብድ ኅቢሙ ወተእኅዙ መንከሰት .... ወሰበ ተእኅዘ አቡነ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት በዝንቱ ደዌ ተጋብኡ ኅቤሁ ዘሶሙ ጾቂቁ።

በዚያች ዕለት የተሰቦ በሽታ መጣባቸው። መነኩሴዎቹም (በበሽታው) ተያዙ.... አባታችን ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት በዚሁ በሽታ በተያዙ ጊዜ (የመንፈስ ቅዱስ) ልጆቻቸው ሁሉም ወደሰቸው ተሰበሰቡ። ይላል።

የእቡነ ኢዎስጣቴዎስ ገድልም ወደ 1330 ዓ/ም ገደማ የእሀል እጥረት እንደነበር ሲያመለክት «ወከነ በውእቱ መዋዕል አበረ እክል ውስተ ኵሉ እህጉር ዘእውደሙ» በዚያ ጊዜ በአካባቢያቸው ባሉ አገሮች የእሀል መታጣት ሆኖ ነበር ይላል። እቡነ ኢዎስጣቴዎስ የሰራዬ ሰው ስለነበሩ «በአካባቢያቸው» የሚለው በሰራዬ አካባቢ ያሉትን አገሮች ነው። ሆኖም ድርቁ በኤርትራ ብቻ ነበር ለማለት አይቻልም።

የደብረ ቢዘኑ (ኤርትራ) አቡነ ዮሐንስ (1362–1440 ዓ/ም ?) ታላቅ ጻድቅነታቸው የታወቀው፤ በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ተሰሚነት ባለው ጸሎታቸው ሰማይን ለጉመው ሦስት ዓመት ሙሉ ዝናም በማስቀረት የኢትዮጵያን ሕዝብ በመገሠጻቸው ነው። በዚህም ምክንያት እሳቸው ሰማይን እንደለ ጉመ እንደነቢዩ ኤልያስ ገደማቸው ደግሞ እንደ ኤልያስ አገር እንደ ቴስቤን ተመስለ እስከዘራ ባመት በመቱ በበዓላቸው እንዘምርላቸዋለን፦

ሰላም ለከ ገሣጼ ሕዝብ አብደንኒ
በከሊእ ዝናም ወጠል መጠነ ፫ ዘመን።
እንበይነ ዝንቱ ኃይልከ ኃይለ አጥናንኒ
ተተርጎመ በኤልያስ ዮሐንስ ከሀን።
ወቢቴስቤን ተመሰለት ቢዘን።

መጥሮን ሕዝብ ሦስት ዓመት ያህል ዝናምና ርኀቡትን በመንሣት
የምትገሥጽ ሆይ፤ ሰላም ለንት ይሁን።
ስለዚህም ስለ እምላክዊ ኃይልህ፤
(ስምህ) ከሀን ዮሐንስ ኤልያስ ተባለ።
(ደብረ) ቢዘንም በቴስቤን ተመሰለች።

በዚያን ዘመን ተከታታይ ድርቅ ብቻ ሳይሆን ተስቦም ተነሥቶ የደብረ ቢዘን መነኰሳት ሳይቀሩ አልቀዋል።

በአፄ ዳዊት ዘመን (1375–1406 ዓ/ም=1382–14 A.D.) በመላው ኢትዮጵያ የተዘረጋ ተስቦ የተነሣ ይመስላል። ሌሎቹን (በዐረብ ታሪክ ጸሐፊዎች የተጻፉትንም) ማስረጃዎች ልተውና በናታችን በቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ገድል የተጻፈውን ልጥቀስ። ተስቦው በዚያን ጊዜ አውሮፖን ያቃጠለት «ጥቁር

ሞት» የተባለው ሰይሆን አይቀርም።

ሁለተኛም እናታችን ከርስቶስ ሠምራ እንዲህ አሉ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ተሰቦ (ብድብድ) በዓለም ሳይ ከጸር እስከ ጸር ተለቀቀበትና ብዙዎች በዎች አለቁ፤ ተጨረሱ። በቤታቸውም ለቅሶና እየየ ሆነ። በዚህ ሁኔታ ፫ ዓመት ቆየ። እንድ ቀን በዋሸየ ሳለሁ ለሰው ልጆች ሁሉ ከእግዚአብሔር ምሕረት አለምን ዘንድ በጎ አሳብ መጣልኝ። በዋሸየ ብቻየን (እየጸለይኩ) ሳለሁ፤ በሩም ዝግ ነበር፤ ከተሰቦ ሠራዊት እንዲ ወደኔ መጣና በዋሸየ በራፍ ቁሞ አለ። በበራፌ ሳይ ሲቀመጥ (በሯ) በገዘ እጄ ተከፈተችለት። ወዲያው እንዲህ ሲል መልስ ሰጠኝ፤ «የእግዚአብሔር ወዳጅ ከርስቶስ ሠምራ፤ እንደምን አለሽ?» እኔም ወዲያው «ሰላምታህን እቀበል ዘንድ አንተ ማነህ?» ስል መለስኩለት። አሱም እንዲህ አለኝ «ስሜ በድል አበራር ነው። አመጣጤም ከሩቅ አገር ነው።» እኔም፤ «እኔ ወደለሁበት ለምን መጣህ?» አልኩት። «ከንቺ ጋር እንድጫወት» አለኝ። «በለ እንጫወት» (አልሁት) በዚያን ጊዜ ቢለዋ ብድግ አደረገና የበራ ስጋ ቆረጠ። ከበራፌ ሳይ የተኙ ሁለት ውሽቶ አሉት፤ ያንን በቢለዋ የቆረጠውን ሥጋ ለነዚያ ውሽቶ ጣለሳቸው። ወዲያው አንዱ ውሽ (ሥጋውን) አንሥቶ ይበላ ጀመር። ሁለተኛው ውሽ ግን አልበላም። እኔም (ለውሽቶ) ጊታ እንዲህ አልኩት፤ «አንዱ ሲበላ ሌላው ለምን አይበላም?» በዚያን ጊዜ ያ ዝም ብሎ ተኝቶ የነበረው ውሽ በሰው ቋንቋ አነጋገረኝ። እንዲህም አለኝ፤ «እንደሰው ልጅ ጊደኛየን እቀማለሁ እንዴ? እኛ የጌታችንን ትዛዝ እንጠብቃለን፤ እንፈራለን እንንቀጠቀጣለንም።» በዚያን ጊዜ «ይኸ ውሽ እንደት በሰው ልጅ ቋንቋ ይናገራል!» እያልኩ እደነቅሁ ተገረምኩም። የነዚያ ውሽቶ ጌታም (እንዲህ ሲል) መለሰልኝ፤ «ውሽቶ እንዲህ በሰው ልጅ ቋንቋ ይናገራሉ። እኛ የፈጣሪያችንን ትእዛዝ እንጠብቃለን፤ እንደናንተ ከእምለክችን ትእዛዝ እንወጣም። ዝሙት አታድርጉ ይለችኋል፤ እናንተ ዝሙት ታደርጋላችሁ። አትስረቁ ይለችኋል፤ እናንተ ትሰርቃላችሁ። አትግደሉ ይለችኋል፤ እናንተ ትገድላላችሁ። እንደዚህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከጣሰችሁ መዓቱን በምድር ሁሉ ይለቅቅችኋል። የእግዚአብሔር ወዳጅ ከርስቶስ ሠምራ፤ ሰሚ ልንገርሽ ከፈጣሪያችን እንደኛ ትእዛዝ ሲመጣ የምንታዘዘው በሊቀ መላእክት ሚካኤል (እማክይኑት) ነው፤ እንፈራለን እንንቀጠቀጣለን። አሱም እንዲህ ይለናል፤ «ሰውን ሁሉ ትገድሉ ዘንድ ከገራችሁ ውጡ» ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ይኸንን ሲለን እንፈራለን እንንቀጠቀጣለን። በዚያን ጊዜ (የኛ) መኪንንትና መሰናንት ከንጉሣቸው ዘንድ ይሰበሰባሉ፤ ከንጉሡም ጋር ይማከራሉ። ንጉሡም ለመኪንንቱ፤ «ሂዱ ከሚስቶቻችሁ ጋር ተመክከሩ፤ ተመክከራችሁም እግዚአብሔር በመጎት እንደደቀጣን ቶሎ እንውጣ» ይሉቸዋል። በዚህ ጊዜ መኪንንት ቶሎ ይመጡና ከሚስቶቻቸው ጋር ይመክከራሉ። ወዲያውም ንጉሡና መኪንንቱ ፈጥነው ይመጣሉ። ከኛ ማህል ግንም ወዳጋሳ የሚቀር የለም፤ ወጣቶችም ሕፃናትም ቢሆኑ። በሚ ልንገርሽ ከርስቶስ ሠምራ፤ እግዚር ከዘዘን በታ ሰንደርስ ንጉሣችን (ከገሬው) ንጉሥ ቤት ይገባል፤ መኪንንትም እንዲሁ ከመኪንንት ቤት። ከኛ ማህል ከሊቀ መላእክት ሚካኤል ትእዛዝ የሚወጣ የለም። በዚያን ጊዜ እንደታዘዝነው እናደርጋለንን፤ እንደናንተ (ትእዛዝ) አናፈርስም። ንጉሥ ንጉሥን ይገድላል፤ መኪንንትም መኪንንትን ይገድላሉ፤ ወጣቶች ወጣቶችን

ይገድሉሉ፤ ሕፃናትም ሕፃናትን ይገድሉሉ፤ ሴቶችም ሴቶችን ይገድሉሉ፤ ወንደች ባርቾ ወንደች ባርችን ይገድሉሉ፤ ሴቶች ባርችም ሴቶች ባርችን ይገድሉሉ። እንደዚህ በሥርዓት የቶምን ነን። አለእኩያው የሚገድል የለም። ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል «(በታ) ቶሎ ውጡ፤ ወደአገራችሁ ተመለሱ» ሲለን ወዲያውኑ ስንፈራ ስንንቀጠቀጥ እንወጣለን። ወደቢታችንም በሰላም እንመለሰለን።

እስከ ዕለተ ሞታችን እንዲህ እንኖራለን። ከርስቶስ ሠምራ፤ ስሚ ሌላ ነገር ልንገርሽ፤ ሰዎች (ስለኛ) «ውሀ ይወስዳቸዋል፤ ወይንም ዝብ ይበላቸዋል።» (ቢሉሽ አትመኝ።) ይሽ ሁሉ እይደርስብንም።» ይሽንን ተናግሮ በጣና ባሕር ላይ በእግሩ ሄደና ደብረ ዳጋ ደረሰ። ወዲያው እኔ ወደለሁበት ተመለሰ። በዚያን ጊዜ እንዲህ ሲል መለሰልኝ «እንግዲህስ ወደገሬ እሄዳለሁ፤ ግን የእግዚአብሔር ወዳጅ ከርስቶስ ሠምራ ሆይ፣ በቅድስት ጸሎትሽ አትርሺኝ።» እኔም «በሰላም ሂድ» አልኩት።

በእዜ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1427-1460 ዓ/ም=1434-1468A.D.) በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው የተሰበሰ መቅሠፍት ቀደም ከሉት መቅሠፍቶች በይበልጥ ይታወቃል። የንጉሡ ታሪክ፤ እንድ ቤቲር ጊሰ ማርያም ሰለሚባል ልዑል የተጻፈው ተአምረ ማርያምና በዚያን ጊዜ የነበሩ ቅዱሳን (በተለይም የነእቡነ ፍሬ ሚካኤል፤ ዘርአ አብርሃም) ገድሎች እየደጋገሙ እንሥተውታል። ታሪኩ እንዲህ ይላል፦

ንጉሡ እዚያ ቦታ (ደብረ ብርሃን) መኖርን ባራዘሙ ጊዜ የተሰበ በሽታ በጣም እየበረታ ሄደ። ብዙዎችም አለቁ። የሚቀብራቸውም አጡ።

ታሪክ ጸሐፊው ንጉሡ ዘርአ ያዕቆብ ያወጣቸውን ሕጎች ሲዘረዝር ተሰበ የፈጀቸው ሰዎች እንዲት መቀበር እንደለበቸው ያወጣውን ሕግ ያነሣል፦

ሰዎችንም ተሰቦ በገደለቻው ጊዜ ያገሩ ሕዝብ ሁሉ ተሰብስቦ ብትርና ጅራፍ በመያዝ ተሰይተው የተጸለየበት ጠበል እየረጨ እንዲቀብሯቸው አዘዘ። (የቀባሪዎቹን) ስማቸውንም ማኅበረ ወንጌል ብሎ ጠራው። ብትራቸውንም በትረ ሙሴ (የሙሴ ብትር) አለው። እንደዚህ ያለደረገ፤ ሁሉም በየሀገሩ የሞተን ያልቀበረ ቤቱ እንደዘረፍ ሀብቱ እንደወሰድበት ለኡሞቻቸው ትእዛዝ አስተላለፈ።

ሕጉ የወጣው ከሰይ እንደየነው ሰው ቀባሪ እያጣ ራሰው የትም ይወድቅ ስለነበር ነው።

በቴርጊሳ ማርያም ከንጉሡ ከዘርአ ያዕቆብ ልጆች አንዱ እንዲያውም አልጋውን የወረሰው በእደ ማርያም ሳይሆን እይቀርም። ስለዚህ ልዑል ከተጻፈው ተአምረ ማርያም ውስጥ እንደህ የሚል ይገኝበታል፦

በዚያን ዘመን ሊነገር የማይችል የተሰቦ ሞት በሰው ሁሉ ላይ ሰፈነ... ከዚያም አንድ ቀን አንድ ሰይጣን የለከፈው ሰው ለአባቱ ያልሆነ ነገር አሰብቶበት መስፍኑ ይሹንን ልጅ (በተርጊሳ ማርያምን) ጠራው። በተርጊሳ ማርያምን እንደጠራ መስፍኑ የላከው ይሹንኑ ያሰበቀበትን ሰው ነበር...። ልጁም እየተጣደፈ ተነሥቶ ተከተለው። ያ ሰው ግን በከፈት በጥድፊያ እያወቀ በወደመው፤ ተሰቦ በለበት መንገድ ወሰደው... እመቤታችን ግን የመስፍኑን ልብ አራርታ ልጁን በደስታ ቃል እነጋገረው። ስበሽታውም (መከላከያ) መድኃኒት ሰጠው፤ «ጠጣ፤ እግዚያብሔር ለበሽታ እንዳይሰጥህ» አለው። ...ንጉሡ (ልጁን) ከመጥራቱ በፊት እንዲ (የበቴርጊሳ ማርያም) ወንድም በተሰቦው ሞተ። ከመስፍኑ ዘንድ ከተመለሰ በኋላም ሌላው ወንድሙ በሆድ በሽታ (በተቅማጥ) ሞተ። በቴርጊሳ ማርያም ግን በመቤታችን በቅድስት ድንግል በጀ ማርያም የጸሎት ኃይል ደነ።... የተሰቦ በሽታ በመስፍኑ እደባባይ በየበታው በጸና ጊዜ መስፍኑ ልጆቹን (ሌሎችንም) ወንዱንም ሴቱንም ጸሎተ ምህላ (እግዚአታ) ወደልዑል እግዚአብሔርና ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል በጀ ማርያም እንዲያቀርቡ አዘዘ። በቴርጊሳ ማርያም ግን በአባቱ በመስፍኑ እደባባይ ሁል ጊዜ ከወንድሞቹ ጋር ደጅ ይጠና ነበር። ከበቴርጊሳ ማርያም ወንድሞች አንዱ አብርት እያለ ሞተ...

ጻድቁ ሕፃን ቅዱስ ቂርቆስ (የውጭ ሰው ነው) በሰማዕትነት ሲሞት እግዚያብሔር የሰጠው ቃል ኪዳን «ቤተ ክርስቲያንህን ከሠራ (ሰው) ዘንድ ተሰቦ አይምጣ፤ በ(ሀገሩም) ውስጥ የውሀ እጥረትና የእህል እሞት አይድረስ» የሚል ስለሆነ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ይሹንን በመተማመን (ወይም የሚያደርገው ቢያጣ) የቅዱስ ቂርቆስን ቤተ ክርስቲያን እሠራ፤ ለጻድቁ መዝሙር ገጠመለት። ለቤተ ክርስቲያኑ ለማገልገያ የሚያስፈልገውን ሁሉ እሱም ልጆቹም እያዋጡ ሰጡ።

ከዚህ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ጎልተው የሚታወሱት የግራኝ ጦርነት፤ የእርሞች ወረራና ታላቁ ድርቅ ናቸው። የግራኝ ጦርነት በ1521 ዓ/ም (1528

A.D) ጀምሮ ያለቀው ከዓሥራ አምስት ዓመት በኋላ በ1536 ዓ/ም (1543 A.D.) ነው። ጦርነቱ መለወጥ አገር የሚነካ ስለነበረ በነዚያ ዘመናት እርሻ የቱን ያህል እንደታ ጉለ መገመት ይቻላል። የዘመኑ ታሪክም (የእዜ ገለውዲምስ ታሪክ መቅድም) ሰያስታውሰው እለለፈም ፦

በዚያን ዘመን ድል በሰንደዲን በር (በዘይላ) እስላሞች እጅ ገባች። በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያኑም ባለሥልጣን ሆኑበት። በምሥራቅ በምዕራብ በደቡብ በሰሜን ያለውን ጦር ሁሉ እሸነፉ። በወርቅ በብር ከህንድ በመጡ የከበሩ ድንጋዮች የታነፁትን ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ እስከመዝረፍ ደረሱ። ከምእመናኑም እብዛኞቹን በሰይፍ ገደሏቸው። ወጣቶችንና ልጃገረዶችን፤ ሕፃናቱን ማርከው ለነውር ሰራ እስከመሸጥ ደረሱ። በዚያን ጊዜ ብዙ ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖት እየተው ወደእስላም ሃይማኖት ገቡ። በሃይማኖታቸው የረጉ ከሥር እንድም አይሆኑም። በዚያ ዘመን እምሰያ የሌለው ታላቅ ረኀብ በኢትዮጵያ ተነሣ።

ጦርነቱ እንደለቀ አሮሞዎች ኢትዮጵያን ሊወርሱ የቻሉት እገሪቷ በጦርነቱ ስለተዳከመች ወራሪን ለመቋቋምና ለመመለስ አቅም ስለነሰት ነው ይባላል። ድርቅ መኖሩን ቢያመለክትም በዚያን ጊዜ ቢገሪቱ የደረሰበትን ቢይኑ ያየ ሰው የገጠመውን መዝሙር ልጠቅስ እወደለሁ። ግዕዙ ወደ እማርኛ ሲመለስ ግጥምነቱ ይቀራልኝ፤ ጣዕሙም ከእቃ ወደ እቃ ሲገለበጥ ነፋስ እንደመታው ጠጅ ይቀነሰል። (መዝሙረ ክርስቶስ መዝሙር 73)፦

ምነው ጌታ ለምን ለዘለለም ጣልከን፤
የተበታተኑትን የምትሰበስብ፤ የጠፉትንም የምትፈልግ።
ግሠጻህን የተቀበሉ ሕዝብህን አስታውስ፤
በመቅሠፍትህ የተገረፉትንም።
ከሁከት ያረፉበት ጊዜ የለቸውም።
ስለዚህ እረመኒዎች ይሰድቡናል።
ጠላት በቅዱሳንህ ላይ ምን ያህል እንደከፋ
ሁሉን ታውቃለህ፤ እንዲነግሩህም አትፈልግም።
እምላክ በሚያደርጉህ ላይ ውርደትን ያመጣል፤
ይልቁንም በቤተ ክርስቲያንህ ላይ።
እነሆ የበሯን መዝጊያ እንደዱር እንጨት አቃጠለው።
እንደ አረኖ ጎጆም ግድግዳዋን ገነጠለው።
ከብሯን አዋረደ፤ አረ ኮሰትም።
የቅዳሴውንም ቤት የከብት ማቆሚያ አደረገው።
በልጅነቷ እንዴት ነበር ከፍ ከፍ ያደረግሃት፤
አሁንስ ከብሯን ለምን ታዋርዳዋለህ፤
ሞገሷንም ታጠፋዋለህ።
በጥፋት ብትወተውትህስ
አረኖ (ቢወርስት) ይሸለልን?
ፈንሔስ ልብህን ያስደሰተው (እምላክ) ሆይ!
እስከመቸ ድረስ በቁጣ ዝም ትለለህ

(ችግራችንንም) ትታገሳለህ?
እንግዲህ ሕግህን ግን ይፈልጋታል?
ስምህንስ በምን እንቀድሳለን?
መጻሕፍቱ እንደሆነ ተታጥለዋል ተደምሰስዋልም።
እናት ለሆዷ ልጆች እንደምትራራ ራራልን።
ሊቶጣ የማይገርፍ ጌታ የታለ?
ተግሪውን የማይገሥጽ አስትግሪም የለም።
ከቁጣ በኋላ የማይምርም አለየንም።
ብትርና አለንጋ ከጥንት ያለ ነው
ሥራውን ላጒደለና ትእዛዝ ለዘነጋ።
ተጸጽቶ የተመለሰንም ይምራታል።
እንደዚህ ያለው በመጻሕፍት ታውቋል፤
ከሰባ ዓመታት በኋላ
ጽዮንን (ኢየሩሳሌምን) እንደራራህለትና
ሰዎቿን እንደማርክ ቸው።
ልጆቿ ከተበታተኑበት ተሰበሰቡ።
የማዳን እራስ ከርስቶስ ሆይ፤
ሕዝብህን ማርክ፤ ጠላታቸውንም ንቀል።
ከተበታተኑበት ሰብስባቸው።
ጥፋተኛ ይማራልና፤ ለማኝም ይሰጠዋልና።
በነቢያት መጻሕፍት እንዲልከው እትብለን፤
«የጥንት ዘመን ጸድቃን ዋኅ፤ ኢዮብ፤ ዳንኤል
እኔን ለመለመን በፊቴ ቢቆሙ እንኳ
ለዚህ ሕዝብ አልራራም።»
ከነዚህ የሕዝብ ታለለቶች (ሰዎች) በጎ ሥራ ይልቅ፤
የጥፋታችን ሚዛን ቢያይል እንኳን
ከሁሉ የሚበልጠውን የናትህን ንጽሕና አስታውስ።
የእግርና የእጅ(ህ)ን ችንካሮችም አስብ።
ትምረን ትራራልን ዘንድ፤ የእምላክ ልጅ እንድኑ ሆይ።

ገላውዲዎስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመቱ ዝናም ጥሎ ሰዎች በእንጨት ሰራ ስር ሽሚያ ከከብት ጋር መጣላታቸው ቀርቶላቸው «ደበ እንደድንጋይ በእግራቸው ረግጠው ነበረ።» ግን ብዙ ሳይቆይ፤ በሁለት ዓመት ውስጥ «ትልቅ ረኀብ ወደቀ፤ በዚህም የክቡርና የልዑል እግዚአብሔር ቁጣ በምድር ላይ ወረደ።»

ግራኝ አሞር ሚዳ እንደወደቀ ጦርነቱ ለጊዜው አቁሞ ነበር። ሆኖም ጥቂት እንደቆየ እንደገና ግጭት ተነሣ። መጀመሪያ እዴ ገላውዲዎስ አደል ዘመተ (አደል ዘይላን ይጨምር ነበረ) በኋላ ደግሞ የግራኝ ባለቤት ወይዘሮ ድል ወምበራ እኔን የሚያገቡ ባሌን የገደለውን የአዴን አጥናፍ ሰገድን (የገላውዲዎስ) ራስ ያመጣልኝ ነው ብሳ ኖሮ እሚር ኑር ገላውዲዎስ እስከለበት ዘምቶ የተመኘችውን እምጥቶ ጥሎሽ ጣለላት። ሞንቅለቱንም ከዘፍ ላይ ሰቀሉት። በዚያን ጊዜ በመሳ ኢትዮጵያ በተለይም በምሥራቅ በኩል ታለቅ ድርቅ ሆኖ ሰውና ከብት እንደቅጠል ረገፈ። በዚያን ጊዜ ሰው እርስ

በርሱ ሰይበላ አልቀረም። ይህ በዓረብኛና በአማርኛ ተጽፎ በሐረር ታሪክ ውስጥ የተገኘው የዚያን ጊዜ ጭንቅ የሚገልጽ ሰይሆን አይቀርም ፦

> በከብት ማለቅ የተነሣ (በሐረር ሕዝብ ላይ) ችጋር ጠናባቸው። ከዚህም በኋላ ገራድ እስላም ተሸመ። ዋሌ ላይ ብዙ ሰው በችጋር አለቀበት። ውሀም ቀድ አልቀረ ስለረጎቡ ጽናት ፮ ሴት ሰው እርዳ በላች። እንድ ሰው ነበር በሐረር፤ በየቀኑ ድህ ይፈልግ ነበረ እያረደ ሊበላው ረኀብ ስለመጥናቱ በ፮ቀን ከ፫ሰዎች ጋር ተቀምጠን የሰው ሥጋ እያረደ የሚበላው ሰውዬ መጥቶ ከደጀፍ ላይ ሥጋውን በሸማው ቋጥር ቆመ። ሥጋ ግዙ የፍየል ሥጋ ነው አለ። (ከኛ ማህል) ፮ደ ሰው ይህ ነገር የሰው ሥጋ መሰለኝ ብሎ ጠረጠረ፤ ጠየቀውም። ቢጠይቀው እዎን አለው። ከዚህ በኋላ ብዙህ አለቀሰ።

ድርቁም ያቆመው የጻድቅ ንጉሥ ራስ ሰቅለችሁ እግዚአብሔር ሊቀጣችሁ ነው፤ አይሆንም አውርዱ ብሎ ደግ መከረ በለመክራቸውና ምክሩንም ስለሰሙ ነው ይባላል። ድርቁ ያመጣው ጉዳት የሚታወቀው በሕዝቡ አለማደግ እንደያውም መቀነስ ነው። ሰምሰሌ እንድ እንደ ኤ እ በ1902 ዓ/ክ (A.D.) የተጻፈ መጽሐፍ በመለከት የግራኝ ጦርነት የተነሣ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከዛሬው (ከ1902 A.D.) ይበልጥ ነበር የሚል እግኘሁበት። ወደ እምስ መቶ ዓመት በሚጠጋ ዘመን ውስጥ ሕዝቡ በማደግ ፈንታ ከለውም ከጎደለ ተስቢና ረኀብ ኢትዮጵያን ሰው እንደ እሸን እንደ ክረምት እግቢ እየፈለ ወደያው የሚጠራባት አገር ያደርጊታል።

የ ጉንደር ዘመነ መንግሥት።

በዚህ ዘመን የተጻፉትን የታሪክ መጻሕፍትና የቅዱሳን ገድሎች እየመረመሩና እየጠቀሱ መጻፍ ድርሰቱን ከመጠን በላይ ያራዝመዋል። ስለዚህ ታሪኩን ሳነብ በማስታወሻ የያዝኳቸውን እንዲሉ አዘረዝራለሁ ከዝርዝሩ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የመስቀል ምልክት (+) በተደረገበት ዓ/ም ያሉት ሲሆኑ ሌሎች አብዛኞቹ ጦርነት ያስከተሏቸው አልቂቶች ናቸው። እነሱንም ያነሣሁት ለምሳሌ ያህል ነው እንጅ የነሱ ብጤዎች እልፍ አልፎ የተመዘገቡ ብዙ አሉ። ረኀብና በሽታውም ቢሆኑ ጸሐፊው ያያቸው ናቸው እንጂ በመሳ ኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደተስፋፉ የሚያውቅ የለም። ጸሐፊው ያሳያቸው በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ብዙ መቅሠፍቶች ይኖራሉ።

ዓ/ም

1583+ ረኀብ ሆነ፤ እህል እንኪ በቅሎ ነበር ግን ከምንቸር የሚባል በሽታ ሰብሉን አጠፋው።
1584+ ረኀብ ተነሥቶ እንዲት ሴት ታንታ ሞተች፤ የቁርበን ጎብስት ተሰረቀ።
1606+ በዚህ ዘመን ግነን ትታ የሚባል ረኀብ መጣ።
1610+ በዚህ ዘመን በጥቅምት ወር ተሰቦ ተነሣ።
1614 የደሞት ሰዎች ጠፉ።

1615 በወግዳ ሕዝብ ጠፋ።
1624 በረን ጠፋ።
1626+ በክረምት ፈንግል የሚሉት ተስቦ ተነሣ።
1630 በዚህ ዘመን እቴ ፋሲል ወደላስታ ዘመቱ፤ ብዙ ሰዎች በረኀብና በብርድ አለቁ።
1632+ በዚህ ዘመን እንበጣ መጣና መሬት የምታፈራውን ፍሬ ሁሉ በላው፤ በሰው ሁሉ ዘንድ ረኀብ ሆነ።
1636+ በዚህ ዘመን በህገሩ ሁሉ ትኩሳት እንደሚያስነሣ በሽታ ያለ ጉንፋን ተነሣ።
1639 በዚህ ዘመን (ንጉሡና ሠራዊቱ) ጉጂም ፋሬ ላይ ሰፍረው ነበር ግን የሞድ በሽታ (ተቅማጥ) በተናቸው።
1645+ በዚህ ዘመን ከበብ የሚባል ተስቦ ተነሣ።
1660 በዚህ ዘመን (እቴ) ወደ ጉጂም ተሸገሩ፤ ብዙዎቹ በረኀብና በሞር አለቁ።
1684 በዚህ ዘመን (እቴ) ዚገምን መቱት፤ ከርስቲያኖች አለቁ።
1685 በዚህ ዘመን (እቴ) ወደደቦኔ ዘመቱ ከርስቲያኖች በረኀብና በውሀ ጥም አለቁ።
1686+ በዚህ ዘመን በክረምት ተናንቄ የሚሉት ረኀብ ገባ።
1692 በዚህ ዘመን እቴ ወደ ጉድሩ ዘመቱ፤ ከርስቲያኖች አለቁ።
1693+ በዚህ ዘመን ወድር (?) የሚባል ረኀብ ገባ።
1696 በዚህ ዘመን ጠሰት መጥቶ የጠሮና የጉንደር ሕዝብ አለቀ።
1697+ በዚህ ዘመን ፈንጣጣ ተነሥቶ ሰው አለቀ።
1702+ በዚህ ዘመን ትል ፈልቶ ረኀብ ሆነ።
1703 በዚህ ዘመን በእምጋራ መሬት ተንሸራቶ ብዙ ሰው ሰጠመ።
1761+ በዚህ ዘመን ኩፍኝ (=ፈንጣጣ) ተነሣ።
1789 በዚህ ዘመን አመድ (በረዶ?) ዘነመ።
1803+
1804+
1805+ ምስት ዓመት ሙሉ (ትግሬን) እንበጣ በላው ኩፍኝ (=ፈንጣጣ ሰውን) ፈጀው።
1848+ በዚያ ዘመን ፈንግል የሚባል በሽታ ተከትሎም (እቴ ቴዎድሮስ የተባሉትን ደጃዝማች ካሳን ነው) የዘመተውንም ሠራዊት ፈጀው ከገርም ያለው በሳገር በበሽታ አለቀ። አልቃሽ እንዲህ አለች፦

በነጋሪትዎ ሞት ተዋርብዎ፤
የወጣው አይገባ ያለው አይቆይዎ።

የአዲስ አበባ ዘመነ መንግሥት።

ንጉሥ ምኒልክ የኢትዮጵያን መንግሥት በጀቸው ለማግበት በሚያቅዱበት ጊዜ በሥርዓተ ንግሣቸውም ዘመን የኢትዮጵያን ከብት ያሟጠጠ የከብት በሽታ ገብቶ ነበር። በሽታውን ያመጣው ጣሊያኖች ሰሜን ኢትዮጵያን ሲይዙ ለሠራዊታቸው ስንቅ ከሀንድ አገር ያመጡት የሥጋና እንዲሁም የጭነት ከብት ነው ይባላል። ይኸ እንዳንድ መጻሕፍት ከንትር የሚሉት በሽታ ያደረሰውን ጉዳት ገና ያልታተመው «የጉጂም ታሪክ» ከዚህ በታች በተጻፈው ሁኔታ ያስታውሰዋል፦

ዳግማዊ ምኒልክ እንደነገሡ ወዲያው የከብት በሽታ መጥቶ በየሀገሩ ፈጀው የሚያርስ በሬ የሚታለብ አሳም ታጣ። የሞተውን ከብት እንኪንና ሰው እውራውና እሞራው ተጠይፍት እሚበሳው እጥቶ አገር ምድሩ ጠነባ። ብቻ ቶርበቱን ለመግፈፍ እንኪን አታከተ፤ ዘመነ ረኀብ ሆነ። ያን ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት (የጎጃሙ) ሽንቅላ ዘመቱና ሠራዊቱን በከብትና በእህል አዳነው።... ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋላቤት ባጅቶ ቢመለስ በጎጃም ረኀብ ጠንቶ ብዙ ችጋረኛ ተጎድቶ በየመንገዱ ወድቶ የነፍስ ምጽዋት እያለ አሰዘነው። ንጉሡም አዘኑ ቢሰውርን እስጠርቶ የጅበለን ጉተራ እስከፍቶ ኢያስጫነ ኢያመጣ በደጀ ሰላም ለወደቀው ሁሉ ችጋረኛ ናሃው። ያን ጊዜ እናት ልጄዋን ጠሳች ዘመድ ዘመዱን ጠሳው። በእህያና በፈረስ ሥጋ እርስ በርሱ ተጣሉ። በረኀብ የሞተውን የሚቀብረው እጥቶ እውሬና እሞራ ተጠየፈው እሳሬ እግዳሚው ዋይ ለልስ ኢያሰ ቅጠል ኢየበጠቀ ሣር ኢያግበሰበሰ በራሰው ላይ ኢየጣለበት ያልፍ ነበር። ያን ጊዜ ከቆሳ ወደደጋ የተሰደደው እንጀሩን ቀጋውን እሞጩን ከደጋ ወደቆሳ የተሰደደው እንኮዩን ከሺሙን ከኩን በመሀል ደረቢ የቀረው ሙረርጁን እከርማውን ሙጂውን ኢየበሳ ወጣ። ለሞት የተቆጠረውም እህል እልመጥነው ብሎ ሰውነቱ ኢያበጠ ሞተ። ፪ቁና እህል በ፩ብር ተሸመተ። [እንድ ብር የዓመት ገቢ በሆነበት ዘመን] ደግሞ ወቦሸማኔ የሚባል እውሬ በነብር ኢየተመሰለ ቤት ኢየቀደደ ብዙ ሰው በሳ፤ ያን

ጊዜ ወቦ ሸማኔውና ጅቡ የቶመ ነው እንጅ የሞተ እይበሰም ነበር። የዚህ ጊዜ እንዲት ደጋ በለቅሶ ዜማ ስታለቅስ እንዲህ አለች፦

ከአቶሬ ላይ ቶሚ ዘቅዝቂ ባየው
የሚከለክለው በሳሞዋይ የለው።
ሰው በሳው እዩት አሳያችሁ።
ተወው እትሉመይ ምነው ኢያያችሁ።

አለች። ከዚህ በፊት በመልክ ቀን እጹ ዮሐንስ ጎጀምን ሰይዘርፈው ከብቱ በጎጀም አረብቶ የሚነጪው ሣር የሚመሰግበት ሜዳ ጠቦት ባሳገሩ ሁሉ በሣር ከልከል በመሬት ድምበር ኢየተጣላ ሲጋመስ ዳኝነት ሲከፍል ይኖር ነበር። እጹ ዮሐንስ ከዘረፈው ከብቱን ፈራ (ንዳድ) ከፈጀው ወዲህ ግን እገሩ ምድሩ ደገሳ ሰውና ፈረስ የሚውጥ የሚያጠልቅ ውድማ ሆነ። የበሬ እርሻ ቀርቶ የፍልፈል እርሻ በረከተ። የፍከራ ኢየሱስ ትንቢት ወየሔርስዋ ለምድር እንዲዋ ወፍልፈል [ምድርን አይጥና ፍልፈል ያርሷታል] ያለው ደረሰ።ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየጋድን ለሀገር ዘእንበለ ፩ጊር [እገሪቱን ያሰንድ ደግ ሰው አሳስቀራትም] ያለው አልቀር ብሎ በጎጀም ንጉሥ ተከለ ሃይማኖት በሸዋ እዲ ምኒልክ ለድጋውና ለሕዝቡ ሁል ጊዜ ይመጸውቱ ነበር።.... በዚያን ዘመን ደግሞ በሸዋ እንሰር ከሚበል እገር እንዲት ሴት ፮ ልጆች በልታ ተይዛ ከእዲ ምኒልክ እደበባይ መጣች ንጉሡም እንሞሞ ከእልፍኝ ደጀፍ ተቀምሞ መረመራት እርሱዋም እምን ቢርስኝ በሳኋቸው አለች። እርሱዋ ግን እንቢንና ፮ ሰው የበላች ትናገ ሥጋ የቀመሰች እትመስልም ነበር። እንጀቱዋ ከጀርባዋ ተለጥቶ እጄዋን እግሩዋን ማደት ወርቡት ትንሽ ደከ ለጥቢ ታሳዝን ነበር። ንጉሡም እንዲት እገሬ ጠፉ ደጋየ ዘመዴ አለቀ ብሎ አዘነ። እንያም ይዘው ያመጡዋት በሳጋርኳዋ የርሱዋን ልጅ ትታ የኛን ልጅ ለይታ ከበላች ፍርድ በቃ ይሰጡን መሞት ይገባታል አሉ። እዲ ምኒልክም ስኔ ስትሉ ተውልኝ ቢጪንታት ቢርባት ነው ደግሞ ሌላ ልጅ ከሳጣሁ ብሎ ነው እንጂ ከባሰባት ልጄዋንም ቢሆን አትተውም ማሩልኝ ብሎ አሰግራት። ወዲያው ልብሱዋን ቀለቡዋን ደርጎ እርሱዋን ማድቤት ልጄዋን ተማሪ ቤት አገባቸው።

ኢትዮጵያን ሦስት ዓመት ያህል ስለገረፉት መቅሠፍት ብዙ ተጽፏል። ያዩትም በሕይወት የደረሰንባቸው ሰዎች ነበሩ። ከነዚህም አንዱ (ልጃቸው መንግሥቱ ለማ በሰተመው መጽሐፈ ትዝታ እንደየነው) አለቃ ለማ ናቸው፦

ከብት አለቀና አደለም ረኀብ የሆነው? ከብቱ ያላለቀበት አገር የለ፤ ጭርስ ብሎ አገር አለቀ፤ በቶላ ምን ምን አልተገኘም። የኔ አበት እስከ ሦስት መቶ ከብት ነበራቸው፤ እንዲት ጥጃ ተረፈቻቸው አሉ። ስሟን «ሰለሀ ድረሽ» አሏት አሉ። ረኃቡን ያስነሣው የከብቱ ማለቅ ነው። በምን ይታረስ? መሬት ሰይታረስ እንዲያው እንደለ ቀረ። ረሀቡ ያን ጊዜውን ከብቱ እንደለቀ ተከተለ፤ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ሰነበተ።

ጅብ ጭርስ አረገው ሰውን። እሁን (የእዲስ አበባ) ሥላሴ የተሠራበት ሰይ የራስ ደስታ አበት የፊታውራሪ ዳምጠው ቤት ነበር የምኒልክ የፈረስ ቤት። እሳቸው ግሺን ተሹመው ሕደዋል ለለታ ወልደ ያራድ ተሰጠ ቤቱ፤ እኛም ኸዚያው ኸንድ ቤት ውስጥ ነነ። ሊሊት «ወሰደኝ! ወሰደኝ! ወሰደኝ!» ሲል ያድራል። በበነጋው ግልዳ ጉባኤ ሲኼድ [ትምርት ስንጀምር ግለት ነው] አለቃ ወልደ ያራድ፦ እንቅልፍ እንደሌለኝ ታውቂል «ለማ፤ ዛሬ ጅብ ስንት ሰው ወሰደ?» ይሉኛል።

«እምስት ስድት እስከ ሰባት ድረስ ወሰደ» እላለሁ፤ በድምጡ በጨኸቱ፤ «ይህን ያህሉ ወንድ ይህን ያህሉ ሴት» እላለሁ። ግ ይወጣል ጅብ ሊከለክል? ሁሉም ደከግ ነው —ረሀብ። ደሞ እሱን ቢወሰደውስ ግን ያድነዋል?

እንዲት ልጅ ወዛ ብላለች —ጋይንቴ ደስታ እሚባል ነበርና እሱ እየረዳት ተነሥታ ፍሎሃ ወረደች። ብዙ ሰው የተቀመጠው እዚያ ነው ይኸ ስደተኛው ሁሉ —ተቀበለና እዚያ አረደና በላት።

ልጆቻቸውን ጥቃቅኖቹን እያረዱ የበሉ ሴቶች ብዙ ናቸው። ሰው ቅጠል በላ፤ ያልተበላ ቅጠል የለም፤ ይኸ ቅጠል ቀረ እሚባለውን ነገር አለውቀውም።

እጨ ምኒልክ ለችግረኛው እርዳታ እንደመጠኑ ማድረጋቸው እልቀረም። ደጃች

ገርማሜ ነበሩ እደ በታች ብዙ እንዲያው ብዙ እሕል ተገኘ ኽሰቸው፤ ብዙ ጉድጓድ ነው ሰው። ለየመቅደሱ ሰው፤ ለየመምራኑ ተሰጠ። እኔም ለኛ ላስተማሪዬ ላለቃ ተመሶ ወርጀ ሞኜ መጣሁ። እኛ ራስ ደርጌ ምስት መቶ ነው አራት መቶ ደውሳ? እሕል ሰው—ኽዚያ ኽገራቸው ኽደ [=ከአድአ] በታች ሮራ አሚበለውን ይዘ ኽጥድጓድ ብዙ እሕል ተገኘ። ለሰደተኛውም ብዙ ሰው። ጎጃሞችንም ሰደዷቸው እዚያ ታች። ጎጃምማ ባጤ ዮሐንስ ተዘርፎ የለም? መጀመሪያ ስደት የጀመረ ጎጃም ነው። ያልመጣ ማን አለ? ትግሬዎችም። አማሌን የመጣ አይመስለኝም።

ይኸ ከሀንድ የመጣ በሽታ ከብቱን ዘጠና በመቶ አንደፈጀውና ሕዝቡም በረኀብ እንድ ሦስተኛው እንደለቀ ይተረክል።

ከዚህ ቀጥሎ ኢትዮጵያን ከደር እስከደር በመግረፍ በሰፈው የታወቀው የጎደር በሽታ ነው። ዕድሜያቸውን በሱ የሚቆጥሩ አሁንም በሕይወት አሉ። የጎደር በሽታ የተበለው ቸነፈሩ በጎደር ወር ስለተሰፈሩ ነው፤ ዘመ ኑም 1911 ዓ/ም ነበረ። እዜ ኃይለ ሥላሴም በሕይወት ታሪክቸው እስታውሰውታል፦

> ከዚህም በኋላ ከጎደር ወር ፭ቀን ጀምሮ እስከ ጎደር ፴ቀን በአዲስ አበባና በሌላውም በኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ የቸነፈር (የግሪፕ) በሽታ ተሰፋፍቶ ነበርና አዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከዐሥር ሺ የሚበዙ ሰዎቹ ሞቱ። እኔ ግን በብርቱ ከታመምኩ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት ተረፍኩ።

ያን ጊዜ አዲስ አበባ ገና የሠላሳ እንድ ዓመት ሕፃን ሆና ሰለ ከዐሥር ሺ የሚበዙ ሰዎች ከሞቱባት ከጃንሆይ ጋር በእግዚአብሔር ቸርነት ከሞት የተረፈው ሰንት ይሆን። ጃንሆይ GRIPPE አሉት እንጅ INFLUENZA በመባል የታወቀው ከዓለም ላይ ወደ ሀያ እምስት ሚሊዮን ሰው የፈጀ ጉንፋን መሰል በሽታ ነው። ከላይ እንደተነገረው በሽታው በሞላ ኢትዮጵያ የዘመተ ስመሆኑ የልዑል ራስ እምሩ ማስታወሻም ተጨማሪ ማስረጃ ነው፦

በሺ፱፻፲፩ ዓመተ ምህረት በርፖና በእስያ እድርጎ የመጣው የነፋስ (የግሪፕ) በሽታ በኢትዮጵያም በመላው አገር ገብቶ ብዙ ሰው ሞተ። ያንጊዜ ሐረር ነበርኩ። እዚህም እሐረርጌ ከህዳር ወር ጀምሮ እስከ ጥር መጨረሻ ሰሞን ድረስ በጣም ከፍቶ በከተማው ውስጥ ብቻ እንኪን ከሰማንያ እስከ መቶ ሀያ በየቀኑ ይሞት ነበር። የታመመው ሰው ልክ እልነበረውም። በሽታውም ትኩሳቱ በጣም እየበዛ እራሱ እየዘረ እአምሮው እየጠፋ ደም እያስታወከ ነው። በቶሎም ከንዱ ወደእንዱ የሚተላለፍ በመሆኑ ብዙው ቢተሰብ እንደለ እየተኛ አስታማሚው ብዙ ችግር ሆነ።

የጉጂም ታሪክ ጸሐፊም በእጥሩም ቢሆን «ነፋስ የሚባል በሽታ ፩ጊዜ መቱን የሚዘልስ [ተርታውን የሚፈጅ ማለት ነው] ከጀርመን የወደቀው መርዝ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በ፩እፍታ ጉጂምና ደሞት ደረሰ ለቀባሪ አታከተ።» ሲል አንሥቶታል። በሐረር ምናልባትም በአዲስ አበባ ሐኪም በሚገኝበት የባሕር ዛፍ ቅጠል እየቀቀሉ መታጠንን ተስፋ አግኝተውበት ነበር። በሌላው በታ ግን የሆነ ያልሆነውን «መድኃኒት» ይሞክሩ ነበረ። የጉጂሙ ታሪክ እንደሚለው፦

> የሕማሙ ባሕል ደግሞ ሳልና ነስር ተቅማጥና ውጋት ፩እይነት ነበረ። እመሉና ምግቡ (መዳኒቱ ማለት ነው) ደግሞ እኩሉ ቂንጣ እኩሉ ጠጅ እኩሉ ኑግና ቆሎ ንፍሮ እኩሉ ቂጣና ቡን ይል ነበረ። ትረፍ ያለው ከርስቶስ ያልቆጠረው የቅቤ ቡና እደነው። በወህኒ ቤት ታሥሮ የነበረው ሁሉ አስታማሚ ሊያጣ ከነሰንሰለቱ ተቀበረ። ያን ጊዜ እባ ኪዳነ ማርያም ፪ኛው ስሙ እባ ውዘውዝ የሚባል ከሰው አስከ እንስሳ እርስዎ የሚል ደግ ባሕታዊ ነበረ። ቁራሽና ውኃ እንጪት የሚያስፈልገውን ሁሉ ሊየለመነ ሊየሰጠ ብዙ በሽተኛ ረደ። ዘመድ የሌለውንም እያስታመመ ቀበረ። ብዙ ትሩፋት ሠራ። ያን ጊዜ ራስ ጎይሉ ደምበጫ ሳይ ሳለ በ፩ወገን ስለ በሽታው እግዚአታ አስይዘ ነበረ። በ፩ወገን የቤት ሥራ ናፋ አድርጎ ደንጋይ ሸክም ጭንቅ ድኃ ጨዋሂ ነገሩ አይሰማ(ለት)ም ነበር። ከበሽታው ይልቅ

ሰው በራስ ኃይሉ እዝኖ ነበረ።

ምን ጣጣ ነው!» ሲባል ሰምተናል። ጣጣ ሲያጋጥመው እንደሀ ያለለም ይገኝ አይመስለኝም። «ጣጣ ፈንጣጣ» ሲባልም ሰምተናል። ታዲያ ጣጣ ምንድነው? የጉጂሙ ታሪክ እንደሚነግረን ከሆነ ይኸም ኢትዮጵያን ከገረፉት በሽታዎች አንዱ ነው።

በዚህም ወር [በጥር 1916?]ክ/ም ሞጌሊ [=ሞያሌ] የሰውነት ነቀዝ የቀሰል ሕመም በሀገሩ ሁሉ ተዘርቶ የእጅና የእግር ጣት ኢያቆሰለ እስቸገር ነበረ። ገን እንደ እሸሀ ነቅሶ ሲያፈርጡት የቁንጫጭት እንቁላል የመሰለ እየወጣ ይድን ነበረ። ይኛ ደግሞ ጣጣ የሚባል ሕማም ራስ ኢያዘረ የሚያም ነበረ። እርሱ ደግሞ በ[ጀን]ኮሳ መገተሪያ በነጠለው ብረት እግሞ [=እግሎ] በእሳት ሲተኩሱት ይድን ነበረ። ስለዚህ ሕማሙን ጣጣ ብለው ስም እወጡለት። እገሌ ወይም እገሊት ጣጣ ታመዋል ይባል ነበረ።

የጣጣቴ መድኃኒት በሀገራችን የተለመደ ነው። በሽታና ረኅብ የሚመጡብን ስለኃጢአታችን መቀሙ ከሆነ ሞያሌና ጣጣ ሰው አስቸገሩ እንጅ ሕዝቡን «መቱን ስላልዘለሱት» ለትንሽ በደላችን ቍንጢሮች መሆናቸው ነዋ።

የኢትዮጵያ ዮሴፍ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በፈርየናውያን ዘመን ሰባት ዓመት የቶየ ረኅብ በግብፅ ገብቶ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ግብፅ በዚያ በረኅቡ ዘመን እንኪን ልትራብ የጉረቤት አገር ሰዎች እህላቸውን የሚሸምቱት እዚያ ነበር። ይኸም የሆ ነበት ምክንያት ዮሴፍ የሚባል ብልህ ሰው ቀደም ብሎ እዝመራው በሠመረበት ዘመን ለከፉ ቀን የሚሆን እህል እንዲከተት ስንጉሡ ስለነገረውና

ንጉሡም የዮሴፍን ምክር ስለተቀበለው ነው። ይኸንን የመሰለ አገር የሚጠቅም ሕዝብን ከእልቂት የሚያድን ምክር ስለሰጠው ምክሩን ራሱ ከሥራ ላይ እንዲያውለው ዮሴፍን ከእስር ቤት አውጥቶ ከበታቹ በመላ ግብፅ ላይ እንደምክትል ንጉሥ እንደጠቅላይ ሚኒስቴር ሾመው። ታሪኩ የሚነግረን የዮሴፍን ብልህነትና ንጉሡ አለፈነቱን በሚገባ ማወቁን ነው። የሕዝብ መሪ ሕዝቡን ከችግር ከማዳን ሌላ ዋና ጉዳይ የለውም። ፈርዖን ይህ ከበድ አለፈነት ስለተሰማው እስከዚያን ቀን ድረስ አልባሌ ለነበረ (ያውም የውጪ አገር) ሰው የጣቱን ቀለበት አውልቆ ሰጠው። ቀለበቱ ጌጥ አይደለም የንጉሡ ማኅተም የተቀረጸበት ሥልጣንን በጅ ማድረጊያ ነው። ያንን ማኅተም የያዘ ጽሑፍ እንደ ንጉሡ ቃል ይከበራል። ኃላፊነቱን በሚያውቅ መሪ ዘንድ የሕዝብ ደኅንነት ከማንኛውም ጉዳይ ተቀዳሚነት እስከዚህ ድረስ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ድርቅ ረኀብ፣ ተስቦ የመንግሥት ጉዳይ ሲሆኑ አይታዩም። እርግጥ አንዳንድ መሪዎች እዚያው እቤተ መንግሥታቸው ድረስ የመጡባቸውን የረኀብ ስደተኞች ሲመጸውቱ ይታያሉ። በመሠረቱ ግን ይሰጉ የነበረው ረኀብ የጦር ሠራዊታቸውን እንዳይቀንስባቸውና ሥልጣናቸውን ሊሰው ሠራዊቱ ያልተጉደበት እንዳይቀናቀናቸው ስለሆነ ያንኑ የተራበውን ሕዝብ ለሠራዊታቸው እህል እንዲያመጣ መልሰው ይጠይቁታል። ለምሳሌ በኅዳር በሽታ ጊዜ የጉጂም ሕዝብ መወዛወዝ እቅቶት ሰለ ለልዑል ራስ ኃይሉ «ፈጠበድኝና እናሞራ: ... ዕለት ዕለት ሺህ ሺህ እንጀራ ራት ሁል ጊዜ ያገባ ነበረ።»

በሀገር ሰላ የሚመጣ ረኀብ የመንግሥት ጉዳይ እንዲሆን ያለመሰልቸት በብዙ ዘዴ ለረጅም ዘመናት የደከመና ውጤቱን በዓይኑ ለማየት የበቃ፤ በዚህም የኢትዮጵያን ታሪክ የለወጠ የኢትዮጵያ ዮሴፍ የምለው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ነው። (መስፍን ጂኖየ ስለሆነ እንቱ እያልኩ መጻፍ ያዳግተኛል።) መስፍንንና እንዳንደኞችንም እንዳበ ኪዳነ ማርያም እንደቅማቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሠሩትን ታላቅ ውለታ ታሪክና የሰማዩ አባታችን በቸርነታቸው ያስታውሷቸው እንደሆነ ነው እንጂ እንዲህ ያሉ የግል ጀግኖችን በይፋ

የሚያከብር መሪና አስተዳደር በኢትዮጵያ ገና አልተነሣም። ዮሴፍ ከእስር ቤት ወጥቶ ሲሸም መስፍን ከሥራው ላይ ተወስደ ታሰረ። መስፍንን እንደማውቀው አሰቸጋሪ ሰው ነው። አሰቸጋሪነቱም ሊሆን የሚገባውን ነገር ምክንያት አያስቀረው በማለት ነው። መስፍን እድሜ ልኩን ሠርቶ አሁን በእዲሱ የጡረታ ሕግ ምክንያት የግል ሥራውን (ጥናት) ያኪያሂዳል። በዚህ ዘመን ሁሉ ቤት አልሠራም። እኔ እንደሚመስለኝ ኢትዮጵያን እንደቤቱ፤ ሕዝቧን እንደቤተ ሰቡ ቆጥሮ ነው። ከመስፍን ጋራ የብዙ ዘመን ጊደኝነት ሲኖረኝ፤ በየጊዜው እየተገናኘን በሐሳብ ስንጋጭና ስንስማማ፤ በየስብሰባውና በየግል ግብዣ ሰው ሁሉ ተበታትኖ ሁለታችን ብቻ ወደኋላ እየቀረን ስንጨቃጨቅ፤ እንደጓደም እዚያው ስናነጋ ኖረን እስከ ዛሬ ድረስ የየት አገር ሰው እንደሆነ አልነግረኝም። ወንድም፤ እኅት፤ አጐት፤ አክስት፤ ወይም ሌላ የሥጋ ዘመድ ይኑረው አይኑረው አላውቅም። እናት አባቱ በልጅነቱ እንደሞቱ እንደጋጣሚ እንድ ቀን አውርቶልኛል። ያንንም ያነሣው እናቱ በሕይወቱ ላይ ያላቸውን ተጽእኖ ለማድነቅ ያህል ነው። በኢትዮጵያ ጉዳይ መስፍን ፊት ለፊት ያለ ይሉኝታ ያለፍርሀት ስለሚናገርና ስለሚጽፍ የሚያደንቁት ብቻ ሳይሆኑ የሚቀየሙትም አይጠፉ። ለወቀው ሰው የመስፍን ቸርነትና ርኅሩኅነት ሞገደኛነቱን እንደሌለ ያደርጉታል።

በ1949 ዓ/ም ትግሬ ላይ ዝናም ሳይጥል ቀርቶ በ1952 ዓ/ም ላይ ረኀቡ ሰውን መቱን መዘለስ ደርሶ ነበር። ለጠቅላይ ግዛቱ ሕዝብ ለርዳታ በቅድሚያ የደረሰለቸው መስፍን ነው። ከሸዋ እህል ያለቸው ሀብታሞች እየፈለገ በነፃ እንዲሰጡ አሰሪድቶ የሰጡትን ወስደ አከፋፈለ። አልበቃም፤ ብዙ ሰውም አለቀ። መስፍን ግን ስንቁን ሳይቀር ሰጥቶ እዲስ አበባ ተመልሶ የገባው ጠኔ እያግተረተረው በብዙ ማቃሰት ነው።

በ1965 ዓ/ም በወሎ ስለደረሰው ረኀብ የማናውቅ ብዙ አንሆንም። እንዲያውም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመውደቅ ያበቁት ምክንያቶች ሲቆጠሩ እሱም እንደንደ ይገባል። በዚያን ጊዜ በወሎ ረኀብ

መግባቱ በምስጢር ተይዘ ኖሮ ምስጢሩ የወጣው JONATHAN DIMBLEBY የሚባለው እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ በፊልም እንሥቶ ስለሰየ ነው ይባላል። ይኸንን ጋዜጠኛ በኢትዮጵያ አዲስ የተቋቋመው ወታደራዊ መንግሥት ምስጋናውን ሊያቀርብለት ተጠርቷል ተብሎ እስተማችን ውስጥ አይተነዋል። ሚስተር ደምብልቢ መመስገን ቢገባውም የወሎን ረኀብ ያወጣ የመስፍን ጥሪት እንጂ እንግሊዛዊው አይደለም።

በዚያን ጊዜ እኔ የዩኒቨርስቲ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዴንት ነበርኩ። መስፍን የማኅበራችን የሥራ ፕሮግራም ሹም ነበረ። የሥራ ፈጻሚዎች ስብሰባ ላይ ምን የሥራ ፕሮግራም የሱ ኮሚቴ እንደወጣልን መስፍንን ብጠይቀው፤ «ረኀብ በወሎ ገብቷልና ዐቅማችንን ሁሉ እሱን መቋቋም ላይ እናውለው። ሕዝቡ ተርቦ የሞተውን በመንገድ እየቀበረ ከወሎ ድረስ በእግሩ እየተጓዘ አዲስ አበባ የመጣ አለ፤ ግን ማህል ከተማ እንዳይገባ ከተቤ ላይ በፖሊስ ታግዷል። ከጥቂት ቀናት በፊት ከደከተር አብርሃም ደሞዝ ጋራ አብረን ሄደን በዓይናችን እይተናል።» አለን። (ዘመኑ ስለራቀ ቃሉን በትክክል አልጠቀስኩት ይሆናል።) ስብሰባውን እንደጨረሰን ከተቤ ወሰደ እመንገዴ ደር የፈሰሰውን ሕዝብ አሳየን። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በነገሩ እንዲገባበትና እርዳታም እንዲሰበሰብ ብንጠይቅ (ያን ጊዜ እኔ ጄኔቭ የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነበርኩ።) መጀመሪያ ተጨባጭ ማስረጃ እንድናመጣ አስፈለጊውን ገንዘብ ብቻ ሰጠን። መጋቢት መጨረሻ ግድም ዓርብ ዕለት ደከተር አብርሃም ደሞዝ፤ ደከተር አሉላ አበተ፤ እኔ ሆነን ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ሲሰና አይሮፕላን ተከራይተን ወደወሎ ሄድን። የደሴን አከባቢ፤ ወደሰሜንም እስከ ወልድያ ድረስ ወደታችም ባቲ ድረስ የቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በዋሰኝ ለንድሮሽር መኪና እየተዘዋወርን በችጋር የሚያልቀውን ሕዝብ አነጋገርን። ድምጻቸውንም በቴፕ ሪከርደር ቀድተን ጣሪሞት ከያዝቸውም እንደንደችን ፎቶግራፍ አንሥተን እሑድ ወደማታ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። ረኀብ የሚያንፈራፍረውንና እውሬ የሚገነጥለውን ሰው ከሚራ እያስተከከሉ ፎቶግራፍ ማንሳት ብዙ ልዩነት የለውም። የኒያ የሽግግሌ

ጥርስ በከሜራየ ብቻ ሳይሆን በአእምሮየም ስለተቀረጸ አሁንም ወለል ብሎ ይታየኛል። እንዲያውም እየዘገነነኝ ለብዙ ቀናት እበንን ነበረ። መስፍን እውሮፕላን ማረፊያ መጥቶ ሁለትንንም በየቤታችን አደረሰን።

ከቤት ስገባ ለካ የትልቋ ልጄ የልደት በዓል የሚከበርበት ቀን ኖሮ ከፈረንጅ አገር የመጣለትን አዲስ ልብሷን ለብሳ፤ አዲስ ጫማ ተጫምታ፤ የኤንሪኮ ኬክና ብስኩት የአገር ድፎ ዳቦም በጠረጴዛው ላይ ተንጣሎ፤ ጊደሮቿ ሁሉ ዓይን የሚማርክ ልብስ ለብሰው ስጠበቅ ደረስኩ። የመንገዳችንን ሪፖርት ለነገ ማድረስ አለብኝ የሚል አጥጋቢ ምክንያት ሰጥቼ የሥራ ጠረጴዛዬ ወዳለበት ክፍል ዘር አልኩ።

ያዘጋጀሁትን ሪፖርት በማግስቱ ለአሱሰና ለአብርሃም አሰይቼ በዋናው ላይ ፈረምንበት፤ እሱን ለኔ አስቀርቼ የተባዛውን ለመስፍን ሰጠሁት። መስፍን ሪፖርቱን፤ ፎቶግራፎችን፤ ቴፕን ሰብስቦ DROUGHT AND ITS CONSEQUENCES የሚል የጂኦግራፊ «ትርኢት» አሰየ። ተማሪዎቹ ያንን አይተው በማግስቱ ሰለማዊ ሰልፍ አደረጉ። ሕዝብ በረኀብ እያለቀ እንማርም አሉ። እኔም ከዚያ ወዲህ ወደ ማስተማሪያ ክፍል አልተመለስኩም። የዚያን ጊዜው ረኀብ ሁለት መቶ ሺህ ሰው ፈጀ የሚባለው የኛ ሪፖርት ያመለከተውን ቁጥር በመቀበል ነው። የወሎ ረኀብ ድብቅነቱ የወጣው ያን ዕለት ነው። መስፍን ከዚያ ቀደም ብሎ ፖርላማ ውስጥ ያሉትን የወሎ ተወካዮች ሞከሯቸው ነበረ፤ እንደተማሪዎቹ ኃይል አልነበራቸውም። ሪፖርታችንን በውጪ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደየውጪው አገር ቂንቂ ተርጉመው ጋዜጣ አወጡት። ሚስተር ደምብልቢ ያንን አይቶ ነው ወደኢትዮጵያ የመጣው። አዲሱ መንግሥት ምስጋና ሲያቀርብለት ለማየት እንድንችል ያህል በስነ ሥርዓቱ ላይ እንድንገኝ ተጋብዘን ቢሆን ዝርዝሩን ለመጻፍ ያመቸን ነበረ።

መስፍን አገሪቱ እንዴት የቱን ያህል ለረኀብ እንደተጋለጠች መሠረታዊ ጥናቱን አሰትሟል:- Mesfin Wolde Mariam, Rural Vulnerability to Famine in Ethiopia. Vikas Publishing house Pvt. Ltd; New Delhi/ Addis Ababa, 1984. ጥናቱ ለሀገር

መድኅን የሚሆኑ ሐሳቦች ስላሉበት ስለድርቁ ለንግድ በጥድፊያ ከተጻፉት ከሌሎች መጻሕፍት ጋር በእንድ አይታይም። የሚያሰዝነው መስፍን በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ስለራሱ ልናውቀው የሚገባውን ያህል አልጻፈም። ስለድርቅ ሁኔታ ጠለቅ እድርጎ ለማወቅ የሚፈልግ ይኸንን የመስፍን መጽሐፍና በታሪኩ በኩልም የሪቻርድ ፖንክረስትን ድርሰቶች ማንበብ ያስፈልገዋል:- Richard Pankhurst, "The History of Famine and Pestilence in Ethiopia prior to the Founding of Gondär," Journal of Ethiopian Studies, Vol. X (1972); "The Earliest History of Famine and Pestilence in Ethiopia," Ethiopian Medical Journal, Vol. XI (1973); The History of Famine and Epidemics in Ethiopia Prior to the Twentieth Century, Addis Ababa 1985.

መደምደሚያ

ከታሪክችን ታላላቅ ምዕራፍች አንዱ የሚመስከረው የኢትዮጵያ መራት የኢትዮጵያን የልጆቿን ደም ጠጥቶ፣ በልጆቿ ሥጋ ደብሮ፣ የልጆቿ አጥንት የሚመረትበት መሆኑን ነው። ገበራዎቹ ሠለስቱ አጋእዝት ወይም ሠልስቱ አጋንንት ረኀብ፣ በሽታ፣ ግዢዎቻችን ናቸው። በእናታችን በክርስቶስ ሠምራ አነጋገር እነዚህ ሁሉ ከልዑል እግዚአብሔር የሚላኩ ስለሆኑ የእናታችንን ቅዠት እርእያ በማድረግ ለሁሉም እንጸልይላቸው። ወምድርኒ ትግብር ፈሲክ ተጎጂበ በደመ ውሉዳ፣ ወዚንም መደ ግብፅ ሰዲ።

ረሃብ ድርቅና መንስኤዎቻቸው

(ከገብርኤል ደንኤል)

ይህ ፅሑፍ በምንም ረገድ የተሟላ ነው በማለት የቀረበ ሳይሆን ለእንባብያን በርዕሱ ላይ ያለኝን ውሱን ግንዛቤ ለማካፈል ነው። እብዛኛውን ጊዜም በንባብ፣ በውይይትና በተመከር ላይ የተመሰረተ ነው።

የርዕሱ አንገብጋቢነት፣ ሁለገብነትና ሁለአቀፍነት አንባቢያን በርጋታ እንዲያስቡበት፣ በሰፊው እንዲተኹበትና መፍትሔ እንዲጠቁሙበት ያስገድዳል።

ይህ ሁኔታ ዓለም አቀፋዊነት ያለው ስለሆነ ከቁጥር ውጭ የሆኑ ተፅዕኖዎችም ሊኖሩ ስለሚችሉ የሚጠቁመው መፍትሔ መለምታዊና ሙከራዊ የመሆን ዕድል ሊኖረው ይችላል። እንደአከባቢውም ተፈፃሚነቱ ይለያያል።

የፅሑፉ ጭብጥ ከሞላ ጉደል ረሃብና ድርቅ ሰው ሰራሽ ችግር ነው፣ ስለዚህም መፍትሔው ሰው ሰራሽ ነው ወደሚለው ያዘማል።

ይህ ማለት ግን የተፈጥሮን ተፅዕኖ በማኪስስ ሳይሆን ሰው የሚችለውን ከልቡና በትክክል ከፈፀመ የቀረው ችግር እስከዚህም ላይሆን ይችላል በማለት ነው። ተፈጥሮን ማማረር መጀመሪያ የእትምን ከደረሱ በኃላ ቢሆን ይመረጣል።

ፅሑፉ በሚከተሉት እርዕስተ ነገራት ተከፍሎ ቀርቧል ፦

፩ መንደርደሪያ
፪ ረሃብ በታሪክ
፫ ረሃብ በኢትዮጵያ
፬ የረሃብ መንስኤዎች

1 የተዘበ የእየር ጠበይ
   ሀ ዝናብና ድርቅ
   ለ የዝናብ መዘበት ምክንያቶች

2 የተዘበ የተፈጥሮ ሃብት እስተዳደር
   ሀ የውሃ ሃብት
   ለ የደን ሃብት
   ሐ ለም እፈር
   መ እሣ፣ የዱር እውራና የቤት እንስሳት
3 ጦርነትና ረሃብ
4 የተዘበ ፖሊሲ
5 የተዘበ ቴከኖሎጂ

6 ድኅነት
7 ጤንነትና ረሃብ
8 እንበጣና ረሃብ
፭ መደምደሚያ

፩ መንደርደሪያ

የረሃብ መሠረቱ የዕለት ጉርስን ሊያሰገኙ የሚችሉ ተፈላጊ ነገሮች ያለመሟላት ነው። ረሃብን ያለመከላከልና ያለማስወገድ ጉዳይ በእሁኑ ዘመን የድህነትና የአስተዳደር ጉድለት ነፀብራቅ መሆኑ ገሃድ ነው። የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጉቱን ለማርከት የተለያዩ ዘዴዎችን ሲጠቀም ቆይቷል። የምግብ ፍላጉትን እስመልክቶም ፍራፍሬ ለቅሞ አውሬ አድኖ ተከፍሎ በልቶ ኖራል። ከዚያም ጎብረተሰብ እየሰፋ፣ እየተከፋፈለ በመሄዱና ፍላጉትም እየጨመረ ስለመጣ አምርቶና አርብቶ መብላት ተጀመረ። ብሎም አምራችና በሳተኛ ከፍል ስለተከሰተ ለገበያ ማምረትና ገዝቶ መብላት ተስፋፋ። የዚህ አዝማሚያ በለገንዘቡ ሲበላ ገንዘብ አልባው ያም ማደር ሆነ። የያም ማደር ለገንዘብ አልባው ብቻ ሳይሆን በበሽታ ለተጠቃው፣ ተፈጥሮ ምርቱን ለደበየበት፣ የሠለም ማጣት ማምረት ለከለከለው ወዘተ ሁሉ ደረሰው።

ረሃብ ከፍተኛው የምግብ እጥረት ደረጃ ነው። አንድ ሰው ረሃብ ደረጃ የሚደርሰው ለረዢም ጊዜ መሠረታዊ ምግቦች ሳያገኝ ቀርቶ፣ ተዳክሞ የራሱን የውስጥ ሰውነት መብላት ጀምሮ፣ መንምኖ ሞት አፈፍ ሲይ ሲደርስ ነው። በዚህ ደረጃ ሰውነት በሽታን ለመከላከል ስለማይችልና ለህዋሰት ተፈላጊ ንጥረ ምግቦች ስለማይኖሩ ረሃብተኛው በመጪ ረሽ በሞት ይገላገላል።

ረሃብ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር አብሮ ያደገ፣ የተፈጥሮና የፍጡራን ውላጅ መልሰም የፍጡራንን ህልውና የሚፈታተን ክስተት ነው። ረሃብ መሰረቱ ምግብ አለማግኘት ሲሆን ከምርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። ለአብዘኛው በኤኮኖሚ ለተደከመው እርሰአደር የረሃብ መንስኤ ተብለው ከሚጠቀሱት የሚከተሉት ይገኙበቸዋል፦

1) የዝናብ በጊዜው አለመዝነብ
2) የማምረት ጉልበት ማነስ፤ ለምሳሌ በበሽታ፣ ማረሽ በለማግኘት፣ ዘር በለማግኘት፣ መሬት በለማግኘት፣ በሰው ሃይል ማነስ ወዘተ_
3) የእርሽ ጊዜ ማነስ ወይም የርሽ ወራት ማለፍ፤ ለምሳሌ በተለያዩ ምክንያቶች ጊዜ መባከን፦ በሰብሰባዎች መብዛት፣ ፍርድ ቤት መመላለስ፣ በዘመቻ፣ በርቀት ወዘተ_
4) ለቤተሰብ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ዋጋ መናርና እነዚህን ለመግዛት ምርትን ያለዋጋው መሸጥ፤
5) የመዋጮ፣ የቀረጥ ወዘተ_ መብዛት፤

6) ለምርት አስፈላጊ ሁኔታዎች አለመሰከት፤ ለምሳሌ ድርቅ፣ ደኖ፣ ውርጭ፣ አንበጣ፣ በረዶ፣ እሳት፣ ጦርነት ወዘተ.



ካርታ-ሀ

አፍሪቃ - በድርቁ ለመጠቃት ላይ ያሉ አገሮች



ካርታ-ሀ



አፍሪቃ
(ተ - የማድጋስካር ደሴት)
ሰሃራ ምድረ በዳ
የአውሮፓ ክፍለ
ግብጽ
ሊቢያ
ቻድ
ሱዳን
ናይጄሪያ
ኢትዮጵያ
ዛየር
ኬንያ
ታንዛኒያ
ዛምቢያ
አንጎላ
ናሚቢያ
ቦትስዋና
ዚምባቡዌ
ሞዛምቢክ
ደቡብ አፍሪካ
ግብጽ
ግብጽ
ግብጽ

ካርታ-ሰ

ኢትዮጵያ

ታሳካቹ ወንዞች

ሀይቆች



፪ ረሃብ በታሪክ

የተለያዩ አከባቢዎች በተለያየ ጊዜያት በመጠን የተለያዩ የረሃብ ዘመናት አሰልፈዋል። ጥንታዊ ተብለው ከሚነገሩለቸው ረሃቦች አንዱ ከሰድስት ሺህ ዓመታት በፊት በድንጋይ ተቀርፃ የተገኘ ቢሆንም የረሃብ ሰቃይ ፅሑፍ ከመጀመሩ በፊትም እንደነበር መገመት ይቻላል።[1]

በ100 ዓ.ም እና በ1921 ዓ.ም መካከል ቻይናን በ1828 ረሃቦች እጥቅተዋታል። ይህም ማለት በየአርባ ቀናቱ አንድ ረሃብ ይከሰት ነበር ማለት ነው።[2]

በእስራ አራተኛው መቶኛ ዘመን ከተሰላፊ በሽታ ጋር በተያያዘ ረሃብ በአውሮጳ እርባ ሰሰት ሚሊዮን ሰዎች ሲሞቱ ሁለት ሰስተኛው የጣሊያን ተወላጅ ነበር።[3] በ1842 ገደማ የአየርላንድ የድንች በሽታ ባስከተለው ረሃብ አንድ ሚሊዮን ህዝብ ሲሞት የዚህኑ ያህሉ ተሰዷል።[4]

ዮሴፍ የሰባቱን ዓመታት የጥጋብና የሰባቱን ዓመታት ረሃብ ዘመን ሲተነብይ የምሰሩ ፈርአን እገሩ በረሃብ እንዳያልቅ እህል በ ጉተራ እንዲከዘን አዟል።[5]

በ1951-53 ዓ/ም በቻይና በሚሰጢር የተያዘው ረሃብ እስከ 64 ሚሊዮን ህዝብ በመጪ ረሰ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ከፍተኛው ነው ይባላል።[6]

በአፍሪቃም ተመሳሳይ የረሃብ ክስተቶች በተለያዩ ጊዜያት ነበሩ፤ አብዛኛዎቹ በፅሑፍ ማህደር ስለአልሰፈሩ ያደረሱት ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ መገመት ያስቸግራል።

በ1960-61 በናይጀሪያ አገር በባያፍራ እርስበርስ ጦርነት ያስከተለው ረሃብ እስከ አንድ ሚሊዮን ተኩል ህዝብ ጨርሷል።[7]

ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ከሃያ የማያንሱ የአፍሪቃ አገሮች በረሃብ ተጠቅተዋል። ለረሃብ የተጋለጠውም ህዝብ ብዛት እስከ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። በጣም የተጠቃው የአፍሪቃ ምዕራብ ክፍል የሳሄል (SAHEL) ተብሎ የሚታወቀው የሞርታኒያ፤ ሴኔጋል፤ ቡርኪና ፋሶ፤ ቻድ፤ ኒዤርና ማሊ አከባቢ ሲሆን የዚሁ ወሰረን ሱዳንን ኢትዮጵያንና ሶማሌን አዳርሷል።

የሚቀጥለው የአፍሪቃ ካርታ በድርቅ በሃይል የተጠቁትን፤ በመጠኑ የተጠቁትንና እስከሁን ደህና የሆኑትን ያሳያል። እንደሚታየው ከግማሽ በሰይ የሚሆኑት በድርቅ ተጉድተዋል (ካርታ ሀ)

ከሰይ ከተጠቀሱት የረሃብ ሁኔታዎች መነሸ ናቸው ተብለው ከሚነገርሰቸው አስፀዕኖች መካከል ድርቅ፤ ጦርነት፤ብዝበዛ፤ በሽታ፤ የአግዚር ቁጣ ወዘተ.. ይገኙበቸዋል።

የአፍሪቃ አገሮች (አብዛኛውንም ከሰሃራ ምድረ በዳ ደቡብ የሚገኙት)

ከፍተኛ የውሃ ሃብት አሳቸው። አብዛኛዎቹም የውሃ አከላት ዓመቱን በሙሉ ሳያቋርጡ የሚፈሱ ሆነው ስለሚገኙ የዘመኑ ረሃብ ሊባባስ የቻለበት ዋንኛ ምክንያት እነዚህን ወንዞች በሚገባ ባለመጠቀም የተነሳ መሆኑ ግልፅ ነው።

ሁለተኛው የአፍሪቃ ካርታ (ካርታ ለ) የሚያሳየው ታላላቆቹን የአፍሪቃ ወንዞች ነው። ካርታው እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ በድርቅና በረሃብ የተጠቁት አከባቢዎች በቂ የውሃ ሃብት ያሳቸው መሆናቸውን ነው። ይህ የሚያመለክተው የረሃቡ ዋና ምክንያት ድርቅ ወይም የተፈጥሮ ሃብት መጒደል ሳይሆን የተፈጥሮሃብት በሚገባ ባለመጠቀም መሆኑ ነው።

በእንግሩ እንደሚታየው የሰሜን አፍሪቃ በረሃማ አገሮች ወንዞችም ቢኖራቸው የረሃብና የድርቅን ስጋት የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶችን በመጠቀም እንደሰወገዱ ነው።

፫. ረሃብ በኢትዮጵያ

በተለያዩ አከባቢዎች የተለያዩ መጠን ያሳቸው ረሃቦች ሳይታወቁ መኖራቸው ቢገመትም መዝገብ የያዘው ረሀብ በመጽሐፈ ስንክሳር[8] የተጠቀሰው የዘመነኛው መቶ ዓመት ሲሆን እሱም በህዝብ ሐጢዓት የተነሳ እግዜር ተቆጥቶ ዝናብ ስለከለከለ ድርቅ ያስከተለው ነው። በ፲፪ኛው መቶ ዓመት እርግማን ያስከተለው ረሃብ ህዝብ እንደፈጀ ይኸው መፅሐፍ ይናገራል።

በዘመነ እምደፅዮንም (1306–1336) እሰቃቂ ረሃብ እንደነበር ይታወቃል።

በ1512–18 ፖርቱጋሊዊው ተጒዥ ፍራንሲስ አልቫሬዝ በትግራይ አንበጣ አህልና ትጠሉን እንዳደጠየውና ህዝብ በረሃብ እንደተጠቃ ፅፏል።

በ1500–32 በልብነድንግል ዘመን፣ በ1532–61 በገላውዲዎስ ዘመን እንዲሁ ረሃብ ነበር። በ1624–59፣ በ1739፣ በ1814 የእንበጣ ረሃብ ገብቷል። በ1264–65 ረሃብና ተላላፊ በሽታ በሃረር በርከታ ህዝብን ማጥፋቱ ይነገራል። በ1336–64 በሰይፈያሬድ ጊዜ በሽታና ረሃብ ገብቶ መላ ኢትዮጵያን እደብይቷል። በ1427–28 በሽታውና ረሃቡ በሰፋት ይዘ የአብሲኒያን ህዝብ ከንጉሡ ጭምር ገድሏል።

ከ1600–1700 ዘጠኝ ታላላቅ ተላላፊ በሽታና ስድስት ከፍተኛ ረሃቦች በኢትዮጵያ ነበሩ።

ከሁሉም አልቶ በሰፋትና በጥልቀት የተፃፈለትና የኢትዮጵያ ታላቁ ረሃብ ተብሎ የሚታወቀው በደግማዊ ምኒሊክ ዘመን 1881–84 በድርቅ፣ በበሽታ፣ በእንበጣና በጦርነት ቁጥሩ ያልታወቀ ህዝብ የጨረሰው ነው። ይህንኑ ሲተርኩ የምኒሊኩ ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረስላሴ እንዲህ ሲሉ አስፍረውታል።[9] «በዚሁ ዘመን ከእግዜር መዓት ታዘ ለምና በራ እየታመመ ያልቅ ጀመር፣ በዚያም ጊዜ እዜ ምኒሊክ በራ ከለቀ እህል እይገኝም፣ እህል ከጠፋ ሰው አይቆይም፣ ይህ ዓመት በእንስሳ ብቻ አይቀርም ብለው የሸዋ ሰው በየአድባራቱ እየተሰበሰበ

እግዚአ በል ብለው እዋጅ አወጁ።»

«ከዚህ በኃላ በዘመነ ማቲዎስ ላሙ በሬው እልቶ እዬ ምኒሊክም በዚህ አዝነው ነበርና ሥርዓተ መንግሥት ለማድረግ አሳሰቡም፤ መጥሪቢያና ደግ አስበጁ፤ ወታደሩም ባሳገሩም እንዲቆፍር አደረጉ፤ በሬ ሰላለቀ በህያና በበቅሎ በፈረስ ታረሰ፤»

«እናትና ልጅ የሚለያይ ብርቱ ረሃብ ሆነ፤ ፈረስ በቅሎ ተበላ፤ ከረሃቡ ከበሽታው የተረፈውን ጦር ፈጀው።»

በእዬ ኃይለሥላሴ ዘመን (የ1964ቱ) ረሃብ ከአስራ አራቱ አስሩን ከፍሳተ አገራት ጉድቷል።{10} በወሎ ብቻ ከሁለት መቶ ሺህ ሰው በላይ በረሃብ አልቋል። ይህ ረሃብ ለ1966ቱ አብዮት ፍንዳታ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። የወሎው ድርቅና ረሃብ ያስከተለው ዕልቂት በ1967 የመርማሪ ኮሚሺን እንዲቋቋም ረድቶ እንደንድ በለስልጣናት በሃላፊነት አስጠይቋል።

በ ኩለ ኔል መንግስቱ ሃይለማሪያምም ዘመን በ1966 የቀጠለው ድርቅና ረሃብ በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹን ከፍሳተ አገራት አጥቅቷል። በ1976/77 ስምንት ሚሊዮን የሚሆኑ ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ አድርጓል። ከዚህ ውስጥ ወደ ሚሊዮን የሚጠጉ ወደ ጉረቤት አገሮች ሲሰደዱ ሁለት መቶሺህ ህፃናት ያለወላጅ ቀርተዋል። ከሰሰት መቶሺህ የማያንስ መሞቱ ይነገራል።{11}

በተከታታይ የታየው ረሃብ በ1976 ዓም ሰድስት ሚሊዮን በ1977 ዓም አስር ሚሊዮን በ1978 ዓም ሰባት ሚሊዮን በ1979 ዓም ሰስት ሚሊዮን ህዝብ ዕርዳታ እንዲፈልጉ አድርጓል።{12} በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የተከሰተው የድርቅና የረሃብ ሁኔታ በዓለም ከታየው ሁሉ ታሳቁና አሰቃቂው ነው ይባላል።

፬ የረሃብ መንስኤዎች

ረሃብ የረጅም ጊዜና የተለያዩ ምክንያቶች ከሰተት እንጅ በተናጠል የአንድ ነገር ውጤት ወይም በየተወሰነ ጊዜ ቀን ቆጥሮ የሚመጣ ነገር አይደለም።እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሂሳ ቀር አከባቢዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የረሃብ ምክንያት ተብለው ከሚጠቀሱት የሚከተሉት ይገኛሉ።

1) የተዛባ የእየር ጠባይ (ዝናብ፤ ድርቅ፤ ጭቀት፤ በረደ፤ ውርጭ...)
2) የተዛባ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር (ውሃ፤ እፈር፤ ደን፤ ዱር እውሬ፤ ጉልበት...)
3) ጦርነት (የርስበርስ፤ የውጭ ጠላት፤ የወታደር ዘረፋ፤ የገበሬ ውትድርና...)
4) የተዛባ ፖሊሲ (የግብርና ድጋፍ፤ የተፈጥሮ ሀብት ልማት፤ መሬት ይዘታ፤ ሰፈራ...)
5) የተዛባ ቴክኖሎጂ (ማዳበሪያ፤ ድቀላ፤ ፀረ-በሽታ...)
6) ድህነት
7) በሽታ
8) እንበጣ፤ወዘተ

ከዚህ ቀጥሎ ከላይ የተዘረዘሩት በመጠኑ ይገለፃሉ።

1 የተዛባ የአየር ጠባይ

(ሀ) ዝናብና ድርቅ፦ በአሁኑ ጊዜ በብዙ አካባቢዎች አሳሳቢ ሆኖ የተገኘው ለረሃብ ዋና ምክንያት ተደርጉ የተወሰደው የዝናብ ሁኔታ ነው። የዝናብ ችግር ተብሎ የሚጠራው የዝናብ ጠርሲ መጥፋት ወይም ድርቅ፣ የዝናብ በተፈለገው ጊዜ በተፈለገው ቦታ በተፈለገው መጠን አለመምጣትና የዝናብ በብዛት መጣል ወይም ጉርፍ ናቸው።

ገበሬ ለእርሻው፣ ዘሉኑና ከብት እርቢው ለሰሩ በዝናብ ላይ ይመካሉ። በኢትዮጵያ የተለያዩ የዝናብ ክፍለ አካባቢዎች ሲኖሩ ባለቧቸው በዝናብ ላይ የተመሰረቱ የእርሻ ወራት አሉ። ዋናው የእርሻ ጊዜ ከሰኔ እስከ ነሐሴ የሚቆየው መኸር ተብሎ የሚታወቀው ገብስ፣ ስንዴ፣ ጤፍ ወዘተ የሚመረትበት ሲሆን መለስተኛ የእርሻ ጊዜ ከመጋቢት እስከ ግንቦት የሚቆየው በልግ ተብሎ የሚታወቀው ማሽላ፣ በቆሎ ወዘተ የሚመረትበት ነው።

ያለፉት ሃያ ዓመታት የዝናብ ሁኔታ በጣም ወላዋይ በመሆን ገበሬውን ችግር ውስጥ በመጣል ለልመና፣ ለስደት፣ ለሰቃይ አብቅቶታል። በጣም የተጠቁ የሰሜኑና የምስራቁ አካባቢዎች ናቸው። የሰሜኑ አካባቢ ደግሞ አብዛኛው እምራች ገበሬ የሚገኝበት ነው።

በኢትዮጵያ ከ500 ሚሊሜትር ዝናብ መጠን በታች የሆኑ አካባቢዎች ደረቃማ በመሆን ለእርሻ አያመቹም። ለምሳሌ እንደ አዲስ አበባ ያሉ በታዎች በመካከለኛ ግምት በዓመት 1250 ሚሊሜትር መጠን ያገኙ ነበረ፣ እንደ አሥመራ ያሉ ደግሞ 450 ያገኛሉ። በጠቃላይ አብዛኛዎቹ እምራች አካባቢዎች ከ500 እስከ 1500 ሚሊሜትር ግንኙት ያስፈልጋቸዋል።

ከ1974 እስከ 1979 በሰኔና በሐምሌ ወራት በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ከተሞች የተመዘገበው የዝናብ መጠን እጅግ ዝቅተኛ ነበር። ይህም መጠን ለእርሻ ስለማይጠቅም ገበሬው በተከታታይ ችግር ውስጥ ወድቋል። እንደ ብሔራዊ አየር ምርመራ ድርጅት ዘገባ በሰኔና ሐምሌ 1979 የዝናብ ሁኔታ በግምት 80 ከመቶ የማያንሰው የአገሪቱ ምድር ለእርሻ ከሚፈለገው የዝናብ መጠን በታች እንደነበረው ያሳያል። (13)

በእንግሩ ደግሞ የዝናብ መጥፋት እንዲህ ሁኖ ሰለ እልፎ እልፎ የሚመጣ ዝናብ ተጠራቅሞ ይዋል ይመስል ደፍ ይሆናል። የዚህ አይነት ዝናብም በንብረትና በሕይወት ላይ ከፍተኛ አደጋ ከማድረሱም በላይ ለም አፈር እየሸረሸረ በመውሰድ አካባቢውን የበሰ ምድረ በዳ ያደርገዋል። በተጨማሪም እንዳንድ በታዎች የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የተገነቡውን ልፍስፍስ መደቦችና ግድቦች ደዘ ይሄዳል። ይህ አይነቱ ሁኔታ ጉልቶ የታየበትም በነሐሴና መስከረም 1981 ዓም ሰሜን ክፍል የጣለው ዝናብ ሲሆን በአካባቢው ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል። የንቧይ ውሃ ሙሰትም ሱዳንን በማጥለቅለቅ በሱዳን ታይቶ የማይታወቅ ከቁጥጥር

ውጭ የሆነ ሁኔታ ፈጥሯል።

(ለ) የዝናብ መዘበት ምክንያቶች ፡ ለዝናብ መዘበት የተለያዩ ምክንያቶች በብዛትንትና ወይም በጋራ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

እንደ ሃይማኖት መፃሕፍት ከሆነ የዝናብ መጥፋት በሰው ልጅ ጥፋተኝነት የተነሳ የሚከሰት የእግዜር ቁጣ ነው። በሰይንስ ደግሞ ከምድርና ከየብስ ወደ አየር የሚወጣው ውሃ እዘል ትነት ማነስ ወይም ጉም ሰርቶ ሰይቀዘቅዝ ሲቀር የሚከሰት ነው።

ለዝናብ መታወክ እንዱ ምክንያት የደን መጥፋት ነው። ደን ብዙ ውሃ እዘል ትነት ወደ አየር በማውጣት ተመልሶ ዝናብ ሆኖ እንዲወጣ ያደርጋል። የደን መጥፋት በዝናብ ላይ ቅፅበታዊ ተፅዕኖ ያደርጋል። በኢትዮጵያ በተከታታይ ከፍተኛ የደን መጥፋት ታይቷል። በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ምድር አራት ከመቶ ብቻ ነው በደን የተሸፈነው (ዘጠና ስድስት ከመቶው ዛፍ የሌለበት ነው ማለት ነው።) የዘመኑ ዝናብ መጥፋት ከዚሁ ምድረ በዳነት ጋር የተያያዘ መሆኑ ይነገራል።(14)

ሌላው የዝናብ መጥፋት ምክንያት «የከርበንዳዮክሰይድ» ጋዝ በአየር ውስጥ ከመጠን በላይ መከማቸት ነው። «ካርበንዳዮክሰይድ» ብዙ ነገሮች በተለያየ መንገዶች ሲቃጠሉ የሚፈጠር ጭስ ነው። ለምሳሌ እንጨት ሲነድ፣ መኪና ሞተር ሲንቀሳቀስ፣ ፋብሪካዎች ሲሰሩ፣ ሰው ወደውጭ ሲተነፍስ ወዘተ ከርበንዳዮክሰይድ ይወጣል። እብዛውን «ካርበንዳዮክሰይድ» አዝዕርቶች ለእድገታቸው ስለሚያስፈልጋቸው ይጠቀሙበታል። ነገር ግን የደን መጥፋትና የጋዙ መጠን መጨመር ከሞተሮች የሚወጣው ካርበንዳዮክሰይድ በዓየር ላይ በብዛት እንዲከማች ስለሚሆን ውጤቱ ጋዙ በመሬት ዙሪያ ማንጣበብ ይሆናል። ይህም እንደጉም በምድር ዙሪያ የሚንጣበብ ጋዝ በተለምዶ ከመሬት የሚንፀባረቅን የፀሐይ ሙራ እፍኖ በመሬት ላይ ያስቀረዋል። በዚህ የተነሳ የመሬት ሙቀት እየጨመረ በመሄድ ጉም እንዳይቀዘቅዝ በማድረግና ጉምን በመበተን ዝናብ እንዳይኖር ያደርጋል። ይህም የታፈነ ሙቀት ከስተት «የአረንጓዴ ቤት ውጤት» «ግሪን ሃውስ ኢፌክት» ተብሎ የሚጠራው ነው።(15)

ለመሬት ሙቀት ብሎም ለዝናብ መዘበት ተጨማሪ አስትዋፅዖ የሚያደርግ የ«እዘን»(OZONE) ጋዝ ነው። እዘን የሚባለው «እክስጂን» መሰል ጋዝ በምድር ዙሪያ በመንሳፈፍ መሬትን ከፀሐይ ከሚመጣው መርዘኛ «አልትራ ቫዮሌት» (ULTRA VIOLET RAY) ሙራ በብዛት ከመጋለጥ ይከላከላል።

የ«እዘን» ከለላ ከሌለ የመሬት ሙቀት ከመጨመሩም በስተቀር ከፀሐይ የሚመጣው ሙራ ሲበዛ የቆዳ ካንሰርና ሌሎች ጉዳቶችን በእዝዕርት ላይ ያደርሳል። ለ«እዘን» ጋዝ መቀነስ ወይም መሳሳት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ ተብለው የሚጠቀሱት ልዩ ልዩ ፋብሪካዎች የሚጠቀሙባቸው ኬሚካሎች ውጤቶች ናቸው። ከነዚህም ኬሚካሎች መካከል «ክሎሮፍሎሮካርቦን»፣ «ሚቲልክሎሮፎርም» እና «ካርቦንቴትራክሎራይድ» ይገኙበታል።(16) በቴክኖሎጂ የቀደሙ አገሮች እነዚህን መሰል ኬሚካሎች

በመጠቀም በሰማይ ላይ የእዘን ከለሳን በማሰሳት ወይም በመቅደድ ዓለም ለመርዘኛው ሥራ እንዲጋለጥ ያደርጋሉ።

ሌሎች የተለያዩ የፉብሪክ ውጤቶች ወደአየር በመትነንና በመንሰፈፍ ከዝናብ ጋር በመቀላቀል አሲድ ዝናብ በመፍጠር መርዘኛ ሆነው በሕይወት ላይ ጉዳትን ያስከትላሉ፤ እዝዕርቶችም በቀላሉ ይጠፋሉ። በባህር ያሉ እንደ እማ ያሉትንም ለምግብ የሚጠቅሙ ነገሮችም ይጐዳሉ። «አሲድ ዝናብ» በጊዜ ብዛት ደንን በመቀነስ፤ እርሻን በመመረዝ፤ የውሃ ነፍሳትን በመጉዳት ረሃብን የማስከተል ችሎታው በቀላሉ የሚታይ አይሆንም።[17] በዚህ የተነሳ በጀርመን፣ በከናዳና በሰሜን አሜሪክ በቀማቸው በመሞት ላይ ያሉ የዘፍ ዓይነቶች እንዳሉ ታውቋል።

በአፍሪታ አህጉር በርከታ ፉብሪክዎች ስለሌሉ የነዚህ አይነት ጭሰቶ ችግር አነስተኛ ነው እንዳይባል በነፋስ እየታዘለ ያልተበከለው አከባቢ ሁሉ የመበከል ዕድሉ ትንሽ አይሆንም።

በመሰረቱ የዝናብ መታወክ ሰው አመጣሽ ክፍል ቢኖረውም የመሬት አቀማመጥ፣ የፀሐይ ሁኔታ የተሳልቅ እሰተ ጉመራዎች ከስተት በአጠቃላይም ከሰው ቁጥጥር ውጭም የሆኑ የተፈጥሮ ሁኔታዎች እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም ሲባል እጅ አጣጥፎ በመቀመጥ የተፈጥሮና የሰልጣኔ እስረኛ ሆኖ መቅረት ያስፈልጋል ማለት አይደለም። የሰው ልጅ ታሪክ ከአከባቢውና ከተፈጥሮ ሂደት ጋር በመታገልና ሀልውናውን ከማረጋገጥ ጋር የተሰናሰረ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

2 የተዛባ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሃብት ከታደሉ ጥቂት አገሮች አንዷ ነበረች። በመሬት ሰፋት፤ በህዝብ ብዛት፤ በዓየር ጠባይ፤ በመሬት አቀማመጥ፣በውሃ ሃብት፤ በደር አሪቃዊት፤ በከብት ሃብት፤ በእማ፤ በባህር በሮች፤ ወዘተ የሚወደደራት ጥቂቶች ነበሩ።

(ሀ) የውሃ ሃብት:- ኢትዮጵያ በርከታ ወንዞችና ሃይቆች አሏት። ዓመቱን ሙሉ ሰያቋርጡ የሚፈሱ ብዙ ናቸው።

የሚቀጥለው የኢትዮጵያ ካርታ (ካርታ ሐ) የሚያሳየው የታወቁትን ትላልቅ ዓመቱን ሙሉ ሰያቋርጡ የሚፈሱትን ነው። እዚህ ካርታ ላይ ያልተጠቀሱ በአከባቢያቸው የታወቁና እንዲሁም ሰያቋርጡ የሚፈሱትን ለእንባቢያን ትቸዋለሁ።

አበር ከመቶ የሆነው የአገሪቱ ምድር ማለትም መቶ ሃያ ሺህ ካሬ ኪሎሜትር የሚሆነው የውሃ ሽፋን ያለው ነው። የወንዞችም አቀማመጥ የከናሳተ አገራቱ ድንበር እንዲሆኑ በመደረግ ለሁሉም አከባቢዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ዋንኛ ተብለው ከሚታወቁት ወንዞች ጥቁር

ዓባይ፣ ተከዜ፣ ባሮና አካቦ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ፣ አዋሽ፣ አሞና ባርካ ይገኙበቸዋል። በተጨማሪም አስራ አራት ሃይቆች አሉ።

ኢትዮጵያ በዓመት ከአንድ መቶ ቢሊዮን ኩብ የማያንስ ውሃ ወደ ውጭ አገሮች ታፈሰለች። የአሞ ወንዝ በዓመት አስራ አምስት ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወደ ቱርክና (ሩዶልፍ ተብሎ ይታወቅ የነበረው) ሃይቅ ይዘ ይሄዳል። ጥቁር አባይ ደግሞ አርባ ሰድስት ቢሊዮን ኩብ አፈር አዘል ውሃ ይዘ ወደ ሱዳንና ግብፅ ይሄዳል።[18]

የግብፅ ህልውና፣ ስልጣኔና ታሪክ የተመሠረተው አብዘኛውን በጥቁር አባይ ውሃ ነው። የውሃን ጥቅም በመገንዘብም ውሃ እንዳይባክን፣ ለክፉ ቀን እንዲውል በማሰብ ግብፃውያን አባይን በመገደብ ታሳቁን ሰው ሰራሽ ሃይቅ (ናስር ሃይቅ ተብሎ የሚታወቀውን) ከአንድ ቢሊዮን ዶላር ያላነሰ ገንዘብ በማውጣት ጥቅም ላይ አውለውታል። በዚህም የተነሳ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ለእርሻ ውሏል። ከዚህም በስተቀር ግድቡ ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ አገልግሏል። ይህም ሲሆን ግድቡ የፈጠራቸው ችግሮች አሉ። ህዝብን ማፈናቀሉ፣ እንደ ቢላርዚያና አንኪሲርኪያሲስ ዓይን አሰዋሪ በሽታ ማስፋፋቱ፣ የጨው መጠንን በአካባቢው መሬት ላይ መጨመሩ፣ ወዘተ_ በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም።[19]

እንደሊብያ ያሉ በረሃ ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎችም ተፈጥሮን ለመቋቋም ልዩ ጥረት በማድረግ አንዳንድ ቆራጥ እርምጃዎችን ወስደዋል። ሊብያ በ1976 ዓም የከርሰምድር ውሃን በመጠቀም ውሃው በመስኖ አካባቢውን እንዲያገለግል ሺህ ዘጠኝ መቶ ኪሎ ሜትር ቧንቧ በመዘርጋት ብዙ መሬት ለእርሻ እንዲውል ተደርጓል። ይህ ሰው ሰራሽ ወንዝ በሰራ ለማዋል አስራ አንድ ቢሊዮን ዶላር ወጭ ተደርጓል ይባላል።[20]

በኢትዮጵያም በቅርቡ የአዋሽ መስኖ እቅድ ዘጠኝ መቶ የእፋር ዘላን ቤተሰቦችን በሁለት ሺህ አምስት መቶ ሄክታር መሬት ላይ በማስፈር እስር ሺህ ሄክታር ደግሞ ለግጦሽ እንዲውል አድርጓል። በእጋዲንም በዋቢ ሸበሌ ወንዝ በመጠቀም 30,000 የሚሆኑ አሰፍራል። 5000 ሄክታር የሚሆን ለእርሻ ውሏል።[21]

በኢትዮጵያ በመስኖ ሊለማ ከሚችለው መሬት ውስጥ አራት ከመቶ ብቻ ሲለማ ዘጠና ሰድስት ከመቶው እንዲሁ ቁጭ ብሏል።

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ በኢትዮጵያ ለመስኖ ሊውሉ የሚችሉትን የውሃ አካላትና ሊያለሙ የሚችሉትን መሬት መጠን ይዘረዝራል።[22]

ለመሰኖ ሊውል የሚችልና የዋለ መሬት መጠን (በሄክታር)

የውሃ ምንጭ	በመሰኖ ሊለማ የሚችል	በመሰኖ የለማ	ጥቅም ላይ ያልዋለ
ባሮና እከቦ	1,000,000	0	100%
ጥቁር አባይ	581,000	0	100%
ተከዜ፣ባርካ፣ጋሽ፣መረብ	172,000	15,000	91%
አሞ	162,000	0	100%
አዋሽ	153,000	65,000	48%
ዋቢ ሸበሌ	83,000	2,000	98%
ሃይቶች	72,000	7,000	90%
ገናሌ፣ደዋ	25,000	0	100%
ጠቅላላ	2,248,000	89,000	96%

የኢትዮጵያ ሰሜናዊ መከከለኛ አከባቢዎች አቀማመጥ ከረብታማና ተራራማ ስለሆኑ ብዙዎችን ወንዞች በቀላሉ መጠቀም አስቸጋሪ ይሆናል። በእንፃሩ ደግሞ እንዲህ አይነቶች ወንዞች ግፊት ስለሚኖራቸው የኤሌክትሪክ ሃይል ለማመንጪት ይረዳል። መልሶ ይህን ሃይል በመጠቀም ውሃው ወደ ሌሎች ደረቃማ አከባቢዎች እንዲደርስ ማድረግም ይቻላል። ለዚህ ሁሉ በመጀመሪያ በጐ ፈቃድ፣ አጣዳፊ ሁኔታዎችን ማወቅ፣ ገንዘብን በተገቢ ቦታ ማዋልን፣ ዕውቀትን መዘተ ይጠይቃል።

(ለ) የደን ሃብት ፦ የደን አይነት የተለያየና ሰፊ ጠቀሜታ ያለው ነው። በቤት ክልል የእንጨት ምንጭ በመሆን ለማገደ፣ ለከሠል፣ ለቤት መስሪያ፣ ለቤት ዕቃዎች መስሪያ፣ መዘተ ያገለግላል።

በእርሻ አከባቢ ደግሞ አፈር በ ጐርፍ እንዳይሸረሸር፣ የ ጐርፍ ፍጥነት በመግታት ውሃው በአለበት እንዲረጋ ለማድረግ፣ ለእንዳንድ ተከሎች ጥሳና ከለላ ይሆናል። የእከሰጅን ጋዝና ትነትን በማውጣት የአየር ሚዘን እንዳይዛባ ይረዳል። ለዝናብ መፈጠርም ምክንያት ይሆናል። በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የሚፈጠርን የካርቦንዳዮክሳይድ ጋዝ በመጠቀም በአየር ላይ የካርቦንዳዮክሳይድ መጠን እንዳይበዛ ይከላከላል። የደር እውሬዎች መጠለያና መኖሪያም ነው።

አንዳንድ ዓይነት የደን ተክሎች የሳስቲክ፣ የወረቀት፣ የዕጣን፣ የቅመማቅመም፣ የመድኃኒት ምንጭ በመሆንና የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ይረዳሉ።

ከላይ የተጠቀሱት የደን ጥቅሞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአገር እድገት፣ ለረሃብ መኖርና አለመኖር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የደን መጠን የመነመነ ነው። አብዛኛው ደን በደቡብና በምዕራብ ከፍል ሲሆን የዚህ አከባቢ የዝናብ መጠን ከደኑ የተነሳ

የተሸለና ጊዜውን የጠበቀ ነው።

ሃያኛው መቶ ዓመት ሲጀምር (ከሰማኒያ ዓመት በፊት ገደማ) የኢትዮጵያ ምድር አርባ ከመቶው ደናማ ነበር። ከአርባ ዓመትም በፊት (ማለት በ1940 ገደማ) ይህ መጠን ወደ ሃያ ከመቶ ዶርሶ አሁን ግን ከአራት ከመቶ የሚያንስ ነው በደን የተሸፈነው።{23} የደን ሽፋን በኢትዮጵያ በዓመት ከሁለት መቶ ሺህ ሄክታር እየቀነሰ ነው ያለው። በልዩ ልዩ ቦታዎች የዘፍ ተከላ ሥራዎችም ቢካሄዱም ቅሉ ተገቢው እንክብካቤ ባለመኖሩ ከተተከለው ሰባት ከመቶ ብቻ ነው የመፅደቅ አዝማሚያ ያሰየው።

ቀጥሎ ያለው የኢትዮጵያ ክርታ (ክርታ መ) የሚያሰየው ከዚህ በፊት የነበረውንና አሁን የቀረውን የደን ሽፋን ነው። በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ለምልክት እንኳ የሚቀር የደን መጠን እንደማይኖር መገመት ይቻላል።

የደን አያያዝን፣አጠባበቅንና ልማትን በሚመለከት በተለያዩ አገሮች የተለያዩ ድንጋጌዎች ቢደረጉም አብዛኛዎቹ ከተግባራዊነታቸው ይልቅ ስማዊነታቸው ያይላል። በኢትዮጵያም የደን ልማት ቢሮ በተለያየ መልክ ተቋቁሞ እንደነበር ቢታወቅም አብዛኛው ትኩረት የደን ልማት ከቀጥተኛና ጠበብ የገቢ ምንጭነት አንፃር እንጅ ደን አስተዋፅዖ ሊያደርግ የሚችልባቸውን የተለያዩ ገፅታዎች በሰፊትና በጥልቀት በማጤን እይመስልም። በትርቡ ለሰፈራ፣ የግሰሰብንም ሆነ የመንግሥት እርሻን ለመፍጠርና ለማስፈፋት ሲባል የሚወሰደው የደን ማጥፋት ዘመቻ ወደፊት ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በመገምገም እይመስልም።

የደን ሁኔታ ጉዳይ እንዲህ ጉልቶ ባለሰሰበበትና ኢትዮጵያም ደናማ በነበረችበት ዘመን እንኳ ሰይቀር አዬ ሚኒሊክ በአገሩ የዘፍ መቀነስን ሲያዩ ይህንን ለመቆጣጠር አዋጅ አስነገረዋል። አዋጁም ባደ መሬት ይዘ የማይሰራበት ከፍተኛ ቀረጥ እንዲከፍል፣ ዘፍ የተከለ ግን ከቀረጥ ነፃ እንዲሆን የሚያደርግ ነበር። ሕዝቡም በዚህ ተገፋፍቶ ዘፍ መትከል እንደጀመረ ይታወቃል።

መፅሐፍ ቅዱስም የደንን ጠቀሜታ በመገንዘብ ዘርቶች እንዲይቆረጡ፣ እንዲይጠፉ በመምከር ለሰው ህይወት ወሳኝና ምግብ ለጋሽ እንደሆኑ ይናገራል።

የደን ተከላ በብዙ አገሮች እየተከሄደ ቢሆንም፣ በስፊት የጠፉ ደንን መተከት አስቸጋሪ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ የሚተከለው የዘር ዓይነት እጂስ ከመሆኑ የተነሰ ዘላቂነቱ ያጠያይቃል። አብዛኛዎቹ ዘሮች የተሸሻሉ የሚባሉ፣ ለመብቀል ጊዜ የማይወስዱ ለደረቃማ አከባቢዎች የሚሆኑ ናቸው ይባላል። ይህ በመሠረቱ ጥሩ አስተዋፅዖ ቢሆንም ነባር ዘሮች በጊዜ ብዛት የአከባቢውን በሽታ፣ ድርቅ፣ ሙቀት፣ ቁር፣ ተባይ ወዘተ ሁኔታ የመቋቋም ችሎታ ስላዳበሩ ለነዚህም በተመከር ለበለፀጉ ዘሮች ተገቢ ቦታ መስጠት ያስፈልጋል።በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች በአሁኑ ጊዜ የደን ወደማ ለዘር እንኳ የሚተርፍ ፍሬ ያስቀረ አይመስልም። ብዙ ሌሎች አከባቢዎች የማይገኙ የዘፍ አይነቶች በጅምላ

መጥፋት የዘርቹ አይነት ከምድር ገፅታ መጥፋት ማለት ነው። ይህም ማለት ብዙ ሚሊዮን ዓመት ያተረፈውን የዘር ዕድገት ውጤት ማደብየት ነው።(24) መልሶም መተከት አይቻልም። ለዚህ ነው ነባር ዘሮች ተመልሰው እንዲረቡ የሚበለው። አዲስ ዘሮች አዲስ ችግር ይኖራቸዋል።

የደን መውደምን ለመቆጣጠር ደንን የሚፈልጉና የሚያጠፋ ሁኔታዎች መርምሮ አመች መፍትሄ መፈለግ ተገቢ ነው። ለደን መጥፋት ወይም መቀነስ ምክንያቶች የተለያዩ ቢሆንም የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ይሆናሉ።

የከተማዎችና የመንደሮች መፈጠር/መስፈፋት ልዩ ልዩ የእንጨት አስተዋፅዖ ስለሚጠይቁ ይህ እንዱና ዋነኛው የደን ጠር ይሆናል።

መንግሥት ሆነ ግለሰቦችም የእርሻ መሬትን ለማስፋት ብዙ ደኖች አጥፍተዋል።

የተለያዩ ጦርነቶች ጠላት የተሸሸገበትን ቦታ ለማጥፋት፤ መሸሸጊያ ለማሳጣት፤ ያለፍርሃት ወደፊት ለመግፋት፤ የጠላትና የአከባቢውን ኢኮኖሚ/እርሻ ለማውደም በቦምብና በእሳት ብዙ ደኖች አጥፍተዋል። በዓየር ሙቀትና ድርቅ፤ በስህተት፤ በበረሃ የተፈጥሮ እሳት፤ ገበሬዎች ለእርሻ ዝግጅት በሚያደርጉት ቃጠሎ የተነሳ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሰደድ እሳት ብዙ ደን ያጠፋል።

እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎችን ለመግታት ተገቢውን ቁጥጥርና እገልግሎት ማበርከት የሕዝብ ተሳትፎ ማስተባበር ሠልም መገንባት የመንግሥት ሃላፊነት ነው።

(ሐ) ለም አፈር :- አፈር ለእርሻ ወሳኝ ነገር ነው፤ የለም አፈር እለመኖር ወይም ማነስ የእርሻውን ውጤትና ዓይነት ይወስናል። ዝናብ እንኪን እንደልብ ቢኖር ተገቢው አይነት አፈር ከልኖረ ውጤቱ ረሃብ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ከረብታማ አከባቢዎች በጣም ብዙ ለም አፈር በወንዝና በዝናብ እየተሸረሸረባቸው አብዛኛዎቹ ቦታዎች ምድረ በዳነት እያሰፈራቸው ይገኛሉ። ይህ አይነቱ ሁኔታ ሊገታ ከሚችልበት ዘዴዎች ለምሳሌ አፈር ከሌለ ባታ አምጥቶ መጪመር፤ መሬትን በተከታታይ ከማረስ መቆጠብ ወይም ማሳደር፤ ዛፍን በመትከል ሽርሽራን መቀነስ፤ ለመሬት ለምነት አስተዋፅዖ የሚያደርጉ እፅዋት መዝራት ወይም እያቀለቀሉ መትከል ይገኝበቸዋል።

በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓመት 1.6 ቢሊዮን ቶን ለም አፈር በውሃና በነፋስ ይሄዳል። ከእንድ ሄክታር መሃል እገር መሬት በዓመት አርባ ቶን ለም አፈር እየተሸረሸረ ይሄዳል።(25)

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ዘጠና በመቶው ህዝብ በግብርና የሚተዳደርና ኢኮኖሚያቸው በእርሻ ላይ በመሠረቱ እገሮች የዚህ አይነቱ ያልተገታ የለም አፈር ወደ ውጭ መሄድ እጅግ በጣም አሰሳቢና መልሶ መተከት ወይም ማቋቋም የማይቻል ሁኔታ ይሆናል። ይህም መፍትሄ እልባ ወደ ሆነ ረሃብና

ካርታ-፬

(" The Challenges of Drought,Relief & Rehabilitation Commission,Addis Ababa,1985,ቁ,45 ") ላይ የተወሠደ

እልቂት ያደርሰል። እንዲህ እድር ጉ ያመለጠን ለም አፈር በሚገባ ተግበር ለይ ይግየል የሕዝቸውን ህልውናና ኢክኖሚያቸውን ከገነቡት መከከል ግብፅ እንደ ጥሩ ምሳሌ የምትወተስ ናት።

የአፈርን ጠቃሚነት ሊ ጉዴ የሚችሉ ልዩ ልዩ ነገሮች ቢኖሩም በእሁኑ ጊዜ እሰጊቢ እየሆነ የመጣው «የአሲድ ዝናብ» (ACID RAIN) ነው። «አሲድ ዝናብ» ልዩ ልዩ የፋብሪካ ጭሶች (ለምሰሌ «ሰልፈር ዳይአክሰይድ» SULFURDIOXIDE፤ «ናይትሮጂን ዳይአክሰይድ» NITROGEN DIOXIDE ወዘተ) ከእየር ጋር በመቀላቀልና መልከቸውን በመቀየር ወደ አሲድነት ሲቀየሩ የሚከሰት ነው። እነዚህም እንደ «ናይትሪክ አሲድ» (NITRIC ACID) «ሰልፍዩሪክ አሲድ» (SULFURIC ACID) ያሉት አሲደች በዝናብ በመታጠብ ምድር ለይ ይግረፍ እዝዕርትን፤ ነፍሰትን፤ ሰውን፤ ይ ጉዳሉ/ያቃጥሳሉ። ከአፈር ጋርም በመቀላቀል ለም አፈርን ከመመረዝና ጥቅም አልባ ከማድረጋቸው በስተቀር ለምርት የሚያስፈልጉ ነፍሰትን ይገድሳሉ።(26) እንደ ኢትዮጵያ ያሉት ብዙ ፋብሪከዎች የሌሉአቸው ከዚህ አደጋ ነፃ ሊሆኑ ይችሳሉ ቢባልም፤ በተለያዩ ሙኔታዎች የተበከለ ዓየር በነፋስ ሃይል ከእንዱ ክፍለ ዓለም ውደ ሌሳ በቀሳሉ ልሚደረስ ችግሩ ዓለም አቀፍ በመሆን ሁሉንም አገሮች ሊ ጉዳ እንደሚችል መገመት ይቻሳል። ይህ ቲክኖሌጂ የወለደው ከስተት ወደፊት ጉልተው የሚታዩና አሰሳቢ አደጋዎች ማስከተሳቸው አይቀርም። የመሬትም እንደዚህ መመረዝ ለረሃብ አስተዋፅያ በቀጥታ እንደሚያደርግ ግልፅ ነው። ይህ ችግር በእሁኑ ጊዜ በከናዳ፤ በአሜሪከና በአውሮጳ እንደዋና አሰሳቢ ጉዳይ ተወስዷል። ሌሎች የሰስተኛ ዓለም አባሳት ግን ብዙም የመመርመሪያ መሳሪያ ልዕግይኖራቸው ጥናቱም ብዙ ገንዝብና ዕውቀት ስለሚጠይቅ፤ እልፎም ከእፍንጫ አርቶ መመልከት እምብዛም ስለሆነ እንዲህ መሰሎችን ነገሮች እናስተናግድም።

(መ) እሣ፤ የዱር እውሬና የቤት እንስሳት :- ስለረሃብ ከተነገረ እሣና የዱር አውሬዎች የሚያደርጉት አስተዋፅያ በቀሳሉ የሚታይ አይሆንም። እንደ ቻይና፤ ጃፖን፤ ከርያ ወዘተ ያሉት በህዝብ ብዛታቸው የዓለም ሁለት ሰስተኛ ገደማ የያዙ ዋናና ተወዳጅ የምግብ ዓይነታቸው ከቢሔር የሚገኙ እንደ እሣ፤ ሎብስተር፤ ሽሪምፕ ወዘተ ያሉ ናቸው። ስለዚህም የእርሻ ትኩረታቸው በዚህም ጭር ነው። ስለሆነም በመሬት ሳይ ብቻ ተስፉ አድርገው በዝናብና በድርቅ ተጉድተው ለረሃብ እጅ አልሰጡም።

ኢትዮጵያ ቀንደኛ የረሃብ አሰረኛ ብትባልም ያሳት የባሔር ምግብ ሃብት ከፍተኛ ነው።

በቀይ ባሔር ዙጠና ሺህ ከራ ኪሎሜትር እሣና ተመሳሳይ ለምግብ ሊውል የሚችሉ እሣ መሰል ነገሮች ሊጠመዱበት የሚችሉ ከልል አሳት። በዓመት ሊጠመድ የሚችለው የእሣ መጠን 66,000 ቶን ነው ይባሳል። በሽምቅ ሾልቶ ሃይቶችም ሃያ ስድስት ሺህ ቶን እሣ ሊጠመድ ይችሳል። ነገር ግን እብዝኛው ህዝብ እሣና ተመሳሳይ ምግቦች እዘውታሪ አይደለም ቢባልም፤ ተገቢው

ትምህርትና እርዳታ ቢሰጠው ተቀባይነት ያገኛል። በመሠረቱ እማ በእልሚ ምግብነቱ የታወቀ ነው። ከዚህም አልፎ በዓለም ገበያ ከፍተኛ ተፈላጊነት ስለአለው ጥሩ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ሊሆን ይችላል።

የዱር አውሬ ከደን መኖር ጋር የተዛመደ ነው። የደን መጥፋት ብዙ የዱር አውሬዎች እንዲያልቁ ወይም አገር ጥለው ወደ ጉረቤት አገሮች እንዲሰደዱ አድርጓል። የኬንያ የዱር አውሬ ፖርክ ኢትዮጵያን ለቀው በሄዱ እንስሳት እያደገ እንደሄደ ይነገራል። የዱር አውሬዎች ለቱሪስት መሳቢያ ከመሆኑም በሰተቀር በተለያዩ አከባቢዎች እንደየአይነታቸው ለምግብነት እየታደኑ ይውላሉ። የቤት እንስሳትን ማለትም ላምን፣ በሬን፣ ፍየልን፣ በግን፣ ዶሮን ወዘተ አስመልክቶም ኢትዮጵያ በዓለም ታድለዋል ከሚባሉት ጥቂት አገሮች መከከል ነበረች። የከብትን ብዛት በሚመለከት በዓለም አሰረኛነቱን ስትይዝ፣ በአፍሪቃ ተወዳዳሪ የለትም። ከላይ የተጠቀሱት እንስሳት ሥጋ ከመለገሳቸው በስተቀር የወተት፣ የቅቤ፣ የእንቁላል፣ የቆዳ ወዘተ ምንጮች ናቸው። በእሁኑ ጊዜ የሚታየው ድርቅ ግን ትናንሽ ኩራዎች በማድረትና ሣርን በማጥፋት ከፍተኛ አደጋ እያደረሰ ነው። እንደሰው እንስሳውም ለረሃብና ለሰቃይ ተጋልጧል።

3– ጦርነትና ረሃብ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ «ኋላቀርና ድሃ» አገሮች ጦርነትና ሠለም ማጣት ዋንኛ ሰው ሰራሽ የረሃብ፣ የድርቅና የድህነት ምክንያት ነው። ጦርነት የሰውንና የእንስሳትን ህይወት በማጥፋት፣ ገበሬውንና ሌላውን ጉበዘዝት ከሥራው በማፈናቀልና በእርስ በርስ መጨራረስ ጦርነት በመግድ የተፈጥሮ ሃብትን (ጫካን፣ ሰርን፣ ውሃን፣ እፈርን ወዘተ) በእሳት በበምብና በመርዝ በማጥፋት፣ ለዕድገት ሊውል የሚገበን ገንዘብ ለጦር መሰሪያና ለወታደር ያለመጠን በማበከን፣ ሠላማዊ ህዝብ ንብረቱን በትኖ ከመኖሪያው እንዲፈናቀል በማድረግ፣ ህዝቡን በልዩ ልዩ መዋጮ በማመንመን፣ ቁስለኛና እክለ ስንኩሳንን በማብዛት፣ ትዳርን በማፍረስ፣ እበት እጥ ልጆችንና በልእልበ ሴቶችን በመፍጠር በተለያዩ ቀጥተኛና

ተዘዋዋሪ መንገደኞች ችግርን፣ ረሃብን ድርቅን ያስከትላል።

በእሁኑ ጊዜ በተጨባጭ እንደሚታየው ድርቅና ረሃብ ያጠቃቸው አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች ጦርነትና ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥት ያጠቃቸው ሁነው እናገኛለን።

በደቡብ ምስራቅ እስያ በካምቡቺያ በ1971 የታየው የምግብ መጥፋት ምክንያት ከዚያ ጊዜ አስር ዓመት በፊት ሰይቂረጥ የተካሄደው ጦርነት ያስከተለው መዘዝ ነበር። በ1975-77 በቻድ፣ በእን ጉሰ፣በኢትዮጲያ በሱዳን፣ በሞዘምቢክ የታየው የድርቅና የረሃብ ሁኔታ ከእርስ በርስ ጦርነት ጋር የገጠመ ነበር።

በተለይ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምረው የተመዘገቡ ረሃቦች ከጦርነትና ከወታደር ዝርፊያ ጋር የተያያዙ ነበሩ። ህዝቡ በዘመቻና በጦር ዝግጅት ጊዜ ወታደሩን የመመገብ ግዴታ ይደረግበት ነበር። ዘመናዊ ውትድርና ከዚህ ዓይነት እስተዳደር የሚለየው የዘመኑ ወታደር ደሞዝ መከፈሉና ህዝቡ ይህን ደሞዝ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመንግሥት በተለያዩ ቀረጦች ማስገባቱ ነው።

አፄ ኒሊክ በ1881 በአፄ ዮሐንስ ላይ ባወጁት ከተት እዋጅ ሲናገሩ (29)፦ «ነገር ግን ከሠራዊት ብዛት የተነሣ እገር እንዳይበድልና እንዳይራብ እኩሌታውን ጦር ወደ ወሎ እኩሌታውን ችሉ ሰደውት ተቀምጦ ነበር።»

«ትግሮች ግን ከመተማ ወጥተው ያፄ ዮሐንስን ልጅ ራስ መንገሻን ይዘው ትግራ ላይ እንደሸፍታ ሆነው ነበር። ስለዚህ አፄ ምኒሊክ ወደ ትግራ ዘመቻ አሰቡ፣ ወደጆቻቸውንም መነኩሰቱን አስጠርተው ጊዜው ረሃብ ሆነ፣ እንዳልቀር እርስ በርሰቸው ትግሮች ጡዋት ማታ እየተዋጉ ሰውም መኪንንቱም አለቀ፤ እንዳልዘምት ለሙ በራው አልቂል ድሃው ይጉዳብኛል ብለው አማከሯቸው... መነኪሰቱም ስርዓተ መንግሥት እድርሰው ወደ ትግራ ይዝመቱ ብለው መከሩ፣ ለዚህም መሰናደው እጅግ ብዙ ነበር።»

«በትግራ አገሩ ሁሉ ገብር የሚዘረፍ ታጥቶ ሠራዊቱ ተርቦ ነበር።»

«ሠራዊቱ ከአምባው ከዋሸው እየገባ እየተታ ኩሰ እህሉን ዘረፈው»

«አፄ ዮሐንስ ጉጂምን ወግተውት ነበርና በዚህ ዘመን ይልቁንም ረሃብ

በ ጉጂም ፅና»

«በዚህ ዘመን የራስ መኮንን ሰዎች ከሐረርጌ ውጋዴን ከሚበለው እገር ዘምተው ብዙ ሰምና በሬ እስገብረው ከሐረርጌ ገቡ፤ ራስ መኮንንም በኢትዮጵያ ሰምና በሬ ታጥቶ እገሩ ውድማ እንደሆነ ያውቃልና ለጌታዬ ለንጉሠ ነገሥት ምኒሊክ ልርዳ ብሎ እምስ ሽህ በሬ እምስት ሽህ ሰም ወደ አንኮበር ሰከ»

ከዚህ ሳይ የተጠቀሰው በአጼ ምኒሊክ ጊዜ ጦርነትና ዘመቻ ምን ያህል ለረሃብ መነሸና መጪ ረሸ እንደሆነ ለማሳየት ነው። መጪ ረሸውና ውጤቱም የኢትዮጵያ ታሳቁ ረሃብ ተብሎ የታወቀው በ1881-84 የነበረውና የኢትዮጵያ አንድ ሰስተኛ ህዝብ ፈጅቷል የሚበለው ነው።

እንደ አለቃ ለማ አየነፍ በ1881-84 ጉጂምን ያወደመው ረሃብ በከፊል የ1879ኙ የአጼ ዮሐንስ ዘመቻ በስከተለው የከብትና የሰው አልቂት ነበር።(30)

«የዮሐንስ ጦር ለሰውም ሆነ ለከብቱ በፍፁም ርህራሄ አሳሳየም»

«የሱዳኑ መሐዲ ጦር በምዕራብ የጉንደርን አከባቢ አወደመው፤ አጼ ዮሐንስ የጉጂም ንጉሥ ተክለሃይማኖትና የሸዋው ምኒሊክ እያሴሩብኝ ናቸው ብለው በመጠርጠር ሊቀጧቸው በመፈለግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር እንዲዘምት አደረጉ። ዘማቹም ያለፈበትን አገር ሁሉ በላው፤ ከዚህ ሁኔታ ለጥቶ ነበር ታላቁ ረሃብ የመጣው»

ፖንከረስት ወታደርንና እንበጣን ሲያወዳድር እንዲህ ብሏል፦ «እንበጣው በሜዳ ያለውን ነው የሚያጠፋ፤ ወታደር ግን የሜዳውን ያጠፋል ከቤት ያለውንም ይዘርፋል።»

ከሳይ የተጠቀሱት የጦርነት፤ የዘረፋ፤ የረሃብ ሁኔታዎች በመጠንና በስፋት እየጨመሩ በአጼ ሃይለስላሴና በኩለ ኔል መንግስቱም ዘመነ እገዝዝ ቀጥለዋል። በኢትዮጵያ ድርቅ እጠቃቸው ከሚባሉት ዋና ዋና ሰፍራዎች በእሁኑ ጊዜ ልዩ ልዩ የትግል እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው ሆነው ይገኛሉ።

በኤርትራ፤ በትግራይ፤ በ ጉንደር፤ በወሎ፤ በአጋዴን የተለያዩ አከባቢዎች የሚታየው የድርቅና የረሃብ ሁኔታ የዘመቻ፤ የጦርነት፤ የሠለም መታወክ፤

የሰደት ወዘተ ዋንኛ ውጤት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አሰራ እምስት ዓመታት በተለያዩ አከባቢዎች በመታየት ላይ ያለው የሦርነት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ነው። በ 1968 ዓም በሰማሌና በኢትዮጵያ መከከል የተከሄደው ጦርነት ከሁለቱ ወገን ያደረሰው የህይወት፣ የንብረትና የተፈጥሮ ሃብት ጥፋት ቀላል አልነበረም። በሃረርጌ ከፍለ ግዛት የደረሰው ጉዳት መጠን ከሃምሳ ሚሊዮን ብር በላይ ይገመታል። የብዙ ሽህ ዘሳን ህይወትን ለማዳን ተብሎ የተሠራ የመሰኖ ግድብ ከአገልግሎት ውጭ ከሆኑት ህይወት አልሚ ፕሪቶች አነዱ ነበር።

በቅርቡ የዓለም መንግሥታት የዕርዳታ ድርጅት የምግብ ዕርዳታ ለማድረስ በኤርትራ ግዛት በሚጀዝበት ጊዜ በነፃአውጭ ድርጅት ተመትተው መኪናዎቹም ምግቡም በእሳት ተቃጥሎ ቀርቷል። ይህ የብዙ ሺህ ረሃብተኞችን ህይወት ማዳን የሚችለው ዕርዳታ እንዳይደርስ መደረጉ የረሃብን መስፋፋት መርዳቱ እይቀርም።

የኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግሥት በሚያደርገው የማውደም ዘመቻ ይህ ነው የማይባል ጥፋት በየአከባቢው ማድረሱ የታወቀ ነው። ይህም መፍትሔ አልባ ሁኔታን በማስፋፋት የሦርነት ኢኮኖሚና እቂምን በማጠናከር ልንወጣ የማንችለው ችግር፤ ረሃብና ድርቅ ውስጥ ጥሎን የዓለም መሰለቂያ አድርጉን እንገኛለን።

4– የተዘበ ፖሊሲ

የሰክትለንዱ ተጋዥ ጀምስ ብሩስ ስለተዘበ አስተዳደር እንዲህ ሲል ፅፏል:- «ትላልቅ ጉንዳኖች፣ የእይጥ መንጋ… ብዙ እህል ፈጁ። ከዚህ ሁሉ መቅሰፈት የባሰው ግን መጥፎ መንግሥትና አስተዳደር ነው። መጥፎ መንግሥት ህዝቡ ከተፈጥሮ፤ ከተመክሮ ያገኘው ንብረቱን፣ ማንነቱን ከመቅበት ያወድምበታል።»[31]

የመንግሥት ፖሊሲ የረሃብና የድርቅን ሁኔታ ለመከላከል፣ ለማስወገድ፣ ወይም

ለማበበስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ብዙ በረሃብና ድርቅ የተጐዱ አገሮች መንግሥታት ስርነቀል፣ ቶራጥ፣ ከአካባቢያቸው ጋር የተጣጣመ እርምጃ መውሰድ ይሰናቸዋል። አብዛኛውን ህዝብ በገጠር የሚኖር አርሶ አደር መሆኑ እየታወቀና የአገሮቹ የኤኮኖሚ መሠረትም ባለቤት መሆኑ እየታወቀ በሰገሩ በድርቅና በረሃብ ሲጠቃ ሁሉም ነገር ወደ እርሻና የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና ልማት ግንባር አለመዋሉ በችግሩ መጠን፣ ዕድገትና ሂደት ላይ የሚገባው ትኩረት እንዲልትሰጠው ይጠቁማል። ብዙ መረበረብና ሁከታ የሚታየው ጊዜዊ በሆነ ምቱዋት ወይም ብድር ማግኘትና የተገኘውን መቀራመት ነው። እንዲንዴም ዘላቂ ተብለው በሰራ የዋሉ ዕቅዶች በጥናት ያልተደገፉ፣ በላዋቂ መካር የተዘጋጁ፣ ወጭያቸው ከጥቅማቸው ጋር ያልተመጣጠነ፣ ከአካባቢው ሁኔታ ያልተጣጣሙ፣ የይስሙላ ይመስላሉ። ዋና ከተማዎችን ማጋጌጥ፣ የተንዛዙ በዓሎችን ማክበር፣ ዓይን የሚስቡ «ሃውልቶችን» ለስም ማስጠሪያ ማቆም የብዙ አፍሪቃ መንግሥታት ተቀዳሚ ተግበራት የሆኑ ይመስላሉ።

ከአገር የተገኘውም ሆነ ከውጭ የመጣ ገንዘብ እዋዋል ኢሚዘናዊ በሆነ መንገድ በሥራ ማስኬጀ፣ በደሞዝና በውሎ አበል ያለበለዚያም ዘላቂ ውጤት በማያስገኝ ተግባር ላይ ይውላል።

ለምሳሌ የሰሄሉ ድርቅ የምዕራብ አፍሪቃን አገሮች በጠቃበት ጊዜ ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶለር በዕርዳታ ተገኝቶ ነበር። ከዚህ ውስጥ፦

35% ለጊዜያዊ ምግብ መግዣ

30% ለውጭ ምንዛሬ አስገኝ ምርትና የተያያዘ መስኖ

4% ለምግብ ጠቀስ ምርት

2% ለተፈጥሮ ሁኔታዎች ማሸሻያ ውሏል።

ይህ እንደሚያሰየው ድርቅን ለመከላከል፣ የአፈርን መሸርሸር ለማቆም፣ ደንን በመተከት ወዘተ ሊረዱ የሚችሉና ዘላቂ መፍትሔ ሊያስገኙ የሚችሉ እርምጃዎች ምን ያህል አነስተኛ ግምት እንደተሰጣቸው ነው።[32]

በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ኢሚዘናዊ የበጀትና የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ ይታያል።[33]

በ1973 ዓም ከታረሰው መሬት 35% የመንግሥት እርሻ ሲሆን ከመንግሥት የእርሻ በጀት አርባ ከመቶውን (40%) ተጠቅሟል። ይህ እርሻ ያመረተው ግን በአገሪቱ በጠቅላላ ከተመረተው አምስት ከመቶው (5%) የሚሆነው ብቻ ነው።

በአንፃሩ 98% የሚሆነው አራሽ ቤተሰብ 95% የሚሆነውን መሬት በማረስ 94% የሚሆነውን የአገሪቱን ምርት አምርቷል። ነገር ግን ከመንግሥት እርሻ በጀት ለተራው ገበሬ የተደረገለት እርዳታ ለመንግሥት እርሻ ከተደረገው እርዳታ ሲወዳደር እምንት ነበር። ለምሳሌ የመንግሥት እርሻ

80% የሚሆነውን የዱቤ አገልግሎት (CREDIT FACILITY)

95% የሚሆነውን የተሻሻለ ዘር (IMPROVED SEED)

76% የሚሆነውን ማዳበሪያና ፅረተባይ (FERTILIZER & PESTICIDES)

ሲጠቀም የእርሶ አደሩ እርሻ ግን ከ20% የሚያንሰውን አግኝቷል። አብዛኛውን ምርት ለሚያመርተው ተገቢ ድጋፍ በቀጥታ ጊዜውን ጠብቆና በብቃት ሊሰጠው ከልቻለ የረሃብና የድርቅ ሁኔታ በአሁኑ አያያዝ መገታት አይችልም።

ለአገር መከላከያና ለጦርነት የሚደረገው ትኩረት እንደዚሁ ለሌሎች የምርትና የዕድገት መስክች ከሚደረገው ትኩረት ጋር ሲወዳደር ኢሚዘናዊነቱ ጉልቶ ይታያል። «የመከላከያ» በጀት ለ1975/76 የተያዘው አንድ ቢሊዮን ብር ሲሆን ከጠቅላላው የአገሪቱ በጀት 46% በመሆን ግማሹ ሊሆን ትንሽ ነው የቀረው። በዚሁ ዓመት ለእርሻና ለሰፈራ 10% ብቻ ነበር የተደለደለው። ከ1971 ዓም ጀምሮ «የመከላከያ» በጀት በመከከለኛ ግምት ከጠቅላላው የአገሪቱ በጀት ከሲሶ አንሰ አያውቅም።[34]

ኢትዮጵያ ከ1971 እስከ 1975 ዓም ሁለት ቢሊዮን ዶላር (አራት ሺህ ሚሊዮን ብር) ያወጣ የጦር መሰሪያ በመግዛት ከሰሃራ ምድረበዳ በታች ካሉት የአፍሪቃ አገሮች በጦር መሰሪያ ብዛት፣ ጥራትና እስከ ሦስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ጦር ለማሰለፍ በመቻል አንደኝነቱን ይዛለች (ደቡብ አፍሪቃን

አይመለከትም)።[35] ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በረሃብ፣ በድህነት፣ በሰደተኛ ብዛት በጎለ ቀርነትም እንደዚሁ አንደኝነትን የያዘች። ኢትዮጵያ ከ150 የማያንሱ ተዋጊ አይሮፕላኖች እንደአሏት ይነገራል።[36] የብራንት ኮሚሽን የእንድ ተዋጊ አይሮፕላን ዋጋ ከአርባ ሚሊዮን ብር በላይ እንደሚሆን የአንድ ተራ ታንክ ዋጋ ደግሞ ሁለት ሚሊዮን ብር እንደሚሆን ገልጿል፣ በእንፃሩ አንድ ታንክ ለመግዛት በሚወጣው ገንዘብ ለሰላሳ ሽህ ተማሪዎች የሚበቁ አንድ ሽህ የትምህርት ቤት ክፍሎች ሊሰራበት ይችል እንደነበር ይጠቁማል።[37]

በእርሻ መሬት ድልዳሉም ረገድ በብዙ አፍሪቃ አገሮች የተዘበ አሰራር ይታያል። ጥሩ ጥሩ ለምና ለመጎጎቻ ቅርበት ያላቸው መሬቶች ለምግብ እህሎች ማምረት ከመዋለቸው ይልቅ የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኙ ለሚችሉ እንደ ቡና፣ ሻይ፣ ትምባሆ፣ ስኪር ጥጥ ወዘተ ላሉ የመንግሥትና የትርፍ ኩባንያዎች ለሚያስተዳድራቸው እርሻዎች ይውላሉ። መንግሥትም ለእንደነዚህ ዓይነቶች መስኩች ቅድሚያ ስለሚሰጥና የተራ ገበሬዎችን ጥሪት ስለማይደግፍ ገበሬው በመንግሥትና ኩባንያ እርሻዎች ተቀጣሪ ሠራተኛ በመሆን ከእምራችነቱ ተገልሎ ጥገኛ ሆኖ ይቀራል። ይህም ዓይነተኛ የረሃብና የችግር ምክንያት ሆኗል።

ለምሳሌ የሳሄል አከባቢ አገሮች የቡና፣ የሻይ፣ የስኪር፣ የጥጥ፣ የከከና የትምባሆ ምርት በዓመት 12% ሲጨምር የምግብ ምርት ግን አቶልቀሏል።[38]

ስለዚህም እነዚህን በማምረት የተገኘ የውጭ ምንዛሪ ውድ የሆኑ መሣሪያዎችን፣ ምግቦችንና መንደለቀቂያ ዕቃዎችን በማስመጣት የበሰ ችግር ውስጥ እየወደቁ ያሉ አገሮች ብዙ ናቸው።

5– የተዘበ ቴክኖሎጂ

አንዳንድ ድርቅና ረሃብ ለማስወገድ ወይም ለመቆጣጠር የሚደረጉ ጥረቶች የሚያስከትሉት ጉዳት እልፎ እልፎ ከቁጥጥር ውጭ በመሆን ተጨማሪና እዲስ

ችግር ይፈጥሩ ይሆናል። ይህን በሚመለከት ሊጠቀሱ የሚገባቸው የማደበሪያ ንጥረ ነገሮች፣ ተባይ የሚያጠፉ መድኃኒቶች፣ ትላልቅ ግድቦች፣ የውሃ ጉድጓዶች፣ የተሸሸሉ ወይም ድቅል ዘሮች ወዘተ ይገኙበቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ነገሮች የሚፈጥሩዋቸው ችግሮች አብዛኛውን ጊዜ የጥናት መጉደል፣ መጠንን አለማወቅ፣ የሌሎችን ተመክሮ አለማጤን፣ አዲስ ነገሮችን ተስገብግቦ ማግበስበስ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህም ጥቅማቸውን ከችግራቸው ጋር አመዛዝኖ መጠቀም የተገባ ይሆናል።

ተባይ የሚያጠፉ መድኃኒቶች ብዙውን ጊዜ ተባይን ብቻ ሳይሆን የሚያጠፉት ለእዝዕርት የሚያስፈልጉ ፍጡራንን አብሮ በማጥፋት ለምርት ተፈላጊ የሆኑትንም ጨምረው ሊያጠፉ ይችላሉ።[39]

ግድቦች አብዛኛውን ጊዜ ትላልቆቹ ከፍተኛ ወጪ ከመጠየቃቸው በስተቀር ብዙ የተማሪ የሰው ሃይል ይፈልጋሉ። በተጨማሪም የአከባቢውን የጨው መጠን በመጨመር የእርሻ መሬቶች ለምርት እንዳያመቹና ለአሣም ማራቢት እንቅፋት ይሆናሉ። ግድቦችና መሰኖዎች እንዳየአከባቢው ሁኔታ ለቀንድ አውጣና ለሌሎች ነፍሳት መራቢት እመች ሁኔታን በመፍጠር ለቢለርዝያና (BILHARZIA) ለዓይን አሰዋሪው እንከሰርኪያሲስ (ONCHOCERCIACIS) በሽታዎች መስፋፋት ምክንያት ይሆናሉ። እነዚህ ድርብርብ ሁኔታዎች በምርትና በሰው ሃይል ተፅዕኖ በማድረግ ለረሃብና ተመሰሰይ ችግሮች አስተዋፅእ ያደርጋሉ።[40]

የተሸሸሉ ዘሮች ብዙውን ጊዜ ከውጭ የመጡ ስለሚሆኑ ለአከባቢው ዓየርና የመሬት ጠባይ እንግዳ በመሆን ዘለቂነታቸው አጠያያቂ ይሆናል። አዲስ ዘሮች በቀላሉ ለበሽታ የተጋለጡ ይሆናሉ። ድርቅን የመቋቋም ጉልበታቸው የተዳከመ ሊሆን ይችላል። ይህም አጠቃላዩ ምርት ላይ በመንፀባረቅ ረሃብን ሊያባብስ ይችላሉ። ስለዚህም በተቻለ መጠን የአከባቢውን ዘሮች በሚገባ በመንከባከብ፣ ተፈጥሮአዊ ማልሚያ ነገሮችን መጠቀም፣ የአፈር አያያዝና አጠቃቀም መቆጣጠር፣ የውሃ አጠቃቀም ማጤን ለዘለቂ መፍትሔ አስተዋፅያ ያደርጋሉ።

6– ድህነት

የምግብ አለማግኘት በመሰረቱ የረሃብ ዋነኛ ምክንያቱ ቢሆንም ሰረ መሠረቱ ድህነት ነው። በአፍሪቃ ድርቅም እያጠቃቸው ረሃብ ግን ያለሸነፋቸው አገሮች አሉ። ይህ ጉልቶ የሚታየው በሰሜን አፍሪቃ ነው። ይህ ሊሆን የቻለበት ዋና ምክንያት የምግብ ፍለጉታቸውን በብዛት የሚያሪኩት በግዢ ስለሆነና አገሮቹ የተፈጥሮ ሃብታቸውን በሚገባ በመጠቀም በቂ ገንዘብ ስለሚያመነጩ ነው። በኢትዮጵያ ረሃብ ያጠቃው ደሀውን ገበሬና ድሀውን ከተሚ ነው እንጂ ገንዘብ ያለውን አይደለም።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓለም በጣም ደሃ ተብለው ከሚታወቁት ዋንኛዋ ናት። ኢትዮጵያ በቂ የተፈጥሮ ሃብትና ይህንንም ለማደበር የሚችል በቂ የሰው ሃይል ቢኖራትም ይህንን የተፈጥሮ ሰጦታ በሚገባ ለማደበርና ለጎብረተሰቡ ጥቅም ለማዋል ስለእልቻለች እንደብዙዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በሰው ሰራሽ ድህነትና ረሃብ ሥር እየማቀቀች ትገኛለች።

የአፍሪቃ አገሮች ድህነት እንዲህ ተጋኖ የሚነገረው ለልመናና ለዘረፋ፣ ለማታለያና ከሃላፊነት ለመሸሽ እንዲያመች ሰበብ ከልሆነ በስተቀር በየአገሮቹ የሚመረተው ምርትና የሚዘዋወረው የገንዘብ መጠን በሚገባ ቢከፋፈልና የህዝብን መሠረታዊ ፍለጉት ለሚያሟሉ ዕቅዶች ቢውል ይህ ሁሉ ባልተወራ ነበር። አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በብድር ዕዳ፣ በዱቤ ተይዘው ዋናውን ሳይሆን የዋናውን ወለድ እንኳ መክፈል አቅቶአቸው ሲገኙ፣ በንፃሩ የነዚህ አገሮች መሪዎች፣ ባለሟሎቻቸውና የውጭ አገር ባልደረቦቻቸው በተለያዩ መንገዶች በሚያሰፍር ሁኔታ የሕዝቡን ንብረት ሲንደላቀቁበት ይታያል።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ናቸው ድህነትን ሰው ሰራሽና የረሃብም ነፀብራቅ አድርገው የሚገልፁት። ይህ ዓይነቱ የእስተዳደር ጉድለት፣ ጭካኔ የተሞላው ብዝበዛና ግለሰብኝነት ለዚህ ዓይነቱ ረሃብና ችግር ዋና ምክንያት ሆኗል።

6– ድህነት

የምግብ አለማግኘት በመሰረቱ የረሃብ ዋነኛ ምክንያቱ ቢሆንም ሰረ መሠረቱ ድህነት ነው። በአፍሪቃ ድርቅም እያጠቃቸው ረሃብ ግን ያላሸነፋቸው አገሮች አሉ። ይህ ጉልቶ የሚታየው በሰሜን አፍሪቃ ነው። ይህ ሊሆን የቻለበት ዋና ምክንያት የምግብ ፍላጉታቸውን በብዛት የሚያረኩት በግዢ ስለሆነና አገሮቹ የተፈጥሮ ሃብታቸውን በሚገባ በመጠቀም በቂ ገንዘብ ስለሚያመነጩ ነው። በኢትዮጵያ ረሃብ ያጠቃው ደሀውን ገበሬና ድሀውን ከተሜ ነው እንጂ ገንዘብ ያለውን አይደለም።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓለም በጣም ደሃ ተብለው ከሚታወቁት ዋንኛዋ ናት። ኢትዮጵያ በቂ የተፈጥሮ ሃብትና ይህንንም ለማደበር የሚችል በቂ የሰው ሃይል ቢኖራትም ይህንን የተፈጥሮ ሰጦታ በሚገባ ለማደበርና ለጎብረተሰቡ ጥቅም ለማዋል ስለእልቻለች እንደብዙዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በሰው ሰራሽ ድህነትና ረሃብ ሥር እየማቀቀች ትገኛለች።

የአፍሪቃ አገሮች ድህነት እንዲህ ተጋኖ የሚነገረው ለልመናና ለዘረፋ፣ ለማታለያና ከሃላፊነት ለመሸሽ እንዲያመች ሰበብ ከልሆነ በስተቀር በየአገሮቹ የሚመረተው ምርትና የሚዘዋወረው የገንዘብ መጠን በሚገባ ቢከፋፈልና የህዝብን መሠረታዊ ፍላጉት ለሚያሟሉ ዕቅዶች ቢውል ይህ ሁሉ ባልተወራ ነበር። አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች በብድር ዕዳ፣ በዱቤ ተይዘው ዋናውን ሳይሆን የዋናውን ወለድ እንኳ መክፈል አቅቶአቸው ሲገኙ፣ ባንፃሩ የነዚህ አገሮች መሪዎች፣ ባለሟሎቻቸውና የውጭ አገር ባልደረቦቻቸው በተለያዩ መንገዶች በሚያሰፍር ሁኔታ የሕዝቡን ንብረት ሲንደላቀቁበት ይታያል።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ናቸው ድህነትን ሰው ሰራሽና የረሃብም ነፀብራቅ እድርገው የሚገልፁት። ይህ ዓይነቱ የእስተዳደር ጉድለት፣ ሞኪኔ የተሞላው ብዝበዛና ግለሰብኝነት ለዚህ ዓይነቱ ረሃብና ችግር ዋና ምክንያት ሆኗል።

7– ጤንነትና ረሃብ

በአስተዳደር ጉድለት፣ በኢኮኖሚ ድቀትና በኋላ ቀርነት በሚደከር ጎብረተሰብ ውስጥ ረሃብ በሽታን በሽታም ረሃብን ያስከትላል። አንድ ህይወት ያለው ነገር ጤናማ ነው ተብሎ የሚነገረው ለኑሮ መሠረታዊ ፍላጐቶች ተሟልተው ሲገኙ ነው። በዝቅተኛው ደረጃ ሰው ለመኖር ውሃ፣ ዓየር፣ ምግብ፣ መጠለያ፣ መሸፈኛ ያስፈልገዋል። እነዚህ ከተሟሉ በኋላ ሌሎች የጎብረተሰብ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲከ ፍላጐቶች እንደየበታውና ሁኔታው መሟላት ይጀምራሉ።

ለሰውነት ምግብ፣ ውሃና ዓየር ወሳኝ ፍላጐቶች ሲሆኑ የነዚህ ማነስ ሰውነትን በማድከም ለበሽታና ለህመም ያጋልጣል። የደከመ ሰውነት በሽታ መከላከል፣ የሰውነትን ልዩ ልዩ ህዋሳትና አካላት ማጉልመስ፣ ተንቀሳቅሶ አምርቶና አዘጋጅቶ መብላት ይሰነዋል። የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ወይም አለማግኘት ለረዥም ጊዜ ሲደጋገም የመጨረሻ ደረጃ ረሃብ ወይም ጠኔ ይደርሳል።

ለረሃብ የተጋለጠ ሰው የሰውነት ክፍሉ እድገት የተቀጨ፣ የጫጫ ይሆናል። አብዛኛውንም ከሁለት ዓመት ዕድሜ በታች ባሉ ህፃናትና እርጉዞች ላይ ያልተሟላ ምግብ አለማግኘት በሚወልዱት የህፃናት እንጉል እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። እንጉል ወሰኝ እድገት የሚያደርገው በዚህ እድሜ ክልል ውስጥ ነው። በልተሟላ ምግብ ያደጉ ህፃናት አስተሳሰብ ችሎታና የእንጉሉ ዕድገት ዝቅ ያለ ሊሆን እንደሚችል ይነገራል።

ድርቅና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች የፈጠሩት የምግብ እጥረት ረሃብና በሽታን ያስከትላል። ረሃብ በጠቃው ህብረተሰብ ተላላፊ በሽታዎች የተስፋፉ ናቸው። በሽታዎቹ የሚያጠቁት ሰውን ብቻ ሳይሆን በሽታን መከላከል ያልቻሉ እንስሳትና እዝዕርትንም ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ ታላቁ ረሃብ ተብሎ በሚጠራው በ1881–84 ረሃብ ጊዜ በሽታ ተስፋፍቶ ነበር። ፀሐፊ ትዕዝዝ ገብረሥላሴ ሲፅፉ፦[41] «በዚህም ዘመን በሽታ ገብቶ ሰዎች ሞቱ ... በዚያን ጊዜ ይህንን በሽታ ታሞ የሚተርፍ የለም» ብለው

«... ቤጌምድር በዚያ በክፉ ቀን በትልቁ ረሃብና በበሽታ ሰው ከብቱም እልቆ እንኪንሰ ለምና በራ፣ ደርና ውሽ እንኪ ባገሩ አይጮህም ነበር።» ሲሉ የረሃብንና የበሽታን አጥቂነት ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ በልምድ፣ በሃይማኖትና በተለያዩ ምክንያቶች ለመበላት የማይፈቀዱ፣ ነገር ግን በሌሎች አገሮች ያለምንም ተፅዕኖ ዘወትር የሚበሉ የሥጋም ሆነ የእህዕርት ምግብ ዓይነቶች በርከታ ናቸው።

የአመጋገብ ልምድን እስከተቻለ ደረጃ ለመቀየር መሞከር የረሃብን ስፋትና መጠን እንደሚቀንስ መገመት ይቻላል።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ወግ አጥባቂ አካባቢዎች የሚዘወተር የምግብ ዓይነት መጥፋት ህዝቡን እማራጭ ያሰጣዋል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው አልፎ አልፎ ህዝቡ መርዘኛ የሆኑ ምግቦችን ያለጥንቃቄ እንዲበላ የሚያስገድደው። ለምሳሌ በወሎ በተከታታይ ድርቅና ረሃብ ህዝቡን ስለአጠቃው የምግብ መጥፋት ጊያ ተብሎ የሚታወቀውን መርዘኛ የሆነ አተር መሰል እህል (LATHYRUS SATIVA) እንዲበላ አድር ጉታል። ይህ የጊያ ተክል ድርቅን የመቋቋም የተለየ ችሎታ ስለአለው ለምልሞ በመታየት ረሃብተኛን ያጊጊል። ይህን የተመገበ ሰው ላስሪዝም (LATHYRISM) የሚባል እን ጉልንና ነርቭን የሚያጠቃ ብሎም የሚያሽመደምድ በሽታ ይይዘዋል። ይህ በሽታ ድርቅና ረሃብ ባጠቃቡት አካባቢ እንደተለለፊ በሽታ ሆኖ ተከስቷል።[42]

በተመሳሰይ አካባቢዎች የሚበቅሉ ገብስ ዓይነት እህሎችን የፈንገስ (FUNGUS) በሽታ ይይዘቸዋል። ይህ በፈንገስ የተለከፈ እህል በሚበላበት ጊዜ ኤር ጉቲዝም (ERGOTISM) የሚባል የደም ስርን በማጥበብ የደምን መተላለፍ የሚከላከል እንደ ጋንግሪ ያለውን በሽታ ያስከትላል። በሰሜን ኢትዮጵያ እንዳንድ በእርዳታ የመጡና የተዘሩ ዘሮች በዚህ የእህል በሽታ በቀላሉ መጠቃታቸውና ከዚህም የተነሰ የተበከለውን እህል የበሉ ሰዎች የኤር ጉቲዝም ቁራኛ እንደሆኑ ይወራል።

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ነባሩን ችግር በማባባስ ህዝቡን ለተጨማሪ ረሃብና

እልቂት ያበቃዋል።።

8– እንበጣና ረሃብ

አፍሪቃ ለረጅም ጊዜ በእንበጣ መንጋ በመጠቃት የልዩ ልዩ አዝርዕት ጥፋት ደርሰባታል። የዚህ ዓይነቱ ችግር በኢትዮጵያ የሚታየው በሰሜን አካባቢዎች ሲሆን የታሪክ ፀሐፎች ስለዚህ ችግር ደጋግመው ይናገራሉ።

በ1512-18 በትግራይ ከፍተኛ ጥፋት ያደረሰው የእንበጣ መንጋ ነበር። ስለዚሁም ፖርቱጋላዊው ተጋዝ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ ሲናገር «ምድር በማይታመን ሁኔታ በአነበጣ ተሸፍኖ፣ ዓየሩ ተሞልቶ የፀሐይ ብርሃን ከልክሎ ነበር» ይላል።

ለ1881-84 ታላቅ ረሃብ እስተዋፅዖ ከደረጉት ጦርነት፣ ድርቅ፣ ተላላፊ በሽታ በላይ እንበጣም ይገኝበታል። በቅርብ በታዩትም የኢትዮጵያ ረሃቦች እንበጣ ድርሻውን አድርጓል።

በተከታታይ በሰሜን ኢትዮጵያ እንደታየው ድርቅና ጦርነት ረሃብን ከስከተለ በኋላ መጠነኛ ዝናብ መጥቶ ህዝቡ ማምረት ሲጀምር እንበጣ መጥቶ ያመረተውን ያወድመዋል። በዚህም የተነሳ ከአንድ ረሃብ ወጥቶ ወደሌላው ይገባል። ይህም ብዙ ጊዜ መንግሥትንና ህዝብን ግራ እጋብቶ ተስፋ ማስቆረጥ ደረጀ የደረሰ ይመስላል። ይበሰ ብሎ እንዳንዱ ከዚህ ችግር ጋር በረደ በመጣል የተዘራውን ያጠፋዋል፣ ጉርፍም እንዲሁ ከፍተኛ አደጋ ያደርሰል። እነዚህ ከስተቶች እየተፈራረቁ ነው ሁኔታውን ተስፋ የለሽ ያስመስሉት።

የእንበጣ መንጋ ከድርቅ በኃላ ከሚመጣ ዝናብ ጋር የተገናኘ ነው። የመራቱ እርጥበት እንበጣ እጂፈለፈል አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል። የዘድሮው የእንበጣ መንጋ በ1920 ዎቹ ከታየውና አስር ዓመት ሙሉ እፍሪቃን ከጠቃው የከፋ ነው ይበላል።

እያንዳንዱ እንበጣ ሁለት ግራም ምግብ በቀን ይበላል፣ በቀን እስከ ዘጠና ኪሎሜትር ይጋዘል። ብዙ ቢሊዮን እንበጣ ያዘለ መንጋ ሰማኒያ ሺህ ቶን ማሽላ

በአንድ ቀን የበሰበት ሁኔታ እንደነበር ሲታወቅ ይህ መጠን እርባ ሺህ ሰዎች ለአንድ ዓመት ይመግብ የነበር ነው።[43]

አንበጣን ለማጥፋት ልዩ ልዩ ፀረ-ነፍሳት መድኃኒት መጠቀም ቢቻልም፣ ፀረ-ነፍሳት መድኃኒት አንበጣውን ከማጥፋቱም በላይ ሌላ ለእርሻ የሚያስፈልጉ ነፍሳትም ጨምሮ ስለሚያጠፋ ጠቀሜታው ከጉዳቱ መመዘዘን አለበት።

አልፎም ለፀረ አንበጣው መድኃኒት የተጋለጠው ምርት በሰው ወይም በእንስሳት በሚበላበት ጊዜ አደጋ የማስከተል ችሎታም ሊኖረው ይችላል። ፀረ-አንበጣ መድኃኒት ለጊዜው በራሪውን አንበጣ ቢገድልም በመሬት ውስጥ የተደበቀውን እንቁላል ስለማይገድል ትንሽ ዝናብ ሲመጣ ችግሩ ተመልሶ ይመጣል።

በውሃና በደን አያያዝ በአስተዳደር መስተካከል መሸሸል የድርቅና የረሃብን አደጋ መቆጣጠር ይቻላል ከተባለ ለአንበጣ አመች ሁኔታዎችን በመቆጣጠር የአንበጣንም አደጋ መቀነስ ይቻላል። የአንበጣ ችግር አህጉራዊ ስለሆነም ተገቢው ትብብር ከሚመለከታቸው ጋር ማድረግ ይረዳል።

፫. መደምደሚያ

የረሃብና ድርቅ መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከሚነገርላቸው ዋና ዋናዎቹ ተጠቅሰዋል። እብሮም ለችግሮቹ መፍትሄ እስተዋፅዖ ያደርጋሉ የሚባሉት በመጠኑ ተጠቅሰዋል።

የተዛባ የዓየር ሁኔታ፣ ኋላቀር የርሻ ዘዴ፣ ከፍተኛ የእፈር መሸርሸርና ለምርት አመች አለመሆን፣ የገበሬው በቂ ድጋፍ አለማግኘት፣ ብዙ ሰውና እንስሳ በትንሽ መሬት ላይ መረባረብ፣ የገብያ ሁኔታ አለመሸሸል፣ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድ፣ የትራንስፖርት እገልግሎት በባለገሩ አለመኖር፣ የሠላም መጥፋትና ሁሉም ነገር ጦርነት ላይ ማተኮር፣ የውጭ መንግሥትና ድርጅቶች የተለያየ ተፅእኖች ማድረግ ወዘተ ችግሮቹን በማወሳሰብ የኅብረተሰብን መሠረታዊ ሀልውና አጠያያቂ ደረጃ ላይ አድርሶታል። በብዙ ዘመናትና ትውልድ

የተመሰረተን በህል፣ልዕልና፣ ኩራት፣ ተመክሮ፣ግንኙነት፣ ተስፋ፣ ታሪክ በማመንመን ላይ ይገኛል።

አብዛኛዎቹ ችግሮች ሰው ሰራሽ ያለበለዚያም የሰው ተግባር ያበሰቸው ሆነው ይታያሉ። የተፈጥሮ ችግር ተብለው የሚጠሩት በአሁኑ ጊዜ በሰው ቁጥጥር ስር ሊውሉ የሚችሉ ጥቂቶች አይደሉም። ነገር ግን እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ በመወሰድ ላይ ያሉት እርምጃዎች ቁንፅል፣ በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ፣ ምልአተ ህዝቡንና ነገረ ተመክሮውን የማያሰትፍ በግል ጥቅም ዝናና በማን አህሎኝነት (በሽንገላ) ላይ የተመሰረተ ያለበለዚያም ባለማወቅ የሚደረጉ ስለሆኑ ብዙ ጊዜ ከሚሰጡት ጥቅም ጉዳታቸው ጉልቶ ይታያል።

በቅሑፍ ውስጥ ጊዜያዊ ዕርዳታዎች የሚያደርጉት አስተዋፅዖ አልተገለፁም። የነዚህ እርዳታዎች መጠነም ሆነ ዓይነት፣ ሊያደርሱ የሚችሉትን ውጤት ለማከስስ ሳይሆን ራሱን የቻለ ቅሑፍ ስለሚወጣው ለለመንከት ነው። በዚህ ረገድ መጠቀስ የሚገባው ብዙ ጊዜ የአገርም ሆነ የውጭ መንግሥታት ለእጭር ጊዜ ዕርዳታ ትኩረት በመስጠት ዘላቂ መፍትሔዎች ላይ የሚያደርጉት ዕርዳታ እስከዚህም ይሆናል። በሌላው ቅንፍ ደግሞ ችግሮቹን ለማስወገድ ቢሮክራሲን ከመቀነስ ይልቅ ለአስተዳደርና ለአፈፃፀም የማያመቹ አውታሮችን በመዘርጋት እራሱን የቻለ ችግር ማብዛት የተለመደ ሆኗል።

በማጠቃለልም በአሁኑ ጊዜ በዓለምም ሆነ በየአካባቢው ለተፈጠሩትና መፈጠር ላይ ሊሉት ተመሰሰይ ችግሮች እያንዳንዱ ግለሰብ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ስለእሰ፣ ለመፍትሔው እንደዚሁ ሊያበረክተው የሚችለውን መፈለግ፣ መወያየትና በተግባር መፈፀምም የግለሰብ ሃላፊነት ነው። አብዛኛውንም እዲሱና የተማረው ትውልድ ይህንን ሁኔታ የማስወገድ የወገን፣ የአገር፣ የትውልድ ሃላፊነት አለበት። ይህን ሁኔታ ለመቀየር የሁሉንም ጎብረተሰብ ከፍል አስተዋፅዎ ይጠይቃል። መፍትሔውም በፈቃደኝነት፣ በበጉ ፈቃድ፣ በመከባበር፣ በሁሉም ተሰትፎ፣ በመተባበር፣ በመቻቻል፣ በብልሃተኝነት፣ በእኩልነት፣ በትጋት፣ በመተማመን፣ በታማኝነት፣ በአርቆና አስፍቶ አስተዋይነት፣ ላይ

የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። ሁሉም የእቅሙን የሚያበረክትበት ወቅት ነው። ከሁሉም በላይ ይልቅ የመንግሥት ህዝቢነት፣ የህዝብ በሁሉም ደረጃ ትጋትና መሰረታዊ ተሰትፎ፣ የህዝብ መሠረታዊ ፍላጉት እርከታ ቅድምያ የሚሰጣቸው ጉደዩች መሆን አለባቸው።

፮– የግርጌ ማስታወሻዎች ( )

1-7 JOHN W MELLOR & SAHAR GAVIAN, SCIENCE, FAMINE: CAUSES, PREVENTION AND RELIEF. Vol. 235 Jan 1987,PP 539

8 The Challenges of Drought. The Relief and Rehabilitation Commission. Addis Ababa, 1985.

9 ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ፣ ታሪክ ዘመን ዘ ደግማዊ ም ኒልክ: 1959።

10 The Challenges of Drought,...

11 Special Report FAO/UN 1984.

12 Ethiopia: Famine Fact Sheet, UN Emergency prevention and Prepardness Group. Addis Ababa Mar. 1988.

13 Early Warning System, RRC, Special Report, Addis Ababa, Aug. 1987.

14 Beyond the Famine, Food for the Hungry Int'l, An Examination of the Issues Behind Famine in Ethiopia, Feb,1988.

15 GAIA, An Atlas of Planet Management, NY,1984. pp 116

16 National Geographic, «Are We Poisoning Our Air,» Vol.171 NO.4. Apr, 1987.

17 Scientific American, «Acid Rain's Threat,» Aug, 1988.

18 National Geographic,« A Dam Against Famine,» Vol. 167 No. 5, May 1985.

19 Ieuan Le, Griffiths, An Atlas of African Affairs.

20 Lloyd Timberlake, Africa in Crisis, 1986. pp198

21 The Challenges of Drought,...

22 Beyond the Famine,...pp97

23 Lloyd Timberlake,... pp129

24 Panoscope, No.6, May 1988. pp11

25 Beyond the Famine,...pp61

26 Scientific American,...

27 Beyond the Famine,...

28 Beyond the Famine,...

29 ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ,...

30 The Challenges of Drought,...

31 James Bruce, Travels to Discover the Source of the Nile, 1790.

32 Lloyd Timberlake,...

33 World Bank, Recent Economic Development and Prospects for Recovery and Growth. 1987

34 Africa south of the Sahara, 1987, pp431.

35 New Africa Year Book, 1984/85.

36 Africa south of the Sahara,...

37 Brandt Commission, Program for Survival.

38 Lloyd Timberlake,...

39 Panoscope, pesticide: a Choice Between Health and Hunger. No.2 Aug 1987.

40 A de Vos, Africa: the Devastated Continent?, Mans Impact on the Ecology of Africa. The Hague,1975

41 ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ,...

42 Gabre-Ab etal, Ethiopian Medical Journal, «Neurolathyrism » a Review and Report of an Epidemic,» Addis Ababa, 1978

43 Africa Report, Special Report-Locust, Sept 1986.

የኢትዮጵያ ረሀብና
የምዕራብ ጋዜጦች አስተያየት

ቀሪኞ ፈይሣና ጊደኞቹ
ሰሜን አሜሪካ

መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያለው ሥነጽሑፋዊ ማስረጃ የሚቀርብላት ታላቅ ጥንታዊ ሥልጣኔ ያለት ታሪክዊ አገር ለመሆኗ በርክታ የታሪክ ሊቃውንት የመሰከሩት ጉዳይ ነው። እንዲያውም በአንድ ወቅት በዓለም ከታወቁት ሦስት ወይም አራት ግዛተ አዜ (KINGDOM) ጋያል አገሮች እንዷ እንደነበረች ይተረክል። ይሁንና ኢትዮጵያ በታሪኪ ደግሞ ድርቅ፣ ረሀብና ጦርነት (እንዳሁኑ አይከፋ እንጂ) እጥታ አታውቅም። እንደውም እንደእንዳንደች ተቺዎች አስተያየት የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው ቢባል ከእውነት በብዙ መራቅ አይሆንም። የቱርክች፣ የግብፃች፣ የፋሽስት ኢጣልያ ወረራዎች፣ የዐድዋ ጦርነት፣ የግራኝ መሀመድ (ጅሐድ) ጦርነት፣ የዘመነ መሣፍንት (እርስ በርስ) ጦርነት፣ወዘ.ተ. እንደምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ። እንዲሁም አያሌ የአውሮፖ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ኢትዮጵያን በሀይማኖት ሰቢያና ቢቻልም ሙሉ በሙሉ እጠቃለው የቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ጥረው ሰይሳከሰቸው ቀርቷል። ሆኖም የተወሰኑ ክፍሎቿን ቆራርሰው በቁጥጥራቸው ስር አውለዋል። ከታወቁት የአውሮፓ ኩሎኒያሊስት አገሮች እንዷ ጣሊያን በዱቼ ሙሶሊኒ አገዛዝ ሥር በነበረችበት ጊዜ በእብሪት ተወጥራ የኢትዮጵያን ከተሞችና አውራ መንገዶች ይዛ እንደነበር የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ገጠሩንማ፣ ዱሩንማ አበት አርበኞች ይዘውት ስለነበር ጣልያኖች ከከተማና ከአውራ መንገድ ሊወጡ አልቻሉም።

ለመሆኑ ኢትዮጵያን ቢቻል ማንነቷን ለማውደም፣ በይቻል ግን ቀስ በቀስ አከሏን እየቆራረሱ ለማዳከምና ፍጹም በቁጥጥር ስር ለማዋል ይህ ሁሉ የከሎኒያሊስቶች የዘመናት ትግል ለምን ተከሄደ?! ኢትዮጵያውያንስ እንደምን በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በሥልጣን ሽሚያ፣ በግዛት ድርሻ ላይ የተመሰረቱ የውስጥ ቅራኔዎቻቸውን ለጊዜው አስዝበው እንደምን እንደአንድ ሰው በመቆም በመጣው የባህር ማዶ ጠላት ላይ ተረባረቡ? ለነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ እንዲሰጡን ሀቀኛ የተሪክ አዋቂዎችን መጋበዝ ግዴታ ቢሆንም ለጊዜው የኢትዮጵያን ታሪክ በእፍሪካና በሌላው ጥቁር ሕዝብ የታሪክ ክልል(context) ውስጥ በማስገባት መመልከቱ የነገሩን ፍንጭ ለማግኘት ያህል ሰይጠቅመን

እይቀርም።

ከእፍሪቃ አህጉር በባርነት የተሸጡት ዝርያ ጥቁር-አሜሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንዲሁም ከባርነት ሽያጭ ቢድኑም ከዚያው በሚወዳደር የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ሲማቅቁ የነበሩ አፍሪቃውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ኢትዮጵያንና ሰንደቅ አለማዋን የትግላቸውና የነፃነታቸው አርማ አድርገው ለመመልከታቸው አያሌ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል። ዘራ ልብ ብለን ብናስተውል በተለይ በጃማይካ ራስተፈሪያን የሚባሉ ማህበረሰቦች የኛን ሰንደቅ ዓለማና አገራችንን ኢትዮጵያን በኩራት ሲታዩበት ነገሩ ለአዬ ኃይለሥላሴ ከለቸው ግለሰዊ ፍቅር ብቻ የመነጨ ይምሰል እንጂ ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት በደረጉት ትግል ውስጥ የእንድ «ኢትዮጵያ የምትባል ነፃ የጥቁር አገር» መሰረው እፍሪቃ በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ስር በወደቀበት ወቅት መኖር ሁኔታ ጋር የተያያዘ ከባድ የነፃነት ፍለጉት ስሜት (emotion) ጋር የተቆራኘ ጉዳይ ነው። እንዳንድ የሰሜን አሜሪካ ጥቁሮችና እስከሁን በነጭ የበላይነት የሚገዙት የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ አለማ በቤተ ክርስቲያናቸውና በሊሎች መሰብሰቢያ ሥፍራዎቻቸው ሁሉ ከማሰየት አልፈው ቤተክርስቲያኖቻቸውን ሰይቀር « church of Abyssinia» ብለው መሰየማቸው ከጥልቅ የነፃነት ፍለጉት ስሜት የመነጨ ድርጊት መሆኑን ያስገነዝበናል።

እነሆ ዘራ እንኪ በነፃው ስሜን አሜሪካ የሚኖሩ ጥቁሮች ከአራት መቶ ዓመት በባርነት በኃላ መብታቸውን ለማስከበር በሕይወት ብዙ መሰዋዕትነት ከከፈሉ በኃላ በወረቀት ላይ ብቻ ሰብአዊ መብታቸው ከተከበረ እነሆ ገና ሃያ ዓመት ሆነው። ይሁን እንጂ ዘራም ቢሆን በዘር ጭቆናውና ከነጭ እኩል መብት ባለማግኘታቸው ለሚያደርጉት ትግል በሚሰበሰቡባቸው የጥቁር ማህበሮች (Negro Community Centers) የአምዱ ምኒልክን ምሥል «ታላቁ አፍሪካዊ ንጉሥ፤ በወራሪ የአውሮፖ ኮሎኒያሊዝም ለይ የእድዋን ድል የተቀዳጀው የጥቁር ንጉሥ» በለው ጽፈውበት በየሰብሰባ አደራሽቻቸው ያሰያሉ። እንደንድ የሥውር ቅኝ አገዛዝ (Neo- Colonial) በሽታ የተጠናወታቸው ነጭ ደራሲያንና (በሰሽሊዝም ሰም ጭምር እየማሉ) አፍሪካዊነታቸውን የዘነጉ ግለሰቦች ጭምር የአፍሪካዊውን ጀግና አጤ ምኒልክን ለባሪያ ግዢና ለጥሬ ሀብት፣ እንዲሁም ለሽቀጥ መቸርቸሪያነት ቅኝ ግዛት ከተቀዳጁ የአውሮፖ ወራሪዎች እኩል «በወራሪነት» ወንበር ላይ እንድናስቀምጥ ይጋብዙናል። ለነዚህ መልሰችን «አሸፈረን» እናደምጣችሁም ብቻ ነው። እረ ለመሆኑ ነፃነት የጠማቸው ጥቁር ሕዝቦች ለምን ኢትዮጵያን የነፃነታቸው ተስፋ ማድረጊያና አለኝታ አድርገው ለማየት ፈለጉ?! ለዚህ መልሱ አጭር ይመስለናል። ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ጥንታዊያን አባቶቻችን በቂንቂ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ሰይሰያዩ ለጊዜው ያላቸውን የውስጥ ቅራኔ ረገብ አድርገው ጠላትን እንደቀትር ንብ ተረባርበው

በመናደፍ በአገራቸው ሰይ የነጭ እገዛዝ እንዳይመሰረት በመታገሊቸውና ለነፃነት ያሊቸው ቀናኢነት በሰንደቅ ዓሊማቸው ሕብረቀለማት በመሊው ጥቁር ሕዝብ ዘንድ እንደ ቀስተ ደመና ጎልቶና ከፍ ብሎ እንዲታይ በማድረጋቸው ነው። ጃግኖች አበቶቻችን ኢትዮጵያውያን በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ስሚማቅቁ ወንድሞቻቸው የነፃነት ሰንደቃቸውን ከፍ አድርገው በማውሰብሰብ በአፍሪካ ምድር የመጀመሪያ ነፃ አገር (ጥንታዊቷን አቢሲኒያ የዘራዋን ኢትዮጵያን) በዘረኛ የአውሮፖ አብሪት የማትደፈር፣ ብቸኛ ነፃ የጥቁር አገር በመገንበታቸውና አለኝታ በመፍጠራቸው ነው። ይህንን የኢትዮጵያ የነፃነት አለኝታነት ዛሬ የነገይቷን ነፃ ደቡብ አፍሪካ ለመመሥረት የሚታገሉትና የሬዲዮ ፕሮግራም ለሕዝቦቻቸው ከአዲስ አበባ ራዲዮ ጣቢያ የሚያስተሊልፉት የነፃነት ታጋዮች ከማንም የበለጠ ያውቁታል።

ይህ የኢትዮጵያ በለታሪክነትና የሥልጣኔ ሀገርነት የማይዋጥሊቸው የነጭ የበለይነት አስፈሬ የአውሮፖ የፖለቲከ፣ የፍልስፍናና የሥነፍጥረት ሊቃውንት ኢትዮጵያ የምትበል አዋኪ (Problematic) አገር የነሱን የነጭ የበለይነት ንድፈ-ሀሳብ የምታፈልስና ብሎም የምታከሽፍ (ለጥቁር ሕዝብ ጥንታዊ ሥልጣኔ ቆርቋሪነትና በነቤትነት በጉልህ ማሰሪጃነት የምታቀርብ) አገር በመሆኗ ስለጥቁር ስልጣኔ-ቢስነት ድምዳሜ በየፋበት ብእራቸው ኢትዮጵያን እንደሚከተለው ይገልጧታል። እንጠቅሰለን፤

> ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ልዩ ከስተት ነች። ኢትዮጵያና ግብጽ ታሪከቸው ሰይቶራረጥ እስከ ጥንቱ ዘመን ድረስ ሊጠቀሱ የሚችሉ ብቸኛ አፍሪካዊ አገሮች ናቸው። ግብጽ በተከታታይ (በአረቦችና በአውሮፖውያኖች) ወራሪዎች ምክንያት ቀስ በቀስ ከራሷ ታሪክ እየራቀች ወደመሄድ ስትቃረብ ኢትዮጵያ ግን ለእጥር ጊዜ በኢጣልያን ከመወረሩዋ በስተቀር ጥንታዊ («እርጅናሌ») መልኳን እንደያዘች ለዘመናት ቆይታለች። በሌላ አነጋገር፣ ኢትዮጵያ ልዮ የሆነ ባህሏን ለዘመናት ጠብቃ ለማቆየት በቅታለች። ይህም ልዮ በሀል ሁለት የተፈጥሮ ተሰጥኦ ካላቸው (Gifted) ሕዝቦች ተራከቦና ጋሊም መዋሃድ የመነጪ ነው። እነዚህ (የዘራይቱን ኢትዮጵያን የመሰረቱ) ሕዝቦች ኩሽች ወይም <u>ቶደቸው ጥቁር የሆነ</u> <u>የነጭ ነገድ ዝርያዎች</u> ምናልባትም የምድሪቱ አብር በቀል (indigenous) ሲሆኑ ሌላው ወገን ደግሞ ሴማውያን ምናልባትም ከአረብ ምድር ፌለሰው የመጡ ሳይሆኑ አይቀርም። (1) (እጽንኦት የነዚህ ፀሐፊዎች ነው)።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የነጭ ዘር የበለይነት ፈላስፎች ነጭ ቀለም ያለበሰ ሕዝብ (የነጭ ዝርያ ያልሆነ ጥቁር) ሥልጣኔ ሊኖረው እንደማይችል ነው የሚነግሩን። ነጮቹ ፈላስፎች የሚነግሩን ይህንን ብቻ አይደለም። ጥቁር ህዝብ ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከተው እንዲችም ነገር እንደሌለ እንደተፈጠረ ያለ (barabrian ወይም Primitive) ነው ብለው

ሊያሰምኑን ይጥራሉ። በነሱ አስተያየት «ጎሳ ቀሩ ጥቁር ሕዝብ» ሥልጡኑ ነጭ የሰጠውን ጥበብና እውቀት እንኪን በእግበቡ ለመጠቀም የአእምሮ ዝግጅት፣ የአስተዳደር መዋቅርና ችሎታ የለውም። እዚህ ሰይ ልብ ብለን ማስተዋል ያለብን ፍጹም ጥቁር አፍሪካዊት የሆነችውን አገር (ኢትዮጵያ) የስልጣኔ ባለቤትነቷን የተጎናፀፈችው በጥቁር ሕዝቦቿ ጥበበኛነት ምክንያት ሰይሆን ሕዝቦቿ በጥቁር ቆዳቸው የተለ ጉመ የነጭ ነት ባህርይ «በመታደላቸው» ሆኖ መቅረቡን ነው። ይህ አሰፋሪ የሆነ የአውሮፖ «ሰይንሰዊ» ትንተና ኢትዮጵያን ከጥቁርነት ወደ ነጭነት መድበ የጥቁር ህዝቦችን የስልጣኔ ቅርስ ባለቤትነት ለመንጠቅ የተዘጋጀ «እውቀት» ነው። የግብጽንና የኢትዮጵያን (የአፍሪካ) ሥልጣኔ መስራችነት ነጭ ቀለም ቀብቶ ጥቁር ሕዝብ በታሪክ ውስጥ የስልጣኔ መስራችነት የለውም ብሎ የሚደነግገው እብሪተኛ አስተሰሰብ ከተራ የሕፃናት እንቶቅልሽ ጨዋታ ምንም ያልተሸለ ቢሆንም በአውሮፖውያን «ሊቃውንት» ተደርሷልና ኢንሰይክሎፒዲያ ብሪታኒካን በሚያህል የእውቀት ማህደር ውስጥ ሥፍራ መስጠቱ ትንሽም ቢሆን ለታዛቢ ሰያሰገርም አይቀርም። በዚሁ እንፃር ግን የምዕራባውያን ፍልስፍናና «ዘመናዊ ትምህርት»(modern education) ስናገበሰብስ ያደግን አበሾችና ሌሎች አፍሪካውያን ምንኛ በእውቀት ሰም ሐሰት ሰንቀሰም እንደነበረ ይህ ምሳሌ አነስተኛ መረጃ መሆኑን እንረዳለን።

ዛሬ የአፍሪካ ሕዝቦች አስተዳደር ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፈራትና መደበር አመቺ ሆኖ አለመገኘት ዓይነተኛው ምክንያት ዘረኛ ፈላስፎች እንደሚተርኩት የጥቁር ሕዝብ ንጥረ-አእምሮ (IQ) ዝቅ በማለቱ ሰይሆን የአውሮፖ ከሎኒያሊስቶች የአፍሪቃንና የሌሳውንም ሦስተኛ ዓለም ከፍሎች በዘረኛ ርእዮተዓለም የተመሠረተ ቅኝ ግዛታቸውን መስርተው በተለይ በእንዳንድ የአፍሪካ ከፍሎች (ለምሳሌ እንደሞዛምቢክና አንጎላ እንዲሁም ደቡብ አፍሪካ) እስከ 500 ዓመት ድረስ ሲቆዩ ሕዝቡን"እደንቁረህ ግዛ"በተባለ ፈሊጣቸው ትምህርት እንዲያገኝ በማድረጋቸው ነው። ለምሳሌም ያህል በሞፈ የዘረኝነት ፍልስፍናቸው በጣም የታወቁት የቤልጂግ ከሎኒያሊስቶች ለምን በቅኝ አገዛዛቸው ሥር ለሚገኘው የአፍሪካ (ከንጎ) ሕዝብ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት እድል እንደሚነፍጉት ሲገልጡ እንዲህ ብለዋል።«የከፍተኛ ትምህርት የቀሰመ አፍሪካዊ የራሱን ወገኖች (አፍሪካውያንን) ሊያገለግል አይችልም።» ስለሆነም፣ እንደቤልጂጎቹ አባባል «አፍሪካውያንን ማሰልጠን ቀስ በቀስ» ነው። የሁለተኛ ደረጃ ወይንም የከፍተኛ ትምህርት ለአፍሪካዊው (ጥቁር ፍጡር) ማቅረብ ማለት ግንፎ ሊውጥ የሚገባውን (ጥርስ ያለበቀለ) ህፃን ልጂ ሥጋ እኽክ ብሎ እንደመጋበዝ ይሆናል«(2)እነሆ በዚህ ዓይነቱ ስንኩል እምነት ሰይ በተመሠረተ እገዛዝ ሥር የቆየችው የቀድሞዋ" ቤልጂጋዊት "ከንጎ ነፃነቷን በተጎናፀፈችበት ዓመት ፲፫ ሚሊዮን በመሃይምነት የሚማቅቅ ሕዝብና

በራሳቸው የግል ጥረት የተማሩ ፲፯ የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን ብቻ ነበሩዋት። አፍሪካ ለአውሮፖ በሰረከበችው ወርቅ፣ እንቁ፣ እርካሽ ጉልበትና ጥሬ ሀብት ምትክ ያገኘችው ቅርስ ማሃይምነትንና ኃላቀርነትን እንዲሁም ድህነትን ነበር።

አገራችን ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አህጉር ጠርሰ ከቀኝ አገዛዝ መላቀቅ አበተዋጽኦ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለመላው የአፍሪካ ጥቁር ሕዝብ የሥልጣኔ ባለቤትነት ቀዋሚ ሐውልት ሆና መገኘቷም ጭምር የሚያሰጠላቸውና የሚያሰደነግጣቸው ዘረኛ የአውሮፖ ፈላስፋዎች ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ መንግሥት በአውሮፖ አቶጣጠር በ1974 ዓ.ም «የኢትዮጵያ መንግሥታዊ መመሪያ ሶሻሊዝም ነው። እኛም መሪዎቿ ከሚዩኒስቶች ነን» የሚል መፈክር አንግበ ብቅ ሲል የጥላቻቸው ንረት የሰማዩን ጣሪያ ዘንጥሎ ሊወጣ መከጀሉን ለለፉት ፲፫ ዓመታት አፈ ቀላጤዎቻቸው በልዩ ልዩ ዜና ማሰራጫዎች (ጋዜጦች፣መጽሔቶች፣ መጽሐፎች፣ ሬዲዮዎች፣ ቴሌቪዥኖች) አማከኝነት ከሚሰነዝሩት ጠዋነት የጎደለው ተራ እሽከሰሴና ዱልዱም ትችቶች መገንዘብ ይቻላል።

ኢትዮጵያ ዛሬ ለደረሰችበት ችግር ከበቂት ዋነኛ ምክኒያቶች አንዱ የቀድሞ መሰፍንትና መኪንንት፣ እንዲሁም ዛሬ በስልጣን ላይ ያለውና በውጭ መልኩ ሶሻሊስት በአሠራሩና በባህርዩ ግን ፍጹም ፊውዳሊዊነት የሚያጠቃው የፐሬዚዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ ጭምር ቢሆንም የኢትዮጵያን ማንነት (identity) ለመደምሰስ ከውጭ የታገሉ በርከታ ኃይሎችም ዓይነተኛ ሚና እንደላቸው መገንዘብ የሀቀኛ ኢትዮጵያውያን ተገቢ ድርሻ ይመስለናል።

የኢትዮጵያ ነገሥታት ከርስትናን ከተቀበሉበት ዘመን ጀምሮ የእስልምና ሃይማኖት በሰ ኡዲ አረቢያ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ሙሉ ለሙሉ ሰላም አግኝታለች ብሎ መናገር ባይቻልም እስልምናን ማስፋፋት ተግባራቸው አድርገው በተቀበሉ ዐረብ ጎረቤቶቿ ዓይን እስከእሁን ድረስ በጎሪጥ መታየቷ ደግሞ በገሀድ የሚታይ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያን አዘውትረው በሚገለምጡ እስላማውያን ዐረቦች አስተያየት የኢትዮጵያ አብዮት በ1974 ዓ/ም እስከፈነዳበት ጊዜ ድረስ አገሪቱ «በእስልምና ባህር ውስጥ የምትገኝ የክርስቲያን ደሴት» ሆና ትቆጠር ነበር። ከለውጡ ወዲህ ደግሞ ከግልምጫም አልፎ አልፎ አልፎ በአገሪቱ ላይ በቀይ ባህር አሸጋግረው ትዝምዝማቸውን እስከመወርወር ደርሰዋል። በዐረብ እስላማውያን ዘንድ እሁን ኢትዮጵያ «በወግ አጥባቂ (ኮንሰርቫቲቭ) ባህር ውስጥ የምትገኝ የኪሚዩኒዝም ደሴት» ነች። አሰዘኝ ነገር ግን ቀድሞም ሆነ እሁን ኢትዮጵያውያን እስላሞች በሀገራቸው መኩራት ብቻ ሳይሆን

በኢትዮጵያ ላይ የተሰነዘረውን ወረራ ሁሉ በመመከት የአገራቸውን ክብር ከመጠበቅ አልፈው ጎሰና ሃይማኖትን ተንተርሰ የሚመጣውን ጥቃት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጎን በቆራጥነት በመሰለፍ ማከሸፋቸውን ሁሉ እነዚህ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችና ፀሐፊዎቻቸው ለመገንዘብና ለማመን አይፈልጉም። በበኩላችን የሀገር ፍቅር ያላቸው ታሪክ አዋቂዎች ይህንን የታሪክ ሀቅና እንዲሁም እኒህ የጎረቤት ጠላቶች ኢትዮጵያውያን በውስጥ ግጭት የተዳከሙበትን ወቅት ጠብቀው እንደአደፈጠ ተኩላ አገራችንን መተናከሳቸውን ከግብጾችና ከቱርኮች ወረራ ጀምሮ ያለውን ጊዜ እንደሚያተኩሩበት ያለንን ተስፋ እንገልጣለን።

በመሠረቱ የዚህ ጽሑፍ መነሻ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክ ዊነት በመዘብዘብ አንባቢያንን ለማታለት ሰይሆን ዛሬ የኢትዮጵያን ማንነት ለማጥፋት ርብርቦሽ የሚያደርጉ ኃይሎችና ድምፃቸውን ጎሳ አድርገው የኢትዮጵያን ውድቀት የሚዘምሩ ጋዜጠኞች ለምንና በምን ሁኔታ ከቀድሞ ጀምሮ ኢትዮጵያን የሚፃረሩበትን የታሪክ ጭለንጭል ለማሳየት ስንል ነው። ይህ ጽሑፋችን በዚህ ታሪካዊ መሠረት ላይ ከልተዋቀረ ደግሞ የትኛው ጋዜጣ ለምን በሚፃፍበት ዘይቤ እንደሚፃፍና ዛሬ ማንም ሊንቃት የቃጣውን ለኛ ግን ከቡር የሆነችውን አገራችንን« ጠብ ያለሽ በዳቦ» በሚል ፈሊጥ እንደሚተኩሲት የቀድሞውን ታሪክ ከእሁኑ እፃፃፋቸው ጋር ለማዘመድ አይቻልም። የምዕራቡ ጋዜጣ አዘጋጅዎችና ጽሑፍ የሚያበረከቱ ቃል አቀባዮችም (ሪፖርተሮች) ከአቢቶቻቸው ከሎ ኢያሊስቶች የተረከቡትን ኢትዮጵያን የማጥለላት ዘመቻ ዛሬ ኢትዮጵያ በደረሰበት አሰዛኝ ማህበራዊ ቀውስ (ረሀብ፣ ጦርነት፣ወ ዘ ተ)ሰቢያ በማሰታከክ ነባር ቂማቸውንና እዲስ ርእዮተ ዓለማዊ ጥለቻቸውን ለመወጣት በጽሑፎቻቸው ሁሉ መከርከም ብቻ ሰይሆን ከዓለም ከርታ ላይ ሊፍቂት እንደቃጡ ለማስተዋል ደግሞ የዛሬውን ከጥንቱ ሁኔታ ጋር አጣምሮ የሚያሳየንን የታሪክ መነጽር ለማጥለቅ ስንችል ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ በምዕራባውያን ጋዜጠኞች ዓይን ስትታይ

ለዚህ ሐተታችን እንዲያገለግሉን ብለን ያገለበጥናቸው የእንግሊዝ፣ የአሜሪካ፣ የካናዳ ጋዜጣዎች የተሰበሰቡት በነሲብ (randomly) ነው። የሰበሰብናቸው ጋዜጣዎች በኢትዮጵያ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር የ1984 ዓም ረሀብ ከጀመረበት ጊዜ እንስቶ ይህ ጽሑፍ እስከተዘጋጀበት ቀን ድረስ ነው።

በሬዲዮዎች፣ በቴሌቪፕኖች፣ በሲሚናር እደራሾች ስለኢትዮጵያ የቀረቡ ዝግጅቶችንና እንዲሁም በሊሎች አገሮችና አህጉራት በእንግሊዝኛና በሊሎች ቋንቋዎች የተፃፉ ጋዜጦችን አልተመለከትንም። እነዚህን በሙሉ

ለወደፊት ተመራማሪዎችና ለእናት ኢትዮጵያችን ተቆርቋሪ ለሆኑ ሐበሾች ሁሉ ጽሑፎቹን እንዲሰበስቧቸው እንዲያጠኑዋቸውና፣ ከቱም ከተቻለቸው፣ በሰምና ወርቅ አማካኝነት የጥናቶቻቸውን ውጤቶች እንዲያካፍሉን እንጋብዛቸዋለን። በኛ በኩል ግን እስከሁን ከሰበሰብናቸው ኢትዮጵያና አፍሪቃ ነክ የጋዜጣ አርእስት ውስጥ አንድ አንኳ ስለአፍሪቃም ሆነ ስለኢትዮጵያ ቀና (positive) የሆነ አስተያየት ይዘ የቀረበ አላጋጠመንም።

ወደ ተነሳንበት ፍሬ ነገር ትንታኔ ከመግባታችን በፊት ግን ምንጊዜም ቢሆን ሚዛናዊ (objective) ነን ብለው የሚለፍፉ የምዕራብ ጋዜጣዎች አዘጋጅዎች በአጠቃላይ አሠራራቸው የካፒታሊስት ሥርዓትን ዓለማቀፋዊ የበላይነትና ገናናነት ለመቀዳጀት የሚጠቀሙባቸው መሠሪ (subtle) ዘዴዎች ጥቂቶችን እናስተውሳለን። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለማስታወስ የምንፈልገው ጉዳይ የሰሻሊስት አገሮች ጋዜጣዎችም ቢሆኑ የዚያን ሥርዓት የበላይነትና ሥልጣን ለይ ያሉትን ፓርቲዎች ፍጹም ወሰኝነት የሚያስጠብቁ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ መሆናቸውን ነው። እዚህ ላይ በሰሻሊስቶችና በካፒታሊስቶች ጋዜጦች መካከል እንድ ሙያ ጠቀስ የሆነ መሠረታዊ ልዩነት መኖሩንም ልንጠቁም ይገባል። ይኸውም ሰሻሊስት ጋዜጦች ግልጽ በሆነ መንገድ የሥርዓቱ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች መሆናቸውን ሲያስታውቁ፣ የካፒታሊስት ጋዜጦች ግን እኛ ለሁሉም የማናዳላ «ሚዛናዊ» ፍጡር ነን ብለው ድፍን የምዕራቡን አንባቢ ያደናግራሉ። በመሰረቱ እነሱም ቢሆኑ ለሥርዓቱ የቆሙ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች ለመሆናቸው ዋነኛ ምስክሩ የየእለቱ ድርጊታቸው ነው። ይህንን ድርጊታቸውን የሚሸፍኑበት ዘዴ ግን በግልጽ ለማን ወገን እንደቆሙ እለመናገራቸው ነው። በእርግጥ ለማን እንደቆሙ ግን የነቃው አንባቢና አራሳቸው አዘጋጅዎቹና ከበርቴ ባለቤቶቻቸው በማያሻማ ሁኔታ ያውቁታል። ምዕራባዊ ጋዜጦች የዋሁን አንባቢ እኛ ዓለማችን ዲሞክራሲን ለማስከበርና ሕዝቡም ለማሰወቅ (to inform) ነው ብለው ያሳምኑታል። የሚያስከብሩት ዲሞክራሲ ግን የማን ዲሞክራሲ እንደሆነ እናውቀዋለን፣ እነሱም ያውቁታል።

ሊብራል (ለዘብተኛ) የሆኑ የምዕራብ ዲሞክራሲያዊ መንግሥታት በመወያየትና በማሳመን (Through consensus) እንጂ በማስገደድና በማስፈራራት (Through coersion) አገር አያስተዳድሩም። ይህ የቆየ የፓለቲክ ባህላቸው ለመሆኑ እይከድም። ይሁም እንጂ በተለይ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣና ሌሎችም የዜና ማሰራጫ ዘዴዎች (mass media) ሕዝቡን ከማሳወቅ ባሻገር በሕዝቡ ዘንድ የገዥ መደቦች የፖለቲክ ፍላጎት እንዲሰርጽ እጅግ በረቀቀ ዘዴ እንደሚጠቅሙ ደግሞ አሌ ሊባል የማይገባ እውነት መሆኑን አያሌ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ጥበብ አዋቂዎች ይናገራሉ።(3) ጊትሊን በተባሉት በዚህ

መስክ እየቂ አገሳለጥ የምዕራባውያን «mass media» እምብርት ተግባራቸው ያሉትን ሥርዓቶች እንዳሉ የሚቀጥሉ ነገሮች ሆነው በሕዝብ ልቡና እንዲቀረጹ የሚረዱ እጅግ ኃይለኛ መሣሪያዎች ናቸው።

እዚህ ላይ አንድ አጥብቀን ልናጤነው የሚገባን ጥያቄ በአንድ ጋዜጣ ላይ አንድ ድርጊት /ክስተት ዜና ሆኖ እንዲቀርብ በበላይነት ማን ይወስናል የሚለው ነው። የትኛው የጋዜጣ ገጽ ላይ በየትኛው አምድ ውስጥ ከምን ዓይነት ዜና ጎን ይቀመጣል?። የዜናው ርእስ ፊደሎችስ ምን ያህል ጎልተው ይዣፉ? ለዜናው አሰማኘ ድጋፍ የሚሰጡ ሥዕሎች ምን ዓይነትና መጠናቸውስ ምን ያህል ነው? እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ጥያቄዎች ሁሉ የጋዜጦች ባለቤቶችና አዘጋጅዎቻቸው ከፍተኛ የህትመት ፖሊሲ ውሳኔ የሚሰጠባቸው ናቸው። በሌላ አነጋገር የትኛውም ዜናና ምሥል በዘፈቀደ እንደተገኘ የሚገፍና በጋዜጣው አከል ውስጥ በአጋጣሚ የሚቀመጥ አይደለም። አልፎ አልፎ የምዕራብ ጋዜጣዎችን አቀራረብ ለምሰሌ ያህል ልብ ብለን ብናስተውል፤ የፍልስጥኤሞች ንቅናቄ መሪ የሆኑት አቶ ያሲር አረፋትና የሊቢያው መሪ ከሎ ኔል ጋዳፊ ምሥሎች አስቀያሚ ሆነው እንዲቀርቡ በተንታቂ ይዘጋጃሉ። ይህ ብቻ በቂ አይደለም። ከምሥላቸውም ስር የሚዣፈው ማብራሪያ እኒያን ግለሰቦችና የሚመሩትን ድርጅት ወይም አገር የተራ ወንጀለኞችና ሽብር ፈጣሪዎች ማህበር አድርጎ ለማቅረብ ሆን ተብሎ ታልሎ ተመርጠውና ተመጥነው ይዣፉ። ይህ ታዲያ ባጋጣሚ የተደረገ የሚመስለን ብዙዎች ብንሆንም ድርጊቱ ሆን ተብሎ ለመደረጉ የስነ ጽሑፍና የጋዜጠኝነት ሙያ የቀሰሙ ሁሉ አበክሪው ይረዱታል። በለለአህጉራችን (አፍሪቃ) እና በለሌሎች የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች የሚወጡ ዜናዎች ሁሉ አጉልተው የሚያሳዩት የኢኮኖሚ ውድቀት፤ የሽብር መስፋፋት፤ የረሀብ መበራንን ነው። እኒህም በሚገባ ተመርጠው ነው እንጂ ከአፍሪቃም ሆነ ከሌላ የሦስተኛው ዓለም ከነዚህ የተሻሉ የኢኮኖሚ ልማትና የማህበራዊ እድገት ዜናዎች ሳይገኙ ቀርተው አይደለም። በምዕራቡ ዓለም የዚህ ዓይነቱ የሦስተኛው ዓለም የውድቀት ዜና መቅረብ ለገዢው መደብ በለለም ተደለድሎ መኖር ዓይነተኛ አስተዋጽኦ አለው። በአፍሪቃ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቢኖሩም በሰፊው የሚዣፍባቸው ምክንያት ለአፍሪቃ ችግር መፍትሔ በመሻት ላይ ያተኮረ ቀና ስሜት ሳይሆን የውድቀቱ ዜና የምዕራቡን ዓለም ሠራተኛ ሕዝብ (working class) ባለው ረክቶ «ተመስገን እምላኬ የባሰ እንደ አፍሪቃ ያለም አለና» ብሎ ብዙ መብት ከቀጣሪዎች ዲታዎች እንዲይጠይቅ ለማድረግ የታቀደ ጭምር ነው። በተጨማሪም «ለኢትዮጵያ የ40 ሚሊዮን ብር ስንዴ በ2 ሰምንት ውስጥ ለከን» የሚለው ዓይነት የአሜሪካ ዜና የምዕራቡ ሕዝብ ተራ ብሄራዊ ኩራትን (እኛ እብሪተኛነት የምንለውን) እንዲጎናጸፍ ለማድረግ የታሰበ ይመስለል። ሌላው በቅርብ ልናጤነው የሚገባ ጉዳይ የምዕራቡ የጋዜጠኝነት

ሥርዓተ ትምህርትና አወቃቀር ነው። የሙያ ትምህርት አሰጣጥም ቢሆን የሚያተኩረው ዜናዎቹ ድርጊቶችንና ክስተቶችን እንዳሉ ፍንትው አድርጎ በሚቀርብበት ሁኔታ ላይ ሳይሆን በመሠረታዊ ትንታኔ (subtle analysis) በጉዳዮቹ ላይ ብይን (judgement) በማሰለፍ የገዥውን መደብ ፍላጎት የሚያንጸባርቁበት ሁኔታ ላይ ነው። የነዚህ ዓይነት ጋዜጠኞች የሙያ ጥበብ (profession) አልፈና አሜጋ ባጭሩ ይህንን ይመስላል።(4) ዛሬ በእንግሊዝ አገር በወ/ሮ ማርግሬት ታቸር፤ በአሜሪካ በኤቶ ሮናልድ ሬገን፤ በካናዳ በኤቶ ብራያን ምሮኒ መሪነት የሚገዙት ወግ አጥባቂ (ከንሰርቫቲቭ) መንግሥታት የየራሳቸው የፖለቲካ ልሳን ቢኖራቸውም «ለሕዝብ ከሚያገለግሉት» ጋዜጣዎች መከከል የመንግሥታቱን (የገዢውን ከበርቴ መደብ) ፍላጎት የሚያንጸባርቁ ያስፈልጉዋቸዋል። እነዚህ ዓይነት ጋዜጣዎች ለከበርቴው መደብ የበላይ ገዥነት የቆሙና በቡርዥዋዎች ባለቤትነት ቁጥጥር ስር ያሉ «ነፃ ነን» ባይ የበለቤቶቻቸውንና የበላይ ጠባቂዎቻቸውን (መንግሥታት) ፍላጎትና ጥቅም ማርከት ዕለታዊ ተግባራቸው ነው። የፖለቲከና የኢከኖሚ እንዲሁም የማህበራዊ ኑሮ «እከክ» ሲያጋጥም ጋዜጣው የመንግሥቱን፤ መንግሥቱም የጋዜጣውን «ጀርባ ማከክ» አይቀርም። ይህ ማለት ግን ጋዜጣዎቹ በሥልጣን ላይ ያሉትን መንግሥታት አይነቅፉም ማለት አይደለም። አሰምረው ይነቅፏቸዋል። ይሁንና ነቀፋቸው ግን እስከዚህ የሥልጣናቸው መሠረት እስኪናጋ ድረስ የጠነከረ አይደለም። መንግሥታቱም ይህንን ውስጣዊ መተሳሰብ ስለሚያውቁበት ጋዜጦችንና አዘጋጅዎቻቸውን አይተናከሉዋቸውም። በኢከኖሚና በቴክኖሎጂ ከዳበሩት ሰባት የምዕራብ አገሮች የእነዚህ የሥሥቱን ሰሜቶች ከሚያንፀባርቁት በርከታ ጋዜጣዎች ውስጥ ሦስቱን ዋና ዋና «ነፃ» ጋዜጣዎች እንጠቅሳለን።

እነዚህም አንደኛ The New York Times (5) በአሜሪከ፤ ሁለተኛ The London Times በእንግሊዝ፤ ሦስተኛ The Globe and Mail በካናዳ ይገኛሉ።

በአገራችን በኢትዮጵያ ዛሬ የፐሬዚደንትነት ሥልጣን የጨበጡት የቀድሞው የጊዚያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበርና የአሁኑ «የሠርቶ አደሮች ፓርቲ» መሪ ከሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም ሰቪየት አቀፍ አቂም በመያዛቸው በኢትዮጵያ ጥቅምና ወታደራዊ ከልል (base) ያጡ የምዕራብ መንግሥታትና የወግ አጥባቂ፤ እንዲሁም የሊብራል ጋዜጦች የነቀፋ ብቻ ሳይሆን የዘለፋ ውርጅብኝ ጭምር ተዶያዙዋቸው። እጅግ አስገራሚ የሆነው ግን «ሰሻሊስት ነን» የሚሉት አፈጮሌ የግራ ክንፍ ጋዜጦች ሁሉ ሳይቀሩ ወንጭፋቸውን ወደኢትዮጵያ መሰንዘራቸው ነው። እንደኢትዮጵያ ያሉ የአፍሪቃ አገሮች ሰቪየታዊውም ሆነ አሜሪከዊ ድጋፍ ሊያገኙ የሚችሉት የእነዚህ ዓይነት አገሮችን የፖለቲከም ሆነ የኢከኖሚ እንዲሁም የዲፕሎማቲክ ጥቅም እስከሰጠበቁ ድረስ ብቻ ነው። ለዚህም ነው አፍሪቃውያን የፈለገው የውጭ ድጋፍ በወታደራዊም ሆነ በፖለቲከ አስታከ

ሊመጣ በጥርጣሬ መቀበል ያለበቸውና በተለይ እርዳታው የወንድማማቾችን መጫረስ የሚያስከትል ከሆነ እርዳታውን «እሸፈረን እንቀበልም» ማለት ያለበቸው። ለሰላም እንጅ ለጦርነት የሚበጅ እርዳታ ለማንም አይበጅምና!

ከለይ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው እንዳንድ የምዕራብ ዓለም የግራ ከንፍ ጋዜጣና መጽሔት አዘጋጆች ሰይቀሩ ዘሬ ኢትዮጵያ በየአግጣጫው ጣዕረ-ሞት በሚተናነቃት ወቅት በሰላም ምሳሰቸው «እንደወደቀ ግንድ» የሚረበረቡበት ምክንያት በእኛ የግል አስተያየት የኢትዮጵያ ወታደራዊ ደርግ የፖለቲከ አመራሩን ሰቪየቶቹን ገለል አድርጎ ከነሱ በለመቀበሉ ይመስለል። እኒህ ጋዜጠኞች «በደከማዋ» ኢትዮጵያ ለይ የሚደረድሩት የነቀፋ ውርጅብኝ የሚሰነዘረው ሪሀብንና አሰፈለጊ ያልሆነው የሰሜን ኢትዮጵያ የወንድማማቾችን መጫረስ በማስታከክ ቢሆንም የጽሑፋቸው ዋነኛ ዓለማ የተደበቀ የፖለቲከ ቂማቸውን ለመወጣት የታቀደ ይመስለናል። «ጅብን ሲወጉ በእህያ ተከልሎ ነው» ይባል የለ! ይህ ግለዊ ግምታችን እንጅ ለጊዜው ተጨባጭ መረጃ የለንም። ፈልገንም አላገኘንም።

እዚህ ለይ ግን አንበብያን ልብ ብለን ማስተዋል ያለብን ጉዳይ የዚህ ሁሉ የቀኝ፣ የመሐል-ሠፋሪና የግራ ወገን ጋዜጣ ሁሉ ዒለማ ያቺው «ደከማዋ»፣ «ኃለቀሩዋ»፣ «ወንጀለኛዋ» -«ሰሸሊሰታዊዋና» ሲያሸቸውም «ከሚዩኒስታዊዋ» የሚሏት ኢትዮጵያ ናት። የወለደች እናት የፈለገውን ቀለም የያዘ ቀሚስ ብታጠልቅ፣ ያሸትን እንጀራ አበት በአበወራ ነት ብትይዝ፣ እናት ነችና ልጆቿ እንደማይጠሏት ሁሉ ከእናት አገራችን ከርሰ ምድር የፈለቀ ምርጫችን ጠልቀን የጠጣንና በእፈሩዋ ለይ የበቀለውን ጥሬ የቃምን ልጆቿ ሁሉ አገራችንን «የራሷ ጉዳይ» ብለን ልንተዋት እንችልም!! የምዕራብ ጋዜጣዎችና ጅምለ ፀረ-ኢትዮጵያ አቂም ያለቸው ኃይሎች ሁሉ ግን ፍለጎታቸው አገራችንን አስከወዲያኛው ከደን እንድንተውና እኛም በየስደት ቦለንበት ሁሉ እንደጠለት የጎሪጥ እየተያየን እንድንተለፍ ነው። ዘሬ ግን ይህንን ደበ ማክሸፍ የእውነተኛ ዘረ-ሐበሻና ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግዴታው ነው። ሌለው ቀርቶ ሰላምታችን በ«ሰላም» ይጀምራል። በመለው ዓለም ለይና ዘሬ ደግሞ በመለው አፍሪቃ የአፍሪቃንም ቀንድ ጠምሮ ሽው በማለት ለይ የሚገኘው ይኸው መልክሙ ቃል «ሰላም» በኢትዮጵያም ውስጥ በእጥጋቢ ሁኔታ እንዲነፍስ ብዙወቻችን እንደምንሸ ጥርጥር የለውም። ታዲያ ኢትዮጵያውያን ብንተዋወቅም በንተዋወቅም ራሳችንን ዝቅ አድርገን «ሰላም»ታ ተለዋውጠን መተላለፉ በሀገራችን እንዲሰፍን ለምንመኘው ሰላም መምጣት አንድ ጠቃሚ እርምጃ ይመስለናል።

ዘሬ በሰደትና በሥራ፣ በጉብኝትና በትምህርት ሳቢያ በምዕራብ አውሮፓና በሰሜን አሜሪከ ትለልቅ ከተሞች እንደጨው ዘር ተበትነን

የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የምዕራብ ዜና ማሠራጫወች (ጋዜጣዎች፣ ሬድዎች፣ ቴሌቪዥኖች ወዘ.ተ.) በደረሱብን እኛነታችንን በሚገዘግዝ ሚዘናዊ ያልሆነ ነቀፋ-ኢትዮጵያ ምክንያት እንገታችንን ደፍተን፣ ሐዘንና ንዴታችንን ውጠን እንድንኖር ለመደረጉ የየእለት ሕይወታችን ቋሚ ምስክር ነውና የሰቀ ተጨባጭ ማስረጃ እንድናቀርብበት የሚጠየቅበት ጉዳይ አይመስለንም። በምዕራቡ ዓለም የዜና ማሠራጫዎች አቀራረብ ኢትዮጵያ «ከሚዩኒስት»፣ «ምስኪን»፣ «ድሃ»፣ «ስማኝ»፣ «በምጽዋት የተሰጠን እህል እንኳ በአግባቡ ለማደረስ የአሰተዳደር ችሎታ የሌላት» እጅግ ኋላ ቀር አገር ናት። የጋዜጦቹ አቀራረብና ቋንቋ ለበለሰና ገራም መስሎ ቢታይም ውጤታቸው በእንድነት ሲደመር ስለኢትዮጵያውያንና ስለመላው ጥቁር ዘር የሚሰጡት ሥዕል እጅግ ለጤነኛ አእምሮ የሚቀፉና አበሻዊ ኩራትን ብቻ ሳይሆን ሰብአዊነትን የሚያዳሽቅ ምዕራባዊ ድምጽ-የለሽ ርእዮተዓለማዊ መሣሪያዎች ናቸው።

ዛሬ ስለኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪካዊነትና ስለሕዝቧም ትክክለኛ ማንነት ለማሰወቅ የሚከጅል ሁሉ ኢትዮጵያን በማናናቅና በማጥላላት ብቻ ካሰተከረ በሰተቀር ዝግጅቱን የሚያሰማበትና ጽሑፉን የሚያቀርብበት መድረክ የለውም። ዛሬ በእንዳንድ የምዕራብ አካዳሚክ ተቋሞች እንኪን የኢትዮጵያን ማንነት እንደልነበረ አድርጎ ማቅረብ የጊዜው አካዳሚክ ፊሊጥ (Fashion) እንዲሆን ለማድረግ የሚጥሩ ገለሰቦችና ቡድኖች ቁጥር ቀላል አይደለም። የገንዘብና የሞራል ድጋፍ የሚለግሷቸውም ምዕራባዊ የፖለቲካ ቡድኖች ግራ ቀኝ ሰይባል በርከታዎች ናቸው። የዚህ ሰይክሎጂካዊ ድሽቀት ውጤቱ አበሻው እርስ በእርሱ እንኪን ለመግናኘት እንዲይችል የግንኙነቱ ማያያዣ ሲሚንቶ የሆነው ኢትዮጵያዊ ኩራቱ በብርቱ ስለተመታ የራሱን ወገን እስከመጥላት ደርሰ «የሐበሻ ዓይን አታሳ ዩኝ» እስከሚባልበት ደረጃ አድርሰታል። ቢያንስ እኛ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢዎች በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ እንዲሁም በሰሜን አሜሪካ ያገኘናቸውን አበሾች ስናናግር የብዘዎቹ አሰተያየት «የአገርን ነገር እንደባር ኔጣ አውልቶ ማኖር ነው» የሚል አሰዛኝና ተስፋ አስቆራጭ ስሜት ነው ያጋጠመን። ይህ ማለት ግን ይህ አሰተያየት ውሎ አድሮ አይለወጥም ወይም የሁሉም አበሻ አሰተያየት ይኸው ብቻ ነው ማለት አይደለም። እዚህ ላይ እኛ ለማሰየት የመንሞክረው የዜና ማሠራጫዎች በምዕራብ ዓለም በተሰደድን እንዳንድ አበሾች ላይ በደረሱት የፐሮፓጋንዳ ዘመቻ እንዲት ድል ሊያደርጉና ሊማርኩን እንደቻሉ ነው። ለምሳሌ ያህል በያለንበት ተሰባስበን እንኪን ኢትዮጵያ ዛሬ የሚያንዣብብባትን የሞት ጥላ ለመግፈፍ ቀርቶ በየምንኖርበት የአውሮፓና የአሜሪካ ከተሞች በማህበር ተደራጅተን እለት በዕለት የሚደርሰብንን የነጭ ዘረኝነት እንደሌሎች ጥቁር ወንሞቻችንና የሦስተኛው ዓለም ሰዎች ሁሉ ለመቋቋም የሚረዳን የጋራ መድረክ መፍጠር አልቻልንም። በህላዊና

ታሪካዊ ኩራታችንን ለመጠበቅ እንኪ እንዳንችል የሰሜት እግረሙቅ ገብቶብን ከመሰብሰብ ይልቅ መበተንን የመረጥን ይመስላል። ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው የከሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ በተነቀፈ ቁጥር እኛነታችን (ኢትዮጵያዊነታችን) ለከስ የቀረበ መስሎን የምንሸማቀቀው ቁጥር ቀለል አይደለም!! በእኛነታችን እስከናፍር ድረስ ለሞራል ውድቀት ያበቁን የምዕራብ ጋዜጣዎች በእኛ አስተያየት ለሕዝብ ፍርድ መቅረብ ያለባቸው ርህራሄ ቢስ ወንጀለኞች ናቸው።

የዚህ ትችታችን ዋነኛ ዓላማ በእኛነታችን ሙሉ እምነት አድሮብን ስመጥር የሆኑ እናት አባቶቻችንና አያቶቻችን ለኢትዮጵያ ብቻ ሰይሆን ለመላው አፍሪቃና ለጥቁር ሕዝብ ሁሉ መኩሪያና መመኪያ የሆኑበትን ታሪክ ከወቅን ለለወቀው ነጭ እንድናከፍልና ከለወቅንም ከሚያውቁና ከመጽሐፍት በመማር የሀገራችንን አኩሪ ባህልና ቅርስ እንድናሰውቅ ለማበረታታት ጭምር ነው። የከሎኔል መንግሥቱን መንግሥት በወንጀለኛነት በመጥቀስ የእኛን ማንነት እንድናፍርበት የሚፈልጉትን ወገኖችና ጋዜጦች ሁሉ እኛም ያንን አገዛዝ ለለመቀበል የምንወዳትን አገራችንን መልቀቃችንን በመጠቆም ጋዜጠኞቹ እንኪን በወሬ በጦር ሜዳም ቢሆን ሄደው ሰይፍ ለመማዘዝ ፍጹም አቅሙና ችሎታው ስለሌቸው የኛን አእምሮና ማንነት የጦር ሜዳቸው እንዲያደረጉ እንደማንፈቅድላቸው መግለጡ ጠቃሚ ይመስለናል። ኢትዮጵያዊነታችንን ግን እንደሠረቀ ሰው ልንሸማቀቅበት የሚገባ ጉዳይ አይደለም። እዚህ እንኪን ያለነው አበሾች እንዳንተባበር እንዳንድ Neo-colonial ደራሲያን በርከታ ከሆኑት መመሰሰሎቻችን ይልቅ ጥቂት ወደሆኑት ልዩነቶቻችን በማትኮር መጽሐፍት ሰይቀር ስለሚያሳትሙ ያንን የትከከለኛ ሊታውንት ሥራ መስሎን እንደለ ያለትችት በመቀበል ጽሑፋቸውን እንደሕግ ተቀብለን መለያየት ጀምረናል። ይህ ሁኔታ አሰዘኝና ለሰሚው ግራ ነው። ሊሆን አይችልም እንጂ የሚሆን ቢሆን ኖሮ የተለያየ ቂንቂ መናገራቸው በእንድነታቸው ጥያቄ ሳይ ያላለያያቸው ስመጥሩ ኢትዮጵያውያንን ለአንድ አፍታ እንኪ ከመቃብራቸው መስከት ብቅ ብለው የኛን የልጆቻቸውንና የልጅ-ልጆቻቸውን «በፈረንጅ» በተፃፉ መጽሐፍትና ጋዜጣዎች አፃፃፍ ሰቢያ ለመጣጣምና ዛሬ አገር የደረሰበትን ችግር በጋራ ለመፍታት አለመሞከር ቢያዩ ምንኛ በኛነታችን በፈሩ ነበር። እዚህ ሳይ ትግርኛ ተናጋሪዎቹን ጀግኖች አብራሃም ደቦጭን፣ ዘርአይ ደረሰንና ጀግናው አሉሳ አባነጋን፣ አርምኛ ተናጋሪ የነበሩትን የም ኒልክ የጦር ሚኒስትርን ፈታውራሪ ሀብተ ጊዎርጊስን (ሀብቴ አበመለ)፣ ጉራጌኛ ተናጋሪውንና የጠለት መብረቅ የነበሩትን ባልቻ አባነብሰንና ሌሎችንም በብዙት መጥቀስ ይቻላል። እኒህ ክቡር ሰዎች ኢትዮጵያን የገነቡት በሰማበለው እማኸኝነት እየተወያዩ ጭምር ሰይቀር ለመሆኑ እንዳንድ አዘውንት ይናገራሉ። እኛስ በፈረንጅ አገር ያለን አበሾች የሀገር ጉዳይ እንኪ ቢቀር በየምንኖርበት አገር

ለግል ጥቅማችንና ለክብራችን፣ ለመብታችን የምንከራበት ነገር እንኪ ማቂቂም ሲያቅተን እንደምን የነዚህ ስመ-ጥሩ ጀግናና ኩሩ ዝርያዎች ነን ብለን እፈችንን ሞልተን መናገር እንችላለን። ዛሬ ይህንን እንዳንገናኝና እንዳንረዳዳ የተጋረደብንን ጊዜያዊ (temporary) ሥነልቡናዊ (psychological) ጽልመት ገሸልጠን በሰደት ያለን የኢትዮጵያ ልጆችና የሐበሻ ዝርያዎች ሁሉ «በባሌ የወጣውን ጀግና፣ በቦሌ የወጣውን ፈሪ» እያልን መከፋፈሉን ትተን እጅ ለእጅ ተያይዘን ቢያንስ በፈርንጅ አገር የሚደርስብን የአውሮፓና የአሜሪካ (አፓርታይድ መሰል) የዘር ጭቆናና የኢኮኖሚ ብዘበዛ ለመቂቂም የምንችልበትና፣ ታሪክ ያለን ሕዝብ መሆናችንን የምናሰውቅበት ሕብረት መፍጠር ይኖርብናል። እቁብ፣ እድር፣ ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ፣ እነዚህና ሌሎች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና፣ የማህበራዊ ተቂሞች ለእበሻ ሕዝብ እንግዳ ነገር አደሉምና በዚህ መልክ እንኪ ግንኙነታችንን መወጠኑና ማጠናከሩ ማለፊያ መነሽ ይመስለናል። እለበዚያ እንኪን ለአገራችን መመኪያ ልንሆን ቀርቶ ለራሳችንም ፈይዳ የማይኖረን በባህር ውስጥ እንደተበተነ ጨው ደብዝችን የማይገኝ ፍጡራን ሆነን እንደምንቀር ሰይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

እስከሁን በቀረብነው ሐተታ የተመለከትነው የምዕራብ ጋዜጦች (ቀኝ፣ ግራ፣ ማህል ሰፈሪን ደምሮ) በግልም ሆነ በቡድን የኮሎኔል መንግሥቱን አመራር በማጥቃት ሰቢያ ምን ያህል በአገራችንና በእኛነታችን ላይ ለረጅም ጊዜ የማይሽር የፕሮፓጋንዳ ነቀርሳ እንደተከለና የእኛንም ሞራል እንደነኩ ነው። እዚህም ላይ ልናስታውሰው የሚገባ ጉዳይ፣ መንግሥት፣ ግለሰብ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ሁሉ የሚያልፉ፣ የሚለወጡ፣ ወይም የሚሞቱ ነገሮች መሆናቸውን ነው። አገር ግን የዚህ ዓይነት እደጋ ሊደርስባት የሚይገባ ስለሆነ በያለንበት ለሀገራችንና ለነፃነታችን መቆም ማለት ስለአገራችን የሚፃፉትን ጋዜጦችና መጽሔቶች እንብበ ከትከክለኛው ማንነታችን ጋር ማነፃፀርና የሚነቀፈውን መንቀፍ ጽሑፍንም መሰብሰብ ጭምር ይመስለናል። ስለሆነም እኛ በነሲብ (randomly) የሰበሰብናቸውን የጋዜጣ ጽሑፎች ኢትዮጵያን በተመለከተ አቀራረባቸው ይዘት በመመራት ብቻ እንደሚከተለው በሦስት ዘርፍ መድበናቸዋል።

ሀ) ቀኝ ክንፍ (ወግ አጥባቂ) ጋዜጣዎች፣
ለ) ለሥላሴ (ማህል ሠፈሪ ወይም ሊብራል) ጋዜጣዎች፣
ሐ) ግራ ክንፍ (ሸሽሊስታዊ በህርይ ያለቸው) ጋዜጣዎች፣

በነዚህ ሦስት እርእስት ሥር የመደብናቸው ኢትዮጵያ ነክ ጽሑፎች ረዘብን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ጉዳዮች የሚነኩ 120 እርእስት በ፲፫ የምዕራብ ጋዜጦች የወጡ ናቸው። ለዚህ ሐተታ የመረጥናቸው ግን 17 እርእስት ሲሆኑ እነሱም ረዘብ ጠቀስና ለረዘብና ለድርቅ ጉዳይ ቀረብ የሚል

እስተያየት ያለቸው ናቸው። በዚህ ትንታኔያችን በአብዛኛው የምንመረምረው ጽሑፎቹን ብቻ ሲሆን እልፎ እልፎም ደራሲዎችንም ጭምር ለማስተዋል እንሞክራለን። የነዚህ የመረጥናቸው ጽሑፎች አርእስት ስሜት (ጣእም) በትርጉም ሳቢያ እንዳይለወጥ ስለሰጋን በተገፋቡት ቋንቋ እንዲቀመጡ መረጥን (7)።

ሀ) ቀኝ ክንፍ (ወግ-አጥባቂ) ጋዜጣዎችና ኢትዮጵያ-ነክ ድርሰቶቻቸው።

የድርሰቶቹን አርእስት፤ እንደሚከተለው ከደረደርን በኋላ ወደ ትንታኔው እንገባለን

፩ «Draught Spreads Death Across Africa» The New York Times, Nov. 4, 1984, p.3.

፪ «Man, Not Nature, Blamed for Many Disasters» The New York Times, Nov, 18, 1984.

፫ "Relief Official Accuses Ethiopia of 'Biting the Hand' that Feeds It" The New York Times, Dec 13, 1984, p. A1 & 13

፬ «Ancient Holy City Starves»The New York Times Dec. 27, 1984 p. A8.

፭ «Human Stupidity, Mismanagement Behind Tragedy in Ethiopia» The Ottawa Citizen January 8, 1984

፮ «Americans Give $40 Million in Two Months To Aid Ethiopia» The New York Times Jan. 1, 1985, A5.

፯ «Playing Games With Starvation» The Washington Post June 16, 1985, P.15.

፰ «Aid Floods Ethiopia, But It Isn't Feeding Its Hungry,» The Gazette, July 6 1985, P.B6.

፱ «Ethiopia Faces Disaster Again, Relief Officials Say» The Globe & Mail, Nov. 13, 1987, P.A13.

ከላይ ከተዘረዘሩት አርእስት ውስጥ በቁጥር ፩ አቅጣጫ የሠፈረውን ጽሑፍ ያቀረቡት በሮም ከተማ የተመደቡ የኒውዮርክ ታይምስ ቃል አቀባይ የሆኑ ሄንሪ ካም (Henry Kamm) የተባሉ ግለሰብ ናቸው። ይህ ጽሑፋቸው የኢትዮጵያ ወቅታዊ አከሎች (ረሀበና ድርቅ) እንደወረርሽኝ በሽታ ወደሌሎች የአፍሪቃ አገሮች በመዛመት ላይ መሆናቸውን ይጠቁማል። የዚህ ጽሑፍ ስውር ዓላማው ግን ኢትዮጵያን የችግር ተለላፊ በሽታ አዛማች አገር ምስል (image) መስጠት መሆኑን ከይዘቱ እንገነዘባለን። ደራሲው ሶማሊያን (የዘሬ የአሜሪካ የፖለቲካ እጋር ነችና) ድርቅና ችግር የማታውቅ አገር ይመስል የሶማልያን ችግር የሚያጠናክረው «ከኢትዮጵያ የተሰደዱ ኢትዮጵያውያንን መቀለቡ ነው» ይላሉ። ጋዜጠኛው በሶማሊያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ

ከሚሸንና ልዩ ልዩ የምዕራብ ርጥባን ሰዉና የሃይማኖት ድርጅቶች እርዳታ መሰጠታቸውንና እንዲውም ሶማሊያ አልፎ አልፎ «በሰደተኞች ሰም ትነግዳለች» ተብላ መከሰሷንም ይሸሽጋሉ። ደራሲው ቁልጭ ያለ ዓለማቸው ኢትዮጵያን የችግር ሁሉ አመንጪ እድርጎ ለማቅረብ ነውና የሰማሌ የድርቅ ችግር የተነሳው በአፍሪካ ከደረሰው የዝናብ እጦት መሆኑ እየታወቀ ከኢትዮጵያ የተሰደዱትን ግለሰቦች ለሰማሊያ የድርቅ ችግር ከዋነኛ ምክንያቶች እኩል ተጠያቂ ያደርጋሉ። የዚህ ክርክር ግልባጭ እነጋገር እስ «ኢትዮጵያ ሰደተኛ አመንጪ እገር በትሆን ኖሮ የሰማሊያ ችግር መሠረታዊ መንሥኤው በአፍሪካ ከተሠራዉ ድርቅ መሆኑን ቁልጭ አድርገው አያሳዩንም። ነገሩ ጠፍቶአቸው ሳይሆን የጽሑፉ ዓላማ የኢትዮጵያን ውድቀት ማጉላት ስለነበር ነው። እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ግን አብዘኛውን ጊዜ ለምዕራብ ጋዜጠኞች «የአፍሪቃ ውድቀት» ሁሉ ምርጥ ምሳሌአቸው ኢትዮጵያ ነችና ሰለአፍሪካ ጉዳይ በወሩ ቁጥር ነገሩ በይመለከታትም ጽሑፋቸውን ለምጠው የኢትዮጵያን ሰምና «ውርደትዋንም» በመዘርዘር የሀገሪቱ ስም በተጠቀሰ ቁጥር ለአደማጭ ወይም ለአንባቢ ረሀብ፣ እልቂት፣ ውድቀት፣ መከራ፣ (by association) ትዝ እንዲል የሚያከሂዱት ሰይከሎጂካዊ ጦርነት (warfare) አንዱ ምሳሌ ይህ ጽሑፍ መሆኑን ነው።

በቁር ፰ (8) እግጣጫ የሠፈረውና በዊልያም ሽውከሮስ (William Shawcross) የተፃፈው ድረሰት በኢትዮጵያ ምስለ-ምድር (map)ና በአንድ በጣም በከሰና እፊቱ ላይ ስቃይና ተስፋ መቁረጥ በሚነበብበት ህፃን ምስል የተደገፈ ነው። የጽሑፍ መነሻ ምክንያት ምግብ ለረሀብተኞች በተፈለገው ጥድፊያ አለመድረሱ ይምስል እንጂ ስውሩ እምብርት ዓለማ ግለሰቡ በኢትዮጵያ ሰሸሊስት ነትና በወታደራዊው አመራር ሳይ ያሳቸውን ርእዮተዓለማዊ (ፀሐፊው ወግ እጥቢቂ ናቸውና) ቂም መወጣት ይመስላል። ጽሑፋቸው ግን በግል ጥላቻ ብቻ የተሞላ እንዳይሆንና በሕዝብም (እንባቢ) ዘንድ ድርሰቱ «ሚዘናዊና እውነተኛ» ሆኖ እንዲታይ እድር ጉ ማቅረብ «የሙያ ግዴታቸው» ነው። ስለዚህም ዘራ በሥልጣን ላይ ያለው «ማርክሰዊ አመራር» በሞት አፋፍ ላይ ለሚገኙ ረሀብተኛ ኢትዮጵያውያን ደንታ የለውም የሚለውን (ለምዕራብ ጆሮ የሚጥም) መልእክት ለማስተላለፍ እንዲያመቻቸው መቀመጫቸው ከኢትዮጵያ የሆነ የምዕራብ አገር ዲፕሎማቶችንና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን እንደ ዜና ምንጫቸው በመጥቀስ እንዲህ ሲሉ ይጽፋሉ። «በርክታ የኢትዮጵያ ከባድ የጭነት መኪናዎች በንግድ ዘርፍ ይሠማራሉ ወይም ለመንግሥቱ የጦር ዘመቻ ተመድበዋል። ይበልጡ ደግሞ አወዛጋቢ ለሆነው አዲስ የሠፈራ ፕሮግራም ዘመቻ ተወሰደአል።» ይህ ዓይነቱ ዜና በምዕራቡ ዓለም ዘራ ደህና ገበያ አለው። የሠፈራውን ፕሮግራም ግን ከለውጡ በፊት የነደፉት የምዕራብ መንግሥታት እርዳታ ለጋሽ «የልማት» ድርጅቶች ናቸው። ይኸውም ከለውጡ በፊት

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የዓለም ባንክ ስለኢትዮጵያ ሰሚናዊ የድርቅ ችግር ባጠኑት ጥናት ሁሉ የአካባቢው ችግር ዓይነተኛና የዘለቄታ መፍትሔ ከሕዝቡ ከራሱን ሕዝብ በብዘት ወደአልሠረረባቸው የኢትዮጵያ ግዘቶች ማዘወር ነው ብለው ለመደምደማቸው በርከታ ተጨባጭ መረጃዎች አሉ። ምዕራባውያን ትላንት (ከለውጥ በፊት) መፍትሔ ብለው ያቀረቡትን የሠፈራ እቅድ ዘሬ የወቅቱ መንግሥት «ኩሚዩኒስት በመሆኑ» ብቻ ይቃወሙታልና የዚህ ዓይነቱ ጋዜጠኛ ሥራና ሥነጽሑፍ ይጥማቸዋል። ምዕራባውያን በሥውርና በግልጽ ከሚያከሂዱት የዲፕሎማቲክና ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ በተጨማሪ የዊልያም ሸውከሮስ ዓይነቱ የጋዜጠኛ ቃለት ጦርነት አንጀታቸውን ያርስላቸዋል። እንንዲህ ዓይነቱን ጋዜጠኛ የዚህ ዓይነቱ ወሬ ጥም ያለቸው አንባቢዎች «ዊልያም ጉሽ፤ እበጃህ! ያሰድግህ፤ ጣመን ድገመን» ብለው ከንጂት መመሪቃቸው አይቀርም።

በቁጥር አራት አንባር በክሊፎርድ ሜይ (clifford D. May) የተፃፈው ዘገባ ደግሞ ከሰባቱ የዓለም አስደናቂ ነገሮች አንደ አንዱ ሆነው ሊቆጠሩ ይገባል ተብለው በብዙ ሊቃውንት የሚነገርለቸውንና የምንከራባቸውን ከቂጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩ ቤተመቅደሶች ያሉበትን የላሊበላን ምድር የረሀብተኞችና የድኩማን መናሽሪያ መሆኗን የሚያበስር ነው። ደራሲው ጽሑፉን ያቀረቡት ከላሊበላ ከተማ «ሆኜ ነው» ቢሉንም ከዚያ ሁሉ የረሀብ፤ የጭንቀት፤ የደዌ፤ የመከራና የሥቃይ ሐተታቸው ውስጥ ስለዚህ አስደናቂ የኢትዮጵያ የሥልጣኔ ቅርሶች (ማለት የቅዱስ ላሊ.በላ አድባራት) አንድ ዓረፍተ ነገር እንኪ አልጠመሩም። ጉድ ነው ሚዘናዊነት፤ የምዕራቡ ጋዜጠኝነት! ትርፉ ትዝብት ነው እንጂ እኒህ ጋዜጠኛ ስለነዚህ መቅደሶች የፈም አልፃፈም ታሪካዊ ደረጃቸው አይቀንስም፤ አይጨምርም። አቶ ክሊፎርድ ሜይ የምዕራቡ ጀሮ አቶብቁቦ የሚጠብቀው ስለኢትዮጵያ ውድቀት ብቻ ለመሰማት እንጅ እንደህ ያለውን እጹብ ድንቅ ታሪካዊ ሥራ የሚያደንቀውን አለመሆኑን አበከረው ያውቃሉ። እንደውም የወቅቱ የምዕራብ ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ የሚያደርጉት እሽቅድምድም ይበልጥ አሰቃቂና የሚዘገንን የረሀብ ቀበሌ (pocket) በመፈለግ ለምዕራብ አድማጮቻቸው «ሰሸሊዝም የሚፈጽመው ጭካኔ ይህን ይመስላልና ፊታችሁን ወደዚያ እንዳታዘሩ» የሚለውን መሠሪ (subtle) መልእክት ለማስተላለፍ ይመስል ነበር። ስለሆነም የኢትዮጵያ ታላቅ የሥልጣኔ ቅርስ ሥፍራም (ላሊበላ) ቀና (positive) ነገር ቢፃፍበት የዚህችን «አስቀያሚ ከሚዩኒስት» አገር ምሥል (image) በምዕራቡ አንባቢ ዘንድ ከመቀየር አልፎ ሥፍራውን እንጎብኝ የሚለው ቱሪስት ስለሚበረክት ጥንቃቄ ያደርጋሉ። እንግዲህ እዚህ ላይ የጋዜጠኛው ተልእኮ ጥንድ መሆኑን ነው። ስለላሊበላ አስቀያሚ ዜና በማውጣታቸው «ሰሸሊስት ኢትዮጵያ» ምን ያህል አሰቃቂ አገር እንደሆነች በሚደረገው የፕሮፖጋንዳ ጦርነት የራሳቸውን የቃለት ጥቃት ለመፈፀም

ያስችላቸውል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከቱሪስቶች ጉብኝት ልታገኝ የምትችል የነበረውን ገበያ በዚህ ጽሑፋቸው አማከኝነት ይደፍኑባታል። «በእንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል» ይሉ የለ ምዕራባውያን በተረታቸው። ግን አንድ ብልህ አንባቢ የዚህ ዓይነቱ (የጋዜጠኛ ከሊፎርድን) ጽሑፍ ባነበበ ጊዜ ሊጠይቀው የሚገባ ጉዳይ አለ። ይኸውም ጋዜጠኛው ስለቅዱስ ላሊበላ ህንፃዎች ምንም ያልፃፈት የጹሑፍ ዓላማ የላሊበላን ከተማ የረሀብ ችግር ለማጉላት ብቻ ስለሆነ ነው እንዳይባል ጋዜጠኛው ከተማዋ በፀረ-መንግሥት ተዋጊ ኃይሎች ተይዛ እንደነበር በዚሁ ጽሑፍ ሐተታቸውን አቅርበዋል። ስለዚህ ጋዜጠኞቹ በኢትዮጵያ ላይ በመድረሱ የተደሰቱበትን ጉዳይ ሁሉ ይጽፉበታል።

በኢትዮጵያ ሊያዩ ያልፈለጉትን ደግሞ ጠርሰ እንደልነበር ሁሉ (እንደሳሊበላ ሕንፃ ጉልህ ቢሆንም) ያልፉታል። ከተማ በፀረ-መንግሥት ወያኔዎች ተይዛ እንደነበር መግለጡ ግን ለጋዜጠኞቹ ሥውር ተልእኮ አንድ ተጨማሪ ነጥብ ስለሆነ በረሀቡ ሀተታ ውስጥ በግድ ቦታ ፈልገው ይደሉታል። የጋዜጠኛው ገሃድ ተልእኮ የረሀብ ዜና መሰብሰብ ቢሆንም የኢትዮጵያን «አሳፋሪና ፀያፍ ጉደዮች» እጉልቶ ማሳየት ደግሞ ደራሲው የተሳኩበት ሥውርና ዓቢይ ዓላማ መሆኑን የምዕራብ ብልህ አንባቢ በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል። በገጽ 29 እና 30 ላይ የሠፈሩት ሌሎች እርእሰት ማለት ቁጥር ፪፣ ፫፣ ፭፣ ፮፣ ፯፣ እና ፱ ይዘት ሥፍራ ለመቆጠብ ሰንል በንተነትናቸውም ርእሰቹ የጽሑፉን ማእከላዊ ዓላማ እንደሚጠቅሙ አንባቢያንን በማሰገንዘብ እናልፋቸዋለን።

ለ) ለሥላሴ (ማህል ሠፈሪ ወይም ሊበራል) ጋዜጣዎች

እነዚህ ዓይነት ግዜጣዎች በጠቃላይ አቂማቸው የምዕራቡን ሁኔታ በሚተነትኑበት ጊዜ «ሊበራል» አቂም ይዘው ቢሆንም የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚመለከት ከወግ-አጥባቂዎቹ ጋዜጣችዎች እምብዛም የተለዩ አይደሉም። ለሥላሴ («ሊበራል») ጋዜጣዎች አንድ ጊዜ ከግራ ክንፍ ሌላ ጊዜ ከቀኝ ክንፍ በመዋዠቅ የሚጽፉ ሲሆን በአቀራረባቸው ደግሞ ማንኛውንም አንባቢ በማያስቀይም መልክ ይመስላል። «ለስላሴ» ብለን የሰየምናቸውም ለዚሁ ብለን ነው ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደሞከርነው ሊበራል ፀሐፊዎች ኢትዮጵያን በሚመለከት (በነሱ አስተያየት ኢትዮጵያ አፍሪካዊ ሶሺየት ሆናለችና) ሲጽፉ በንድ በኩል ፀረ-ሶሺየት ኮሚዩኒስት ፕሮፖጋንዳቸውን ለመንዛትና የተደበቀ ፀረ-ጥቁር ሕዝብና ፀረ-አፍሪካ አቂማቸውን ያንፀባረቀበት ሁኔታ ታይቷል። በዚህ ረገድ በእኛ አመለካከት እንኪን ሊበራል ነጮች ቀርቶ «ኩዩዩኒስቶች ነን ለዓለም ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ አንድነት ነው የቆምነው» የሚሉት ሶሺየቶች እንኪ አዘውትረው ከዘረኝነት

ነፃ አለመሆኖውን የሚመሰክሩ አያሌ ድርጊቶች መጥቀስ ይቻላል። (8) የምዕራቡን ዓለም ሁኔታ እግሩ ምዕራብን የረገጠ የጥቁር ዘርና ኢትዮጵያዊ ሁሉ ስለሚያውቀው በዚህ ላይ ምሳሌ አንጠቅስም። በዚህ «ለ» ክፍል ለምናከናውነው ትንታኔ የተጠቀምንባቸው የጋዜጣ ጽሑፎች በሙሉ የተገኙት ከካናዳ ነው። ይህም የሆነው በጋጣሚ ሳይሆን ሆን ብለን ነው። ለዚህ የመረጥነው ጋዜጣ በተለይ ቶሮንቶ ተብሳ በምትታወቀው የካናዳ የኢከኖሚና የበህል ዋነኛ መናኸሪያ ከተማ የሚታተመው The Toronto Starን ነው። የቶሮንቶ ስታር ሌሎች በእግሪካ ከሚታተሙ ጋዜጣዎች ለየት ብሎ ያገኘንበት ምክንያት በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ፒር ኤልየት ትሩዶ ስር ለ16 ዓመታት ያህል በሥልጣን የቆየውንና አሁን ግን የዋና ተቃዋሚነት የፖለቲካ መድረክ ይዘ የሚገኘውን የሊበራል ፓርቲ ስለሚደግፍ ነው። ከዚህም በላይ ካናዳ በዚህ የፖለቲካ ፖርቲ የሥልጣን ዘመን «ዘረኝነት በኛ ዘንድ ፈጽሞ የለም፤ እኛ የብዙ ብሔሮችና በህሎች (multi-ethnic & multicultural) አገር ነን» ብሳ ድምጿን ጎሳ አድርጋ የምትናገር አገር ስለነበረች የዚህን ፖርቲ አቂም የሚደግፍ ጋዜጣ ለኢትዮጵያ ከሌሎች የአሜሪካ ጋዜጦች የተሸለ የዜና አቀራረብ (coverage) ይሰጣል በማለት ነበር። ይሁንና ግምታችንና የጥናታችን ውጤት የሰማይና የመሬት ያህል መራራቃቸውን እንባቢዎች ሊገነዘቡት ይችላሉ። በቶሮንቶ ስታር ከወጡት በርካታ ርእሶች ውስጥ የሚከተሉትን ብቻ ለናሙና ያህል ወስደናል።

፩ «Marxist Atrocities Reported in Ethiopia « Relief Camps» The Toronto Star August 1, 1986, P.A13.

፪ «African Nations Cry poor But Lavish Money on Armies» The Toronto Star, March 24, 1988, p.A26.

፫ «5 Million Ethiopians Face Starvation,» The Toronto Star, Nov. 22, 1987, P.H2

፬) «Fight Famine, Not People Geldof Urges Governments,» The Toronto Star, Dec. 2, 1987.

፭) የካርቱን ሥዕል በገጽ 90ላይ የተመለከተ፤ The Toronto Star, Dec. 22, 1987.

ሀ

በመጀመሪያ በቁጥር አምስት እንግር የተጠቀሰውን የካርቱን ሥዕል ልብ ብለን እናስተውል። እንደምስሉ አቀራረብ ነዋሪነቱ በሰሜን የምድር ዋልታ (pole) የሆነው የገና አበት (Santa Claus) በምቹ ወንበሩ ላይ ተጉዘጉዞ ተቀምጦ ዙሪያው ለህፃናት የሚናኛቸው ልዩ ልዩ አሻንጉሊቶችና መጫዎቻዎች ተከቦ

Tuesday, December 22, 1987

EDITORIAL



ይታያል። በጠኔ ምክንያት እጆቹና እግሮቹ የሰለሉበትና አለእድሜውም ፀጉሩ የተመለጠበት ህፃን የገናው አባት ጭን ላይ ተቀምጦ አፈን ከፍቶ እንደወሰፈ በሸለ ጣቱ ለገናው አባት ጉርርውን ያመለክተዋል። አጽሙ ብቻ ከቀረው ህፃን መቀመጫ በኩል የሚታየው እራፊ ጨርቅ ህፃኑ የሚወክለው ኢትዮጵያን ለመሆኑ የሚያሳየን በእንግሊዝኛ Ethiopia ተብሎ ተጽፎበታል። የዚህ ምስል ጭኔ የተሞላበት አቀራረብ መሆኑን መረዳት የሚቻለው የምዕራብ ህፃናት ሁሉ በገና ወቅት የሚጠይቁት መጫወቻ እንጂ እህል እንዳይደለ ከቃላት የበለጠ ይነግረንና እጥንቱ የገጠጠው ህፃን (ኢትዮጵያ) ግን ከህፃናት መጫወቻ በሰተቀር እህል በጠገቡ የሌለውን «ሰንታ» ወደጉርርው የሚልከው ምገብ ሲጠይቀው መታየቱ ነው።

ይህ እንኪን በኢትዮጵያ ምድር ላለው አበሻ እኛም እዚህ ለለነው (ችግሩን ለልቀመስነው) የአገሪቱ ተወላጆች መጥፎ ምስል (image) በያለንበት ሕብረተሰብ አእምሮ እንደሚቀርጽ መረዳት አያዳግትም። ስለዚህም ነው ለእንዳንድ ፈረንጆች «ኢትዮጵያዊ ነኝ» ብለን ስንነግራቸው፤ «ታዲያ ወደዚያ ትመለሰለህ/ሽ?» ብለው በድንጋጤ የሚጠይቁን። እንደውም እንዳንደቹ ኢትዮጵያዊነት ማለት ረሀብተኝነት የሚመስላቸው «አ እንተ/እንቺ እድለኛ ነህ/ነሽ በዚህ ጊዜ እዚህ መኖርህ/ሽ» የሚሉን። የዚህ ዓይነት ከርቱኖች በምዕራብ ዓለም ኢትዮጵያን አስመልክቶ ወጥተዋል። ይህ እጅግ አሰቃቂ ሥዕል በልዩ ልዩ የምዕራብ ጋዜጣዎች ከሚወጡ መሰል የምዕራቡ የኃይልና የሀብት እብሪት መግለጫዎች እንደእንዱ በምሳሌነት ተወሰደ እንጂ ከሁሉም የከፋው ነው ማለት አደለም። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ግን ደጉና ሀብታሙ የገና አባት የምዕራቡን ዓለም ለጋሥነት የሚያሳይ (image) መሆኑን ነው። የዚህ ዓይነቱ ምስል ከምዕራብ (መጽዋቹ ዓለም) ተወላጆችና ከእኛ ከሐበሾች (የተመጽዋች ዓለም) ተወላጆች አእምሮ አንድያውን ከዚህ ዓለም በሞት ከልተለየን በሰተቀር እንደምን ሊፋቅ ይችላል?! የዚህ ዓይነቱስ ምስል (image) ዛሬ በሰደት ከየምንኖርበት የምዕራቡ ዓለም ሕብረተሰብ ፊት (በጥቁርነታችን ከሌለው ጥቁር ሕዝብ ጋር ከሚደርስብን ዘረኝነት በተጨማሪ) በምን መልክ እንድንታይ ያደርገናል?! «ምስኪን ረሀብተኛ ስደተኞች!» ይህ ሳይኩሎጂክዊ ውጊያ ቀስሉ ለአእምሮአችን ሥቃይ ለሆድ እቃችን ነቀርሳ ሆኖብን የሚያሰቃየንን በባእድ ምድር የምንኖር አገር ወዳድ አበሾችን ቢታችን ይቁጠረን።

ይህ በምዕራቡ ዓለም ረሀብተኛ የሌለ የሚያስመስለው የገና አባት ምስልስ

የምዕራቡን ዓለም የማጂት ምስጢር ለመሸፈን የቀረበ አይደለም ወይ የሚለውን ብልህ ጥያቄ እልፎ እልፎ እንባቢዎች ያነሳሉ። በእንግሩስ እንደ ኢትዮጵያ በእሰቃቂ ሁኔታ ለይ አይገኙ እንጂ በምዕራቡ ዓለም በተለይ በአሜሪካ አገር ረሀብተኞች የሉም ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል እንዴ? አይቻልም። ይህንንስ ዓይን ያወጣ ነጭ ውሸት እኛ በአሜሪካ ትለልቅ ከተሞች የምንገኝ ኢትዮጵያውያን አንቀበለውም። በአሜሪካ በችግርና በረሀብ አለንጋ ከሚገረፉት ይበልጡኑ ከ400 ዓመታት በፊት ከአፍሪቃ በባርነት ተሽጠው የመጡ ጥቁር ወገኖቻችን ዝርያዎች አይደሉምን?! የነዚህ ወገኖች አሜሪካዊነት እጅግም የፈየደላቸው ነገር እንደሌለ እያሉ አዋቂዎች ይናገራሉ። (9) ከጥቂት ወራት በፊት ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት በዲሞክራቲክ የፖለቲካ ክልል በመወዳደር ላይ የሚገኙት ታዋቂው ጥቁር አሜሪካዊ አቶ ጄሲ ጃክሰን ዘራ ብዙ የአሜሪካ ጥቁሮች የሚገኙበትን ሁኔታ «አሜሪካዊ እፖርታይድ» የሚሉት ለዚህ አይደል!

ከላይ በተራ ቁጥር ፮ የተጠቀሰው ርእስ የሚያመለክተው ምን ያህል የአፍሪካ ሕዝቦች እየተራቡ የአፍሪካ መንግሥታት የተራቀቀ የጦር መሣሪያ እንደሚያከማቹና ምን ያህል በርካታ ወታደሮች እንደሚያሰለጥኑ ነው። ነገሩ እውነትነት ቢኖረውም እንድ የተገደፈ ሀቅ አለ። ይኸውም በነዚሁ የአፍሪቃ አገሮች በጦርና በኤኮኖሚ እንዲሁም በፖለቲካና በንግድ አማካሪነት የሚመደቡት የምሥራቁም ሆነ የምዕራቡ አገር ወኪሎች የየሀገራቸውን የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ ውጤቶች ለነዚሁ ምስኪን የአፍሪቃ አገሮች ለመሸጥ ሲሉ በረጅም ጊዜ ብድር ሰምና በወታደራዊ እርዳታ እነዚህኑ «የረቀቁ» የሚሏቸውን ነገር ግን «ኋላ ቀር» መሣሪያዎቻቸውን እንደሚያራግፉባቸው ነው። ወደ ጽሑፉ ቁምነገር እንመለስና የጽሁፉን መጠን እንመልከት። ለዚህ ርእስ የእንድ ጋዜጣ ገጽ ከእምሰቱ እራቱ እጅ የተለቀቀለት ሲሆን በሁለት ትለልቅ ፎቶግራፎች መረጃነት (illustration) የተደገፈ ነው። ደራሲው አቶ ጆን ኤድሊን (John Edlin) በዚምባቡዌ (ሐራሬ) የተመደቡ ሪፖርተር ናቸው። የጽሑፋቸውን ታማኝነት ለማጠንከር ጣልቃ ከስገቧቸው ምስሎች (pictures) እንዱ በሰሺየት ሕብረት የተሠሩ ሮኬት አመንጣቂና ሚሰኢል ተሸካሚ ከባድ የጦር ከሚወኖችን የሚያሰይ ይገኝበታል። በሥዕሉ ስር የቀረበው ማብራሪያ እንዲህ ይላል። «ድህነት ያደሸቃቸው የአፍሪቃ ሀገሮች ይህንን የኢትዮጵያ ሮኬት ማምጠቂያ ከባድ መኪና የመሰለ አላቸው። ግን ረሀብተኞቻቸውን ለመመገብ ገንዘብ ይለምናሉ። ኢትዮጵያ ከዓመታዊ በጀቷ 9.3% (ጋዜጠኛው

የእሀዝ ስህተት የፈፀሙ ይመስለናል) ለመከላከያ ስትመድብ ከሰሺየት ሕብረት ሁለት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ የጦር እርዳታ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ተቀብላለች።» እዚህ ላይ የጋዜጠኛው ጠቢ የጦር መሣሪያው ለምን ከሰሺየት ሆነ ይመስላል እንጂ ለምን የምዕራብ አውሮፖ አገሮች የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪዎችስ ለብዙ የአፍሪካ አገሮች እንደሚሸጡ ጠቁመው ይህንን ድርጊት በጠቃላይ እያወገዙም ነበር?! ሌላው ሥዕል ደግሞ በንቃት ተሰልፈው በሙሉ ትጥቃቸው በረድፍ የሚያልፉ አፍሪቃዊ ወታደሮች ያሳያል። ከሥዕሉ ሥር የተፃፈው ማብራሪያም እንዲህ ይላል። «በአፍሪቃ ብዙሐኑ ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጉታቸውን የሚያረኩበትን ሁኔታ እየተነፈጋቸው ወታደሮቹ ግን በሚገባ ደሞዝ ከመከፈላቸውም በላይ ሽክ ብለው የሚለብሱና በሚገባ የሚመገቡ ናቸው። ከዚህ በላይ የሚታዩት ወታደሮች ኢትዮጵያውያን ናቸው።» ለዚህ አቀራረብ ለምን ኢትዮጵያ ተመረጠች? እኛ እንደምንገምተው ለዚህኛው ምሥልና አገላለጥ መመረጥ የሚገባው የደቡብ አፍሪካ ወታደራዊ ተቂም ነበር። ደቡብ አፍሪቃ የኒውኩሊየር መሣሪያ ሰይቀር በምሥጢር እስት ይባላል። በጥቁር አገር ላይ ወታደሮቹ ነጮች ናቸው። ጥቁር ሕዝብ በቴክኖሎጂ በደበረችና በበለፀገች ደቡብ አፍሪቃ ለዓይን በሚያሰቅቅ ሁኔታ ይኖራል። እኒህ ጋዜጠኛ እውነት ሚዘናዊ ከሆኑ ለምን ይህንንም ሁኔታ አልጋለጡም ነበር?! ደራሲው ግን ከደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ጋር የዘርም ሆነ የርእዮተዓለም ፅብ ስለሌላቸው ሁለቱንም ሥዕሎች ከሚጠሏትና ከሚያጥላሏት ከኢትዮጵያ ብቻ እንዲሆን ወስነው መሳው አፍሪቃን እንደለመዱት እግራቸውን አንስተው ተሰድበዋል።

ይህ ከላይ የተመለከትነው አቀራረብ የሚያሰየን ኢትዮጵያ በጠቃላይ ለመላው ዓለም ጥቁር ሕዝብና በተለይም ለአፍሪካ ሕዝቦች መልክም ምሳሌ የምትሆንበትን ጉዳይ፣ ማለት የቀድሞ ሥልጣኔዎቿን ጋርዶ አፍሪቃውያንን ቀርቶ ኢትዮጵያውያን የሚያፍሩበት አስቀያሚና የባህል-የለሽች (Savages) አገር አድርጎ ለማቅረብ የተቀናበረ የምዕራብ ጋዜጦች የማደናቆሪያና ስም የማጥፊያ ዘመቻ ነው። የጆን ኤድሊን ጽሑፍ ይዘት ግን ከኢትዮጵያ ጠኔ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ሲሆን በጠቅላላ ጥቁሩ የአፍሪቃ ክፍል ምንኛ በወታደራዊ ወጪ የተወጠረ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ቀድሞው ኑስ ቢሆን መች ይሽ ተከደና የጋዜጠኛው ሥራ መሆን የነበረበት የዚህን ምንጭ ማሰየት ነው።

ወደ ጋዜጠኛ ጆን ኤድሊን ዝርዝር አቀራረብ ስንገባ በኢትዮጵያ፣ በሞዛምቢክ፣ በአንጎላ ያሉት ፀረ-መንግሥት ኃይሎችና መንግሥታቱ

የሚያደረጉትን የጦር ግብ ግብ ነካክቶ ሦስቱም አገሮች በእፍሪቃ ጦርነት የፈለጓቸው፣ በዓለም የመጨረሻ መናጢ ድሆችና በማርክሲስት–ሌኒኒስት መንግሥታት የሚገዙ መሆናቸው ይገለጥልናል። በኛ አስተያየት ይህ ዓይነቱ የዜና አቀራረብ ሐሰተኛ ከመሆኑም በላይ በርእዮተ–ዓለማዊ (ideological) ጠለትነት የተመሠረተ ነው። ምክንያቱም አንጎላና ሞዘምቢክ በተፈጥሮ የተዋቡና ለም አገሮች ናቸው። እንደኢትዮጵያ እንኪ ድርቅ ደጋግሞ ነክቶአቸው አያውቅም። የሁለቱም ብርቱ ችግሮች ሶሻሊስታዊ አመራራቸውን የሚቃወምና በዘር መድልዎ የሚያምነው የደቡብ አፍሪቃ (አፖርታይድ) አገዛዝ ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ ፀረ–መንግሥት ኃይሎች ናቸው። በደረሱባቸው ወረራና ጥቃት ሰቢያ ሰይወዴ በግድ ከብሔራዊ ገቢያቸው ይበልጡ ለመከላከያ ይመድባሉ። ከሁሉም በላይ አንጎላ የተፈጥሮ ነዳጅ ዘይት ክምችት ያላት ነዳጅ ዘይት አውጭና ላኪ አገር እንደመሆኗ ወደፊት ከእንዳንድ የአውሮፖ አገሮች የተሸለ ለመበልፀግ ችሎታ (potential) ያላት አገር ናት። አገራችን ኢትዮጵያም ብትሆን የዘመናት አስተዳደር ጉድለትና ቀውስ፣ የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት (natural disasters) የገጠማት አገር ብትሆንም በውጭና በሀገር ቤት ያለነው ተቆርቋሪ ልጆቿ ታጥቀን ለልማት ብንነሣ ምድሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ሀብትና ከሁሉም በላይ ችግር የማይበግረው ሕዝቧን በማቀናጀት የማደግና የመበልፀግ ዕድሏ ሰፊ ነው።

የጋዜጠኛ ጆን ኤድሊን ጽሑፍ ዓይነተኛ ዓለማ ምን እንደሆነ በቅጡ ለመረዳት የጽሑፋቸውን ጥቂት የመጨረሻ ፀረፍተ ነገሮች ማጤን ይበቃል። ጽሑፉ በጠቃላይ ይዘቱ የአፍሪካን ድክመትና ውድቀት ለማወጅ የታቀደ ሆኖ የሚከተሉት የማጠቃለያ ሐሰቦች ሠፍረውበታል። እንደሰቸው ድምዳሜ ኢትዮጵያ፣ ሞዘምቢክና፣ አንጎላ በአፍሪቃ እናት ላይ የሚያናጥረውን የ170 ቢሊዮን ዶላር የምዕራብ ዓለም ዕዳ ለለመክፈል አፋቸውን ከሚያሞጣሙጡት አገሮች ግንባር ቀደም ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ይላሉ ጋዜጠኛው፣ ከሰሸሊስት አገሮች ለታዳጊ (developing) አገሮች የሚላከውን የጦር መሣሪያ እርዳታ ከፍተኛውን ድርሻ ያገኛሉ። ለጥቀውም እንደሚሉት፣ ሦስቱ አገሮች በየወሩ የጦር መሣራያ ከምር ከየወደባቸው እያራገፉ በየወሩ ደግሞ የምዕራብ የምግብ ዳረጉት በዚያዋ መጠን እንዲመፀወታቸው እጃቸውን በማርገብገብ ይማጠናሉ። እንግዲህ በጋዜጠኛው አቀራረብ ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት በሦስተኛው ዓለም ውስጥ ጉልህ የሆነ የሥራ ክፍፍል አላቸው። ይኸውም፣ የምስራቁ (ሶሻሊስት)

ዓለም የድሀ አገሮች ሕዝቦች እርስ በርሳቸው መተራረጃ የሚሆናቸውን መሣሪያ ሲያቀርብ የምዕራቡ (ካፒታሊስት) ዓለም ደግሞ የሞት መድኅኒት የሆነውን የምግብ (ሰብአዊ) እርዳታ ብቻ ይለግሳል። በርግጥ ይህ ለምዕራብ የዋሃን አንባቢ ጆሮ ይጣፍጥ እንደሆነ እንጂ ነገሩን እውነት ነው ብሎ የሚያምን ከቶ አይገኝም። ምክንያቱም ምዕራቡን ዓለም (በአሜሪካ ፊታውራሪነት እየተመራ) በእንጎላ፣ በሞዛቢክና በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን ወንድማማቾች እርስ በርስ የማጫረሱበት የጦር መሣሪያ ለእንጎላው የአቶ ዮናስ ሰቪምቪ ቀኝ እከራሪ ሽምቅ ተዋጊ ድርጅት፣ ለሞዛምቢኩ የደቡብ አፍሪቃ ቅጥረኛ ኤም ኢን አር (M.N.R.ወይም ሬናሞ) ድርጅት እንዲሁም በኢትዮጵያ ያለውን መንግሥት ለሚቀናቀኑ ሁሉ «በሰብአዊ እርዳታ» አሰበው እንዲያቀርቡ ራሳቸውን ፕሬዚዳንት ሬግን በየጊዜው በሚሰጡት የሬድዮ መግለጫ ያልደበቁት የአደባባይ ሚስጥር ነው። (10) ታዲያ ግዜጠኛው እውነት ሚዛናዊ (objective) ከሆኑ ይህንን እውነት ዉለፍ አድርገው ምነው በዘገባቸው አሳከፈሉንም?።

እኒሁ ጋዜጠኛ ለአፍሪቃ አህጉር ጠቅሰሳ ያሳቸውን ንቀት በሚከተለው ዓይነት ያንፀባርቃሉ። «አፍሪቃ በዓለም የመጨረሻ መናጢ ድሀ፣ በልማትም ፍጹም ኋለቀር አህጉር ናት። የሕዝቧም ወሊድነት (fertility-rate) አህጉሪቱ ካለት የእህል ማምረት ችሎታ ጋር ሲነፃጸር ከፍተኛ ነው።» ትንታኔአቸውንም በመቀጠል፣ በ35 ጥቁር የአፍሪቃ አገሮች ውስጥ አንድ ሚሊዮን ወታደሮች መኖራቸውን ገልጠው በእንፃሩ ግን 30,000 ደክተሮችና 1.75 ሚሊዮን አስተማሪዎች ብቻ እንዳሉ ያስረዳሉ። በአፍሪቃ የወታደሮችንም ሥርዓተ-አልበኝነት (indiscipline) ሲገልጹ መለዮ ለባሾች በናይጀሪያ ትጥቃዊ ዝርፊያ እንደሚያከሂዱ ገልጠዋል። ቀጥለውም በዚኢር የደሞዝ ወቅት ያለፈባቸው ወታደሮች ሰለማዊውን ሕዝብ ምግብና መጠጥ ሰይቀር እንደሚነጥቁ ያመለክታል። ጽሑፉ ግን እነዚህን ወታደሮች ከትኩተው ያሰደጉት የምዕራብ የጦር ድርጅቶች መሆናቸውን በፍጹም አይነግሩንም። ጋዜጠኛ ጆን ኢድሊን በ22 የአፍሪቃ አገሮች ውስጥ ወታደራዊ እምባገነን እገዛዝ የአስተዳደሩ ፈሊጥ መሆኑን ጠቁመው መሪዎቹ (ፈሰ ያለበት ዝለይ እይችልም እንደተባለው) ከሥር ፍንቀላ (coup d'etat) ስለሚፈሩ ወታደሮቻቸውን ከመጠን ያለፈ እንደሚንከባከቡ ያብራራሉ። አሰዘኙ ነገር ግን ጋዜጠኛው እንደነሞቡቱ ሴሴኮስና እንደነኢዲ አሚን ዓይነቶችን የአፍሪቃ መሰለቂያዎች ከአምላ አለቃነት ከትኩቶ ወደመሪነት ደረጃ ያደረሰቸው የምዕራብ ጌቶቻቸው ድጋፍ መሆኑን አለመግለጣቸው ነው።

በዚህ ጉዳይ የአፍሪቃ ሰፊ ሕዝበች ተጠያቂ አይሆኑም። እርግጥ ወደፊት የሰሺየት ሕብረት አፍሪቃዊ ቡችላዎችም ደህና የርዕዮተ ዓለም «ኩቲ» ለመሆን በመሠልጠን ላይ እንዳሉ አፍሪቃና ሐቀኛ ልጆቿ ያውቃሉ። ይህንን ያህል ሐተታ ስለ «ጥቁር አፍሪቃ» ያዥጎደጎዱት ጋዜጠኛ ጆን ኤድሊን ስለደቡብ አፍሪቃ የነጭ አገዛዝ (Apartheid) መንግሥት ምን ያህል ከበድ ወንጀል ሊነግሩን ይሆን እያልን በጉጉት ስናነብ ያንን እስከፊና ኢሰብዊ አገዛዝ በሚከተለው ልስላሴ የተሞላበት ገራ-ገር አስተያየት ያሰናብቱታል። ለማስረጃም ያህል የሚከተለውን ጥቅስ እናስተውል፤

> ደቡብ አፍሪቃ እራሷን ለመከላከል በርካታ ገንዘብ ታጠፋለች። ባለፈው ረቡዕ (ይህ ጽሑፍ በቀረበበት ዋዜማ) የደቡብ አፍሪቃ ወታደራዊ በጀት ወደ 22.6% ከፍ በማለት ጠቅላላ ወጪው ወደ $4.1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲያሻቅብ እድርጎታል። ይህም እስካሁን ከተመደበው የወታደራዊ በጀት ከፍተኛው መሆኑ ነው። (11)

የታለ የደቡብ አፍሪቃ የዘር መድሎ ጉድና ጥቁሮች የቆዳቸው ቀለም ብቻ በገዛ ሀገራቸው ወንጀል ሆኖባቸው እንደአበደ ውሻ እየታደኑ የሚገደሉበት ሁኔታ እንደሞዚምቢክ፣ አንጎላና ኢትዮጵያ «ውድቀትና ጉድ» የተዘከዘከው?! እጹ የምዕራብ ጋዜጠኞች ሚዘናዊነትና ሐቀኛነት! እየነው ጉዱን! ቀደም ሲል እንደገለጥነው ሁሉ በተራ ቁጥር ፩፣ ፫፣ እና ፬ እንባር የተጠቀሱትን የጋዜጣ እርእስት ሥፍራ ለመቆጠብ ስንል እንባቢያን እንዲመረምሩዋቸው እያበረታታን እናልፋቸዋለን።

(ሐ) ግራ ክንፍ (ሊፍቲስት ሰሻሊስት ባህሪይ ያላቸው) ጋዜጣዎች

ነገሩን በብርቱ ምርምር በመደገፍ ካሳጤኑት በስተቀር ባጠቃላይ የምዕራቡ የግራ ክንፍ ጋዜጠኞች ኢትዮጵያን የሚያስተውሉበት ዓይን በጣም ግራ የጋባል። እነዚህ የግራ ክንፍ ጋዜጣዎች በራሳቸው ሦስት በታ ሊከፈሉ ይችላል። እነሱም የሰሺየት ሕብረትን እቂም የሚደግፉ የከሙ ኒስት ፓርቲ ልሣኖች፤ የን ኡስ ከበርቴ «ሰሻሊስት» ነን ባይ ጋዜጣዎችና እንዲሁም የሠራተኛ ማህበራት ጋዜጣዎች ናቸው። እነዚህም እንዲሁ እንደየ እቂማቸውና እንደየባህሪያቸው ሊከፈሉ ይችላሉ። ለዚህ ጽሑፋችን ግን ይህ ትንታኔ አስፈላጊ ስላልመሰለን በየክፍሉ የመመደቡን ነገር እዚህ ላይ እንገፋበትም። በእጭሩ ግን ለሞስክ እቂም ድጋፍ የሚሰጡ የምዕራብ የከሙ ኒስት ፓርቲ ጋዜጣዎች በሚጽፉአቸው ሐተታዎች የኢትዮጵያን «ትክክለኛ ገጽታ» ለማሰየት እንደሚሞክሩ ተገንዝበናል።

ይሁንና እነዚህም ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ልዩ አፍቅሮት ኑሮአቸው ሰይሆን ከምስክ ጋር ያላቸውን ርእዮተዓለማዊ አንድነት ለመግለጥ የሚያደርጉት

ይመስለል። የኢትዮጵያን መንግሥት በመቃወም ሰቢያ የኢትዮጵያን ማንነት እንደልነበረ ለማድረግ የሚጥሩ የየመንደሩ የምዕራብ ንዑስ ከበርቴ ሰሻሊስት ነን ባይ ጋዜጣዎች በርከታ ናቸው። የነሱም ጥላቻ የተመሰረተው ኢትዮጵያ ሰቪየት አቀፍ (pro Sovit) በመሆኗና ሰሻሊስታዊ መመሪያዋን ከነሲ ባለመቀበሏ ይመስለል። ሌላም ምን ማለት ይቻለል። በዚህ ጉዳይ ላይ ግን አረጋግሞ ለመፃፍ በቂ ምርምር ስላላደረግን ይህ የግላችን እስተያየት ብቻ መሆኑን ለአንባቢያን እንገልጣለን።

ከቀኝ ክንፍ ከማህል ሠፈሪ ጋዜጣዎችና ጋዜጠኞች የኢትዮጵያ ጊዳይ እቀራረብ ጋር ሰናወዳድረው አብዛኞች የምዕራብ ሰሻሊስት ጋዜጠኞችና ጋዜጣዎች በተሸለ ሚዘናዊነት ለማቅረብ ይሞክራሉ። ይሁን እንጂ ዘሮ ዘሮ ያው የምዕራብ የአተናተን ዘዴ ስለሚከተሉና ስለኢትዮጵያ ሁኔታ በቅርብ ስላለጠኑ በቁንጽል ወሬ ላይ የተመሠረተ አደገኛ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ የሚደርሱበት ጊዜ ብዚ ነው። ስለዚህም የነዚህ ጋዜጣዎች የዘወትር ኢትዮጵያን መመልከቻቸው መነጥር መልኩ ይህ ነው ብሎ ለመናገር ያዳግታል። ከምዕራቡ ዓለም የግራ ክንፍ ጋዜጣዎች ለናሙና የመረጥናቸው ኢትዮጵያ ነክ አርእስት የሚከተሉት ናቸው፤

፩) "Ethiopia: They Don't Have to Starve" Socialist Worker, February 1988 page 1.

፪) "Ethiopian Journey", The Canadian Tribune March 21, 1988., Page 6

፫) "Ethiopia: Famine Menace Returns, "The Guardian, April 6, 1988 Pages 10 11

እነዚህ ከላይ ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ፫ የተዘረዘሩትን እርእስት ከቀኝ ክንፍና ከማህል ሰፈሪ ጋዜጣዎች ኢትዮጵያ ነክ እርእስቶች ጋር በማስተያየት የምንመለከተው ዓይነተኛ ልዩነት አለ። ይኸውም ቀደም ሲል እንደመለከትነው የአንድ ጽሁፍ ርዕስ የሚጸፍበት ጉዳይ እምብርት ሐሰብና አልፎ አልፎም የጋዜጠኛውን አቂም መጠቆሚያ እንደመሆኑ መጠን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ሦስት እርእስት ግና ስናነባቸው ይዘታቸው የጥላቻና የቂም መወጫ መልእክቶች አያስተላልፉም። ስለዚህም ነው እነዚህ ቢያንስ በጋዜጠኛነት ሙያ እንኳ ሚዛናዊነት (Objectivity) እየተባለ የሚጠራውን ጉዳይ በኢትዮጵያ ሁኔታ የጠበቁ ይመስላሉ ብለን የገመትነው። ወደ ጽሁፎቹ ትንታኔ እንግባ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ሦስት የግራ ክንፍ ጽሁፎች ውስጥ በተራ ቁጥር ፫ እንኖር የተመዘገበውን እንመልከት። ይህ ሰምንታዊ ግራ ክንፍ ጋዜጣ የሚታተመው በኒው ዮርክ ከተማ ነው። የዚህ ዘገባ ፀሐፊ ወ/ሮ ካተሪን ወትሰን (Catherne Watson) የተባሉ ጋዜጠኛ ናቸው። ጋዜጠኛዋ ጽሁፉን

ሲያዘጋጁ በኢትዮጵያ በተለይ በትግራይና በኤርትራ ስፊ ጉብኝት አድርገዋል። ጋዜጣው ለዚህ ጽሁፍ ገጽ 10እና 11ን በሙሲ የለቀቀ ሲሆን እትኩሮቱም የድርቅን ችግር ለመቋቋም በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሴቶች ልዩ አስተዋጽኦ እጉልቶ (በስዕል ጭምር) በማሳየት ላይ ነው። ጋዜጠኛዋ የአለም አቀፍ ቀይ መስቀልን አስተያየት በመጥቀስ በኤርትራ 100% እንዲሁም በትግራይ 75% የዘንድሮ ሰብል በድርቀት ምክንያት እንደጠፋ ጠቅሰው በጉብኝታቸው የታዘቡትን ሁሉ በእጭሩ ይዘረዝራሊ። አብሮአቸው የሚጓዘው አስጎብኝአቸው ኢትዮጵያዊ ጋር ሲወያዩ የጂሬቶችን መድረቅ የተራርቹን ደን አልበ መሆን እንደተመለከቱ ገልጠው በተለይም በሁለቱም ክፍለተ ሀገር ለረጂም ጊዜ የቆየው የፀጥታ መታወክም ጭምር ለችግሩ መባባስ አይነተኛ አስተዋጽኦ እንደሰቸው ከሐበሻው አስጎብኛቸው ቃል የሰሙትን ይጠቅሳሊ። በአበሻው አስጎብኛቸው አባባል የሰሜን ኢትዮጵያ ምድር ከ3,000 ዘመን ያሳነሰ የታሪሰ በመሆኑ ለሙ አፈር ተሸርሽሮና በንፈስ ተጠርጎ ስለለቀ ምድሩ እርሻ ታክቶታል።

ወ/ሮ ከተራን በደቡብ ኤርትራ በመጊዝ ላይ ሳሉ በመንገድ አቶ ሠመረ አብርሃም የተባለውን ጎልማሳ ሐበሻ አግኝተው ያደረጉትን ጭውውት ይጠቅሳሉ። በጋዜጠኛዋ አቀራረብ አቶ ሠመረ የ40 ዓመት ጎበዝ ገበሬ ነው። በአጋጣሚም ከሱ ጋር የተገናኙት ያሉትን 8 በሬዎቹን ለመሸጥ ወደገበያ እየነዳ በመሄድ ላይ እንደለ ነው። በዚህም ወቅት ጋዜጠኛዋ አቶ ሠመረን ለምን በሬዎቹን እንደሚሸጥ የምሬት ንግግሩን እንደለ ያቀርቡልናል።«ምንም ምርጫ የለኝም። በዚህ ዓመት ከእርሻዩ ላይ አንድም የእህል ዘር አልበቀለበትም » ጋዜጠኛዋ በአቶ ሠመረ አነጋገር ምን ያህል ልባቸው እንደተነካ ከጽሑፋቸው ድምዳሜ መረዳት ይቻላል። እንደሰቸው አባባል አቶ ሠመረ በሮቹን ዘንድሮ በችግር ምክንያት ሽጧልና በሚቀጥለው ሰኔ ዝናብ ቢጥል እንኪ የሚያርስበት በሮች አይኖረውም።

ጋዜጠኛ ከተራን የኢትዮጵያን ችግር በአቶ ሠመረ ተዉበጭ ሁኔታ እማኝነት እጉልተው ከሰዩ በኃላ የምዕራብ ቀኝ ክንፍ (ከንሰርቫቲቭና ሊበራሎቹንም ደምረው) ጋዜጣዎች ለረሀቡ ያሳቸውን የተዛባ አስተያየት ይነቅፋሉ። ወ/ሮ ከተራን እንደሚሉት የምዕራብ ጋዜጣዎች የኢትዮጵያ ረሀብ እንዴት እንደዚህ በአጣደፊ ይደከማል» ብለው ሕዝቡ ሆን ብሎ ቀጠሮ ሰጥቶ የጋበዘው ይመስል በብስጭት ይጽፋሉ ይላሉ «እንዲንደቹ ደግሞ » ይላሉ ጋዜጠኛዋ «ቀድሞ የምግብ ተራድኦ ሲያደርጉ የቆዩ ለጋሰች ሁሉ የመሰላቸትና የመታከት (aid fatigue) ይታይባቸዋል ብለው ይተነብያሉ። ይህ ግን በፍጹም ያልተከሰተ ጉዳይ ነው» በማለት ጋዜጠኛዋ ጽፈዋል።(12) ቀጥለውም እንደንድ የምዕራብ ጋዜጣዎች የኢትዮጵያን ችግር አስመልክተው የሰጡትን ስሜተቢስና ኢሰብአዊ አስተያየት በመንቀፍ ከዚህ የሚከተለውን አስተያየት ይሰነዝራሉ።

ሌሎች ብዙ (የምዕራብ) ጋዜጣዎች ይህንን አጋጣሚ (ማለት የረሀቡን ወቅት)ራሱን ሰሻሊስት ነኝ ብሎ የሚጠራውን የፐሬዚደንት መንግሥቱ ኃይለማርያምን መንገስት የነቀፉ ውርጂብኝ ለማዥጎድጎድ ተጠቅመውበታል። በእድሀሪ አቷሙ የታወቀውና በብዙዎች ዘንድ ተነባቢነት ያለው የብሪታኒያ ታብሎይድ (Tabloid) ጋዜጣ ማለት ዘ ሰን (The Sun)(13) እየተባለ የሚታወቀው የዘንድሮውን የኢትዮጵያ ረሀብ በፐሬዚደንት መንግስቱ አሰቦ በጣም ጉልሀና ደግቅ በሆነው ርዕሱ አግኝንት ሰበት ሚሊዮን ለሚሆኑ አንባቢዎቹ ለኢትዮጵያ ረሀብተኞች እርዳታ እንዲደሰጡ እንዲህ ሲል ያዘቸዋል፤ «[ለኢትዮጵያ ረሀብተኞች ፍሌም] አትለግሱ»(14)

በጋዜጠኛ ከተራን አስተያየት የእነዚህ ሁሉ የምዕራብ ጋዜጣዎች ነቀፋዎች የኢትዮጵያን ከሰሺየት ሕብረት ከለመጠን መጠጋት እጥብቀው ለሚፈሩና ለሚጠሉ ምዕራባውያን ጆሮ የሚጥም ቢሆኑም አስተያየቶች ኢሰብአዊና ከመጠን በላይ ተገቢነት የሌላቸው ናቸው እኒሁ ጋዜጠኛ እንደሚሉት ኢትዮጵያ ከአፍሪቃ አገሮች እንኪ አሁን በላት ሁኔታ ሰትወደደር የመነጠች ድሃ ሆና ሰለ ከምዕራቡ ዓለም ዓመታዊ የነብስ ወከፍ (per head) የልማት ድጋፍ ያገኘችው $9 የአሜሪከን ዶላር ብቻ ሲሆን ሌሎች ድሆች የአፍሪቃ አገሮች ግን በአንፃሩ የ$20 የአሜሪከን አማከኝ የነብስ ወከፍ ዓመታዊ የልማት ድጋፍ ተሰጥቶአቸዋል። ወ/ሮ ከተራን ሰሸሊስት ጋዜጠኛ ቢሆኑም «ሰሸሊስት ነኝ» የሚለውን የፐሬዚደንት መንግሥቱን መንግሥት ጭቀነትና ሚዘናዊነት በተመላበት አግበብ በለው መንገድ ነቅፈዋል። እንጥቀስ፤ «ከ47 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከመቶ ዘጠናው እጅ አርሶ አደር ነው። መንግስቱ ገበሬው ሰብሉን ለመንግስት ሰብል ግዥ ድርጂቶች በዝቅተኛ ተመን እንዲሸጥ በማድረግና በተለይም በገጠሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመሬት ይዘታ ለውጥ የመንደር ምስረታ ሰፈራ ጣቢያ (resettlement) ወ ዘ ተ ጥንቃቄ በጎደለው ችኩልነት ተፈጽሟል። እነዚህ እርምጃዎች ተገቢነት ቢኖራቸውም አፈፃፀማቸው ግን አሰጪና (harsh) ነበር።»(15)

እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ቁምነገር ጋዜጠኛዋ በሰሸሊስት እምነታቸው ላይ የተመሠረተ ድጋፍ ለፐሬዚደንት መንግሥቱ ሰይሆን ለኢትዮጵያ አብዮት ቢሰጡም ይኸው ድጋፋቸው እንደቀኝ ከንፍ ጋዜኞች አስተያየት ፍጹም ጭፍን አይደለም። በኤርትራና በትግራይም ሰለሚገኘው የወንድማማቾችና እህትማማቾች መተላለቅ ሲያብራሩ የሕዝብ እልቂትን፤ የንብረት መውደምንና ብሎም የረሀብን ችግር ማበባሱን ጭምር የሙያ ብስለትና ዉ ዋነት (professional ethics) በተመላበት አፃፃፍ አቅርበዋል። እዚህ ላይ በአጭሩ ለማለት የሞከርነው ወግ አጥባቂ ወይም ቀኝ መንገደኛ (conservative) ጋዜጠኞች የኢትዮጵያን ችግሮች በማስታከክ ለራሳቸው ስርዓት (ካፒታሊዝም)

የፐሮፖጋንዳ ትርፍ ለማስገኘት እንደሞከሩት ሁሉ ምዕራባዊ ሶሻሊስቲ ጋዜጠኛ ከተራን ለሶሻሊዝም ድል ማንፀባረቂያ የፐሮፖጋንዳ ጥቅም ለመሸት አልፈለጉም ነው።

ከላይ ርእሱ በ (ሐ) ሥር በተራ ቁጥር ፩ እንዳር የሰፈረው ጋዜጣዊ ዘገባ ሱዛን ሻው (Susan Shaw) በተባሉ ጋዜጠኛ የተፃፍ ነው። ጋዜጣው ኃያላን መንግስታትን (ማለት ሞስኮንና ዋሽንግተንን) አዘውትሮ የሚነቅፍ የአለም አቀፍ ሶሻሊስቶች (international socialists) ልሳን ነኝ የሚል ወርሐዊ እትም ነው። ለዚህ ጥናታችን የተጠቀምንበት ዘገባ የጋዜጣውን የሽፋን ገጽ ይዘ በጉልህ ፊደሎች አማክይነት በችግር ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን በፍጹም መራብ እንደማይገባቸው በማመልከት የርሃቡን መጠን እጉልቶ ለማሰየት በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ የሚገኝ የህፃን ምስል ጠምሮ ያቀርባል።

ጋዜጠኛ ሱዛን ሻው እንደ ሌላዋ ሴት ጋዜጠኛ ከተራን ሁሉ ጽሑፋቸው ለምዕራብ ሶሻሊስት አነባቢያቸው የኢትዮጵያን ችግር ሰፋትና ጥልቀት ቁልጭ አድርጎ ለማሰየት የታቀደ ነው። ጋዜጠኛዋ ሶሻሊስት ናቸውና የኢትዮጵያ ችግር ምን ያህል የዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚ መዋቅርና የምራቡ የምግብ እህል ስርጭት ፖሊሲ ውጤትም ጭምር እንደሆነ በማመልከት የፖለቲከና የርእዮተዓለም ጠለቶቻቸው የሆኑትን የምዕራቡን ዓለም ቡርዥዋዎች መክርከማቸው አልቀረም። ፀሐፊዋ እደሚሉት በአለም ላይ ከቶ እንደ አሁን ጊዜ በምዕራቡ ዓለም የምግብ እህል የተትረፈረፈበት ጊዜ የለም። በዚህ ወቅት ግን ሰባት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በተለይ በትግራይና በኤርትራ የሚገኙ ህዝቦች በረሀብ አለንጋ መገረፍ እንደሌለባቸው ሙግታቸውን ለምዕራቡ ሶሻሊስት አንባቢዋቻቸው ያቀርባሉ። እኒህ ጋዜጠኛ ለዚህ እጭር ጽሑፋቸው በሰጡት ድምዳሜ አማክኝነት ለአንባቢዎቻቸው ትምህርት ሲሰጡ እንዲህ ይላሉ። «ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የምዕራብ ፍርፋሪ ዳረጎት አይደለም። እነሱ (ኢትዮጵያውያን) የሚያስፈልጋቸው በቴክኖሎጂ የተራቀቁት የምዕራብ አገሮች የምግብ እህል ስርጭት ፖሊሲ ለውጥ ነው። ይሁን እንጂ ይህ በካፒታሊዝም ስር የሚሰክ ጉዳይ አይደለም፤ ምክንያቱም በዚህ ሥርዓት ገደብ የለሽ ትርፍ የማግበስበስ ፍላጎት ይህንን የፖሊሲ ለውጥ ጨርሰ አይቀበልምና ነው። ይህ ሊሰክ የሚችለው የማናቸውም ዓይነት ውጤቶች የማምረት ዓላማ የሕብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት በሆነበት በሶሻሊስታዊው ዓለም ብቻ ነው።»(16)

ለዚህ ጥናታችን ከተመለከትናቸው ግራ ክንፍ ጋዜጣዎች ውስጥ ከላይ በሐሙራ (ሐ) ሥር በተለይ በተራ ቁጥር ፪ እንዳር የሠፈረው በሰሜን አሜሪካ ከታወቁትና ነባር ከሆኑት የኮሚዩኒስት ፖርቲዎች ልሳን እንዱ የሆነው The Canadian Tribune ነው። ማንም አንባቢ እንደሚገምተው ሁሉ ይህ ፖርቲ ለሶሺየት ሕብረት የኮሚዩኒስት ፓርቲ ዓለማና እቋም ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጥ

ፓርቲ ነውና ልሰ ኑም ይህን ኑ እቂም አዘውትሮ የሚያንፀባርቅ ይመስላል። ይኸው ጋዜጣ ከላይ በጠቅስነው እትሙ ለኢትዮጵያ አብዮት አጠቃላይ የሆነ «በዓለምአቀፋዊነት» ላይ የተመሠረተ የሚመስል ድጋፍ ኢትዮጵያ ውስጥ በተጨባጭ በመካሄድ ላይ ባሉ የሕዝብ ትግል ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ ይሰጣል። የጋዜጣው አጠቃላይ ባህርይ ይህን ኑ ይመስላል ብለን አፋችንን ሞልተን እንዳንናገር ለዚህ ጥናታችን ባጋጣሚ ካገኘነው በስተቀረ ሌሎች እትሞችን አልተመለከትንም ስለዚህም በዚህ እንድ እትም ላይ ብቻ በማትኮር አጠቃላይ የሆነ አስተያየት ከመስጠት እንቆጠባለን።

The Canadian Tribune በተለይ በMarch 21, 1988 በገጽ 6 ላይ በወጣው እትሙ በኢትዮጵያ የአንድ ዓመት የሥራ ጊዜ ያሳለፉ ባልና ሚስት፣ ዶክተር ቻርልስና ወይዘሮ ሳሊ ዴቪስ የተባሉ ግለሰቦችን በማነጋገር ሰፋ ያለ ቃለመጠይቅ አቅርቧል። በቃለ መጠይቁ በአጠቃላይ የተንፀባረቀው አስተያየት የትሪቡን ጋዜጣ ባልደረባ የምዕራብ ቀኝ ክንፍ ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን የማንቋሸሽ አቀራረብና ርእዮተዓለማዊ ፕሮፖጋንዳ ለማክሸፍ ባይቻል እንኳ ለማቻቻል (Counter balance) የታቀዱ ጥያቄዎቻቸውን በመመለስ ላይ ነው። የተጠያቂዎቹ አስተያየት በአጭሩ ከሌሎች ጋዜጦች አቀራረብ የተለየ ቀናነት(Positiveness) ያለውና ቀጥተኛከተናጋሪዎቹ እንደበት እንደፈለቀ የተነፈ ነው። ሥፍራ ለመቆጠብ ስንል ቃለመጠየቁን እዚህ አንተረጉምም። ግለሰቦቹ የተናገሩት ሲጠቃለል የኢትዮጵያ ሕዝብ ለልማት ያለው፣ ጉጉትና ታታሪነት የሚያደንቅና አገሪቱ ግን በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት አበሳዋን በማየት ላይ የምትገኝ መሆንዋን የሚያመለክት ነው።(17)

ማጠቃለያ

የአውሮፖና የአሜሪካ (ባዕዳን) አፍሪቀኞች (Africanists) ስለአፍሪቃና ስለመሰለው ጥቁር ሕዝብ የሚጽፉት ታሪክ ውስጥ ብዙ የተዛቡ፣ የተጣመሙና አልፎ አልፎም በመሰሪ ጥበብ የተገደፉ ድርጊቶችና ከስተቶች መኖራቸውን በርከታ የአፍሪቃ ዘር የሆኑት (Negro) የታሪክ ሊቃውንት እየተገነዘቡት በመሄድ ላይ ናቸው። ጥቂቶችም «ፈረንጂ» ነጭ ቀለም የቀባውን የጥቁር ሕዝብ ታሪክ እውነተኛ ቀለሙንና በህሪዩን ለመስጠት እየታገሉ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ በቀርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በጣም ልዩ ሥፍራ ሊሰጣቸው የሚገቡ አፍሪቃዊው የሴኔጋል ተወላጅ የታሪክ ሊቅ ሸክ አንታ ዲዮፕ (Cheik Anta Diop) ይገኙበታል። እሰቸው ከደረጉት ተጋድሎ ዋነኛው ላለፉት 180 ዓመታት ያህል የአውሮፖ የታሪክ ሊቃውንቶች የግብጽን ሥልጣኔ የነጮች ሥራ ውጤት አድርጎ ለማቅረብ የተደረገውን ሬቂቅ ሊብነት በአኩሪና አንጀት አርስ ምርምሮቻቸው አማከኝነት ድል በመንሰታቸው ዛሬ የግብጽ ሥልጣኔ የጥቁር (Negroid) ሕዝብ የሥራ ውጤት ነው ብለን አፋችንን ሞልተን ወደ ምንናገርበት የታሪክ ዘመን ላይ ተሸጋግረናል። እኒህ የአፍሪቃ ሐቀኛ ልጅ ይህንን በያደርጉ ኑሮ የአውነተኛውን የአፍሪቃ የታሪክ ቅርስ በፈጣሪነት አውሮፖውያን ሊሰለፉ

አልነበረንም? ለዚህም ነው የሪቡ ታሪክ ፀሐፊ/ደራሲ የሌለው ሕዝብ ማንነቱን በትክክል የሚያቀርብበት ታሪክ የማይኖፍለት። ይህንን ለማለት የበቃነው ለዚህ ጥናት የመረመርናቸው የጋዜጣ ጽሑፎች ሁሉ በኢትዮጵያ ልጆች ቢቀርቡ ኖሮ ምንኛ በይዘታቸውና በአቀራረባቸው ከዚህ ለየት ያሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመገመት ነው። የምዕራብ ጋዜጠኞች ከቀኝ፣ ከመሐልና ከግራ ከንፍ እንፃር (Perspectives) ለየራሳቸው የርዮተዓለምና የፖለቲከ ትርፍ ለማግበስበስ ቢጥሩም በረሀብ የተጎዱ ኢትዮጵያውያን ፈጣንና ነብስ-አድን እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ በቃላት ሊገለጽ የማይችል እርዳታ የምዕራቡ ሕዝብ እንዲሰጥ ረድተዋል። ይህ የኛ ጥናት ግን ያተኮረው በዚያ ላይ ሳይሆን ኢትዮጵያ ከምዕራብ ሆነ ከምሥራቅ «የረሀብ ማስታገሻ እርዳታ» በተቀበለች ቁጥር ብሔራዊ ኩራቷንና በማጣት ረገድ የምታገበው «የውርደት» እዳ በአንድ ትውልድ ዘመን ከፍሎ የማትጨርሰው መሆኑን ለመጠቆም ነው። ከሁሉም በላይ የዚህ ጥናታችንን መሠረታዊ ምክንያት የምዕራብ (ባዕዳን) ጋዜጠኞች የኢትዮጵን ረሀብ በማስታገስ ተግባር የተሸፈነ «ሰብአዊ ተልእኮ» አሰበው በዜና አቀራረባቸውና በልዩ ልዩ ዘገባቸው በእናት ሀገራችን ማህፀነ-ታሪክ ውስጥ ለዘለዓለም የማይሽር ነቀርሳ እየቀበሩና እንኪን የባዕዳንን አስተያየት ቀርቶ የእኛንም በውጭ አገር የምንገኝ እንዳንድ ልጆቿን አመለከከት እየጠመዘዙ ለአገራችንና ለማንነታችን የሚያስደነግጥ የማይለሽነት ሁኔታ ላይ እስከምንገኝ ማድረሳቸው ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ጭምር ነው። ይህ ዓለማችን ባይሰከልንም እንኪ ይህንን ጽሁፍ ያነበቡ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ በነገሩ ለመወያየትና ለመነጋገር የሚያስችሏቸው በቂ ምክንያት ከፈጠርን እንደምዕራቡ ዓለም ጋዜጠኞች የርእዮተዓለምና የፖለቲከ ሰሆን የተዳፈነ የሀገር ፍቅርን ስሜት በማከፈል ረገድ «ትርፍ አጋብሰናል» ብለን ልንከራ እንችላለን።

ማንም ሰብአዊ ፍጡር ሊገምተው እንደሚችለው ሆዱን ሞልቶ የማያድር ሕዝብ ብሔራዊ ኩራት ሊኖረው ከቶ አይችልም። ይህንን ከቀድሞ ኩራዎች ኢትዮጵያውያን የበለጠ የሚያውቀው ሕዝብ ያለ አይመስለንም። ባለፉት 15 ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ የረሀብ ምንጭ የፈለቀባትና የረሀብ ጎርፍ ያጥለቀለቃቸው ምውታን ምስኪኖች ከርሠመቃብር ምስል(image) ተሰጥቷት በመላው የምዕራቡ ዓለም የዜና ማሠራጫ ድርጂቶች ሲነገርላት ከርሟል። እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት 15 ዓመታት የተጎናፀፈችውን ይህንን የተመጽዋችነት ምስሏን ከመላው ዓለም ሕዝቦችና በተለይም ከራሷ ሕዝቦች አእምር ፍቆ ለመጨረስ የአንድ ትውልድ ዘመን (ከ60 እስከ 70 ዓመታት)አይበቃትም። ይህም ሊሰክ የሚችለው ተፈጥሮ (Mother nature) ፊቷን ብትመልስልንና ድርቅ በዝናብ፣ ጦርነት በሰላም መተክት የጀመረ እንደሆነ ነው።

በዛሬው የፈጣን ቴክኖሎጂ ዘመን የምዕራቡ ዓለም የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሁሉ ለግንዘብ፣ ለፖለቲከና፣ ለርእዮተዓለም ትርፍ የሚነግዱ

በመሆናቸው የቴሌቪዥን ጊዜም ሆነ የጋዜጣ ገጸች መከራያ ዋጋ በጣም ውድ ነው። በዚህም የተነሳ አንድ እውነትን አበጥሮና አንጠርጥሮ ለማቅረብ የሚፈልግ ምሁር የሥራውን ውጤት በነዚህ መገናኛ ዘዴዎች ለማቅረብ አይከጅልም። ከዚሁ ከኛ አስተያየት ጋር የተቀራረበ አስተያየት ያላቸው የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አዋቂ የሆኑት አቶ ፒራግሪን ወርሰቱን በምዕራብ ጋዜጣዎችና ቴሌቪዥኖች ሀቀን አንጥሮ ለማውጣት አይቻልም በማለት "What Journalism is" (18) በተባለው ጽሑፋቸው ያትታሉ። ከሥራቸው እንጠቅሰለን፤

> «ግንኛውም እውነተኛ ጀርናሊስት በጋዜጦች ውስጥ የሚገኘው ሀቅ መጠን ምን ያህል ዝቅተኛ መሆኑን ሲገነዘብ በታላቅ ሀዘን ይመሰጣል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በተለይ ጀርናሊስቶች ሆን ብለው በመቅጠፍ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሆነው ሳይሆን በጠቃላይ የዘመኑ (የምዕራብ) የጋዜጠኝነት ሙያ ባህርይ እውነቱን አንጠርጥሮ ለማቅረብ የሚደረገን ጥረት ሁሉ የመገታ አዝማሚያ ስለአለው ነው። ይህ ዓይነቱ ችገር ገን እጅግ በከፋ ሁኔታ የሚታየው በቴሌቪዥን የዜና ማሰራጫ ዘገባና ትኞት ፕሮግራሞች ነው።»(19)

ይህ ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ችግር በተለይ በአፍሪቃ ዊነታቸው ምክንያት ከተሰማቸው ግለሰቦች ውስጥ እንዱ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ዩ ኤስኮ) የበላይ ኃላፊ የነበሩት ሲ ኤጋሳ ዊው አህማዱ መህታር እምባው ይገኙበታል። እሳቸውም የምዕራብ ዜና ማሰራጫ ድርጅቶች የአፍሪቃንና የሌሎችንም የሦስተኛው ዓለም ሁኔታ በትክክል እያንፀበርቁምና እዲስ የዓለም የዜናና የመገናኛ ሥርጭት ሥርዓት (New World Information and Communicaton Order) ተመሥርቶ የምዕራባውያን የዜና ማሠራጫ ዎች እንደሸቸው የሦስተኛውን ዓለም ጉዳይ ማዳከራቸውን ማቆም አለባቸው በማለት ጥናት አቀረቡ። በጥናታቸውም ውስጥ የዚህ ዓይነት ድርጅት ከልተመሠረተ የሌሎች ድሀ አገሮች ትክክለኛ ሰሚት፣ ፍላጎትና ምኞታቸው እንዲሁም እውነተኛ ማንነታቸው እይታወቅላቸውም በማለት ተከራከሩ። የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ አልዋጥላቸው ከላቸው አገሮች ውስጥ በተለይ አሜሪከና እንግሊዝ ከዩ ኤስኮ ድርጅት መውጣት ብቻ ሳይሆን የዩ ኤስኮን ድርጅት በእምብርኩ የሚያስኬደውን አሰፋሪ እርምጃ ወሰዱ። ይኸውም የድርጅቱ 30% ገቢ የነበረው መዋጮአቸውን ሲያቋርጡ እውነተኛ ለአፍሪቃና ለሌሎች የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች ተቆርቋሪ የነበሩት ግለሰብ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አበል አገሮች ዘንድ ታማኝነትና ተሰሚነት (Credibility) እንዲያገኙ አድርገው ስማቸውን አጠፉት። እንዲሁም በገንዘብ አበከኝንት፣ በአስተዳደር በዳይነትና፣ በሰሽሊስትነት ወነጀሏቸው። በዚህም ተጽዕኖ የተነሳ አህማዱ መህታር እምባው ለ14ዓመታት ያህል የገነቡትን ድርጅት የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ አቅርበው መሰናበት ገዱታቸው ሆነ።

እንደ አህማዱ ማህታር እምባው አፍሪቃ በምዕራብ ማሠራጫዎች የሚሰጣት የዜና ሽፋን (Coverage) የአህጉሪቱን ትክክለኛ ሁኔታ የማያንፀባርቅ መሆኑ ያበሰጫቸው ሮበርት ፖልመር የተባሉ እንግሊዛዊው የአፍሪቃ ወዳጅ የጋዜጣኝነት ሙያ ምሁር የሚከተለውን ትዝብት የተሞሰበት አስተያየታቸውን ይሰነዝራሉ።

> በአውሮፖና በለሜን አሜሪካ አህጉሮች ታሳለቅ የፖለቲክ መሪዎች ከቢታቸው በወጡና በጣቡ ቁጥር የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ደጅአፈቸው ለይ ተከልኩለው ይጠብቷቸዋል። እነዚህ ጋዜጠኞች ከዓመት ዓመት የፖለቲክ መሪዎቹ የተነፈሱትን ሳይቀር ይቀርፃሉ። ይህንን ሁኔታ ኪቪን ሀሚልተን የተባለው የተለቪዥን ጋዜጠኛ ፍጹም ልዩ ከሆነው የአፍሪቃ ሁኔታ ጋር ያነፃጽረዋል። በሀሚልተን አባባል ከአፍሪቃ መሪዎች የምንሰማው እንዳች ነገር የለም። ስለአፍሪቃም ታሪክ (ሆነ የአሁኑ ይዘታ) የምንሰማው ዘግቦ የውድቀት፣ የድሽቀት፣ የረሀብ ወይም የእንግሊዝ ነገስታት ጉብኝት ለይ ያተኮረ ነው። ምዕራባዊ የዜና ማሰራጫዎች የቀድሞዋ ሮዴሽያ የዘራ ዚምባብዌነቷን ስትቀዳጅ (የነጭና ጥቁር ዘር) እልቂትና የደም መፋሰስ ተንብየው ነበር። (ይህንኑ እልቂት ለመቅረጽ ከጅለው) የጠቁት ትንቢት እልይዝ ሲሳቸው የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ከተታቸውን ቀረቃቅበው የዚምባብዌን ምድር ለቀው ወጡ። እነሆ ዛሬ እገሪቱ ነፃነቷን ከተቀዳጀች ጀምሮ ሰላደረገችው የልማት እንቅስቃሴ ከምዕራባውያን ቴሌቪዥኖች የቀረበ አንዳች ነገር የለም።(20)

እኒሁ ታዋቂ የጆርናሊዝም ሙያ ምሁርና ደራሲ በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ የዜና ማሰራጫዎች እንዴት አድርገው ሕዝባቸውን ከማደናቆር አልፎ ወደ ዓለም አቀፋዊ መሐይምነት ደረጃ እንደወረዷቸው ሲያትቱ እንዲህ ይላሉ፤

> «የምዕራብ ቴሌቪዥኖች አፍሪቃን በሚመለከት (ከደቡባዊት አፍሪቃ በስተቀር) የሚያደርጉት የዜና ሽፋን ከ1960ዎቹ ወዲህ እጂግ በጣም እየቀነሰ ሄዷል። የምዕራቡ ዓለም የዜና ሪፖርተሮች ኢዲ አሚን የፈፀሙትን እልቂት፣እራሳቸውን ንጉሥ ብለው በሰየሙት በካሳ በዓለ-ንግስ፣ በሮዴሽያ የርስ በርስ ጦርነት፣ እንዲሁም በአፍሪቃ ቀንድ የረሀብን ሁኔታ ለመመልከት በብዛት ወደ አፍሪቃ ተልከው ነበር። ይሁን እንጂ በቴሌቪዥኖቻችን መስኮቶች የሚመጣልን የአፍሪቃ ትዕይንት ትንግርታዊው (Spectacular) የያፉ (Bizarre) እና ከምር አስደንጋጭ የሆነው ነው። ይህ እቀራረብ ደግሞ አፍሪቃንና አፍሪቃውያንን ዝቅ አድርጎ የመመልከት የምዕራብ ዓለም በሽታን(Stereotypes)ጭራሽ ያባብሰል። እኛ(እንግሊዛውያን) ተከታታይ የሆኑ፣ የአፍሪቃን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚመለከት (Series) የአፍሪቃውያንን የእለት ከእለት ኑሮ የሚቃኝ የቴሌቪዥን

አቀራረብ እናገኝም። በዚህም የተነሳ የቢ ቢ ሲን አለም አቀፍ ከሚከታተሉት እንግሊዛዊ አድማሮች በስተቀር አልፎ አልፎ ስለአፍሪቃ በቴሌቪዥን የሚቀርቡ ለየት ያሉ (ልብ የሚነኩና አሰዛኝ) ዜናዎች ሲያዩ ሁኔታውን ከአህጉሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚያነፃጽሩበት አፍሪቃ ነክ አውቀት የለቸውም። ዛሬ በዜና ማሰራጫዎች ኃይል በጣም የተጠጋጋችው ዓለም አቀፋዊ መንደራችን (World) ውስጥ ዜናዎችን ከእንግሊዝ ቴሌቪዥን ብቻ የሚዘግነው የእንግሊዝ ሕዝብ ያለው ዓለም አቀፋዊ ጠቅሰሳ እውቀት በአፍሪቃ የመንደር ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚያስተምረውና የቢ ቢ ሲን አለም አቀፍ አገልግሎት ከሚያደምጠው የገጠር መምህር ያነሰ ነው። ይህ ደግሞ ታሰቅ እንቶቅልሽ (irony) ነው።(21)»

እሪ ለመሆኑ ትሰልቅ ዓለም አቀፍ የዜና ማሰራጫዎችን ልናምናቸው እንችላለን? ተብሎ ለሚጠየቅ-ጥያቄ መልሰችን «በጭራሽ እንችልም» ነው። በእረግጥ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ በዜና ማሰራጫዎች ታማኝነት ያለው ዜና ለማቅረብ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ጥበብ ውጤቶች እንደሰተለይት ግንኙነት ዓይነት ለዓይን ለማመን በሚያዳግት ደረጃ ለይ ደርሰዋል። ይሁንና በአቅራቢዎቹና በዜና አዘጋጂዎቹ የግልና የቡድን እንዲሁም በዜና ማሠራጫዎች በለቤቶችና በመንግስቶቻቸው የማይረከ የፖለቲከና የኢከኖሚ ጥም የተነሳ ፍጹም ከግል ጥቅም ፍላጎት ነፃ የሆነ ዜና በዘራዋ ዓለም አገኛለሁ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው ትርፉ። ይህንን አሰመልክተው በአሜሪከ የፔንሲልቭኒያ ስቴት ሴኔተር የሆኑት አቶ ሬቻርድ ኤ ስናይደር በፔንሲልቭንያ ስብሰባውን ሰከሄደው የኸርሺይ ሮታሪ ክበብ በደረጉት ንግግር ቀኝ መንገደኛ (right wing) አሜሪከኖች እንኳ ከፍተኛ የዜና ማሰራጫዎችን አምነው እንደይቀበሉ አሰስበዋል።(22) እኒሁ ግለሰብ የቴሌቪዥንን ኃይል (power) በሚመለከት በምሰሌ ደግፈው ለአድማጮቻቸው ያቀረቡት ታሪክ በጭሩ እንዲህ የሚል ነበር። ከጥቂት ዓመታት በፊት ታዋቂው አሜሪከዊ ሚሊዮኔር ሄልሰን ሮከፌለር ለኒው ዮርክ ስቴት ገዥነት ደግመው ለመመረጥ ይፈልጋሉ። ለዚሁ ጉዳይ ብለው በኒው ዮርክ አውራ ጎዳናዎች እየተዘዋወሩ ሕዝቡ እንዲመርጣቸው አለፊ አግዳሚውን እየጨበጡ በመግጠን ሰይ እንዳሉ ሁኔታውን ለአሜሪከ ሕዝብ ለማቅረብ ታዋቂው ጋዜጠኛ ደቪድ ብሪንከሊይ ፈልገው ኖሮ ከሰቸው ባሸገር ቆመው ያስተውሰሉ። በዚህን ጊዜ ተሰሰፊው ሕዝብ ለገዥነቱ በታ ምረጡኝ የሚሉትን የኒው ዮርክ ገዥውን ሮከፌለርን ትቶ ጋዜጠኛውን ደቪድ ብሪንከሊይን እንደከበባቸው ይነገራል። ሴኔተር ሪቻርድ ስናይደር እንደሚሉት ደቪድ ብሪንከሊይ እንዲያ ለእለፊ እግዳሚው ሕዝብ ብርቅ ሆነው የታዩበት ምከንያት ሲገልጡ እንዲህ ብለዋል። ጋዜጠኛው በየምሽቱ በቴሌቪዥኑ መስከት እማከኝነት ወደእያንዳንዱ አሜሪከን ቤት ስለሚገቡና ታዋቂነትን ስለተረፉ ነው። ይህ የሴናተሩ ምሰሌ የሚያመለክተን

በቴሌቪዥን ተደጋግሞ የሚታይ ነገር በቀለሉ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ምን ያህል ሊያገኝ እንደሚችል ነው። እንግዲህ በዚህ መሰል ኃይለኛ መሰሪያ አማካኝነት በጠላትነት የተሞላ (hostile) አልፎ አልፎም ሐሰትና ስህተት የተደበለቀበት ዜና የሚነገርለት ኢትዮጵያ ምስል (image) በምዕራብ አንባቢ፣ ተመልካችና አድማጭ አእምሮ ውስጥ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም። የሴነተሩ ነቀፋ "ከኮንሰርቫቲቭ" አቂማቸው የመነጨ ቢሆንም የሚያሰየን እንድ እውነት አለ። ይኸውም ዘመናዊ የዜና ማሰራጫ ዎች እቀራረባቸው ወደፈለጉበት አቅጣጫ በመቆለመም የኃያላኑ መንግሥታት ጥቅም ማስከበሪያ ዋነኛ መሣሪያ መሆናቸውን ነው። እዚህ ልንገነዘበው የሚገባ አንድ ቁም ነገር አለ። ይኸውም የአሜሪካ ጋዜጠኞች ስለተወለዱበትና ስለአደጉበት ሕብረተሰብ በሚያቀርቡት የተሰሳተ ዜና አንዳንድ አሜሪካኖችን ስሜት ነክተው የሚያስቆጡ ከሆነ እኛማ እፍሪቃውያንን እስት በእስት በምእዕራብ ዜና ማሰራጫ ድርጂቶች ስለሚደርስብን ውርጂብኝ ምን እናውራ! በተለይም እናት እገራችን «ኮሚዩኒስት ነችና» በእፍ ጢሟ ትደፋ ብለው ከግልብ(Shallow) እውቀታቸው በመነጨ የጎሪጥ እስተያየት የሚገሪምሟት ብቻ ሳይሆኑ ባልተወለደ እንጀታቸው በጭካኔ ብእር ሲያንገላቷት ምን ስሜት ይሰማን? በብእሩ ጦርነት እንዳንገጥማቸው ስለ ኢትዮጵያ ቀና የሚናገር ነገርን ሁሉ "ጆሮ ዳባ ልበስ" ብለው አያዳምጡም። እንደውነቱ ከሆነ ስንቶቻችን በምዕራቡ ዓለም ከተሞች የምንገኝ ሐበሾች ነን እልፎ እልፎ በመኖሪያ ቤታችን ከሚኖረው የቴሌቪዥን ሰጥን ጋር (ሰው የሆነ ይመስል) «እሪ ጉድ ነው ይኸ ልክ አደለም!» እያልን ስንሟገት የምናመሸው?!

በጠቃላይ የምዕራብ ዓለም ጋዜጠኞች አፍሪቃን በተለይም ኢትዮጵያን በሚመለከት (ከግራም ከቀኝ እንፃር ቢጽፉ) «በሰው ቁስል እንጨት ሰደድበት» እንደተባለው ዓይነት የኢትዮጵያችንን እኩሪና ገናና ታሪክ ሁሉ በደርግ ሳይ ባሳቸው ቂም በቀል ብቻ ተነሳስተው የውብ እገራችንን መልክ በጭንቀትና በረሀብ፣ በሀዘንና በመከራ ቀለሞች በተነከረ እራፊ ሸፍነው « አስቀያሚነቷን » እጉልተው ለማሳየት ሲጥሩ በብስጭት እየበገንን «ተው ቻለው ሆዴ!» እያልን ወደየእለት «ሽቀላችን» እንሰማራለን። እንዲሁም በታሪክ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቂንቂ በፍጹም የማንለያየውን ሐበሻ ሕዝቦች በገጠመን እሰዘኝ ጊዚያዊ የወንድማማቾች ፀብ ሰቢያ ጣልቃ እየገቡ ኃይለኛ የሆነውን የብዕር መሣሪያ በመጠቀም ይበልጥ እንድንለያይና በመከከላችን የዘወትር ጥላቻ እንዲሰፍን ሲያደርጉ እናየዋለን። ይሁን እንጂ ይህ ድርጊታቸው ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን አፍሪቃውያንና ድፍን ጥቁር ሕዝቦችን ለማጥቃት የተነሰነሰ መርዝ መሆኑን የምንገነዘብበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ አለን። እኒህ የምዕራብ ጋዜጦች የአፍሪቃን ሕዝብ ታሪክ በማጥ ጭቃ ውስጥ ደለው ቢረመርሙም ይህ ድርጊታቸው እንደእሰት የሚያንገበግባቸው ሀቀኛ ልጆቿ ታሪኪን መልሰው ንጹህ ለማድረግ እስከ ዛሬ ያጠፉትን ጊዜ ያህል

እንደማይወሰዱም አንጠራጠርም። በተለይም እናት ኢትዮጵያችንን በሚመለከት በእገር ቤትም ሆነ በሰደት ላይ ያለነው ልጆቿ የሚሰማንን የሰሜት አንድነት አበው ባወረሱን አፍአዊ (oral literature) እንጉርጉሮ እየታገዝን እንደምንተባበር ያለንን ምኞት በመግለጥ ሐተታችንን እዚህ ላይ እንደመድማለን።

«...አገራችን ታማ ተኝታ በልጋ ላይ ፣
ወዴት እንሄዳለን ሞት ሽረቷን ሰናይ ! ?...»

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Encyclopedia Britannica, 1983, P . 1006
2. Rodney, Walter, How Europe Underdeveloped Africa, 1976, P. 265.
3. Gitlin, T. The Whole World's Watching. Berkeley; University of California Press, 1980.
4. Gans, H. Deciding What's New. New York: Vintage Books, 1980 ; Tuchman, G . Making News. New York; Free Press, 1978.

5. በርከታ የአሜሪካን አንባቢዎች ይህንን ጋዜጣ በሊበራልነት ይመድቡታል ። እኛ ግን የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚተነትነው መልኩና በፀረ-ኢትዮጵያ ባህርዩ በወግ-አጥባቂነት ለዚህ ሐተታ መድበነዋል።
6. በዚህ ርእሰ ስር ግራ-ዘመም (left - leaning) የሆኑ የሠራተኛ ማህበር የሶሻሊስት ፖርቲዎች የኮሚኒስት ፖርቲዎችናእንዲሁም በገል የተቋቋሙ «ራዲካል» ቡድኖች ጋዜጣዎችና መጽሔቶች ሊከተቱ ይቻላል።
7. እዚህ ላይ የጋዜጠኝነትና የሥነጽሑፍ ሙያ እንግዲ ለሚሆንባቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንድ ነገር በቅድሚያ ማዝከር እንወደለን። ይኸውም በጋዜጠኝነት ሙያ የእንድ ጽሑፍ ርዕሱ የሥነጽሑፍ እምብርት መባሉንና ቃላቱም ለማጥቃትም ሆነ ለመደገፍ ታቅደው በከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚመረጡ ነው። በተጨማሪም እንባቢዎች ሁሉ በጋዜጣ ላይ የተፃፈውን እንብበው ለመጨረስ ጊዜ ስለሚያጥራቸው የርእሱ አመራረጥ ጊዜ ለሌለው እንባቢ በቂ የሆነ ፍንጭ ስለነገሩ እንዲሰጥ ሆኖ ይታቀዳል። እዚህ ላይ እርእሰቱ ደራሲው ሊጽፍበት የቃጣው ዋነኛ ሐሳብ መነሻ ነው ብሎ መደንገጉም ሰይጠቅም አይቀርም። አንዳንድ ጊዜ የእርእሰቱ ይዘት የደራሲውን እቂምና የጽሑፉን አቅጣጫ ይጠቁመናል። ዜናው ሥዕል ሲጨመርበት ደግሞ ነገሩን ይበልጥ ያጠናክረዋል። ከ10 ሺህ ቃላት ድርሰት አንድ ሥዕል ማውጣት የአንባቢውንም ሆነ የደራሲውን ጊዜ ከመቆጠቡም በላይ ነገሩን 10 ሺህ ጊዜ ያጎላዋል።
8. ለትምህርት ወደ ሶቪየት ሕብረትም ሆነ ወደ ምዕራብ አውሮፖ የሚላኩ አፍሪቃውያን ወጣቶች ተመሰሰይ የሆነ የዘር መድልዎ እንደሚደርሰባቸው The New African እየተባለ የሚጠራ መጽሔት አራት ገጽ ሐተታ በApril 1988 እትም አውጥቷል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በሶቪየት ሕብረት በመማር ላይ የሚገኙ አፍሪቃውያንን አስተያየት በመጥቀስ ደራሲው ለማመን የሚያዳግቱ ታሪክች ሁሉ ይነግሩናል። ጽሑፉ እንደሚለው «የሶቪየት ሕብረት ሥርዓተ ትምህርት የአፍሪቃን ፍለጎት ለማሟላት ታቅዶ የተዋቀረ በለመሆኑ ከብድ ውጥንቅር ይፈጥራል።» በሶቪየት ሕብረት ስላለው (ከምዕራብ አውሮፖና ከአሜሪካ ያልተለየ ዘረኝነት ሲተነትኑ ቀጥሎ የተመለከትነውን የመሰለ መሪር እንጋገር ከወጣት አፍሪቃውያን ይጠቅሳሉ። « በመጀመሪያ [እኛን አፍሪቃውያንን] ዝንጀሮዎች እሉን' አለ እንዲ ተማሪ። ' እሁን ደግሞ ኢይድስ [ናችሁ] ይሉናል። በመጀመሪያ ወደ ሶቪየት ሕብረት እንደመጣሁ እንዲህ ያለው ዘለፋ ስሚቲን በጋይል ስለሚጎደው በጣም እናደድ ነበር። እሁን ግን ነገሩን ለምጀው [ብዙም አልበሳጭም።] (ለዚህ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት The New African የApril 1988 እትም ከገጽ 24-27 ይመልከቱ)
9. አቶ ሌሪ ብራውን (Larry Brown) የተባሉ የሀርቫርድ ዮንቨርሲቲ የሕዝብ ጤና ፕበቃ ፕሮፌሰር በፃሬዚደንት ሮናልድ ሬገን ዘመን የታየው የአሜሪካ ኢኮኖሚያዊ እድገት « 20 ሚሊዮን ለሚሆኑ አሜሪካውያን ረሀብተኞች» ምንም ፋይደ እንደልሰጠ በሰጡት

መግለጫ ነው። በዚሁ መግለጫቸው ፕሮፌሰር ሌሪ እንደጎድ ቢተሰቦች «በቀን ከእንድ ምግብ የበለጠ እንደማይበሉና» እንደጎደቹም « በእንድ ምግብ ብቻ ለጥቂት ቀናት እንደሚቶዩ እመልከተው የዚህም ጦሰ ምንጭ እልር እልር «ሬገኖሚክስ» እየተባለ የሚጠራው ሰለው ይበልጥ የሚሰጠው የፕሬዚደንት ሮናልድ ሬገን የኢኮኖሚ አስተሰሰብ ነው ይላሉ። (ስዚህ "20 Million Americans Hungry Task Force Blames Reaganomics" The Toronto Star) October 27, 1987, P. A 3 ይመልከቱ)። ታዲያ «ዘረኝነትና ችግር የለብንም በሚሉ ከናዳውያን ዘንድም በቶሮንቶ ከተማ ብቻ ከ 60,000 ያለነሱ ረሀብተኞችና በርከታ በረንዳ አደሪዎች መኖራቸው እልር እልር በዚያው ከተማ ከሚኖሩ ግለሰቦችና ከልዩ ልዩ ዘገባዎች መረዳት ይቻላል።

10. በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያሰፈልግዎ ከሆነ የተሰፈጽዮን መድኅኔን መጽሐፍ Eritrea: Dynamics of a National Question (1986) ይመልከቱ። የኢ ኤል ኤፍ ድርጅትም ዘራ እንደቀድሞው ሰሸሊሰት እለመሆኑንና በማርከሲዝም የማያምን መሆኑን በራሱ የህቡዕ ሬዲዮ ጣቢያ በሰጠው መግለጫ ያብራራል። በዚህ ሐተታ ውሰጥም በቅርቡ የእሜሪካው ፕሬዚደንት ሮናልድ ሬገን የሰሸት ጎብረትን መሪ አቶ ሚኸኤል ጉርባቾብን ሞስኮ ሲያናግሩ እንዴ እጀንዳቸው የኤርትራ ጉዳይ መሆኑ እንደታሰቅ ድል ጠቅሰታል። በእኛ የግል አሰተያየት ግን ኃያላን መንግሥታት የችግሩ አክል እንጂ የመፍትሔ መሰጫው ወገን ባለመሆናቸው የነሱ በእኛ ጉዳይ ላይ መነጋገር እንደታሰቅ ድል ሆኖ መታየት የለበትም። በታሪክም የምንረዳው የእውሮፖ ኃያላን መንግሥታትና ኩሎኒያሊሰቶች የእፍሪቃን ችግር እመንጭዎች እንጂ ፈቺዎች ሆነው ያገኘንበት ምዕራፍ የለም። ለእፍሪቃ ችግር መፍትሔ ሰጪዎቹ እኛው እፍሪቃውያን ስለሆንን ለሕዝቦቻችን ሰላማዊ ሕይወት የምንመሰርትበት ሁኔታ ላይ በማትኮር ፊታችንን ከጦርነት ወደ ሰላም ብንመልስ ይሸል ይመስለናል።

መረጃውን ለማግኘት «Rebel Radio Notes Superpower's Role in Eritrea» የተሰኘው ጽሑፍ በ Daily News Report Sub- Saharan Africa(FBIS-AFR-88-092) በተለይ በገጽ 2 እንቀጽ 2 ከመስመር ስድስት ጀምሮ ይመልከቱ።

11. ይህንን ጥቅስ ከ The Toronto Star በMarch 24, 1988 በገጽ A 26 ላይ ወስደን የተረጎምነው ነው።

12. The Guardian April 6, 1988, p. 10.

13. ሌላው በሰሜን እሜሪከ ዘ ሰን (The Sun) ተብለው ከሚታወቁ ጋዜጦች ውሰጥ አንዱ ቶሮንቶ በሚባለው የከናዳ ከፍተኛ ከተማ የሚታተመው ነው። ይህ (The Toronto Sun) ጋዜጣ በብዙ የከናዳ ነዋሪዎች ጥቁሮችና በሌሎችም ነጭ ያልሆኑ ማህበረሰቦች ሁሉ ከሦስተኛው ዓለም ወደ ከናዳ ለሚመጡ ጥቁሮችና ሌሎች ነጭ ያልሆኑ ወገኖች «እሚገራንቶች» ሁሉ በጎ አስተያየት የሌለው «ዘረኛ» ጋዜጣ ነው እየተባለ ይነገርለታል። ይህ ከእንግሊዝ አገሩ ታብሎይድ The Sun ጋር በእየነፍና በወግ-አጥባቂ አቋሙ የሚወዳደረው ጋዜጣ የረጅም ጊዜ አዘጋጅ የነበሩት ግለሰብ አቶ ፒተር ወርቲንግተን (Peter Worthington) ስደተኛ የሚታወቁ ወደ ከናዳ ነጭ ያልሆነ (በተለይ አፍሪከዊ ጥቁር) እሚገራንት እንደይመጣ ከሚከለከሉ የቀኝ አክራሪ (ለምሳሌ በእሜሪከ እንደ አርያን ሬስ (Aryan race) ነን የሚሉ ዓይነቶች) ቡድኖች ጋር በመተባበር ለመሥራታቸው ሌሎች ፀሐፊዎችና ጋዜጣዎች የመሰከሩባቸው ግለሰብ ናቸው። እኒሁ ፒተር ወርቲንግተን የተባሉ ለጥቁር ዘር ሁሉ ንቀት ጥለቻና ፋሽስታዊ አመለካከት ያሳቸው ግለሰብ ጋዜጠኛ ለመሆናቸው ዋነኛው ምስክሩ በመላው ዓለም የተጠላውን የደቡብ አፍሪቃ (Apartheid) አገዛዝ መንግሥት የበለይነት ለማስጠበቅ ከሚታገሉ የሰሜን እሜሪከ ዘረኛ ድርጅቶች ጋር እብሮ በመሥራት እስተዋጽየ ማድረጋቸው ነው። የጥቂት

ነጮች አገዛዝ (Apartheid) በሃያ አራት ሚሊዮን ደቡብ አፍሪቃውያን ወንድሞቻችን ጫንቃ ላይ ለዘለዓለም እንደተጫነ እንዲኖር በሰሜን አሜሪካ የሚታገሉት አቶ ፒተር ወርቲንግተን የደቡብ አፍሪቃ ወንድሞቻችንን የነፃነት እንቅስቃሴ እንደ ተራ የሽብር እንቅስቃሴ ለማስመሰል ርእሱ "The A.N.C. Method: Violence" የተሰኘ የ25 ደቂቃ የፕሮፖጋንዳ ቪዲዮ የደቡብ አፍሪቃው ነጭ ፕሬዚዳንት የፒ ደብሊው ቦታ ቀኝ እጅ በመሆን ባለፈው ዓመት እውጥተው በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ። የፒተር ወርቲንግተን ፀረ የደቡብ አፍሪቃ ጥቁር ሕዝብ ትግል ቪዲዮ በሰሜን አሜሪካ ከእጽናፍ እስከ እጽናፍ በሚገኝ ፀረ አፓርታይድ ከሚቲዎችና ግለሰቦች ታውቶለቸዋል። ለፒተር ወርቲንግተን የአፍሪቃና ለመላው የጥቁር ሕዝብ ጠላትነት ከዚህ የተሻለ ቀዋሚ ምስክር ሊገኝ አይችልም።

የፒተር ወርቲንግተን ፀረ ጥቁር ሕዝብ ቪድዮ ከ70 ዓመታት በላይ የነጮችን የበላይነትና ቅኝ ገዥነት አልቀበልም ብሎ የተነሳውን አፍሪካን ናሽናል ኮንግሬስ (A.N.C) ብሔራዊ የእርነት ንቅናቄ እንደወንጀለኞች ቡድን አድርገን ያቀርበዋል። በፒተር ወርቲንግተን የቪዲዮ አቀራረብ በደቡብ አፍሪቃ ዘራ ያው ፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ያሉት ጥቂት ነጮች ሳይሆኑ ኤ ኤን ሲ (A.N.C) የተባለው የነፃ አውጭ ድርጅት ነው። ፒተር ወርቲንግተን የነጭ ውሸት ቁልቁለ ነፊ ጋዜጠኛ ለመሆናቸው ከዚህ የተሻለ ማስረጃ ከቶ ከየት ይገኛል። አቀራረባቸው ውስጥ ስንገባ እጅግ «እማተረሽ» በሆነው የቪዲዮ ፊልም ጥበባቸው በመመራት ታዋቂውንና መለ እድሜአቸውን ለደቡብ አፍሪቃ ጥቁሮች ነፃ መውጣት መሰዋዕት ያደረጉትን የአንጋፋውን መሪ የኔልሰን ማንዴላን ባልንጀራና የትግል ጓድ አቶ አሊሸር ታምቦን በምዕራብ ዓለም የዜና ማሠራጫዎች እንዲጠሉ ከተፈረደባቸው ከሊቢያው መሪ ምአመር ጋደፊና ከፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅት መሪ ከያሲር አረፋት ጋር ያቀርቧቸዋል። በፒተር ወርቲንግተን ቤት የፐሬዚዳንት አሊሸር ታምቦ ምስል ከነዚህ ከምዕራቡ ዓለም «እጅግ ከተመሉ » ሰዎች ጋር በረጋ- ሠራሽ ጥበባቸው ተቀምጮ ቀረበና አሊሸር ታምቦ ሊጠሉ ነው። ለእንድ የምእራብ አገር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅነት የበቃ ሰው እHከዚህ ድረስ በዘር ጥላቻ የተጨማለቀ ተራ ድርጊት የሚሰራ ሆኖ ሲገኝ ሰንቶች የምዕራብ ጋዜጠኞች ከዚህ ነፃ ናቸው ብሎ የመገረም ጥያቄ ማንሰት የብልሀ እንባቢ የዘወትር ተግባሩ ነው።

ይህ የፒተር ወርቲንግተን አፓርታይድ ደጋፊና የደቡብ አፍሪቃንና የመላው ጥቁርን ሕዝብ የሚያናንቀው ቪዲዮ እሁንም በሰሜን አሜሪካ C-FAR (Citizens For Foerign Aid Reform) በሚባል በከናዳ በታወቀው ድርጅት እማኝነት በመሰራጨት ላይ ይገኛል። ይህ ድርጅት እንደሰሙ ለሦስተኛው ዓለም የተሸለ እርዳታ ለማስገኘት የሚታገል ይመስላል። ዓለማው ግን በሦስተኛው ዓለም እርዳታ መሰጠት ያለበት ቀኝ አከራሪ የፖለቲካ ፍልስፍና የሚከተሉ መንግሥታት በተቷቷመበት አከባቢ ብቻ እንዲሆንና እንዲሁም እንደኢትዮጵያ፣ እንጎላና ሞዛምቢክ ያሉ አገሮች ከምዕራቡ ዓለም ሰብዓዊ እርዳታ ጭምር እንዳያገኙ በምዕራብ መንግሥታት ዘንድ ቅስቀሳ (Lobby) ማድረግ ነው። የዚሁ የC-FAR ሊሰው ዋነኛ ተግባር በከናዳም ሆነ በሰሜን አሜሪክ ነጭ ያልሆኑ (Non-white) የሦስተኛው ዓለም ሕዘቦች (ከእፍሪቃ፣ ከእስያ፣ ከላቲን አሜሪክ) የኢሚግራትነት (የስደተኝነት) እድል እንዳያገኙ መከላከልና ጨርሶ እንዲነፈጋቸው መታገል ነው። ይህ ድርጅት ታዲያ በመሰው አሜሪክ ፀእፀያፊ ዘረኛ ተግባራቸው ከታወቁት «ኩ ክለክስ ክላን» ጋር በተገበር የሚመሰሰል ከናዳዊ (ሰሜን አሜሪክዊ) ድርጅት አይደለምን? በዚህ የግርጌ ማስታወሽ ላይ ስለቀረበው ሐተታ ተጨማሪ መረጃ ከሰፈለገው ቀጥሎ የምንጠቅሰውን ጽሑፍ ይመልከቱ። "Helping to wage propaganda war for south africa." The Toronto Star, May 18, 1988, P.A26.

እነሆ በጥቁር ሕዝብ ጥላቻቸውና በአፓርታይድ ሥርዓት ደጋፊነታቸው የታወቁት ፒተር ወርቲንግተን (Peter Worthington) እኛ አፍሪቃውያን ማንነታቸውን ደህና አድርገን የማናውቀው ይመስል ፤ እኒሁ በከናዳና በአሜሪካ የሚኖሩ ጥቁርና ጠይም ሕዝቦች እንደጭራቅ ለሚፈሩዋቸው ዘረኛ ድርጅቶች ተገቢራዊ አገልግሎት ለሚሰጡ ጋዜጠኛ በእፍሪቃ ቀንድ በኩል ለሚገኘው ችግር የወንድማማቾችን አሰዛኝ መተላለቅ ለማስቆም ሳይሆን ለምዕራቡ ዓለም የርዕዮተ-ዓለምና የፖለቲካ መሪገጫ መሬት የቶሬቶሩ መስሏቸው የኢትዮጵያን ችግር እንደሸቸው በማደከር ጽፈዋል። ዘር ዘር ለመላው ጥቁር ሕዝብ ደንታ የሌላቸውና ጥላቻ ያላቸው መሆኑን ከከናዳው ድርጊታቸውና ደቡብ አፍሪቃን ከሚመለከተው ሺዲዮአቸው እንረዳለንና በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት የሞከሩት በዚያ ለሚኖሩት ጥቁር ሕዝቦች ልዩ የርህራሄ ልበና በቀደ ጥገና ገብቶላቸው ሳይሆን በኤርትራ ችግር በረሀብ ሁኔታ እስታከው ያለቸውን የከረረ ፀረ-ሰሽሊስት ጥላቻ በኢትዮጵያ ላይ ለማውረድ ብለው ነው። በአየፈፋቸው ይዘትም የፀረ ኮሙኒስት ውቃቢአቸው ነግሮአቸው የየፋት ጉዳይ ከልሆነ በስተቀር እውነትም ለአፍሪቃ ቀንድ ጥቁር ሕዝብ የሚያዝኑ ከሆነ ኤርትራን ብቻ ሳይሆን ለምን ሌሳውን የኢትዮጵያን ክፍል እንዲሁም ሶማሊያን ጭምር ጎብኝተው አይጽፉም ነበር? የኤርትራ ጉብኝታቸው ለአቂማቸውና ለርዕዮተ ዓለም ትግሳቸው የተቃጣ እንጅ ለእውነተኛ (objective) ጋዜጠኝነት አለመሆኑ በጽሑፋቸው አማከኝነት ደስታቸውን እንዲህ በማለት ያበስሩልናል። «ዘሬ ከበሬቱ ይበልጥ በኢፒ ኤል ኤፍ ዘንድ ማርክሲዊ ባህሪይ አለየሁም።» (ለዚህ ጽሑፍ ማረጋገጫ The Toronto Sun,April 25, 1988, p. 36 ይመልከቱ። በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፈ ያለ ትንታኔ ለማግኘት በተስፈጽጮን መድነኔ Tesfatsion Medhanie ደራሲነት የተጻፈውን Eritea: Dynamics of a National Question የተሰኘውን መጽሐፍ ያገላብጡ።

ጋዜጠኛ ፒተር ወርቲንግተን በኢፒ ኤል ኤፍ ቁጥጥር ስር ያለውን የኤርትራን ክፍልና ሱዳንን ጎብኝተው በእየለቱ ከአንድ እስከ ሁለት ሙሉ የጋዜጣ ገጸች በመጠቀም በተከታታይ (series) ለእምቡት ቀኖች ከአፕሪል 24 ቀን 1988 እስከ አፕሪል 28 ቀን, 1988 ጽፈዋል። የጽሑፋቸው የመጨረሻው ክፍል (ማለት April 28, 1988) በክሎኔል መንግሥቱ ጋይለማሪያም ላይ መፈንቅለ መንግሥት እንደሚካሄድ ብቻ ሳይሆን እንዲከሄድ ተማጽኖአል። በእኛ በጽሐፈዎች አስተያየት እንኪን አንድ ክሎኔል አሰር ክሎኔል መንግሥቱን ቢፈነቅሉ ማን ቅር ይለዋል። ኢትዮጵያን ግን ልታፈርሷት አትችሉም ነው እኛ የምንለው።ለኤርትራ ችግር የክሎኔል መንግሥቱ መፈንቀል መፍትሔ አይሆንም እንጂ ከሆነማ እሰየው ያርግሳችሁ እንላለን። የእኛ ምኞት ኢትዮጵያ በዲሞክራሲያዊ አመራር የተገነባ መንግሥት ተፈጥሮ ልጆቿ በሰላምና በደስታ እንዲኖሩ ነው። ፒተር ወርቲንግተን ግን ለክሎኔል መንግሥቱ ጋይለማሪያም መፈንቅለ እገዛዝ (ብሎም ሞት) በተመኙበት እንደበታቸው ለደቡብ አፍሪቃ የነጮች ጠቂኝ (አፓርታይድ) መሪ ለፒ ደብሊው ቦታ እገዛዝ ለዘለለም ዕድሜ የሚመኝበት ሺዲዮ መቅረፃቸው አስገራሚ ብቻ ሳይሆን ደከግ ዘረኛ ሰው መሆናቸውን አጋለጡ። ጥቁር ይጠላሉና ለኤርትራ ህዝብ እቶረቶራለሁ ቢሉ ማን ያምናቸዋል!!

14. "Ethiopia:Famine Menace Returns" The Guardian. April 6, 1988, ገጽ 10ና 11 ይመልከቱ
15. እንደላይኛው።
16. ይህ ጥቅስ የተወሰደውና የተተረጎመው ከ Socialist Worker No.133, February 1988, p. 1 ላይ ነው።
17. ለተጨማሪ ማብራሪያ «Ethiopian Journey» የተባለውን ጽሑፍ ከ The Canadian Tribune, March 21, 1988, Page 6. ይመልከቱ።

18. Peregrine Worsthorn, "What Journalism is ከ Time & Tide, Winter 1988, P. 60 ይመልከቱ።
19. እንደላይኛው።
20. ለዚህ ማስረጃ Robin Palmer የፃፉትን "Africa in the Media" የተባለው ጽሑፍ ከAfrican Affairs ቅጽ 86 ቁጥር 343 የኤፕሪል 1987 እትም በገጽ 246 የመልከቱ።
21. እንደላይኛው ገጽ 247
22. Richard A. Snyder, "Can We Trust the big media is our news free of bias?" in vital speeches of the day, vol. 58, No 6, January 1, 1985, p. 171
23. ከዚህ አነጋገር የምንማረው ጉዳይ ማንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚጽፍ ጋዜጠኛ ቢያንስ ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪቃ ሕዝቦች ባህል፣ አኗኗር፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና አፍሪቃን ዛሬ የራጥን አሥር የያዘት ድህነት ዋነኛ ምንጩ ምን እንደሆነ ከነመፍትሔው ጥምር የሚያሰውቃቸው የታሪክ፣ የሰስዮሎጂ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ እውቀት እንደሚያስፈልጋቸው ነው። በምዕራብ ባህልና አመለካከት (Value) ያደገ ግለሰብ «ጋዜጠኛ» ስለተባለ ብቻ የአፍሪቃን ትክክለኛ ማንነትና ገጽታ ያቀርባል ብሎ መጠበቅ «ሰማይ በደሮ ሲታረስ ለማየት እንደመጠበቅ» ያለ ከንቱ ምኞት ነው። ለማያከብሩት ሕዝብየተከበረ ድርሰት ያቀረቡ ደራሲዎች እስከሁን አለጋጠመንምና!

ሰላም በኤርትራ

ከደስተር ያዕቆብ ሀይለማርያም

(1) መግቢያ

በንኩል እስተዳደር ከተፈጥሮ ሁኔታዎች መበላሸት ጋር በመተባበር ዘራ አገራችን የጦርነት ማሰ፣ የጠ ፍ ዋሽ አድርጎአት ከዓለም ሕብረተ ሰብ በብልጽግናና በ ኑሮ ደረጃ የመጨረሻውን ደረጃ ይዛ ትገኛለች። በራስዋ ተማምና በተራራዎችዋ ተከልላ፤ በጀግኖችዋ ተጠብቃ፤ መብቷንና ጥቅሟን እስጠብቃ ያልኖረችውን ያህል ዘራ ኢትዮጵያ በምንና በምን የዓለም መድረክችና ሸንጎዎች እንደምትገኝና፤ እንዲሁም በዓለም ሕብረተ ሰብ ዝናና እድናቆት ባተረፈችበት በኦሊምፒክ ውድድሮች ትሰተፍ እትሰተፍ ወሰኝዋ በአለፈው ሰቭየት ሕብረት ስትሆን ዛሬ ደግሞ ሰሜን ኮርያ ሆናለች። እንደዛሬ እያድርገውና ጣሊያኖች በማጭበርበር በ1889[1] ዓም የተፈረመው የውጫሌን ውል ለውጠው «ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነትዋ በኢጣሊያ በኩል ታከናውናለች» የሚል እንቀጽ በመጨመራቸው የአገራቸው ልዕልናና ክብራቸውን ለማስጠበቅና ለማስከበር የትናንት በስቲያ ኢትዮጵያውያን በ1896 ዓም ጦርነት አንስተው በዘመናዊ ትጥቅ የተሰለፈውን የጣልያ ጦር ድባቅ በመምታት ከአኒባል ወዲህ ለመላው የጥቁር ዘርና ለነፃነታቸው ታጋዮች ሁሉ መመኪያ የሆነ አንድ ትልቅ ገድል በታሪክ ማስመዝገባቸው ስንገነዘብ ስለዘራዎቹ መሪዎች «የነብር ጭንጋፍ አነር» ያሉትን የአበቶችን ተረት ያስታውሰናል።

ገበናችንን ለበዕድ ሰንገልጥ፤ በወዳጆቻችን ተከብረን፤ በጠላቶቻችን ታፍረን፤ ድህነታችንን ችለን ያልኖርነውን ያህል ዘራ እንጀታቸውን ከአጥንታቸው ጋር ተጣብቆ መለውን ዓለም ያስለቀሱ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ለረሃብ ቂሚ ምልክት ሆነው በቴሌቪዥንና በሬድዮ የበለጌ መሰለቂያ አድማጩን ማሰቂያ ሆነዋል።

አገራችን ለምትገኝበት ለእነዚህና ለሌሎችም ብዙ አሰቃቂ ሁኔታዎችና ብሔራዊ ውርደቶች ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም፤ የብሔሮች ውዝግቦችና የእርስ በርስ ጦርነቶች በተለይም በኤርትራ የሚካሄደው ከእንጋፋዎቹ ምክንያቶች አንዱ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ስለኤርትራ ችግር ያለኝን አስተያየትና ለችግሩ የሚመስለኝም መፍትሔ በጽሑፍ ለቀርብ ያሰብኝ በኤርትራውያን ሊቃውንትም ሆነ በሌሎችም ያልተዘከረ ልዩ ሃሳብ እቀርበለሁ በዬ ሰይሆን፤ የኤርትራ ጉዳይ በመፈራራት፤ በመከባበር፤ የእንዱን ወገን ስሜት እጎዳለሁ በማለት ሃሳባቸውን ያልሰነዘሩ ስለኤርትራ ችግር መፍትሔ ቅን ሃሳብ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ለግልጽ ውይይት፤ ለክርክር፤ ብሎም መፍትሔ መስጥ

የሚታያቸውን ሃሰብ በግልጽና በለማመንታት እንዲሰነዝሩ ለመጋበዝ ነው። ስለብሔሮች ጉዳይ፣ ስለኤርትራ፣ ወይንም በጠቅላላው ስለኢትዮጵያ የግዘት እንድነትም ሆነ መነጣጠል መጻፍ ወይንም መደገፍ ወይንም መንቀፍ «ጠበብ ብሔርተኛ፣ «ትምክህተኛ» ወይንም «ጎበና» የሚል ስም የሚያሰጥ ቢሆንም ይህንን ከንቱ ትችት በመፍራት ሃሰብን ማመቅ አይገበም። እንዳንድ እራሳቸው ምንም ሳያበረክቱ መንቀፍ ብቻ የሚቀናቸው አፍራሽች እንዲህ ዓይነቱ ውይይት የሰደተኞች «ምን ልሥራ» ባይነት ነው ብለው ይቆጥሩት ይሆናል። ከአሜሪካ ሆኖ ስለኤርትራ ችግር መወያየት በመሠረቱ የተሟላ ሊሆን ባይቻልም እንድ ሃሰብ ከየትም ይመንጭ ከየትም ተፈጻሚነት የሚኖረው በብዙዎቹ ድጋፍ ሲኖረው እንደመሆኑ መጠን የኤርትራም ግምባሮች መሪዎች የኢትዮጵያውያን ስሜትና አስተያየት በየጊዜው እንደሚለኩትና እንደሚያደምጡ ስለማያጠራጥር የሚቀርበው ሃሰብና ትችት ቀጥተኛና የተባ ውጤት ሊኖረው ይችላል።

እንዲሁም ዛሬ በፈርስና በኢራቅ፣ በምዕራብ ሰሐራና በሞሮኮ፣ በእን ጉሳና በዘሪኛዋ ደቡብ አፍሪቃ፣ በአፍጋኒስታን መንግሥትና ሙጃ ሽዲን፣ በሰንዲ ኒስታና በኩንትራዎች፣ በሰሜንና በደቡብ ኮርያ፣ በሱዳን መንግሥትና በሱዳን ነፃ አውጪ ድርጅት፣ ወዘተ የቆዩ ውዘግቦች በሰላም ለመፍታት የሰላም ጭለንጭል በታየበት በዘሬው ወቅት፣ እንዲሁም በአገራችን ቀጥተኛና የተባ ውጤትና ተጽእኖ በሚኖረው ሰቭየት ሕብረት «በግላሰኖስት» አማካኝነት ለመሠረታዊ ለውጥ አሰፍሰፉ በምትገኝበት በዘሬው ጊዜ የአገራችን ዋነኛ ጭንቀት እንስቶ መወያየት ወቅታዊ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ከ27 ዓመታት እልቂት በኋላ ጦርነቱ ምንም ውጤት አለማምጣቱ የተገነዘቡ ኢትዮጵያውያን፣ እንዲሁም ቀደም ሲል በመርሆ ደረጃ እንኳን የኤርትራን ነፃነት ይደግፉ የነበሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ ግምባሮች መሪዎች ጋር በነበራቸው የሻከረ ግንኙነት ምክንያት ዛሬ አቋማቸውን ቀይረው የኤርትራ ነፃነት በመርሆ ደረጃ እንኳን ስለሚቃወሙ የዚህ ውይይት አስፈላጊነቱ ጉልህ ያደርገዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ የበሰለና የሞቀ ክርክርና ትችት ማከሄዱ ለሁለቱም ወገኖች ጠቃሚነቱ ግልጽ ነው።

ከዛሬ 18 ዓመታት በፊት ጀምሮ እስከዛሬ የቀኝ አክራሪዎች «እንድነት ወይንም ሞት» [2] ወይንም የግራ ተስፈንጣሪዎች «ማንኛውም የብሔር ውዝግብ በመገንጠል ይፈታል» በማለት ለ18 ዓመታት የተመላለስንባቸው እርጌ ጎዳናዎችን ትተን በ27 ዓመታት ጦርነት ተመክሮ ላይ የተመረኮዘ ውይይት ብናካሄድ የበለጠ ጠቃሚ እንደሚሆን ግልጽ ነው። የብሔሮች ጥያቄ ውይይት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲነሳ [3] የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ያልተመረኮዘ፣ በአንድ ፎርሙላ ላይ ብቻ የተወሰነ ስለነበረ ውጤት አላመጣም፣ ውይይቱም አልተስፋፋም። እንዲሁም የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕብረትና እንድነት ለሁለቱም ብልጽግናና እድገት የሚበጅ፣ የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር

መቶየት የሁለቱም ሕልውና ጥያቄ መሆኑን፤ የኤርትራ መገንጠል የኢትዮጵያን አንገት እንደመቁረጥ ይሆናል የሚሉ ከርከሮች በሌሊ ወቅቶች በሌሎች ስለተብራሩ እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊ አይደለም።

በእገሪቱ ያለው የብሔሮች ችግር በኤርትራ ብቻ ነው፤ ሌሎች ብሔች የሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች ፍሬ ቢስ ናቸው ለማለት ሳይሆን ይህ ጽሑፍ በኤርትራ ላይ ብቻ ያተኮረው የሌሎቹን ጥያቄዎች ሌላ ጊዜ እንመለስባቸዋለን በማለት ነው።

2. የኢትዮጵያና የኤርትራ ታሪካዊ ግንኙነት

ኤርትራ የኢትዮጵያ እንድ አከልና አይነተኛዋ ክፍል ነበረች አልነበረችም በሚለው ላይ ብዙ ክርክር ተደርጎበታል። በሪኽት ሃብተ ሥላሴ (1980 49) ከ300 ዓ.ም አከባቢ ጀምሮ አብዛኛው የኤርትራ ከፍል ምዕራብ ኤርትራም ጭምር እንዲሁም መሳው ትግራይ የአከሱም መንግሥት ግዛት እምብርት እንደነበሩና፤ ይህም ግዛት በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ተዳክሞ እንደተንከታከተ ጽፈዋል። በዶክተር በሪኽት እሰበል ግን የዘሬይቱ ኢትዮጵያ ከጥንታዊት አክሱም ተከታትሎ የወረደች ሰትሆን በ19ኛው መቶ ዓመት የተገነቧች በውስጥዋ ብዙ ቅኝ ግዛቶችን አምቃ የያዘች አገር ናት። [4] ሆኖም ግን በጉዳዩ ገለልተኝነት ያሳቸው የታሪክ ሊቃውንት ዘሬ ሐማሴን፤ አክለ ጉዛይ፤ ሠራዬ፤ ወዘተ በመባል የታወቁት የኤርትራ ከፍሎች የአከሱም ግዛት አከሎች መሆናቸውን ገልጸው የዘሬይቱ ኢትዮጵያ በተለይ የሰሜኑ ከፍል ደግሞ ቀጥተኛ የጥንቷ የአከሱም ተዋራጅ እንደሆነች ያረጋግጣሉ።

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-1468) የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በነበሩበት ወቅት ደህሳክ፤ ምጽዋና የጠረፍ ግዛቶቻቸው «ምድረ ባህሪ» ወይንም «ባህረ ነጋሽ» ብለው ይጠሩ እንደነበረ ታሪክ ጸሐፊዎች ያረጋግጣሉ። እንደዚሁም የኢጣልያ አገር ጎብኖች በ1482 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ጊዜ ደህሳክ ደሴትና ምጽዋ የኢትዮጵያ አከሎት እንደነበሩ ጽፈዋል። ዝነኛው የፖርቱጋል አገር ኻብኝና ጸሐፊ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ በ1520 ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ምጽዋ ደሴትና አከባቢዋ «ምድር ባህሪ» በመባል ይታወቅ የነበረ የኢትዮጵያ አንዱ ከፍል እንደነበረ በማረጋገጥ ጽፎአል። (Alvarez 1881:3), (Crawford 1958:43)

በ1557 ዓ.ም ቱርኮች ምጽዋን ይዘው ለተወሰኑ ጊዜያት ከአስተዳደሩ በኋላ የማዕከላዊው መንግሥት ሥልጣን ተዳክሞ አገሪቱ በመሳፍንት አስተዳደር በተከፋፈለችበት በዘመነ መሳፍንት ኤርትራና ትግራይ ራሳቸውን የቻሉ አስተዳደር ሆነው ቆይተዋል። የአውሮፖ ኢምፔርያሊዝም የአፍሪካን አገሮች በከሎኒነት ለመቀራመት በወሰነው መሠረት «ምድረ ባህሪም» በጣልያኖች እጅ ወድቃ በጣልያ ንጉሣዊ ድንጋጌ መሠረት በ1890 ዓ.ም ስሟ ወደ «ኤርትራ»

ተለወጠ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ታሪካዊ እውነታዎች ታመኑም አልታመኑም፣ እውነትም ይሁኑ ውሸት፣ ታሪካዊ ሐቆችም ይሁኑ ፕሮፖጋንዳ እንድ የማያጠራጥር ሁሉም የሚያውቀው ሐቅ አለ። ይኸውም ፖለቲካው ወደ ጎን የተተወ እንደሆነ፤ በተለያዩ ወቅትም ይሁን ያለ ማቋረጥ፣ በከፊልም ይሁን በሙሉ፣ ኤርትራ የጥንታዊት ኢትዮጵያ አካል ከመሆንዋም አልፎ የሰሜኑ ኢትዮጵያ እምብርትና የሥልጣኔዋ ምንጭ የታሪክዋ ግንድና መሠረት እንደነበረች አሌ ማለት አይቻልም። በምንም ጎሣ ስም እንታወቅ በምንም፤ ከሰማችን ስር ብዙዎቻችን ኤርትራውያን ነን ብንል ሐቅ ነው።

3 ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ነች?

ኢትዮጵያ በውስጧ ቅኝ ግዛቶችን አምቃ ይዛ እነዚህ ቅኝ ግዛቶችን ትበዘብዝለች በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰ የሰነዘሪች ሰማሊያ ነች። (Major Asseged 1984:4)። የኤርትራ ጥያቄ ግን ለብዙ ዘመን የብሔር ጥያቄ ሆኖ ከቆየ በኋላ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች የሚለው ከርከር ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ የተነሳ እንጂ ትግሉ ከተጀመረበት ጊዜ እንስቶ ተዋጊዎቹ የተሰለፉበት ዓላማ አይደለም። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችና ተራማጅ ግለሰቦች ኤርትራ የራስዋን እድል በራስዋ እንድትወስን ሲደግፉ ለዚህም ዓላማ መስዋትነትን ከፍለዋል። በ1976 ዓ.ም የኤርትራ ሕዝባዊ ነፃ አውጪ ግምባር ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ያሳንደች ውይይትና ምርምር የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው፤ ኤርትራም እንደማንኛውም ቅኝ ግዛት ነፃ መውጣት አለበት በማለት መፈክሩን በቀየረበት ጊዜ በኢትዮጵያ የኤርትራ የራስን እድል በራስ መወሰን ደጋፊዎች የሚጠብጡትን አጥተው በኤርትራ ግንባሮችና በኢትዮጵያውያን ደጋፊዎቻቸው መሃከል ከፍተኛ ውዥንብር ተፈጠረ። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት (ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ) የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲን (ኢሕአፓ) ከትግራይ ከፍል ሐገር ለማስወጣት በአሲምባ በከፈተው ጦርነት ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍን ሪድቶአል የሚለው ጥርጣሬ ምንጩ ኢሕአፓ የኤርትራ ቅኝ ግዛትነት እልቀበልም በማለቱ ነው የሚል ከሰ ኢሕአፓ ደጋግሞ አቅርቦአል። ቲ.ፒ.ኤ.ኤፍ ግን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት መሆንዋን ማመኑ ከኢ.ፒ.ኤ.ኤፍ ጋር በ16/8/80 ዓ.ም በተፈራረመው የጋራ መግለጫ እረጋግጦአል። በዚህም መሠረት ቲ.ፒ.ኤ.ኤፍ «ኤርትራ ሕዝብ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል» የሚደግፍ መሆኑን ሲያረጋግጥ የቲዎሪም ሆነ የገቢር ችግር የገጠመው አይመስልም። (የህ.ግ.ሐ.ኤና. የሕ.ወ.ሐ.ት የጋራ መግለጫ 1980: 2)። ኤርትራ በውን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ከሆነች በቋንቋ፣ በባህል፣ በ ኑሮ ዘይቤና በጠቅላላው በአስተሳሰብ ከኤርትራ ጋር የምትመሳሰለው የትግራይ ክፍለ ሐገር እንዴት የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት

እንዳልነበረች ግልጽ አይደለም።

ኢትዮጵያ ቀኝ ገዢ አገር ናት ኤርትራንም በቀኝ ገዢነት ይዛለች ሲባል፣ ደንበሩዋን አቋርጣ የሌሎችን ባዕዳን ሕዝቦች ሃብት ለመበዝበዝ ስትል እነዚህኑ ባዕዳን ሕዝቦች በቁጥጥሩዋ ስል እውነ ከመሃከል አገሩ ሕዝብ በተለየ የጭቆናና የብዝበዛ ሕግ ታስተዳድራለች ማለት ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ ቀኝ ግዛት ነች ሲባል በኬንያ፣ በኡጋንዳ፣ በታንዛንያ፣ ወዘተ እንደነበረው በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በኑሮ ዘይቤና በእስተሳሰብ ፍጹም የማይመሳሰሉ በህር አቋርጠው ከመጡ እንግሊዘች እስተዳደር ጋር ይመሳሰላል ማለት ነው። እንግሊዘችም ሆነ ፈረንሳዮች በቀኝ ግዛቶቻቸው እንዳደረጉት ኢትዮጵያ የኤርትራን ሃብት ለመበዝበዝ ኤርትራውያንን ከለሙ መሬታቸው ነቅለው ኢትዮጵያውያን ሰፍረውበት ሕዝቡን በበታችነት በመቁጠር ይገዛሉ ማለት ነው። ፊውዳል ኢትዮጵያ በመጠኑም ቢሆን የካፒታሊዝም ጭሰንጭል ያቆጠቆጠች የነበረችውን ኤርትራን በቀኝ ግዛትነት ይዛለች ሲባል፣ ቀኝ ገዢዎችና ተገዢዎች ከሚገኙበት የኤከኖሚና የሰሻል ደረጃ ጋር አይጣጣምም። ኢ.ፒ.ኤ.ኤፍ የኢጣሊያ፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ቀኝ ገዢዎች ከፒታሊስቶች መሆናቸውን ገልጾ የቀኝ ገዢዎቹ መሠረተ ዒላማ በአገራቸው የሚገኘው ከፒታል መውጪያና መስፋፊያ መፈለግ ስለነበረበት ኋላ ቀርና ከፊል ፊውዳል የሆኑትን አገሮች በመግዛት መበዝበዛቸውን ገልጾአል (EPLF Memorandum August 1978) ኢትዮጵያ እራስዋ ትናንት በአሜሪከን ኢምፔርያሊዝም ዛሬ ደግሞ በሶሻል ኢምፔርያሊዝም የእጅ እዙር ቀኝ አገዛዝ እግር ተወርች የተጠፈረች አገር ስትሆን፣ እንዴት ቀኝ ገዢ እንደምትሆን ግር ይሰል። በኢ.ፒ.ኤ.ኤፍ መሪዎች አባባል ግን ኢትዮጵያ የካፒታሊስትነት ሥርዓት ማህበር የሚጠይቃቸው ሁኔታዎችን ስለምታሟላና በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ነባራዊ ሁኔታዎች የተገላቢጦሽ ስለሆነባቸው ኢትዮጵያ ቀኝ ገዢነትዋ በአሜሪከን እርዳታ መሆኑንና በአሜሪከ መኪል ነት መሆኑን ገልጾዋል። ዛሬ በአሜሪከን እግር ሰቭየት ሕብረት የተተካች ቢሆንም ኢትዮጵያ ኤርትራን በቀኝ ግዛትነት የያዘችው በሰቭየት ሕብረት ተጠሪነት ነው የሚል በአሜሪከ ሳይ የሰነዘሩት ክስ ግን በሰቭየት ሕብረት ሳይ አልሰነዘሩም። (Ogbagzi 1988:645) ሰቭየት ሕብረት ወታደራዊ ዊውን መንግስት በመደገፍ የምትጫወተውን ሚና ከቀን ስህተት የመነጨ መሆኑን ኢ.ፒ.ኤ.ኤፍ፣ ደጋግሞ አሰስበአል።

እንግዲህ በጭሩ የኤርትራ ግምባሮች ዋናው ከርክር ኤርትራ በታሪክም ይሁን በባህል፣ በቋንቋ፣ በኑሮ ዘይቤ፣ ወዘተ ከኢትዮጵያ ፍጹም የሚያገናኛት ነገር ስለሌለና ሌላም አገር ስለሆነች ከኢትዮጵያ ነፃ ወጥታ የራስዋን መንግሥት መሥርታ በፈለገችው ሥርዓት መተዳደር መቻል እለበት የሚል ነው።

ኤርትራና ኢትዮጵያ ከሳይ ከአጭሩ እንደተጠቀሰው የታሪክ ግንኙነት የማያጠራጥር ሲሆን በባህልና በኑሮ ዘይቤ በእስተሳሰብ ወዘተ የተመሳሰሉ

ሁኔታም ስለማያከራክር እነዚህን ግልጽ ሁኔታዎችን ወደ ጎን ትተን በእሁኑ ወቅት የዓለም ሕብረተሰብም ሆነ የዓለም ሕግ ኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አድርጎ ይመለከት እንደሆነ ማየቱ ለውይይቱ ተጨማሪ ነጥብ ይሆናል። የዓለም ሕግ ከብዙ ልውውጦች በኋላ ስለአገሮች ልዕልና (ሰቨሬንቲ) ዘራ የደረሰበት ነጥብ እንድ ሕብረተሰብ ልዕልናውም አገርነቱ የሚወሰነው በሌሎች የዓለም መንግሥታትና ሕብረተሰብ ልዕልዊነቱ ወይንም አገርነቱ ሲታወቅ እንጂ በውስጡ ያለውን ሕዝብ በቋንቋ በባህል በጎሣ መመሰሰሉ አይደለም የሚል ነው።

በዚህም መሠረት በአንድ ነፃ አገር ውስጥ በጎሣና በቋንቋ በባህል ወዘተ መለያየት ምክንያት በብሔሮች የሚነሱ ውዝግቦች የቅኝ ግዛት ጥያቄ አድርጎ ከለማየቱም ሌላ እንደሀ ዓይነቱን ጥያቄ መደገፍ በአንድ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንደመግባት በመቁጠር ያወግዘዋል። ስለዚህ ነው የኤርትራ ጥያቄ በተባበሩት የዓለም መንግስታትም ሆነ በገለልተኛ አገሮች ጉባዔ በሌሎችም ዓለም አቀፍ መድረክች ይሁን (ከአረብ ሊግ ሌላ) በግል ሃገሮች (ከጥቂቶች በስተቀር) ቀጥተኛና ግልጽ ድጋፍ ሊያገኝ ያልቻለው። በተጨማሪም ከእነዚህም የዓለም ሕግ ውስጥ በክይሮ በ1964 ዓ.ም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ በአባላት መሃከል በጊዜው የነበረው የግዛት ክልልና በቅኝ ገዢዎች የተከለሉ ወሰኖች የማይጣሱና የማይለወጡ መሆኑን ደንግገ። ስለዚህ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ማለት በቲዎሪ፤ በታሪክ እንዲሁም በዓለም ሕብረተሰብ ፊት ሐቀኛና በግቢር ሊተረጎም የሚችል መፈከር አይደለም።

4) የኤርትራ መለየት።

ኤርትራ እጅግ ቢያንስ ለ60 ዓመታት ከኢትዮጵያ ተለይታ በልዩ ልዩ ባዕዳን እጅ ገብታ መኖርዋ ከሌሎች የኢትዮጵያ ከፍሎች ልዩ ጠባይ ስለሰጣት የኤርትራ ጥያቄም ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች ጥያቄ ተለይቶ መታየትና ለችግሩም የተለየ መፍትሔ መሻት ያስፈልጋል። በዚህ እረገድ መዘንጋት የሌለበት ኤርትራ በ1952 ዓ.ም በፈደራሽን ከኢትዮጵያ ጋር በተቀላቀለችበት ጊዜ የራስዋ ሰንደቅ ዓለማ፤ የራስዋ ሕግ አውጪ ከፍል፤ የራስዋ ሕግ አስፈጻሚ የመንግሥት ዘርፎች፤ እንዲያውም ከመሃሉ አገር ከነበረው የለቀና የደረጀ በዲሞክራቲክ ሕገ መንግሥት ላይ የተመሠረተ አስተዳደር ነበራት። በኤርትራ ውስጥ ለተከሄደውና ለሚከሄደው አልቂትና ፍጅት ከመንስኤው ጀምሮ እስከ ዛሬ ላለበት አስከፊ ሁኔታ ተጠያቂዎቹ፤ ለምን ዓለም በዋስትና የደነገገልን ፈደራሽን ያለፈቃዳችን ፈረሰ፤ ለምን ዳብሮ የነበረው ዲሞክራቲክ አስተዳደራችን ተደመሰሰ፤ ለምን ቋንቋችንና በህላችን ተናቀ በማለት ለዚህ ሃቀኛ መብታቸው የሚታገሉትን የኤርትራ ተዋጊዎችን አይደለም። ለ27 ዓመታት በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ መኖር፤ መራብ፤ መጠማት፤ መታረዝ ዘወትር በሞት ጥላ ስር መኖር ቅንጦት ነው የሚል የለም። ከኤርትራ ተዋጊዎች

እንደንደቹ በትምህርት ቤት አብሮ አደጎቻችንና ወዳጆቻችን የነበሩና እንደማናችንም በመኪና መንፈላሰስ፣ በለሰለሰ አልጋ ላይ መተኛትና በቅንጦት መዋር በልገደዳቸውም ነበር። ሆኖም ግን የግል ቅንጦትና ድሎት ለመብታቸው በመሰዋት ለእመ ኑበት ጉዳይና ዓላማ እንዲህ በቁርጠኝነት በመታገላቸው ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የኩራት ምንጭ ሉሆ ኑ ይገባል። ለዚህ ሁሉ እልቂት ጥፋተኞችስ ይልቅ በፈውዳል ኩራትና ትምክህተኝነት የተወጠሩ እነራስ እንደርጋቸው መሣይን እነጂ ኔራል አብይን በሹመት ቂጥጥ እድርጎ የኢርትራ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርና ባህል የገዘገዘው ፈውዳሉ መንግሥትና ከሰላም ድርድር ይልቅ ጣቶቹን ወደ ብረት ቃታ የሚያስቀድመው የዛሬው ወታደራዊው መንግሥት ናቸው። እንደውነቱማ ከሆነ ትናትናም ሆነ ዛሬ ከኢርትራውያን በጎ ፈቃድ አልጠፉም ነበር። ኢትዮጵያ በተለያዩ ጠላቶች በግብጽች፣ በቱርክች፣ በጣልያኖች ወዘተ በተወረረችበት ወቅት አብዛኛው በሰሜ ኑ በኩል ስለሆነ የጦርነቶቹን ገፈት በመጀመሪያ ቀማሽች ሆነው ኖሬዋል። በ1952 ዓም የቀድሞው የጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የወደፊት እድል በተባበሩት መንግሥታት በሚወሰንበት ጊዜ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ (Medhane 1988:2) ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ኣለመቀላቀል ፈቃደኝነቱን ገልጸአል።[5] በታሪክ የተመዘገቡት የነአብርሃም ደቡጭና ሞገስ አስገደም ገድል፣ የእነጸሐፊ ትዕዛዝ ሎሬንዝ ውስታዎችን ትተን በዛሬው ትውልድ የኤርትራ ችግር በሰላም እንዲፈታ የታገሉት እነጂ ኔራል አማን እንደም፣ ተማሪውንና ሠራተኛውን ከኃይለሥላሴ ፈውደ ቡርኜዋ መንግሥት ጋር የረጅም ጊዜ ትንቅንቅ በተያያዘበት ወቅት ከተማሪ ጎን በመሰለፍ መሪነቱን በማበርከት ለአብዮቱ መጠንሰስ መረንዲትና መቀጣጠል አስተዋጽአ ያደረጉት እነጎሩይ ተድሳን፣ እነአማ ኑኤልን፣ እነኢሳያስ አፈወርቂን፣ እነበረኸት ሃብተሥላሴን ለናሙና ያህል መጥቀስ ይቻላል።[6]

እንዲሁም ኤርትራውያን መብታቸውን ለማስከበር ያላቸው ቁርጠኝነት የሚደነቅና የሚከበር ቢሆንም፣ ከ27 ዓመታት ጦርነት በኋላ ግን ሐቀኛና በሥራ ላይ ሊውል የሚችል የሕዝቦችንም ጥቅም የሚያስጠብቅ መፍትሔ መሻትና መቀበል ይኖርበቸውል።

5) ለሰላም ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች።

ዛሬ የኤርትራ ጥያቄ በቅኝ ግዛትነት ስም ይታወቅ በብሔር በመሠረቱ የፖለቲከ መሆ ኑንና ችግሩም በዘለቂነት ሊፈታ የሚቻለው በፖለቲከ ድርድር እንጂ በጦር ኃይል እንዳልሆነ ሰአሁ ኑ ወቅት በእድለቢነት ሰይሆን ሁኔታውን በቅን በገለልተኝነት ለተመራመረ ሁሉ ግልጽ እየሆነ መጥቶአል። 27 ዓመታት በእሰት የተፈተ ኑ በሙሉ ቁርጠኝነት የሚዋጉና ለምን እንደሚዋጉም አጣርተው የሚያውቁ የኤርትራ ግንባሮች በጦር ሜዳ ተሸንፈው ይበተናሉ ማለት ዘበት

ነው። በአንጻሩም ከ40 ሚልዮን ሕዝብ በላይ የሚያስተዳድር መንግሥት፣ ራሱ መንግሥቱ ተወዳጅ ባይሆንም በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ዓለማ ይዟ፣ በእንድ ኃያል መንግሥትና በተከታዮቹ ያልተወሰነ የጦርና የዲፕሎማቲክ ድጋፍ እያገኘ የሚዋጋ መንግሥት አንዳንደች እንደሚሉት (Berhe June 1988:7) ይሸነፈል ማለትም ዘበት ነው። ውዝግቡ በሰላም እስከአለቀ ድረስ ከሎኔል መንግሥቱ በእንድ ሕዝበ ትርዕይት ላይ እንዳሉት ጦርነቱ ለብዙ ትውልድ ይቀጥላል። ስለዚህ ውዝግቡ በሰላምና በድርድር መጪ ረስ እማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። ለ13 ዓመታት ግራ እጅ እያነሱ እናሸንፈለን ማለት ድልን አያጎናጽፍም። እንድሁም በኢትዮጵያ ሕዝቢዊ ዲሞክራሲ ተመሥርቶአል፣ ሥልጣን ለበለቤቱ ለሰፊው ሕዝብ ተመለሰ ብሎ እራስን መደለል (ሕዝብ እልተደለለም) ለችግሮቹ መፍትሔ አይሰጥም [7]። በአንጻሩም ደግሞ አሜሪካ ሆኖ «የኤርትራ ተዋጊዎችም አይዘአችሁ ታሸንፋለችሁ ጦርነቱን ቀጥሉ» እያሉ እሰቱን ማራገብ የአገሪቱን ችግር አይፈታም። የኤርትራን ወጣትም የእሰት እራት ከመሆን አያድነውም። እንዲሁም በኤርትራኖች በኩል ከመኢሰን ጋር ትርጉም የለሽ የወደጅነት ውል መፈራረም ወይንም ከቲ ፒ ኤል ኤፍ ጋር የጋራ መግለጫ መፈረም የሕዝቡን ችግር ያበብሰዋል እንጂ ዛሬ አገሪቱ ለለችበት ከፍተኛ ችግር መፍትሄ አይሆንም፤ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ችግር አቅልሎ ማየትም ያስመስላል።

ይልቁንስ የአዲስ አበባ መንግሥት መሪዎች አገሪቱ ያለችበትን ከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግር በጥሞና በሃቅ መርምረው ትክክለኛውን መፍትሔ መሸት ይኖርበቸውል። ዛሬ በሥልጣን ያሉ ግለሰቦች እጅግ ቢበዛ ከ50 ዓመታት በኋላ እንደሌሉ ተገንዝበው፤ አገር ግን ዘላለማዊ፤ ዕድሜዋ በዓመታት የማይለካ መሆኑን ተረድተው፤ የእርስ በርስ ጦርነቶች እንዲቆሙ፣ በሕዝቦች መሃከል እርቅ እንዲወርድ፣ ሕዝቡ ከሃገሩ ከመሸሽ ይልቅ እናት አገሩን አቅፎና ደግፎ እንዲኖር፣ የለሸቀው ኢኮኖሚ እንዲያንሰራራ፣ ሕዝቡ ወደ ተመረጠበት ተግባር እንዲመለስ እማራጭ የሌለው መፍትሔ በኪሎ ኔል መንግሥቱ የሚመራው መንግሥት ከሰልጣን ገለል ብሎ ሥልጣን ለበለቤቱ ለሰፊው ሕዝብ በውን ማስረከብ ነው። ቅን አገር ወዳድ ወታደሮች በተለያዩ ወቅት በናጁርያ፣ በጋና በላቲን አሜሪካና በእስያ ሥልጣን በበጎ ፈቃደኝነት ለበለቤቱ ለሰፊው ሕዝብ ያስረከቡ ሲሆን የሃገር ፍቅር በልበናቸው ከለ ለኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግሥት በለሥልጣኖችም በተለይ የሚከብድበት ምክንያት የለም።

ይህ መሆን ያለበት የኤርትራም ሆነ የሌሎች ብሔሮች ችግር መፍቻው ቁልፍ በኢትዮጵያ በሕዝብ ነፃ ምርጫ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ስለሆነ ነው። የኤርትራ ግምበሮችም ሆነ ሌሎች ከእዲስ አበባው ወታደራዊው መንግሥት ጋር ድርድር ለመጋበት ምን ጊዜም ፈቃደኛ መሆናቸው የሚያጠራጥር ነው። ወታደራዊው መንግሥት ከኤርትራ ሕዝብም ሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ደም ከመቃባቱም ሌላ ፈዙን ወዲያ ትቶ በሕዝብ ምርጫ የተመሠረተ በለመሆኑ ኤርትራውያንም ሆነ ሌሎች ከማን ጋር ድርድር

ይግቡ የሚለው ጥያቄ ያነሳል። ነገ ሌሊ መንግሥት መጥቶ ድርድሩን ቢሽርስ? ወይንም ይህን ኑ መንግሥቱ ተጠሪነቱ ለሕዝብ ሰላልሆነና፣ ድርጊቱን የሚነቅፉና የሚያጋልጡ ፓርቲዎች ስለሌሉ ሰምምነት ከተደረሰ በኋላ ተነስቶ ሰምምነቱን ቢያፈርስስ? እዜ ጋይለ ሥላሴ የዓለም መንግሥታት ውሳኔ 390 በመጣስ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ተመሥርቶ የነበረው ፌዴራሽን 1962 ዓ.ም ሲያፈርሱ ተጠሪነታቸው ለሕዝብ ባለመሆኑ እንዲሁም በኢትዮጵያ ትንጣት የዲሞክራሲ ጭለንጭል ባለመኖሩ ይህንን ሕገ ወጥ ድርጊት የሚቃወም አልተገኘም። ከአገራችንም አልፎ እንዲሁም በደቡብ ሱዳን እናንያ የነፃነት ታጋዮችና በእምበገነኑ በሱዳኑ ወታደራዊ ገዥ ጀፋር ኤል ኒሜሪ መሃከል ከ17 ዓመታት ጦርነት በኋላ በ1972 ዓ.ም ተደርጎ የነበረው ድርድር ኑሜሪ እፍርሰት አገሪቱን እንደገና የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ዘፈቃት። የኤርትራ ግንባሮች ከእዲስ አበባው መንግሥት ጋር ቢደራደሩ ሁለቱም በውሳቸው ጸንተው እንዲኖሩ ለሌሎች መንግሥታት በተለይም ለሃያላኑ መንግሥታት ዋስትና ሊሰጡ ይችላሉ የሚል ከርከር ሊኖር ይችል ይሆናል። ዘሬ ዓለም ሁለት ኃያላን መንግሥታት በተቀራመቷት ጊዜ ከተዋዋዮቹ አንዱ ቢከፋው ከአንደኛው ኃያል መንግሥት ጉያ ሊገባ ስለሚችል የውጭ መንግሥታት የሚሰጡት ዋስትና ዋጋ ቢስ ነው። ውል ጣሹ መንግሥት እጅግ ቢበዛ ሊደርስበት የሚችለው ከኤኮኖሚ ማቀብ ሊያልፍ አይችልም። ስለዚህ «እድበስብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» ነውና በአንተም ተው፣ በአንተም ተው ግልግል የኤርትራ ግንባሮች ከእዲስ አበባው መንግሥት ጋር ድርድር ገብተው ፍጥጫው ረገበ ጦርነቱ ለግዚውም ቢቆም ዘላለማዊ ሰላም ተመሠረተ ማለት አይደለም። ስለዚህ የማይጣስና ዘላለማዊ ውል ተደራድሮ ሊገባ የሚችለው ከላይ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ የሚቋቋም ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ብቻ ነው።

የኤርትራ ግምባሮችም ሆኑ ሌሎች ግንንም ከግይወክለው ከእዲስ አበባው ወታደራዊ መንግሥት ጋር ድርድር ለመግበት ፈቃደኛ ባይሆኑ ሰላም ፈላጊዎች አይደሉም ብሎ መውቀስና ማውገዝ አይችልም። «በሬ ካራጁ ጋር ይውላል» እንዲሉ ኢሰያስ አፈወርቂና አህመድ ናስር ከደርግ አባሎች ጋር ዝግ ስብሰባ ለምን አልተቀመጡም የሚል ወቃሽ ከለ እነተፈሪ በንቲ በተገደሉ ማግስት ከሎኔል መንግሥቱ በገዘ ወንድሞቻቸውና ወገኖቻቸው ላይ ቀይ ሽብር ከተት በአወጁበት ወቅት በአደባባይ ለመለው የኢትዮጵያ ሕዝብ «ለቁርስ ሲያስቡን ለምሳ እደረሰናቸው» ያሉትን ማስታወስ ያሻዋል። ስለዚህ ለብሔሮች ችግር በተለይም በኤርትራ ያለው እልቂት ቶሞ ዘላቂ መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው የእዲስ አበባው ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን ለቅቆ በምትኩ እጁ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በኤርትራውያን ደም ያልነከረ በኤርትራኖች ሊታመን የሚችል ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ተቋቁሞ ሲገኝ ብቻ ነው።

ለዚህም የመጀመርያው እርምጃ በኢትዮጵያ ፖርቲዎች እንዲቋቋሙ መፍቀድ፣ ማበረታታትና መርዳት እንዲሁም በአሁኑም ወቅት ተቋቁመው

ያሉት ከሕቡዕነት ገሃድ ወጥተው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ሕጋዊ ማድረግ ነው። እነዚህ ፖርቲዎች ከተቋቋሙ በኋላ ከእነዚህ ፖርቲዎች ወይንም አብዛኛው የሕዝብ ድጋፍ ያለው ፖርቲ የተውጣጣ መንግሥት መቋቋም ይኖርበታል ማለት ነው። በእሁኑ ወቅት ሥልጣን በሞኖፖል የያዘው ብቸኛው ፖርቲ ኢሠፖም በአባላቱ ፈቃድና ፍላጎት የተቋቋመ እውነትም ተከታዮች ያሉት ፖርቲ ከሆነ ከሌሎች ለወደፊት ከሚቋቋሙት ወይንም ዛሬም ተቋቁመው ከሚገኙት ፖርቲዎች ጋር በመወዳደር ለሥልጣን ዴሞክራሲያዊ ሽግያ ከማድረግ የሚያግደው ነገር መኖር የለበትም። ዛሬ በሥልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦችም በዚሁ ፖርቲያቸው አማካይነት በሥልጣን ሊጋሩ ይችላሉ።

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ማንንም የማይወክል መንግሥት የኤርትራ ችግር መፍታት አለመቻሉ ግልጽ ሆኖአል። በተጨማሪም በጠቀሳሉው ለአገሪቱ የወጠነው ፕሮግራም ከሥራ ላይ ማዋል አቅቶት ይኸ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ወዲህ በብዙ እረገድ አገሪቱ ወደ ኋላ ሄደች እንጂ ወደ ፊት አልገፋችም። እዚህ ላይ እንግዲህ ትልቁ መሰናክል ይኸ መንግሥት እነዚህን ተሪድቶ በፈቃደኝነት ከሥልጣን ገለል ያለለ እንደሆነ ነው። ሆኖም ግን የኤርትራ ግንበሮችም ይሁኑ ሌሎች ለሰላም ድርድር ተቀዳሚ ሁኔታ ያሁኑ መንግሥት ከሥልጣን ገለል ብሎ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ማቋቋም መሆኑንና ከኢትዮጵያ ጋር በፈዴራሽን ለመኖር ፈቃደኛነታቸው ቢገልጹ በእሁኑ መንግሥት ላይ ወታደራዊ ግፊት ሊደርስበት ይችላል። በፈዴራሽን ለመኖር ሁለቱም ወገኖች በዴሞክራሲ አስተዳደር የተመሠረቱ መሆን አለባቸው። ያለ ዴሞክራሲ የፈዴራሽን አስተዳደር ሊኖር አይችልም። ፈዴራሽን በፈዴራል አስተዳደር የሚተዳደሩት ክፍሎችን እኩልነትና ነፃነትን ያመለክታል። ብዙ ጊዜ የሚዘነጋና መረሳት የሌለበት አንድ ጉዳይ በዚህ የውጭ ወይንም ባዕድ ጠላት በማይታይበት የወንድማማች ጦርነት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ማለቃቸውና ወታደሩም ከቤቱና ከንብረቱ ተፈንቅሎ በቀበሮ ጉድጓድ መኖር መሰልቸቱና መውጪያ መንገድ መፈለጉ ነው።

በእንጻሩ ደግሞ የኤርትራ ግንበሮች የኤርትራ ሕዝብ ሕጋዊ ተወካዮች መሆናቸውን በረጅም ትግል ያረጋገጡ ቢሆንም ከሁለቱ ድርጅቶች ተለይቶ መደራጀትና ፖርቲ ማቋቋም የሚፈልጉ ቢኖሩ መብታቸው መጠበቅ ይኖርበታል። በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ የፖርቲዎች መፈቀድ አስፈላጊነቱ በድርድሩ ወቅት እውነተኛዎቹ የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ተወካዮች ተገኝተው በሕዝቡ ፍላጎት የተመሠረተ ማንም በእሸው ጊዜ የማይሽረው ዘላቂነትና ተቀባይነት ያለው ሰምምነት እንዲደርሱ ነው።

በቅድሚያ ግን ሁለቱም ወገኖች በእርግጥም ለዚህ እልቂት ገደብ አበጅተውለት ወዝግቡን በሰላም ሊዉርሱ በውን የሚፈልጉ ከሆነ ያለ

ማመንታትና በድፍረት ሊቀበሉአቸው የሚገቡ ምንአልባትም የሚያሰደስቱ ሐቆች አሉ።

ኢትዮጵያውያን ኤርትራ፣ ጎሻም፣ አርሲ፣ ከፋ፣ ወይንም ትግራይ እንዳልሆነንትና ቀደም ሲል እንደተገለጸው የራስዋ ሰንደቅ ዓላማ፣ ዲሞክራሲያዊ አሰተዳደር እንደነበራት አውቀውና ተቀብለው ለድርድር መዘጋጀት ይኖርበቸዋል። በተጨማሪም የኤርትራ ችግር በሃቅና በፍትሕ እንዲፈታ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ያዋሃዳትን የ1952 ዓ.ም የጎለም መንግሥታት ውሳኔ 390 በአጸ ኃይለሥላሴ መንግሥት በ1962 ዓ.ም መሻር ሕገ ወጥ ድርጊት መሆኑን ይቀበላሉ። ምናልባትም ይኸ ፌዴራሽን ኢምፔርያሊስቶች በአፍሪካ ቀንድ እግራቸውን ለማስገቢት አስበው የኤርትራ ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ከሚዘን ሰያገቡ፣ ያደረጉትም ሊሆን ይችላል። የሆነው ሆነ፣ ታሪክን ወደ ኋላ መመለስ አሰቸጋሪ ነው። በእውን ብንነጋገር በኢትዮጵያ የቅኝ አስራሪዎችም ሆኑ የግራ ተሰፈንጣሪዎች ከትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት መሪዎች ሌላ፣ የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል የሚደግፍ መኖሩ ያጠራጥራል። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅትም መሪዎች ለጊዚያዊ ጥቅም ይሁን በውን እምነውበት መሆኑ ግወቅ አይቻልም። ይኸንን ሁሉ መሰዋዕትነት ለከፈሉ ለኤርትራውያን ይህንን መስማት ከባድ ሊሆን ይችላል። ግን ሐቁ ይኸው ነው። ሆኖም ከየእትጣጫው በሚደረጉ የግልም ሆነ የእደበባው ውይይቶች መደምደም እንደሚቻለው ለኤርትራ በጎ ፈቃድ ያላቸው ቅን አሳቢ ኢትዮጵያውያን ኤርትራ ከኢትዮጵያ በእንድ የፖለቲካ ሐረግ (የሰለለም ቢሆን) ግለት በፌዴራሽን፣ በኮንፌደሬሽን ወይንም በሌላ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ጋር እሰከተያያዘች ድረስ የኤርትራውያን ልዩነትና ሊኖራቸው የሚገባ መብቶችን ይደግፋሉ። ፌዴራሽን ወይንም ኮንፌደሬሽን ብዙ ደረጀዎች የያዙ ቃላት እንደመሆናቸው መጠን፣ የውጭ ጉዳይ በፌዴራል መንግሥት ስር ይሁን አይሁን፣ ግንዘብና ፊይናንስ ነክ ጉዳዮች በየግላቸው ያስተዳድሩ፣ እያንዳንዳቸው የፖሊስ ኃይል ይኑራቸው አይኑራቸው የመሰሰሉ መለስተኛ ጉዳዮች በድርድሩ ወቅት የሚፈቱ ጉዳዮች ናቸው።

6) ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ በዝርዝር የሰፈሩ ሃሳቦችና አስተያየቶች በሚከተሉት አጫጭር ሞብሮች ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

ሀ) የኤርትራ ግምባሮች ከዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ጋር በፌዴራሽን ለመኖር ፈቃደኝነታቸው በግልጽ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስታወቅ።

ለ) በቅድሚያ ግን የአሁኑ ማንንም የማይወክለው የአዲስ አበባው መንግሥት ከሥልጣን ወርዶ፤ በምትኩ ለወደፊት የሚቋቋመው፤ ተቋቁመው በሕቡዕነት የሚገኙ ፖርቲዎችና ኢሠፖም ጭምር ሕዝቡን የሚወክል መንግሥት

ለማቋቋም ዲሞክራሲያዊ ሽግግ አድርገው ከሚቋቋመው የሕዝብ ተወካይ መንግሥት ጋር ብቻ ለመደራደር ፈቃደኝነታቸው መግለጽ።

ሐ) ኤርትራ በረጅም ትግል የተፈተኑ ግምባሮች የምትወክል መሆኑ የማያጠራጥር ቢሆንም ከግምባሮቹ ውጭ ለመደራጀት የሚፈልጉ ኤርትራውያን ካሉ በሚያቋቁሟቸው ቡድኖች ወይንም ፖርቲዎች እማከይነት እንዲወከሉ መፍቀድና መርዳት።

መ) የኤርትራ ተወካዮች ቡድን ከታወቀ በኋላ ከኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ጋር ድርድር ገብተው የፈዴራሽኑ ዝርዝር ሁኔታዎችን መወሰን ።

ሁለቱም ወገኖች የያዝዋቸው አቋሞች በጣም የከረረ እምነቶችን ያዘለ ነው። ኢትዮጵያውያን ነፃነታቸውን ለማስከበርና ሕልውናቸውን ለመጠበቅ እንዲሚታገሉ አድርገው እንደሚቆጥሩት ያህል ኤርትራውያንም ደግሞ ለነፃነታቸውና ለመብታቸው እንደሚታገሉ ያምናሉ። በለዚህ ሁለቱም ወገኖች ከአቋማቸው ፈቀቅ ማለት ከባድ መሆኑ የሚከድ አይደለም። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ መሪነትና ዝም ብሎ በሰሚት መነዳት ሐቁንና ምኞትን መለየት ከትግል መማርና፣ እንዲሁ ዝም ብሎ በትግል ማለፍ የሚለየው። እነዚህን እውነታዎች ከለመቀበልና ከለመረዳት ኢትዮጵያውያን ኤርትራ እንደሌሎቹ ከፍለተ ሐገራት የኢትዮጵያ አንዷ ክፍል ሐገር ነች፣ በዚሁ መሠረት ትተዳደራለች እስክእሉ ድረስ የኤርትራ ግምባሮችም ከነፃነት ወይንም ከመገነጠል ሌላ ግንኙነት ለመቀበል እስክልፈቀዱ ድረስ፣ ይሽ እሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት ግዳይ የማይጣልበት፣ ጀግናና ፈሪ የማይለይበት የወንድማማች እልቂት ይቀጥላል። ኤርትራም የጦርነት ማሳ ሆና እገሪቱም በድህነት እየማቀቀች የዓለም ተመጽዋች ሆና የዘሬው ትውልድ በታሪክ ተወቃሽ ሆኖ ዘመን ያልፋል ዘመን ይተካል።

የግርጌ ማስታወሻዎች

[1] በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙት ዓመተ ምህረታት በሙሉ በአውሮፖውያን አቆጣጠር መሠረት ነው።

[2] ማህተማ ጋንዲ ይህንን መፈክር ሲያሰሙ የራሳቸውን ሞት ጠቅሰው እንጂ የሌሎችን አልነበረም የኢትዮጵያዎች «እንድነት ወይንም ሞት» ሲሉ ግን ከሞቱ አከባቢ ከአንድ ሺህ ኪሎሜትር በላይ እርቀው ስለሌለው ሞት ነው የሚርከሩ።

[3] በ1969 ዓ.ም ዋለልኝ መኮንን ይህንን አስመልክቶ በተማሪዎች ጋዜጣ እንድ እንቀጽ ጽፎ ብዙ እዲስ አሰበች ሰለተነሱ በእዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መኮንን አደራሽ ውስጥ አሰፋ ምህረቱ፣ ንጉሤ አየለ፣ ፋሲካ ሲደልልና ይሽው ጸሐፊ የተሰተፈበት የመጀመሪያው የብሔሮች ጥያቄ ውይይት ተካሂዶ ነበር።

[4] በ1935 ዓ.ም ኢትዮጵያ በጣልያን እጅ በወደቀችበት ጊዜ የኬንያው ጆሞ ኬንያታ ኢትዮጵያ የመለው የአፍሪከና የጥቁር ዘር መመኪያ እንደነበረች ሲገልጹ የናይጄርያው ናምዲ እዚኪዌ ደግሞ የመጨረሻዋ የተቀደሰች የአፍሪቃ የነፃነት ርሪ፣ የማትገረሰስ የነርች ወራሪ መከች ቋጥኝ የአፍሪከ የነፃነት ሰንደቅ ነች በማለት እሞጋገሰዋታል።
የኢትዮጵያ ነፃነት ስመዋጀትም ጥቁር አሜሪከኖች «ብራውን ከንደር» «ብሰክ ኢግል እቭ ሃርለም» በሚሉ ስሞች ተደራጅተው ከኢትዮጵያውያን ጎን ተዋድቀዋል። እንዲሁም ብዙ አፍሪከውያን ለኢትዮጵያ ነፃነት ብዙ ተጋድሎ እድርገዋል። ታድያ ዛሬ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ናት ሲባል እነዚህ አፍሪከውያን፤ ጥቁር አሜሪከውያንና የከሬብያን ሰዎች በሙሉ ተሰበተው ነበር ከማለት ሌላ ምርጫ የለም። ኢትዮጵያ መቼም ቅኝ እንደልነበረችና እንደልሆነችም Teshale Tibebu «Process of state Formatinon in modern Ethiopia 1850–1974» Proceedings 2nd Interational Conference on the Horn of Africa p. 13–40 እጥጋቢ በሆነ መንገድ ተንትነውታል።

[5] የኢርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር በመቀለሰል ፈቃደኛ አልነበረም፣ አብዛኛው የኢርትራ ሕዝብ ተቃውሞአል የሚልም ወገን ከርከር አለ።

[6] ሕሩይ ተድላ በእእ ዩኒቨርሲቲ ኮሎጅ ተማሪዎች መሪነት ተማሪውን ያነሳሱ ሲሆኑ፣ ኢሣያስ አፈወርቂ ደግሞ እእ ኢንጂኒሪንግ ኮሎጅ ለሁለት ዓመታት መተማሩበት ወቅት በተማሪዎች ንቅናቄ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ መሆኑ አይዘነጋም። እንዲሁም በሪሽት ሃብተሥላሴ የኢትዮጵያ መንግሥት በለሥልጣን በነበሩበት ጊዜ በሰውር የተማሪዎች መሪዎችን በሃሰብ ይረዱ ነበር። አብዮቱም እንደፈነዳ በዓለም ቢንክ የነበራቸው ከፍተኛ ደረጀ ለቅቀው ሰፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእደረገላቸውን ጥሪ አክብረው ኢትዮጵያ በመመለስ በምርመራ ኮሚሽን በማገልገል ለአብዮቱ እድገት አስተዋጽእ እድርገዋል።

[7] መንግሥቱ ጋይለ ማርያም በሚይ 28 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ ለውጭ አገር ጋዜጠኞች በሰጡት መልስ መንግሥታቸው በሕዝብ ሙሉ ፈቃድና ምርጫ የተቋቋመ መሆኑን

ገልጸው፣ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ስለመስፈን ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል። " Could there be any other country in the world that has gone to this extent of guaranteeing the freedom of its people?" (Mengistu Hailemariam 1988: 21)

የጽሑፎች ዝርዝር

Alvrarez F. Narrative of the Portuguese Embassy to Abyssinia during the years 1520-1527 tr. and ed. by Lord stanley (London Hakluyt Society 1881)

Berket Habte Selassie, Conflict and Intervetion in the Horn of Africa, Monthly review Press, (London 1980)

Berhe Habte Ghiorgis, "Prospects for Peaceful Settlement of the war in Eritrea" Journal of Eritrean Studies, Summer 1988.

Crawford, O.G.S ed. Ethiopian itineraries (Circa 1400-1524) London hakluyt society 1957)

E. P . L. F Memorandum August 1978

የህ.ግ.ሕ.ኤና የሕ.ወ.ሕ.ት የጋራ መግለጫ 1980

Major Asseged, Ethiopia. Revolution and War,
Ph.D Dissertation, University of Denver, Colorado, 1982.

Medhane, Tesfatsion, Eritrea: Dyanamics of a National Question, B.R. Gruner, Amsterdam 1986

Qgbazgi, Yohannes, "Behind the Etho-Eritrean Federation. The Conspiracy Thesis" Journal of Eritrean Studies, Summer 1988.

Teshale Tibebu, "Process of State Formation in modern Ethiopia 1850-1974" Proceedings 2nd international conference on the Horn of Africa, New York School of Social Reasearch, New York May 29-30, 1987.

አስተዋጽኦ ላደረጉ ምሥጋና

ለዚህ ትጥር ተጥተኛ አተዋጽኦ ላደረጉ ስማቸዉ ከዚህ ተጥሎ ለተዘረዘረ ግለሰቦች የመጽሄቱ አዘጋጅ ክፍል ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል።

አቶ አበበ ደምሴ ፣
የህብረት መጽሄት አዘጋጅ፡ የዚህን ትጥር ግማሽን በኮምፒዉተር በማዘጋጀት ስለረዱን፣

አቶ ብንያም ጥላሁን ፣
የዚህን ትጥር ግማሽን ጥሬት ባለዉ ሁኔታ በኮምፒዉተር አዘጋጅተዉ ሊላም ብዙ የሃሳብና የቶሳትሰ ድጋፍ በመለገሳቸዉ፣

ጳሽን ኢንጂኔሪንግ ኩባንያ፣
መጽሄቱ አሁን ደዞ የሚገኝዉን አቅድ ለማገኘት ኩባንያዉ ያልተቆጠበ ጥረት በማድረጉና ሊላም ቴክኒካዊ ምክር በመለገስ በኩል ስለተባበሩን፣

አቶ ፈለቀ 'አርምዴ
በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ስአል ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ናቸዉ። ለዚህ ትጥር ተስማሚ የሆነ ስአል በፈለግንበት ጊዜ ከስራዎቻቸዉ አንዱን በመለገስ ስለረዱን ከልብ እናመሰግናቸዋለን።

ፕሮፌሰር ሃይሌ ገሪማ፣
ፕሮፌሰር ሃይሌ በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ የፊልም ጥና ክፍል ፕሮፌሰር ናቸዉ። በዚህ መጽሄት ሽፋን ላይ የሚታየዉን ፎቶግራፍ ከስብስቦቻቸዉ መካከል አዉጥተዉ በመለገሳቸዉ በጣም እናመሰግናቸዋለን።

ዶክተር አበራ ሞላ፣
በአንስላት በተለይም በክብት ህክምና በዶክትሬት ደረጃ የተመረቱ ሲሆን የዚህን ትጥር ርእሰ አንቀጽ አዲስ በፈጠሩት የግእዝ ፊደል በማዘጋጀት ስለረዱን ከአድናቆት ጋር እናመሰግናቸዋለን።

ወይዘሮ አሥራት/ ወ ሥላሴ ለለገሱልን ስጦታና

ላደረጉልን እርዳታ ከልብ እናመሰግናቸዋለን።

* * *

በመጽሔቱ ውስጥ ማስታወቂያዎችን
ማስገባት ስለመሰንን ማስታወቂያዎች
ያሏቸው ሁሉ በቅድሚያ
እንድትልኩልን።

ሙሉ ገፅ	$ 160
ግማሽ ገፅ	$ 80
ሩብ ገፅ	$ 40

ደብዳቤዎች

ይድረስ ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች

በመጀመሪያ ጥንታዊ አበቶች ባወረሱን ወግ መሠረት ከራሳችን ገቅ በማለት አክብሮት የተመላበት ሰላምታችንን ለናንተ ለአዘጋጅዎችና ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለሆኑት እንባቢዎቻችሁ ሁሉ በጋለ ስሜት እናቀርብለን።

ለጥቀንም በመላው ዓለም ከምድር እድማስ እስከ እድማስ በሰገሮች ተበታትነን የእገርና የወገን ፍቅር፣ ናፍቶት፣ የወገኖቻችን ችግርና ቸነፈር፣ የምዕራብ ዜና ማሰራጫዎች ፀረ-ኢትዮጵያ ውርጅብኝ እያስጨነቀን የሆዳችንን ብሶት ሁሉ የምናወጋው ወገን ከጐናችን በምንፈልግበት እንግብጋቢ ወቅት ሰምና ወርቅን ይዛችሁ ብቅ በማለታችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ እያልን የኛንም መሥፈሪያ የግይገኝለት ፈንጠዝያ ጭምር እንገልጥለችኃለን። ማናቸውም በሰደት በባዕዳን እገር የምንገኝ «እበሾች» ሁሉ እንደምናውቀው መተንፈሻ እጥቶ በ«ፈረንጅ እገር» የተዳፈነ ብሶታችንን፣ ከእሳት የጋለ የሀገር ፍቅር ስሜታችንንና እገራችን ከገቢኝበት ማጥ መንጥቶ ለማውጣት ሁለችንም የኢትዮጵያ ልጆች ለምናደርገው ውይይት እስከሁን ከጠቢብ ፖለቲከና ርእዮተዓለም ነፃ የሆነ እገር-አቀፍ መድረክ ለጣነው ሁሉ ሰምና ወርቅን ታላቅ የእርይታና የአለኝታ መሠረተ ድንጋይ እኑራችኃልና ጥረታችሁ ይሳክላችሁ እያልን መልካም ምኞታችንን ስንገልጥለችሁ በናንተ ያለንንም ከፍተኛ ኩራት በመግለጥ ጭምር ነው። እኛም ብንሆን በአውሮፖ፣ በአፍሪቃ (ከኢትዮጵያ ውጭ) እንዲሁም በሰሜን አሚሪክ የተበታተንን ጊደኛሞች ብንሆንም እቅማችን በፈቀደው ሁሉ መጽሔቷን እንድትቀጥል ለማድረግ በምታደርጉት ጥረት ሁሉ የምንተባበራችሁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ቃል እንገባለችኃለን።

የናንተ የጥናት መጽሔት ከመጀመሩዋ በፊት በየአለንብቸው የአውሮፖና የሰሜን አሜሪክ ከተሞች የሚወጡ ጋዜጣዎች ፀረ-ኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ ሳይሆኑ ፀረ-ብሔረ ኢትዮጵያ ሆነው ስለገነናችው በሁኔታቸው ሳይ በመወያየት ብሔራዊ ኩራታችንን በስደትም ቢሆን ለማስጠበቅ ምን ማድረግ ይገባናል ብለን በደከማ እቅማችን እንዳንድ እቅዶች ለመወጠን በምንጣጣርበት ጊዜ ሰምና ወርቅ መውጣቷን ሰምተን ከየቦታው ተፈላልገን እስከሁን የወጡትን እትሞች አግኝተን እነበብናቸው። «እሰየው ያሳድጋችሁ» እያልን በእበራ ጠለ የበርሀ ጭን እንደሚቶርጥ ገበራም በእርከታ ሲታ ብዙ ተነፈስን። በውጭ እገር ከተበታተነው «የሀገር ልጅ» ሁሉ የሚበጅ መሠረት ሰምና ወርቅን በመጣላችሁ ተበራተን እኛም በአጋጣሚ ከአምስት ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች የተውጣጣን የኢትዮጵያ ልጆች ነገር ግን ከልጅነታችን ጀምሮ የቅርብ ጊደኞች የሆንን በሥስት የተለያዩ አህጉራት ብንገኝም በያለንበት የስደት

እገርቾ ሐሳቦቻችንን በደብዳቤዎችና በሰልክ ጥሪዎች በመለዋወጥ እነሆ እንድ «የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሀገር የወገን ፍቅር፣ የባሕልና የታሪክ ጥናት ከበብ» ብለን የሰየምነውን ትንሽ ነገር መሠረትን። ዓለማዎቻችንም ጥንታዊ እበቶችና እናቶች የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የብሔረሰብ፣ የያታ ልዩነቶች ሰያግዷቸው እንደምንም እገራችንን እሁን ያገኘችውን ቅርፅዋን አስይዘው እንደስተሳለፉልንና ለዚሁ ተግባር የከፈሉትንም መሥዋዕትነት ጭምር ለማጥናት ነው። ተጨማሪው ዓለማችን የኢትዮጵያ ታሪክ የእፍሪቃም ታሪክ አክል! እንደመሆኑ የሌሎች እበቶችና እናቶች እፍሪቃውያንን ባሕልና ታሪክ እንዲሁም ፀረ-ቅኝ እገዛዝና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሎቻቸውን በማጥናት የተከሰተልንን እውቀት ሁሉ ከወገን ጋር ሁሉ ለመካፈል ነው። በእርግጥ ይህ ተግባር በምዕራብ ዓለም ከእለታዊ ሙያተኞች ያልተሸለ (የሽቀላ) ኑሮ ለምንገፉ ግለሰቦች የገንዘብና የጊዜ መሰዋዕትነቱ ቀላል ባይሆንም የቻልነውን ያህል ለመጣር ወገቦችን ታጥቀን ተነስተናል። «የእንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ጉዘ በእንድ እርምጃ ይጀመራል» ሲሉ ስለሰማን በትንሿ ጅማሬአችን እናፍርም።

ቀደም ሲል ለመግለጥ እንደሞከርነው የጂአግራፊ መራራቅ ሰያግደን የዓመት የሥራ ፍቃዳችንን ሁሉ መሰዋዕት እያደረግን በደረገነው ጥረት የከበበችን የመጀመሪያ እስተዋፅእ የሆነችውን ይህችን «የኢትዮጵያ ረሀብና የእዕራብ ጋዜጦች እስተያየት» የተሰኘች ጽሑፋችንን ስናቀርብላችሁ ደስታችንን እየገለጥን በተለይ በኢትዮጵያ «ጠኔ» ላይ በምታተኩረዋ እትማችሁ የሚቻል ከሆነ ብታወጡዋት ምስጋናችን እክብሮታ የተመሰበት መሆኑን ጭምር በማረጋገጥ ነው። ወደፊት በሰላም እና በእካባቢ (ENVIRONMENT) እንደምታተኩሩ ያለንን ምኞት እንገልጣለን።

ኢትዮጵያዊ/ሐበሻዊ ባሕሰችንና ማንነታችን በምዕራባዊያንም ሆነ በምሥራቃውያን ተራ ፕሮፓጋንዳ እንደይረገጥ ለመታገል ከቀረጡ ወገኖቻችሁ ውስጥ የሆነው፣

እነቀሪቾ ፈይሣ፣
ከሰሚን አሜሪከ፤

ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች
ከጌትነት ቢሆነኝ
አዲስ አበባ

የመጀመሪያዎችን ሰስት እትሞች እንብቤአለሁ። መልክም ጅምር ነው። በእንባቢያን መልዕክት ሳይ እንደተመለከተው እንደሌሎች ቀደምት መጽሔቶች ብልጭ ብሎ ብሎ ድርግም እንዳይል እደራየ የጠበቀ ነው።

መጽሔቱ እንደጀመረው የምርምር ይሁን፤ ስሜታዊ እይሁን።

ታሪክ ያጣመመና በአሉባልታ የተሞላ ታሪካዊ እቀራረብ መጽሔቱን ሊያሰንቁት ይችላሉ።

እሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበት የንቃት ሕሊና ደረጃንም በየጊዜው መገምገሙም ተገቢ ነው። ከንቃተ ሕሊናው በታች የሆነ አቀራረብ መጽሔቱን ያሰንቀዋል፤ ከንቃተ ህሊናው በላይ ከሆነም ተፈላጊነቱ ለተወሰነ የምሁሩ ክልል ብቻ ይሆንና እንባቢው ያንሰል፤ ከዚያም ከገፋ የምሁሩ መከራከሪያና መነታረኪያ መድረክ ይሆናል። ይህም የራሱ የሆነ ጉድለት ይሆናል።

ዛሬ ሕዝቡ ከትግሉ ብዙ ተምሯል። በከንትርባንድም በሌለ ባገኛት ሬዲዮ ብዙ ያዳምጣል። በገበሬ ማሕበሩም ሆነ በወጣቱ፤ በከነማው በኩል ስለሰሽሊዝም ስለጎብሬት ሥራ ማጎበር፤ ስለልማት ወዘተ እውቂል። የገበሬ የልማትና የእስተዳደር ከድሬ ሥራ እልፈታም አስተምሮታል። ቅድመ ፮፮ የነበረው ሰውም በእዲሱ እየተተካ ነው። መሠረተ ትምሕርት ብዙ ሕዝብ እደርሷል። ከዚያም ጋር የእከባቢ ጋዜጦች በመጠኑም ቢሆን ብቅ ብቅ ብለዋል። ቴሌቪዢን እሥመራ፤ ጎንደር፤ መቀሌ፤ ባሕር ዳር፤ ማርቆስ፤ እዲስ አበባ፤ ደብረ ዘይት፤ ናዝሬት፤ እዋሽ፤ ሐረር፤ ድሬደዋ፤ ጎባ፤ አሰላ፤ ሻሸመኔ፤ እዋሳ፤ ይርጋለም፤ አርባ ምንጭ፤ ጅማ፤ ነቀምት፤ ወዘተ..... ስለሚደርስ ቴሌቪዢን መግዛት ደግሞ እንደ ሬዲዮ ስለሆነ በዚህ በኩል ሕዝቡ ምን ያህል እንደሚማር መታወቅ አለበት። በሬዲዮ በኩል በእማርኛ፣ እርምኛ፣ ትግርኛ፣ ትግሪ፣ አፋርኛ፣ ሶማልኛ ይነገራሉ። ትምሕርት ቤቶች በጣም ተስፋፍተዋል። ገጠሩ ሁሉ ትምሕርት ቤት ከፍቷል። ታዲያ ይህንን ሕዝብ አሰንሰ ማየት እይቻልም። በሌላ በኩል ፀረ-መንግሥት የሆኑ የፖለቲከ ድርጅቶች የበኩላቸውንም ስለሚያደርጉ በዚህ ትግል ውስጥ ያለ ሕዝብ በቀላሉ ሊታይ የሚገባው እይደለም። እንዳንደቹ ግን የሕዝቡ ሥነ ልቦናዊ ዘይቤ መቀየሩን አልተረዱም። እናንተም ይህን እንድትረዱ ያሻል።

ስለእዲሱ ርዕሰችሁ ማለትም ስለድርቅና ጤኔ በዚህች ደብዳቤ መግለጽ ይቸግረኛል። ልቀጥል ብል አንድ መጽሔፍ ይሆንብኛል። ለጊዜው ይህ ችግር በቀንጽልነቱ ብቻ የሚታይ መሆን የለበትም። ሁለንተናዊ ገጽታው ሊዳሰስ ይገባዋል። ለእንድ ሰምንት ቀርበው እጠናንን የሚሉት ፈረንጆች እገሪቱ የከሙኒስት ሥርእት ስለምትከተል ነው ብለው ይደመድማሉ። ብዙ ቢያትቱም መድምደሚያቸው ያው ነው።

ይህን የተፈጥሮ ችግርና ሌሳውንም የኢከኖሚ ችግራችንን በሚገባ ተገንዝበናል። የምርት ዘመቻ የሚባለው ተጀምር እንደነበረ በየጉባዔው «ከፅቅድ በላይ ተመረተ፣ ከፅቅድ በላይ ተሠራ» እየተባለ መሬቱ ሁሉ በወርቅ እንደተነጠፈ እየሆነ ሪፖርት ይቀርብ ነበር።

ምድሪ ሹም እውነቱን በመናገሩ ከሥልጣኑ እንዳይወርድ በመፍራት ዋሸ፤ በዚህ ዓመት ግን ሀቁ ወጣ።

ታዲያ እዚህ ላይ እንድ የቁም ነገር ቀልድ ልናገር።

እንድ ከተሜ ፍሪጅ ነበረው። እንድ ቀን ብድግ አለና ለጊደኛው ፍሪጁን ለመሸጥ እንዲሰበ ይነግረዋል። በዛሬ ጊዜ ፍሪጅ እይገኝም። እንዴት ትሸጠዋለህ ይለዋል ጊደኛው። ፍሪጁ ምን ያደርግልኛል። ሥጋ

የለም፣ ጎመን፣ ድንች፣ ወዘተ ዋጋው ተወዷል። ምርት የለም ስለዚህ መሸጡ ነው የሚሸለኝ ይለዋል። ጊደኛው ሞኝ ነህ ለምን ስኬቱን ነቅለህ ከኢትዮጵያ ሬዲዮ ጋር አታገናኘውም! ያን ጊዜ ምርቱ በሽ በሽ ሆኖ ፍሪጅህ ውስጥ ይገባል እለው ይበሳል። በእርግጥም በዚያን ወቅት በሬዲዮ የምርት ማደግ በብዛት ይወራ ነበር።

ወደ ዋናው ፍሬ ነገር ልመለስ የድርቅ ችግር በሚለው ርዕስ መታየት የሚገባው ብየ የግምነው። የተፈጠሮ ችግር ምን ማለት ነው? ከምን ይነሳል፣ የተፈጥሮ ችግርን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች፤

– የእየር መዛባት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ሁሪኬን፣ እሣተ ገሞራ፣ ጦርነት ....

የተፈጥሮ ችግር የሚያጠቃቸው አከባቢዎች? ለምን?

የተፈጥሮ ችግርና ኋለ ቀርነት ያላቸው ግንኙነትና ልዩነት
–መንገድ –አስተራረስ
–ገበያ –ትርፍ አምራችነት

የተፈጥሮ ችግርና የመሬት ይዘታ፣ የልማት ስትራቴጂ፤ ግንኙነት
–ሰፈራ –የመንግሥት እርሻ
–መንገድ መሥራት –የጎብረት ሥራ ማሠራት ሁኔታ
–የመሬት ይዘታ
–ለውጭ ምንዛሪና ለሃገር ውስጥ ብሌት የሚመረተው ሬሺዮ
–የማኔጅመንት ችግር –የምርት ሥርዓት
–የሕዝብ እገልግሎት ጎብረት ሥ/ማ

የተፈጥሮ ችግርና የአከባቢ ሠለም መታጣት ያላቸው ግንኙነት
–ግንኙነት መቋረጥ –ለማምረት መቸገር
–የሰው ኃይል መቀነስ –ወዘተ

የተፈጥሮ ችግርን ለመቋቋም የተወሰዱ እርምጂዎች፤

–አፈጣኝ ነፍስ አድን እርምጂዎች
–መሀከለኛ ጊዜ እርምጂዎች
–ዘላቂ መፍትሔ እርምጂዎች

የተፈጥሮ ችግር በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ከሰተት ሰይሆን በተለያዩ ጊዜዎች መከሰቱን፤ ጊዜውንና ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰ

እርዳታ የሰጠው ጥቅምና ያስከተለው ችግር

በወቅቱ ነፍስ አድን መሆኑ በዚሁ አጋጣሚ
–ግድብ ተሰርቷል። –ክሊኒክ ተሰርቷል።
–እርከን ተሰርቷል። –ዘፍ ተተክሏል።

ከእርዳታው ጋር አብረው የተከሰቱ
–የእርዳታ ሰጭዎች የበላይነት
–የርዕዮተ ዓለም ብረዛ
–የውስጥ አስተዳደር ጣልቃ መግባት
–የደመወዝ ደረጃዎችን ማዛባት። ለምሳሌ WORLD VISION የተባለው ለሹፌር ብር 850 መክፈል ስለጀመረ በመሰሪያ ቤቶች ችግር ፈጥሮ ነበረ።
–እርዳታ አድራሽ ተብሎ የተሳከው በሽታ ሌሎች ያልተለመዱ የወሲባዊ ግንኙነቶች ዘዴዎችን ማስገባታቸው
–እንደጋጆ ሰላዮች መሆናቸው
–በእደላ ወቅት ሌብነት፣ አድልዎ ወዘተ መከሰት፤ እንዲ ቁጥር በመሰሰቱ እዲሰ የመጣ መኪና ሞተር ተነቅሎ መርከቶ ገብቷል። ሰንዲ የብዙ ሹማምንትን ቤት ሠርታለች፣ መኪና ሆናለች፣ ዊስኪ ሆናለች፣ የፖለቲካ መሣርያ ሆናለች፣ ምን ያልሆነችው እስ? ብሔራዊ ጦርም ሆናለች።
–በኢትዮጵያ የዕግግስ መቋቋም ለእርዳታ አሰጣጥ እዲስ የአሠራር ብልሀት መሆን።
–ሌሎች እንደ ወሀሀት፣ ሽዕቢያ የመሰሰሉት እርዳታ ሰጭ ነን ማለታቸውና ለሕዝቡ ሰይደርሱ በመቅረታቸው፣ መንግሥት ለመግበት ባለመቻሉ ሕዝቡ ለረሀብ መጋለጡና ሲብስበት ኪሳ እየጣሰ መምጣቱ 1976–1977።
–በ1979 የእርዳታ አሰጣጥ ከሌላው ጊዜ የተለየው በመጠለያ መቀመጥ መክልከሉና ድርሻውን እየያዘ መመለሱ።
–በሰላም መታጣቱ ምክንያት እህል ወደከተማው የሚገባው መጠን በማነሱ የከተማው ሕዝብም ለእርዳታ ተቀባይነት መታረቡ የነበረው ከስተት፣ ይህም ለምዝበራ እመችቶ እንደነበር /እሥመራ/
–በ1979 «ሁሉም ነገር ወደሞር ግንባር» በተባለበት ወቅት ከICRC ጋር መንግሥት የገጠመው ውዝግብ ረሃብ-የፖለቲካ መሳሪያ እንዲሆን የተደረገው ጥረትና ውጤት
–ረሃብና ኢትዮጵያ ተመሰሰይነት ሊይዙ መድረሳቸውና የሕዝቡን ብሔራዊ ኩራት መንከቱ
–ሠፈራ መጀመሩ፣ ወሀሀትን ማስቆጣቱ፣ (የሰው ሀይል ይቀንሳል) ይህንም የፖለቲካ መሣሪያ ለማድረግ የተደረገው ጥረት፤ በሰፈራም ወቅት የአሠራርና የአፈጻጸም ችግር
–የሰደተኞች መብዘትና ለፖለቲካ ውዝግብ አመቺ መሆን
–በእንደንድ ሽቀጦች ላይ የተጣለው የታክስ ጭማሬ ወዘተ
–መደምደሚያው ኢትዮጵያ ሰፊና ሀብታም አገር ነች፤ ኢትዮጵያ በከፊል እንጂ በሙሉ ልትራብ አትችልም። የተፈጥሮ ችግር

ያለጠቃው ሊለውን ሊረዳ ይችላል። ሆኖም
-የምርት ሀይል ዝቅተኝነት
-የሠለም መታጣት
-የማኔጅመንት ጉድለት ዋናዎቹ ስለሆኑ በእነዚህ በኩል ጥረት መደረግ እንደለበት ቢጠቀስ መልክም ነው እለለሁ።

ጌትነት ቢሆነኝ
አዲስ አበባ

****

ም ስ ጋ ና

ሰምና ወርቅ ቁጥር 4 በማሰራጨት በኩል የረዱንን ሁሉ እናመሰግናለን= በተለይም፤

ዶ/ር እርቁ ይመርና	ችካጎ
አቶ ብንያም ጥላሁንና	ሲያትል
አቶ አንዱአለም ተፈራና	ካሊፎርኒያ
ወ/ት አዜዛ አቅድምና	አልበርታ ካናዳ
አቶ መልመድ አሊና	ሳስካቱን ካናዳ
ወ/ት ምንትዋብ እርአደና	አትላንታ
አቶ መሠረት አሰነና	ቴክሳስ
አቶ ተገኘ ሀይሌና	ፍሎሪዳ
አቶ ብርሃኑ ነጋሽና	ፊሪንሳይ
አቶ ታደሰ ዘሪሁንና	ሰዊድን
ወ/ት ሀረገወይን ምሥግኩና	ዋሽንተን
አቶ ፋሲል ይርጉና	ቺካጎ
አቶ በድሩ ሱልጣንና	ቴክሳስ

ማስታወቂያዎች

የሚተላለው እትም (3ኛ ዓመት ቁጥር 7) መስከረም ፱፱ ዓ.ም ለይ ስለሚወጣ ጽሑፎች ያሏችሁ በቅድሚያ እንድትልኩልን እናሳስባለን።

* * *

በመጽሔቱ ውስጥ ማስታወቂያዎችን ማስገባት ስለወሰንን ማስታወቂያዎች ያሏችሁ ሁሉ በቅድሚያ እንድትልኩልን።

ሙሉ ገፅ	$ 160
ግማሽ ገፅ	$ 80
ሩብ ገፅ	$ 40

ማስታወቂያዎች

ይህ እትም ዘግይቶ በመውጣቱ ምክንያት እንዳንድ ቀደም ብለው የተላኩ ጽሑፎች ላይ የተመዘገቡ ሀቆች አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ላይጣጣሙ ስለሚችሉ አንባቢዎች ይህን እያስታወሱ እንዲያነቡ እናስገነዝባለን።

* ***** ልዩ ምስጋና******

የዳሸን ኢንጂኒሪንግ ኩባንያ ለዚህ ቁጥር ያደረገውን ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማድነቅ ልዩ ምስጋና እናቀርባለን።

፩ኛ ፡ ፀርቅ ፡

ሰሸጎብያን ፡ ሸጭር ፡ ማስታወሻ ፡

ሰምና ወርቅ ድርጅት የመጽሔት አዘጋጅ ድርጅት ነው ። ይህ ድርጅት ለትርፍ የሚሠራ ድርጅት አይደለም ። በሽያጭም ሆነ በስጦታ የሚያገኘውን ሚገኛውንም ገቢ በቀጥታ ድርጅቱ ለመጽሔቱ ማስፋፊያ ያውለዋል ። የመጽሔቱ አዘጋጆች ጊዚያቸውን መስዋዕት በማድረግ ያለክፍያ ያገለግላሉ ። ወደፊት መጽሔቱ መክፈል የሚችልበት አቅም ሲደርስ አስፈላጊ ሰሆኑ አባላት ተጎቢውን ወጪ ያደርጋል ።

በመጽሔቱ ለሚታተሙ ጽሑፎች ድርጅቱ የተወሰነ ኃላፊነት ቢኖረውም ፣ የጽሑፍ ችግ ይዘት አለመልክቶ የሚነሳ ጥያቄ የሚመለሰው በጽሑፉ ደራሲ ነው ።

ሰደራሲያን ፡ ሸጭር ፡ ማስታወሻ ፡

መጽሔቱ ታትሞ አገዲወጣ ጽሑፍ የሚልኩ ደራስያን የሚከተለውን መመሪያ አገዲገነዘቡ አገጠይቃለን ።

ሀ/ ለመጽሔቱ የሚሰክ ሚገኛውም ጽሑፍ ለሚገበብ የሚያስችግር ፣ ግልጽና ሥርዝ ድልዝ ያልበዛበት መሆን አለበት ።

ለ/ ለመጽሔቱ የሚሰክ ጽሑፍ ዋናው ወይገም ግልባጩ ከደራሲው ጋር ቀሪ አገዲሆን ያስፈልጋል ።

ሐ/ ለመጽሔቱ የሚላኩ ጽሑፎች ለመታተም ቅድሚያ የሚሠጣቸው ኢትዮጵያን በሚመለከት ሚገኛውም ነጥብ ሳይ አዲስ ሀሳብ ፣ አዲስ ዜና ፣ አዲስ ትገተና ወይገም አዲስ መረጀ የያዙ አገደሆነ ነው ።

መ/ ደራሲዎች ጽሑፎቻቸው በሠነድና በማስረጀ የተደገፉ ፣ የምርምርና ጥናት ጽሑፎች አገዲሆኑ ወይገም የምርምርን ባህል የሚያደብሩ አገዲሆኑ ጥረት አገዲ ያደርጉ ይጠየቃሉ ።

ሠ/ ደራሲዎች የሚልኩት ጽሑፍ ከጅገጽ ያልበለጠ ቢሆን ይመረጣል ። ከፍተኛ ጥናት የሚያደርጉ ደራሲዎች ሥራቸውን በልዩ መልክ ማውጣት አገዲቻል አለቀድመው ከአዘጋጂው ክፍል ጋር በደብዳቤ ግንኙነት ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

ረ/ <u>የሰምና ፡ ወርቅ ፡</u> አዘጋጅ ክፍል ደራሲያን የሳኩት ጽሑፍ ላይ አርማትገና የማስተካከል ተግባር ሲፈጸም ደራሲዎች ጽሑፋቸውን አገዲመለከቱት የማድረግ ኀሳፊነት አለበት ። ደራሲያን ጽሑፋቸውን ባለቶኪይ መመለስ ይኖርባቸዋል ።

ሰ/ ደራሲያን ያልተለመዱ ቃላትን ማለተዋወቅ በሚፈልጉበት ጊዜ በቃላቱ ሥር መሥመር አገዲያስቀምጡና የቃላቱን ፍቺ በግርጌ ማስታወሻ ወይም በጉኑ አገዲገልጹ ይጠየቃሉ ።

ሸ/ ደራሲዎች ለሚያቀርቡት መረጀ ፣ ዜናና ለጽሑፎቻቸው ይዘት ተጠያቂዎች ናቸው ።

ቀ/ የመጽሔቱ ዕድሜ በሽያጭ ገቢና በሥጦታ(በልግሥና) በሚገኘው ገቢ ላይ የተመሠረተ ለሰሆነ አገባብያን የተቻሳቸውን ያህል ድጋፍ አገዲያደርጉ ይጠበቃሉ ።